# የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ጭብጦች

## ከእውነተኛ የክርስትና ኃይማኖት የሚገኘውን ሰላምና ደስታ የሚገልጽ ጥናታዊ ጽሑፍ

**DUNCAN HEASTER**

Carelinks, PO Box 152, Menai NSW 2234 AUSTRALIA

www.carelinks.net  email: info@carelinks.net

1. እግዚብሔር 1

የእግዚአብሔር መኖር 1.1

የእግዚአብሔር ማንነት 1.2

የእግዚአብሔር ስምና ባህርዩ 1.3

መላዕክቱ 1.4

2. የእግዚአብሔር መንፈስ 22

ትርጉም 2.1

የሚያነሣሣ መንፈስ 2.2

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች 2.3

የስጦታዎች መሠረዝ 2.4

የመጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛ የታመነ መረጃ፣ ምንጭና ምስክር 2.5

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች 60 3.

3.1 መግቢያ

3.2 በኤዴን የተሰጠው ቃል ኪዳን

3.3 ለኖኅ የተሰጠ ቃል ኪዳን

3.4 ለአብርሃም የተሰጠ ቃል ኪዳን

3.5 ለዳዊት የተሰጠ ቃል ኪዳን

እግዚአብሔርና ሞት 102 4.

4.1 የሰው ተፈጥሮ /ባህርይ/

4.2 ነፍስ

4.3 መንፈስ

4.4 ሞት ራስን መሳት ነው

4.5 ትንሣዔ

4.6 ፍርድ

4.7 የሽልማት ቦታ ገነት ወይስ መሬት?

4.8 በእግዚአብሔር ተጠያቅነት

4.9 ገሃነም

5. የእግዚአብሔር መንግሥት 142

5.1 መንግሥትነቱ ስተረጎም

5.2 መንግሥቱ አሁንም አልተቂቂመም

5.3 የእግዚአብሔር መንግሥት ስላለፈው ዘመን

5.4 የእግዚአብሔር መንግሥት ስለመጪው ዘመን

5.5 ሺኛው ክፍለ ዘመን

6. እግዚአብሔርና ክፉ ነገር /ኃጢአት/ 168

6.1 እግዚአብሔርና ኃጢአት

6.2 ዲያቢሎስና ሰይጣን

6.3 ጋኔን /መናፍስት/

7. መሠረተ ክርስቶስ 190

7.1 ስለኢየሱስ

7.2 የድንግል ልደት

7.3 በእግዚአብሔር ዕቅድ የክርስቶስ ቦታ

7.4 «በመጀመሪያ ቃል ነበር»

8. የኢየሱስ የተፈጥሮ ባህርይ 211

8.1 መግቢያ

8.2 በእግዚአብሔርና በኢየሱስ ያሉ ልዩነቶች

8.3 የኢየሱስ ተፈጥሮ

8.4 የኢየሱስ ሰውነት
8.5 የእግዚአብሔርና የእየሱስ ዝምድና

9. ጥምቀት በኢየሱስ 229
9.1 የጥምቀት ዋና ጥቅም
9.2 እኛ እንዴት መጠመቅ ይኖርብናል
9.3 የጥምቀት ትርጉም
9.4 ጥምቀትና ድነነት /መዳን/

10. በክርስቶስ ሕይወት 248
10.1 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት
10.2 ጸሎት
10.3 ስብከት
10.4 የቤተክርስቲያን ሕይወት
10.5 የዳቦው መቆረስ /ቁርባን/
10.6 ጋብቻ
10.7 ጊደኝነት

Carelinks, PO Box 152, Menai NSW 2234 AUSTRALIA

www.carelinks.net email: info@carelinks.net

# 1. እግዚብሔር

# 1.1 እግዚአብሔር አለ

«.. ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔርም እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን የስፈልገዋልና. /ዕብራውያን 11.6/

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ፍላጎት እግዚአብሔር ስለመኖሩ ለሚሹ ሳይሆን እግዚአብሔርን አምነው ወደእርሱ መምጣት ከሚፈልጉ እንጂ። በረቂቅ የተሠሩት አካሎቻችንን /መዝ 139.14/ ስንመረምር በአበባ ላይ የምናየውን ቅርጽ ስናስተውል፣ በብሩህ ሌሊት ወሰን የሌለውን ጠፈር ስንቃኝ፣ እንዲሁም ቁጥር ስፍር የሌላቸውን የሕይወት ነፀብራቆች በጥንቃቄ ስንመረምር እግዚአብሔር የለም ብሎ ከማመን አለ ብሎ ማመን የበለጠ ለመንፈስ ይቀላል።

እግዚአብሔር ባይኖር ሥርዓት ሊኖር አይችልም። በዓለም ውስጥ ስለአለውም የመኖር ምክንያት ትርጉም ለመስጠት አይቻልም። ይህ እግዚአብሔር መኖሩን በማይቀበሉት ሕይወት ላይ ሲንፀባረቅ ይታያል። ከዚህም የተነሣ ይመስላል በቁሳቁስ /ማቴሪያል/ ከሚያመልኩት ዘብዛኛዎቹ በተወሰነ መልኩም ቢሆን እግዚአብሔርን ወደመቀበለል ሲሄዱ የሚስተዋሉት። ይህ ደግሞ ሊያስገርመን አይገባም።

ሆኖም፣ «የሁሉም የበላይ አንድ ኃይል አለ በሚለው አደናጋሪ አስተሳሰብና «እግዚአብሔር በእርግጠኝነት አለ» ብሎ በማመን መካከል በተለይ ደግሞ እግዚአብሔርን አምነው ለሚቀበሉትና ዋጋ እንደሚከፈል ሰፊ ልዩነት እንዳለ ሊገናዘብ ይገባል። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደዕብራውያን ሰዎች በምዕራፍ 11 በቁጥር 6 ላይ...

«ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔርም እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንድሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» ያለው።

መጽሐፍ ቅዱስ እስራኤሎች /የእስራኤል ወገኖች/ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን በሰፊው ይተርካል። ይኸውም፣ የእግዚአብሔርን መኖር በማመናቸው ነው። የእግዚአብሔርን መኖር መቀበላቸው እንዳለ ሆኖ እግዚአብሔር በሰጣቸው ቃል ኪዳን ላይ ያላቸው አመኔታ ግን ጥብቅ አለመሆኑ በተደጋጋሚ የሚወሳ ነው። ታላቁ መሪያቸው ሙሴም እግዚአብሔር እንደተናገረው ለእስራኤላውያን...

> «...... እንግዲህ እግዚአብሔር ከሰማይ በላይ ከሰማይ በታችም በምድር አምላክ እንደሆነ ሌላም እንደሌለ ዛሬ ዕወቁ በልባችሁም ያዙ። ለእናንተ ከእናንተም በኋላ ልጆቻችሁ መልካም ይሆን ዘንድ። አምላክ እግዚአብሔርም ለዘለዓለም በሚሰጣችሁ ምድር ዕድሜያችሁ ይረዝም ዘንድ እኔ ዛሬ የማዝዛችሁን ሥርዓቱንና ትዕዛዙን ጠብቁ» ብሏቸዋል።
> /ዘዳግም 4. 39..40/

ስለሆነም፣ እግዚአብሔር አለ ብለን በአዕምሮአችን ብቻ ብንይዝ በራሱ በቂ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አያሳጣንም። ይልቁንም ፈጣሪ እንዳለ ከልብ የምናምን ከሆነ ሥርዓቱንና ትዕዛዙን መጠበቅ ይኖርብናል።

የዚህ እናታዊ ጽሑፍ ማጠንጠኛ ትዕዛዘቱ የትኞቹ እንደሆኑ ማመላከትና ትዕዛዙን ለመጠበቅ እንደሚቻል ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱን በጥልቀት እየዳሰስን በምንሄድትም ጊዜ የእግዚአብሔርን መኖር ዕውነታ የበለጠ እየተገነዘብን እንሄዳለንና።

« እንግዲያስ እምነት በመስማት ነው።

መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፤፤ /ሮሜ 10፡ 17/ በተመሳሳትም «.. እኔ ግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ያለሁም
የምኖርን ነኝ። /ኢሳ 43፡ 13/
ስሜም አምላክ ነው ይህም ሀቅ ነው። ሲል ስለእግዚአብሔር
ነቢዩ ኢሳያስ ስለመጪው ጊዜ ተንብየዋል።

ሐዋሪያው ጳውሎስ «በርኤ» ወደተባለች ከተማ መጣ ከተማዋ ዛሬ በሰሜን ግሪክ ትገኛለች። እንደተለመደው ወንጌል /መልካሙን ዜና/ ሰበከ፤ ነገር ግን የከተማው ሕዝብ የጳውሎስን ቃል በመቀበል ፈንታ የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበለሉ /የጳውሎስን አይደለም/

> «ልበ ሰፊዎች ነበሩና ነገሩ እንደዚህ ይሆንን ብለው ዕለት ዕለት መጽሐፍትን መረመሩ ቃሉንም በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ» /የሐዋ ሥ 17. 11.12/

እምነታቸው ካላቸው የአዕምሮ ዝግጁነትና ፍላጎት እንዲሁም በየቀኑ መጻሕፍትን በመመርመራቸው ነበር እንጂ እግዚአብሔር ቃሉ ወደአዕምሯቸው ይገባ ዘንድ መንፈሳዊ «የልብ ቀዶ ጥገና» ስለአደረገላቸው አልነበረም። ወደ « ቢሊ ግራሓም» ተጋድሎ ወይም ወደጴንጤ ቆስጤ ጉባዔ ገባ ወጣ የሚሉት ተዓለም ሕዝቦች አማኞች ናቸውን እነዚህ ጉዳዮች መጻሕፍትን በመመርመር ምን ያህል ጊዜ አለፈ እውነተኛ የመዓሕፍት ቃሎች በትክክል ባለማገናዘብ አዳዲስ አማኞች የክርስትና እምነት ልማድ ሸሽቲቸዋል።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ እናንተም ታምኑ ዘንድ መጻሕፍትን አንብባችሁ የምትረዱበትን አውታር መዘርጋት ነው። እውነተኛ የወንጌል ስብከት በመስማትና እውነተኛ እምነት በመያዝ መካከል ያለው ተዛምዶ በወንጌል ስብከት ብዙ ደምቆ የሚገኝ ነው።

« ከቆረንቶስ ሰዎች ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ» /የሐዋ ሥ 18፡8/
«አሕዛብ ከአፌ የወንጌልን ቃል ሰምተው አመኑ» /የሐዋ ሥ 15፡7/
«እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ ይሆናል» /ራዕይ 22፡3.4/

እንደዚህ ያለውን አበረታቺ ተስፋ ቧውነት ካመንበት በሕትወታችን ላይ ትርጉም ያለው ተጨባጭ ውጤት ይኖረዋል፡፡

« .-.ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለእርሱ ሊያይ የሚችል የለምና» /ዕብራ 12፡14/

መማል አይገባም ፤ ምክንያቱም

«.....በሰማይም የሚምለው በእግዚአብሔር ዙፋንና በርሱ ላይ በተቀመጠው መማል ነውና» /ማቴ 23፤22/
እግዚአብሔር አካላዊ /እንዳለ የሚታይ/ ካልሆነ ይህ አባባል ስሜት አይሰጥም፡፡
« ... እርሱ እንዳለ /በክርስቶስ/ እናየዋለንና...
በእርሱም ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንፁሕ እብደሆነ ራሱን ያነፃል፡፡ /ዮሐንስ 3፤ 2...3/

በዚህም ዓለም «ስለሰማያዊው አባት» ያለን ግንዛቤ በጣም ጎደሎ ነው፤ ግን በኢህ ዓለም የጨለማ ሕይወት አሻግረን ወደፊት በማየት በመጨረሻ እግዚአብሔርን መገናኘት ይኖርብናል፡፡ እርሱን በአካል በማየት ያለማወላወል በአዕምሮአችን ስለእርሱ ካለን ግንዛቤ ጋር ማጣጣም አለብን፡፡ ስለሆነም፤ ካለው ፍጹም ጥልቅ ሥቃይ ሳይሸነፍ ኢዮብ በመጨረሻዋ ሰዓት ከእግዚአብሔር የሚጠብቀው ደኅንነት በመናፈቅ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ዝምድና በመፍጠር እግዝአብሔርን በጽናቷ አስደስቷል፡፡

«....ይህ ቁርበቴ ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ
ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ።
እኔ ራሴ አየዋለሁ። አይኖቼም ይመለከቱታል።
ከእኔ ሌላ አይደለም፤ ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል።»
/ኢዮብ 19፡ 26....27/

ሐዋሪያው ጳውሎስም ከሌላ ሥቃይና የግርግር ሕይወት እንዲህ ብሏል፣

«.... ዛሬ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፣
በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን....»
/ቆረንቶስ 13፡12/

ስለእግዚአብሔር የሚኖረን ትክክለኛ ግንዛቤ ስለመጻሕፍት ለሚኖረን ሌሎች ጠቃሚ አካሄዶች ወሣኝነት አለው፤ ሆኖም አንድ ውሸት ወደ ሌላ ውሸት እንደሚያመራ ሁሉ ስለእግዚአብሔር ሊኖር የሚችል የተሳሳተ ግንዛቤም እንዲሁ መጻሕፍት የሚሰጡትን ዕውነታ ሁሉ እንዳይታይ ያደርጋቸዋል።

ይህ ክፍለ ጥናት በሙሉ ካልሆነም በከፊል አሳማኝ ከሆነ «እግዚአብሔርን በዕውነት ታውቀዋለህን? ወደሚለው ጥያቄ ይወስደናል። አሁን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስለእዝግአብሔር በተጨማሪ የሚሰጠውን ቀጥለን እንመለከታለን።

«ሕዝቦችም ያወድሱት» /1 ቆረን 15፡11/
«....ምሣለው ይህ ነው። «ዘሩ» የእግዚአብሔር ቃል ነው።
/ሉቃስ 8፡11/ በሾላው ዛፍ የተመሰለው ስለእምነት ነው።
/ሉቃስ 17፡6/ ይህ የሚያመለክተው ዕምነት የሚገኘው

«የዕምነት ቃል»ን ከመቀበል መሆኑ ነው። /ሮሜ 10፡8/
«በዕምነት ቃሎች»ና በተከተልኸው «በመልካም ትምህርት»
ቃል ተመገብ /1 ጢሞ 4፡6/ በእግዚአብሔርና በቃሉ ያምን ዘንድ ልብህን ክፍት አድርገው። /ገላትያ 2፡2/
/ዕብራ 4፡2/

በሐዋሪያው ዮሐንስ ስለጌታ ሕይወት በጽሑፍ የተመዘገበው እንዲህ ይላል «... እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል።» /ዮሐንስ 19፡35/ እናም የእግዚአብሔር ቃል «እውነታ» ነው። /ዮሐንስ 17፡17/ እናምን ዘንድ።

## 1.2 የእግዚአብሔር ማንነት

በመጽሐፍ እግዚአብሔር የዕውነት ተጨባጭ አካላዊ ማንነት ያለው ስለመሆኑ በግል መስፈሩ ሞገሳዊና ያሸበረቀ መልዕክት እንደሆነ ያመለክታል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ በመጻሕፍት ጎልቶ መስፈሩም የክርስትና ኃይማኖት መሠረታዊው ትምህርት ነው። እግዚአብሔር አካላዊ ካልሆነ ልጅ ሊኖረው ፍጹም አይችልም። ያውም «የክብሩ ማንፀባረቂያና የባህርዩ ምሣሌ የሆነ ልጅ /ዕብራ 1፡3/ በተጨማሪም በባዶ ህዋ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ፣ በመንፈሳችን የምናስበው፣ በአዕምሮአችን ውስጥ ብቻ የምናስበው ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወት የዘራበት የየግል ግንኙነት ሊኖረን ፍጹም አይችልም። አበዛኛው ኃይማኖት እንደዚህ ያለ ተጨባጭነት የሌለው ስሜታዊ አስተሳሰብ መኖሩ አሳዛኝ ነው።

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ሊለካ የማይችል ታላቅነት ስላለው እግዚአብሔርን በመጨረሻ ልናየው የምንችል መሆናችንን የተሰጠውን ግልጽ ቃል ኪዳኖች ላይ የብዙ

አሕዛብ እምነት አጊጉል መደረጉን ልናገናዘብ የሚገባን እስራኢል የእግዚአብሔርን «ቅ
ርጽ» /መልክ/ ዮሐንስ 5፡37/ ለማየት እምነት አጥቷል። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር አንድ የሆነ ቅርጽ ያለው መሆኑን ነው። እንደዚህ ያለው እምነት የሚመጣው እግዚአብሔርን ከማወቅና በቃሉም ከማመን ይሆናል።

> «....ልበ ንፁሖች ብፁዓን ናቸው «እግዚአብሔርን ያዩታልና» /ዮሐንስ 5፡8/
> .... የእግዚአብሔር ባሪያዎች እርሱን ያመልኩታል /ያገለግሉታል/፤ ፍቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግንባሮቻቸው ይሆናል።» /ራዕይ 22፡3...4/

እንደዚህ ያለውን አበረታቹ ተስፋ በእውነት ካመንበት በሕይወታችን ላይ ትርጉም የለው ተጨባጭ ውጤት ይኖረዋል።

> «.... ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀድሱም ዘንድ ፈልጉ ያለ እርሱ ሊያይ የሚችል የለምና» /ዕብራይ 12፡14/

## 1.3 የእግዚብሔር ስምና ባህርዩ

እግዚአብሔር ካለ ስለእሱነቱ ሊነግረን የሆነ ዘዴ አቅዶ ይሆናል ብሎ ማሰቡ ተቀባይነት ያለው ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚብሔር ለሰው ልጅ የተገለጸበትን የሚያውጅ ነው ብለን እናምናለን። እና ስለዚህም የእግዚብሔርን ባህርይ እናያለን። የእግዚብሔርን ቃሉ እንደራሱ «ዘር» /1 ጴጥሮስ 1፡23/ አደርጎ የሚአራው ለዚህ ነው።

«ዘር» የተባለው ቃሉ ከእኛ አዕምሮ ጋር ሲገናኝ አዲስ ነገር፣ ማለትም እግዚአብሔር ጠባይ /ባህርይ/ ያለው እንደሆነ

በአዕምሮአችን ውስጥ ይፈጠራል። /2 ቆረንቶስ 5፡17/ ከዚህም አኪያ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በራሳችን ሥራ ላይ ካዋልን፣ ትምህርቶቹንም ከወሰድን «የጁን መልክ መቅስምን» /ሮሜ 8፡29/ የበለጠ እንቀበላለን። ይህ ባህርይ አምላክ ፍጹም ምሣሌ መሆንን ያመለክታል። /ቆላስኒስ 1፡15/ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊነት ሲጠኑ የሚገኘው ጥቅም ይኸው ነው። ታሪካዊ ክፍሎቹ ከሰዎችና ከአሕዛብ ጋር እግዚአብሔር ያለውን ግንኙነት በብዙ ቦታዎች የሚያነሱበት ምክንያት ይህ ነው።

በእብራይስጥ ቋንቋ የግለሰብ ስም በባህርዩ ብዙ ሲንፀባረቅ ይታያል። ለአብነትም አንዳንድ ግልጽ ምሣሌዎችን እናንሳ፣

«ኢየሱስ» ማለት «አዳኝ» ሲሆን «ህዝቡን ከኃኢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን /«ኢየሱስ»ትለዋልህ» /ማቴ 1፡21/ ይላልና።

«ብርሃም»... « የብዙ አህዛብ አባት» ማለት ነው።
ለብዙ አህዛብ አባት አድርጌሃለሁና፣ /ዘፍጥረት 17፡15/

የእግዚአብሔር ስሞችና ማዕረጎች ስለእርሱ ብዙ መረጃ /የበለጠ ዕውቀት/ እንደሚሰጡ የምንጠብቀው ለዚህ ነው። ምክንያቱም፣ በእግዚአብሔር ባህርይና ፍላጎት ብዙ ሁኔታዎች አሉ። እግዚአብሔር በእርግጥ ከአንድ በላይ ስሞች አሉት። ስለእግዚአብሔር ስም ዝርዝር ጥናት ማድረግ የሚሻለው ከጥምቀት በኋላ ነው። ባህርዩም ልክ እንደሰው የሚገለጽ በጌታ የሚኖረው ሕይወታችን ነው። ከዚህ የሚከተለውም የመግቢያ ያህል ብቻ ይሆናል። ፈታኝ ከሆነ ሕይወቱ ሙሰረ እምነቱን ለማጠናከር ሲል ስለእግዚአብሔር የጠለቀ ዕውቀትን በፈለገበት ወቅት፣

«.... የእግዚአብሔርን ስም ዐወጀ። እግዚአብሔርንም

በፊቱ አልፎ እግዚአብሔር መሐሪ ሞገስ ያለው ታጋሽም
ባከብዙ ቸርነትና እውነት እስከሺህ ትውልድም ቸርነትን
የሚጠብቢ ሃበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል
በደለኛውንም ከቶ የሚያነጻ» አምላክ እንደሆነ ተናግሯል፡፡
/ዘፀአት 34፡ 5...7/

ይህ የእግዚአብሔር ስሞች ባህርያቱን የሚያቃጥል ግልጽ መተግመኛ ነው፡፡ ባህሪያቱን መያዙ ደግሞ እግዙአብሔር በአካል ስለመኖሩ ማሥረጃ ነው፡፡ የመንፈሕስ አፍ ቢሆን ግን እነዚህ ባህሪያት ይኖሩታል ብሎ ማመን ትርጉም አይኖረውም፡፡ እግዚአብሔር በዚያ ይታወቅ፣ በህዝቦቹ ይታወስና ይጠራ ዘንድ አንድ ልዩ ስም መርጧል፡፡ የእርሱ ሰዎች ያለው ፍላጎትም ማጠቃለያው ይኸው ነው፡፡

እስራኤላውያን በግብጽ ባሮች ነበሩ እግዚአብሔር ያሰበው ዓላማ በእነርሱ ያድር ዘንድ ፈለገ፡፡ ግብጽን ለቅቀው ቃል ወደተገባላት ሀገር ተደፋፍረው ይወጡ ዘንድ እግዚአብሔር ለሙሴ ስለስሙ ነገረው፡፡ /ቆረንቶስ 10፡1/

ከመጠመቃችንና ጉዞአችንን ወደእግዙአብሔር መንግሥት ከመጀመራችብሥን በፊት የእግዚአብሔርን ስም በተመለከተ መሠረታዊ መርሆችን ልንረዳ ይገባናል፡፡

ለእስራኤል ልጆች እግዚአብሔር ስሙ «ያህዌህ»
እንደነበርና ትርጉሙም፣ ያለና የሚኖር እኔ ነኝ»
/ዘፀአት 3፡13...15/ ማለት እንደሆነ በግሯቸዋል፡፡
የስሙ ትርጉም ደግሞ ትንሽ ሰፋ ይላል

«....እግዚአብሔር ደግሞ ሙሴን አለው፡፡ ለእስራኤል

ልጆች እንዲህ ትላለህ፣ የአባቶቻችሁ አምላክ የአብርሃም
አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብም አምላክ እግዚአብሔር
ወደእናንተ ላከኝ፡፡ ይህ ለዘለዓም ስሜ ነው፡፡ እስከልጅ
ልጅ ድርስም መታሰቢያዬ ይህ ነው፡፡» /ዘፀአት 3፡15/

ስለዚህ የእግዚአብሔር ሙሊ መጠሪያው «ጌታ እግዚአብሔር» ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን በአብዛኛው ተጽፎ የሚገኘው በእብራይስጥ ስለሆነ ወደእንግሊዝኛ ትርጉም ከዚያም ወደአማሪኛ በሚተረጎምበት ጊዜ ስለእግዙአብሔር የተጻፉት ቃላት ብዙ መሳታቸው አይቀርም፡፡ ከብዙዎቹ ከተለመዱት የእግዚአብሔር ትርጉም ቃላት አንዱ «ኤሎሂም» የሚለው ሲሆን ትርጊሜውም «ኃያሎች» የእግዚአብሔር «መታሰቢያ» ማለት ይሆናል፡፡ ከዘህ አኪያ፣ እርሱን እያስታወስን ስሙን እንድንጠራ የሚፈልገው «ያህዌህ ኤሎሂም»

ትርጉሙ «ቡበድን በግርማ ሞገስ
/በኃይል/ የሚገለጽ ማለት ነው፡፡
ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ዓላማ ባህርዩንና እሱነቱን በቡድን ለሚገኙ ለብዙ አሕዛብ መገለጽ ነው፡፡ በቃሉ መታመን ደግሞ እኛ ሰዎች የእግዚአብሔርን አንዳንድ ባህሪያት ለራሳችን ማዋል እንችላለን፡፡

በተወሰነ ደረጃ እግዚአብሔር ራሱም ለዕውነተኛ አማኞች ገልጿልና፡፡ ግን የእግዚአብሔር ስም ለመጪው ዘመን የተተነበየ እርሱን በባህርዩና በተፈእሮው በመሠሉ ሕዝቦች መሬት እስክትሞላ ድረስ የሚጠብቅ ይሆናል፡፡ /2 ጴጥ 1፡4/ ከእግዚአብሔር ፍላጎት ጋር ራሳችንን ለማቀራረብ ከፈለግን፤ እንደገናም ላለመሞት እግዚአብሔርን ለመምሰል ካሻን በተሚላና ፍጹም ግብረገብነት ባለው ሁኔታ ለመኖር

ከተመኘን፤ ከእግዚአብሔር ስም ጋር መዋሃድ ትኖርብናል፡፡ ለዚህ መንገዱ በስሙ ማለትም በ«ያህዌህ ኤሎሂም» ስም መጠመቅ ይገባናል፡፡ /ማቴ 29፡19/ 19/ ይህ ደግሞ የዘለዓለማዊ የመሬት ወራሾች የአብርሃም /ዘሮች/ ያደርገናል፡፡ /ገላት 3፡27/ ዘፍጥ 17፡8 ፣ ሮሜ 4፡13/፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ 3.4 ላይ በሰፊው ይተነተናል፡፡

## 1.4 «መላዕክቱ»

እስካሁን በነበረው ጥናታዊ ጽሑፍ ያገናዘብነው ሁሉ በአንድ ላይ የተከተለው መላዕክቱን ግንዝቤ ውውጥ በማስገባት ነው፡;

- ♦ አካላዊ ተጨባጭነት ህያው ፍጡር
- ♦ የእግዚአብሔርን ስም መሸከም
- ♦ የእግዚብሔርን መንፈስ መተላለፊያዎች ፈቃዱ ይፈጸም ዘንድ
- ♦ የእግዚአብሔርን ባህርይና ፍላጎት በማገናዘብ
- ♦ እናም በዚህም እግዚአብሔር ራሱን በመግለጽ

በጥናታዊ ጽሑፍ 1.3 እንደጠቀስነው ወደ እብራይስጥ ተራ ቂንቂ ሲመለስ «እግዝአብሔር» ኤሎሂም» ነው፡; ትርጊሜውም «ኃያሎች» ይላል፡፡ እነዚህ የእግዚአብሔርን ስም የያዙት «ኃያሎች» ደግሞ ኳረሱ ጋር ባላቸው ቅርብ ትስስር «እግዚብሔር» ተብለው በሚገባ ሊጠሩ ይችላሉ፡; እነዚህ ህያዎች መላዕክት ናቸው፡;

የዓለም መፈጠር ታሪክ በዘፍጥረት 1 እንዲህ ይለናል፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረትን በተመለከተ አንዳንድ ትዕዛዛትን ተናገረ «እናም ተደረገም» .. መላዕክቱ ናቸው እነዚህን ትዕዛዛት ተግባራዊ ያደረጉት፡፡

«... ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኃያላን ተቃሉንም ድምጽ የምትሰሙ መላዕክቱ ሁሉ እግዚአብሔርብ ባርኩ። /መዝ 103፡20/

ስለሆነም፣ እግዝአብሔር ዓለሙን ስለመፍጠሩ ስናነብ ሥራዎቺ ሁሉ በእርግጠኝነት የሚከናወኑት በመላዕክቱ መሆኑን መገንዘብ አሳማኝ ይሆናል።

ኢዮብ በ38፡7 ይህንኑ ይጠቁማል። አሁን በዘፍጥረት 1 ላይ የተመለከቱትን የፍጥረት ድርግቶችን አቅለል የማድረጊያ ትክክለኛ ጊዜ ነውና በስድስቱ ቀናት የተከነወኑትን እናስተውል....

በመጀመሪያው ቀን «... እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ»
/ቁጥር 3/
በሁለተኛው ቀን « ... እግዚአብሔርም በውሃዎች መካከል ጠፈር ይሁን፣
በውኃና በውኃ መካከልም ይከፈል አለ። እግዚዘብሔር ጠፈርን
አደረገ፣ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውሃዎች
ለየ፤ እንዲሁም ሆነ፤፤ እግዚአብሔር ጠፈሩን ሰማይ ብሎ
ጠራው ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ። /ቁጥር 6.7/
በሦስተኛው ቀን «... ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ሥፈር ይሰብሰብ።
የብሱም ይገለጥ አለ። እንዲሁም ሆነ /ቁጥር 9/
በአራተኛው ቀን «.... እግዚአብሔርም አለ ቀንና ሌሊት ይለዩ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ በምድርም ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ ። እንዲሁም ሆነ።» / ቁጥር 14 15/

በአምስተኛው ቀን «.... እግዚአብሔርም አለ. ውኃ፣ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሽ ታሰገኝ ፤ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ይብረሩ፤ እግኢዘብሔር ታላላቅ አንበሪዎችን የሚበሩትን ወፎች ሁሉ ፈጠረ።» /ቁጥር20 21/» እንዲሁም ሆነ»
በስድስተኛው ቀን «.... እግዚአብሔር አለ ምድር ህያዋን ፍጥረታትን
እንደወገኑ፣ እንስሳትንም ተንቀሳቃሾችን፣ የምድር አራዊትንም እንድወገኑ ታውጣ። እንዲሁም ሆነ» /ቁጥር 26/ ሰው የተፈጠረው በዚያ በስድስተኛው ቀን ነው።

«... እግዚአብሔር አለ .. ሰውን በመልካችን እንደምሣሌያችን እንፍጠር። /ዘፍጥ 1፡26/ ለዚህ ቁጥር በጽሑፋችን 1.2 ላይ አስተያየት ሰጥተንበታል። ለጊዜው «እግዚአብሔር» ስለራሱ ብቻውን በአካል እየገለጸ አለመሆኑን ማመላከት በቂ ይሆናል። ሰውን እንፍጠር ሲል «እግዚአብሔር» ከአንድ በላይ አድርጎ ራሱን እየገለጸ መሆኑን ያመለክታል። «እግዚአብሔር፣ የሚለው ቃል በእብራይስጥ «ኤሎሂም»ኃያላኖቹ» ማለት ከሆነ መላዕክቱን ሲገልጽ ነው። መላዕክቱ በምሳሌያቸው ሰው የመፍጠራቸው እውነታ እነርሱም ልክ የእኛን አካላዊ ቅርጽ ያላቸው መሆኑን ነው። ስለዚህም መላዕክቱ በጣም ዕውነተኛ የሆኑ ህልውና ያላቸው የሚታዩና የሚጨበጡ፣ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮአዊነት የሚጋሩ አካሎች ናቸው።

የእግዚአብሔር ተፈጥሮ /የመከለኮት ተፈጥሮ/

- «ኃጢአት ሊሠራ የማይችል፣ ሮሜ 9፡14 መዝ 90፡2 /ማቴ 5፡48/ /ቶማስ 1፡13/
- «ሊሞት የማይችል፣ ህያው /1ጢሞ 6፡16/
- «በኃይልና በጉልበት የተሞላ »ነው። /ኢሳያስ

40፡28/ ይህ የእግዚአብሔርና የመላዕክቱ ተፈጥሮ ነው።

እናም ኢየሱስ ከትንሣዔው በኋላ የተሰጠውና /ሐዋ 13፡34 ራዕይ 1፡18 እብራ 1፡13/ ለእኛም ቃል ኪዳን የተገባልን ተፈጥሮ ነው። /ሉቃ 20፡35..36 2ጴጥሮስ 1፡4 ኢሳያስ 40፡28...31/

## የሰው ተፈጥሮ በአንጻሩ ደግሞ

- «በከሰረ ተፈጥሮአዊ አእምሮው ለኃጢአት የተጋለጠ» /ኤርምያስ 17፡9 ማርቆስ 7፣21...23/
- «ሟች /የሚሞት/ ሮሜ 5፡12...17/
- «አእምሮአዊና አካላዊ ጥንካሬው ውሱን የሆነ ነው። /ኢሳያስ 40፣30 ኤርምያስ 10፡23/

መልካምም መጥፎም የሆኑ ሰዎች ሁሉ ያላው ተፈጥሮ ይህ ነው። የዚያ ሁሉ ተፈጥሮ መጨረሻው ሞት ነው። /ሮሜ 6፡23/፤ በሟችነት ሕይወቱ ኢየሱስ የነበረውም ተፈጥሮ ይህ ነው። /እብራ 2፡14..18፣ ሪሜ 8፡3/ ዮሐንስ 2፡25 ማርቆስ 10፡18/ «ተፈጥሮ» ብለን ከእንግሊዝኛ የወሰድነው ቃል "nature" የሚለው ቃል ግልፅ አለመሆኑ ደግሞ የበለጠ ልናብራራው የማንችል ከባድ ነው።

> ከመላዕክቱ ሁለቱ በሶዶም ከተማ ወደሚገኘው ሎጥ ቤት መጡ። ሎጥ በሰዶም እንደሚኖረው ተራ ሕዝብ ነበር። ሎጥም ማታ ከእርሱ ጋር እንዲያድሩ ጋበዛቸው። ግን የሰዶም ሰዎች ወደ ቤቱ መጡና በዛ መልክ በዚህ መእተው ያደሩት ሰዎች የት አሉ፤ ብለው ጠየቁት። ሎ እነዚህ ሰዎች እናንተን ምንም አላደረጉም አላቸው። በመንፈስ ተነሳሽነት የተመዘገበውም «ሰዎች» ይላቸዋል። /ሰዎቹ/ መላዕክቱ እጃቸውን ዘረፋና ሎጥን አዳኑት። ሰዎቹም ለሎጥ አሉት .. «ጌታ ሰዶምን እናጠፋ ዘንድ ልኮናል» /ዘፍጥ 19፡1..5 8፡10 12፡13/

ስለእነዚህ ጉዳዮች፣ አዲስ ኪዳን «መላዕክቱ» በሰው አምሣል መሆናቸውን ያረጋግጣል። «እንግዶቹን ለማስተናገድ ዝንጉ አትሁን ለጥቂቶቹ /ለአብርሃና ሎጥ ለምሣሌ/ የማያውቁቸውን መላዕክት አስተናግደዋልና»። /እብራ 13፡2/

«ያዕቆብ ሌሊቱን በሙሉ ከእንግዳው ሰው ጋር ታገለ» /ዘፍጥ 32።24/ «በኋላም መላዕክት እንደነበረ ተነገረን» /ሐዋ 12፡4/

«ኢየሱስ በተነሣበት /ሉቃ 24፡4/ ና በአረገበት /ሐዋ 1፡10/ ወቅት የሚያበሩ ነጭ ልብሶች የለበሱ ሁለት ሰዎች ነበሩ»። እነዚህ በግልጥ መላዕክት ነበሩ።

የሰው መስፈሪያ መላዕክትም እንዲሁ » /ራዕይ 21፡17/ ወደሚለው መደምደሚያ እንደሚያመራ አስተውል።

## መላዕክት ኃጢአት አይሠሩም

መላዕክት የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ባህርይ ስላላቸው አይሞቱም። ኃጢአት አይሠሩም ሞትን ስለማያስከትል። ይህ መላዕክት ኃጢአት እንደማይሠሩ ያረጋግጣል።

በግሪክና በዕብራይስጥ ቋንቋ «መልአክ» ማለት «መልዕክተኛ» ነው። መላዕክቱ የእግዚአብሔር መልዕክተኞች ወይም አገልጋዮች፤ አዛዦች ስለሆኑ ኃጢአት ይሠራሉ ብሎ ማሰብ አያስኬድም።

ስለሆነም፣ በግሪክ ቋንቋ «አገሎስ» «መልዕክተኞች» ስለሰው ልጆች በሚናገርበት ጊዜ /ለምሣሌ መጥመቁ ዮሐንስ /ማቴ 9፡52/ ና ተላላኪዎቹ የነበሩት ሰዎች /ጀምስ 2፡25/ የላቸዋል። ተሰው ተላላኪዎች ግን ኃጢአት እንደሚሠሩ ግልጽ ነው።

ሁሉም መላዕክት /ጥቂቶቹ ብቻ አይደሉም/ ኃጢአት የማይሠሩ መሆናቸውን በግልፅ የሚከተሉት ምንባቦች ያስረዳሉ::

«እግዝአብሔር በሰማይ ዙፋኑን አዘጋጀ:: መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች:: ቃሉን የምትፈጽሙ ብርቱዎችና ኃያላን የቃሉን ድምፅ የምትሰሙ መላዕክቱ ሁሊ እግዚአብሔርን ባርኩ:: ሠራዊቱ ሁሉ ፈቃዱን
የምታደርጉ አገልጋዮቹ እግዚአብሔርን ባርኩ ሕመዝ 103፡ 19..21/
አመስግኑት፤ መላዕክቱን ሁሉ... ሠራዊቱን አመሰገኑ»
/መዝ 148፡2/

«መላዕክቱ መንፈስን ሁሉም አያከናውኑም፤ ድነነት ወራሾች ይሆኑ ዘንድ ስለእነርሱ ለማከናወን ወደፊት ተልከዋልን? /ዕብ 1፡13..14/

«ሁሉም» የሚለው ቃል ተደጋግሞ መገለጹ የሚያሳየው መላዕክቱ ለሁለት ቡድን አለመከፈላቸውን፣ አንዱ ጥሩ ሌላው ኃጢአተኛ አለመሆኑን ነው:: የመላዕክቱ ተፈጥሮ በግልጽ የመረዳት ጥቅሙ የታማኝነት ዋጋው የእርሱነቱን ተፈጥሮ መጋራቱ ነው::

«እርሱ ዋጋ ያላቸው፣ የማያገቡ ከእንግዲህ ወዲህም የማይሞቱ ከመላዕክቱ እኩል የሆኑ» /ሉቃ 20፡35..36/ ይህን ጭብጥ መያዝ ጠቃሚ ነጥብ ነው:: መላዕክቱ ሉሞቱ አይችሉም:: «...ሞት ... መላዕክቱን አያዛቸውም:: /ዕብራ 2፡16/ መላዕክት ኃጢአት የሚሠሩ በሆን ኖሮ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ዋጋ ያለው ሽልማት የሚሰጣቸውም ኃጠ .አት ሊሠሩ ይችሉ ነበርና:: እናም ኃጢአት ሞትን ማስከተሉ ሲታይ /ሮሜ 6፡23/ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚባል ነገር አይኖርም ነበር:: ኃጢአት የመሥራት መንገዱ ካለ የመሞቱም እንደዚሁ::

ከዚህም አኳያ፣ መላዕክቱ ኃጦአት ይሠራሉ ካልን በእግዚአብሔር ቃል የተገባልን ዘለዓለማዊ ሕይወት ትርጉም የለሽ ያደርገዋል።
«መላዕክቱ» የሚለውን ቃል በምናነሳበት /ሉቃ 20፡35..36/ ጊዜ የምንረዳው መላዕክቱ በክፍል በክፍል ኃጢአተኛና ጻድቅ ሳይሆኑ አንድ ክፍል ውስጥ መሆናቸውን ነው።

መላዕክት ኃጢአት የሚሠሩ ቢሆን በሕይወታችንና በዓለም ጉዳዮች ላይ የጻድቅ ሥራ ሊሠራ ከቶ አይቻልም ነበር። እግዚአብሔር በመላዕክቱ አማካይነት እንደሚሠራ ማሳወቁን ስናስተውል፤ /መዝ 103፡ 19..21/ በእግዚአብሔር «መንፈስ ተሠርቷል» ማለትም የሚያደርጋውን ድርጊቶች ሁሉ በመላዕክቱ አማካይነት በእርሱ መንፈስ /ኃይል/ ነው። /መዝ 104፡4/ ለእግዝአብሔር ታዛዠነት መላዕክቱ የላቸዉም የሚባል ካለ ፈጽሞ አያስኬድም። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ ምድር ይመጣ ዘንድ በርትተው በየቀኑ ፀሎት ማድረግ አለባቸው። ፈቃዱ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር ትሆን ዘንድ /ማቴ 6፡10/ የእግዚአብሔር መላእክት ኀጢአተኞቹ የሰማዩ መላዕክት ጋር የሚሽቀዳደም ከሆነ ፈቃዱ ሙሉ በሙሉ እዙያ ሊተገበር አይችልም ነበር። በኃጢአትና በታዛዡነት መካከል የማያቋርጥ ጦርነት ይኖር ነበር። ነገር ግን .....

ብዙ «የክርስቲያን» አብያተ መላዕክት ኃጢአት ሊሠሩ ይችላሉ የሚል ሃሳብ አላቸው። እንደዚሁም ኃጢአተኛ መለዕክት ለኃጢአትና በምድር ላይ ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ኃላፊነት ( ተጠያቂነት) አለባቸው የሚል እንድምታ ይሰጠ-ታል። በጥናታዊ ጽሑፍ ክፍል 6 በተሟላ እናየዋለን። ለገዜው ግን የሚከተሉትን ነጥቦች እንመርምር-----------

እኛ ከመፈጠራችን አስቀድሞ ፍጥረት ነበር ማለት ይቻላል።
በዘፍጥረት 1 እንደተመዘገበው ያሁኖቹ መላዕክት የመጡት ክፉና ደጉን ለይተን ለማስተዋል እንድንችል ነው። /ዘፍጥ 3፡5/

ከእኛ አስቀድሞ ከነበሩት ጥቂቶቹ በዚያን ዘመን ኃጢያአት ሠርተዋል የሚለውን ያጠቃለለ ባይሆንም ይህ ሁሉ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ የሚመላለስ የሰው ተፈጥሮን ያመለክታል። አሁን ሁኔታ ግንዛቤ በመስጠት መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ኃኢአተኛ መላዕክት እንደሌሉ ፣ መላዕክቱ በሙሉ የእግዚአብሔር ታዛዦች መሁናቸውን ነው።

- ♦ በሰማያት ኃጢያአት የሚሠሩ ሊኖሩ አይችሉም። እግዚአብሔር «ክፋት ሚያዩት የጠሩ ዓይኖቹ » /ሐብ 1፡13/ስላሉት ። በተመሣሣይ ሁኔታም /መዝ 5፡45/ ከእርሱ ጋር ክፋት አይኖርም ሞኙ በእግዚአብሔር ሰማያዊ ወንበር ላይ አይቆምምና ሲል ይገልፀዋል።

ኃጢያተኛሻለ ብሎ ማሰብ በሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር አመጽ የሚያነሣሣ በነዚህ ምንባቦች ላይ በግልጽ ሠፍሮ ከሚነበበው ጋር ይፃረራል።

- ♦ የግሪክ ቋንቋ «መላዕክት» ማለት «ተላላኪ» ነው እናም ከላይ እንዳየነው የሰው ልጅ የሌለውን ሰው ተላላኪነት ስለሚመለከት የዚህ ዓይነት «ተላላኪ» ኃጢያአት ሊሠራ ይችላል፡ የሚል ስሜት ይኖራል።
- ♦ ክፋት አለ የሕይወት አሉታዊ ሥራዎችም በኃጢያተኞች እንደሚሠራም ወቀሳ ማቅረብ በኃይማኖት የለሾች ሃሳቦች አሏቸው ።
- ♦ በአሁን ሰዓት የኃጢአተኛ መላዕክቱ የመኖር ሃሳብን የሚደግፍ መጽሐፍ ቅዱስ ሊያምታቱ የሚችሉ ምንባቦች ጥቂት ናቸው። እነዚህ ሰይጣንን ከማሳደድ ጋር ከአንዳንድ አሳታሚዎች የሚታይ ነው። እንደዚሁ ያሉ ምንባቦች የበለፀገውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትንሀርት እንዲቃረን መንገድ መስጠት ግን የለበትም።

## ስለምዕራፍ /ጥናት/ 1 ጥያቄዎች

1. በእግዚአብሔር እምነታችንን ለማበልጸግ ከሁሉም የበለጠ ምን ይረዳል ?
   ሀ/ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ
   ለ/ የፀሎት መጽሐፍን ማንበብ
   ሐ/ ክርስቲያኖችን ማነጋገር
   መ/ ተፈጥሮን መመልከት

2. ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው የእግዚብሔር በጣም ትክክለኛ ትርጉሙ ?
   ሀ/ በአዕምሮአችን ውስጥ የሚኖር ሃሳብ
   ለ/ በከባቢ አየር ላይ ያለ ትንፋሽ መንፈስ
   ሐ/ እግዚአብሔር የለም
   መ/ ተጨባጭ ቁሳዊ ሰው

3. እግዚአብሔር ------------ ነውን ?
   ሀ/ አንድነት /ሕብረት/
   ለ/ ሥላሴ
   ሐ/ በአንድ ውስጥ ብዙ መላዕክት
   መ/ በምንም መንገድ መግለጽ የማይቻል

4. የእግዚአብሔር ስም «ያህያዌ ኤሎሂም» መባሉ ትርጉሙ ምንድነው ?
   ሀ/ እሱ ወደፊትም የሚኖር
   ለ/ ሞገስ ባላቸው ህያውን ፊት የሚገለጽ
   ሐ/ አንድ ታላቅ
   መ/ ጥንካሬ

5. «መልአክ» የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
   ሀ/ የሰው አምሳያ
   ለ/ ክንፍ የተላበሰ
   ሐ/ መልዕክተኛ
   መ/ ረዳት

6. መላዕክት ኃጢአት ይሰራሉን ?
   ሀ/ አዎ

## 21 የእግዚአብሔር መንግሥት

### ለ/ የለም

# 2. የእግዚአብሔር መንፈስ

# 2.1 የእግዚአብሔር መንፈስ ትርጊሜ

እግዚአብሔር ስሜትና ርኅራኄ ያሉት በተጨባጭነት የእውነት አምላክ ስለሆነ ስሜቶቹንና ፍላጎቶችን ከእኛ ጋር የመጋራት መንገዶች ይኖሩት ዘንድ ይጠበቃል። ልጆቹ የሆን እኛ ሰዎችም በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ባህርያት መጋራታችን ከዚሁ የተነሣ ነው፡፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ የሚፈጽመው «መንፈስ» ነው። እኛ እግዚአብሔርን ለማወቅ ፍለሰጎት ካለንና ከእርሱም ጋር ሙሉና ብርቱ ግንኙነት እንዲኖረን ከፈለግን «የእግዚአብሔር ነብፈስ» ምን እንዶህነ፣ እንዴትም እንደሚሠራ ማወቅ ይገባናል።

«መንፈስ» ለሚባለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ለመስጠ ት ቀላል አይሆንም። ለምሣሌ ወደ ሠርግ ተጋብዘህ ብትሄድና «በዕውነት ቆንጆ መንፈስ ሠርሁ ላይ ነበር» ብትል ለማለት የፈለግኸው ሁኔታ ጥሩ ነበር፤ ማንኛውም ዝግጅት ጥሩ ነበር፤ እያንዳንዲ እድምተኛ በደንብ ለብሶ ነበር፤ ምግብ ቆንጆ ነበር፤ እድምተኛው እርስ በራሱ በመግባባት ይገባበዝ ነበር፤ ሙሽራዋ ተባለች ወዘተ ሁሉ ማለት ይሆናል። እነዚያ ሁ የተለያዩ ነገሮች በአንድ ላይ የሠርጉ «መንፈስ» ገለሳጮች ሆኑ። በተመሰሳሰሳይም የእግዚአብሔር መንፈስ ስንል የእርሱ መግለጫ የሀሆኑትን ሁሉ ማለት ይሆናል። በብሉይ ኪዳን ላይ «መንፈስ» የምንለው ቃል በቀጥታ ወደ እብራይስጥ ሲመለስ «እስትፋስ» ወይም «ኃይል» ማለት ስለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ የእሱ «ስትፋስ» ወይም ኃይል ማለት ስለሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ የእሱ «እስትፋስ» አዕምሮውን /አስተሳሰቡን/ የሚየያንፀባርቅ የእግዚአብሔር ዋና ፍሬ ነገር ሊሆን ነው። «መንፈስ» የሚባለውን ቃል እንዴት የአንድን ሰው አዕምሮ ለመግለጥ እንደምንገለገልበት ምሣሌዎች እናስቀምጥ፣

የሐዋርያው የጳውሎስ ወደሮሜ ሰዎች በ15፡19 «ስለመንፈስ ቅዱስ ኃይል» እንደጻፈው «መንፈስ ቅዱስ» እነደዚሁ መላበሻ የሌለው የእግዚአብሔር ኃይልን አያመላክትም።

የሰው ልጅ የሚያስባቸውን በሚፈጽማቸው ተግባራቱ እንደሚገለጹ በመጽሸፍ ቅዱስ ትምህርት ለላይ የተለመዱ እንደሆኑ ያስቀምጣል። /ምሣሌ 23፡7፤ ማቴ 12፡34/ ይሸውም በራሳችን ተግባራት በትንሹ የሚንፀባረቁ መሆነናቸው ይህችኑ ሐቅ ነው የሚያረጋግጥልን። እኛ አንድ ነገር እናስብና ተግባራዊ እናደርገዋለን። የእግዚአብሔም መንፈስ እጅግ ከዚህ በላቀ ከፍተኛ ደረጃ ይሁን እንጂ አንድ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር የእርሱን ማንነት፣ ባህርይ /ወዳጅነት/ ዓላማ /ፍላጎት/ የሚገልጽበት ኃይል ከሰው ልጅ አንድ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር ያስባል እናም ነገሮን ያደርጋል።

’’...እንደተናገርሁ በርግጥ ይሆናል እንዳሰብሁም
እንዲሁ ይቆማል።’’ /ኢሳያስ 14፡24/

የእግዚአብሔር ኃይል

አያሌ የመጽሐፍ ምንባቦች የእግዚአብሔርን መንፈስ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር በግልጽ ያያይዙታል። ዓለምን ለመፍጠር፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፈ ነበር። እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ ብርሃንም ሆነ። /ዘፍጥረት 1፡2...3/

ሁሉም ነገሮች ለምሣሌ ብርሃን የተፈጠሩበት ኃይል የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡

''በመንፈሱ ሰማያት ውበትን አገኙ፤ እጁም በራሪቱን እባብ ወጋች'' /ኢዮብ 26፡13/

'' በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ፡፡ ሠራዊታቸውም ሁሉ በእስትንፋሱ'' /መዝ 33፡6/

ስለሆነም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ

- የእርሱ እስትፋስ
- የእርሱ ቃል
- የእርሱ እጅ ተብሎ ይገለጻል፡፡

ከዚህም አኳያ እግኢአብሔር ሁሉንም ነገሮች የሚያሳካው በእርሱ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ አማኞች እንደገና ይወለደዳሉ /ዮሐንስ 1፡13/ ማለትም በእርሱ መንፈስ፡፡ /ዮሐንስ 3፡3..5/ የእርሱ ፈቃድ በሥራ ላይ የሚውለው በእርሱ መንፈስ ነው፡፡ ስለአለው ተፈጥሮአወዊ ክስተት ስንናገር እኛም የምናነበው ''...መንፈስህን ትልካለህ፤ ይፈጠራሉም፡፡ የምድርንም ፊት ያድሣለህ፡፡'' /መዝ 104፡30/ ይህ መንፈስ ይህ ኃይል ሁሉንም ነገሮች ጠብቆ የያዘ፡ የፍጥረትም መንገድ /ምክንያት/ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ብርቱ ግባት ከሌለበት ይህ አሳዛኝ ሕይወት ይደናቀፋል ብሎ ማሰብ ቀላል

ነው። ኢዮብ ስለዚህ ዓለም ሕይወቱ በሰለቸ /በደከመ/ ጊዜ ስለዚሁ በሌላ ነቢይ ተነግሮታል።
"... እርሱ ልቡን ወደራሱ ቢመልስ መንፈሱንና እስትንፋሱን ወደራሱ ቢሰበስብ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድነት ይጠፋል። ሰውም ወደአፈር ይመለሳል።" /ኢዮብ 34፡14...15/

በጥናታዊ ጽሑፋችን 4.3 ላይ የተሰጠን መንፈስና ሁሉም ፍጥረት የእኛ ሕይወት መጽናኛ /ድጋፍ/ እንደሆነ እናያለን። እኛ "የሕይወት ነፋስ እስትንፋስ ያለው ሁሉ" /ዘፍጥረት 7፡22/ ስንወለድ ከእግዚአብሔር የተሰጠን /መዝ 104፡30፣ ዘፍጥ 2፡7/ አለን። ይህ የእግዚአብሔርን " የሥጋ ሁሉ መንፈስ" /እብራ 12፡9/ ያደርገዋል። ሁሉንም ፍጥርተ ዓለም ደግፎ የያዘው የእግዚአብሔር የሕይወት አንቀሳቃሽ ጉልበት ነውና መንፈሱ የትም ቦታ አለ። በመንፈሱ አማካይነት እግዚአብሔር ሁልጊዜም ከእርሱ ጋር እንዳለ ዳዊት በመንገዘቡ በእግዚአብሔር መንፈስ /ኃይል/ በእያንዳንዱ ሥፍራ በዳዊት አዕምሮና አስተሳሰብ ሁሉ የእርሱ መኖርን አምኖ ተቀብሏል። ስለዚህም ምንም እንኳን እግዚአብሔር በገነት መንበር ቢቀመጥም በመንፈስ አማካይነት የትም ቦታ አለ ማለት ነው።

"...አቤቱ መረመርኸኝ አወቀኸኝም አንተ መቀመጠ ንና መነሳቴን ዐወቅህ ሃሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ... ከመንፈስ ወዴት እሄዳለሁ? ከፍትህስ ወዴት እሸሻለሁ?... እስከባህር መጨረሻም ብበር በዚያ እጅህ ትመራኘኛለች

/በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት/ ቀኝህም ትይዘኛለች'' /መዝ 139፡2 7 9 10/

መንፈስ ቅዱስ

''የእግዚአብሔር መንፈስ'' የሚለው ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ በመሆኑ በቀላሉ ለመረዳት እንደማይቻል ከላይ አስተውለናል። የእግዚአብሔርን አዕምሮና ጠባይ /ባህርይ/ እንዲሁም ደግሞ አስተሳሰቡን በሥራ ላይ የሚያውልበትን ኃይሉን ማለታችን ነው። ''በልቡም እንዳሰበ እንዲሁ ነውና'' /ምሣለ 23፡7/ እናም ስለሆነም የእግዚአብሔር ''አስተሳሰቡ'' በዚያም መንፈስ ''እግዚአብሔር መንፈስ ነው'' /ዮሐንስ 4፡24/ በጣም ሰፊ ሆነውን የእግዚአብሔርን መንፈስ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ''መንፈስ ቅዱስ'' ብለን እናነባለን።

''መንፈስ ቅዱስ'' የሚለው ቃል በሐዲስ ኪዳን ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ በሁሉም ላይ ተጽፎ ይገኛል። ይህ በብሉይ ኪዳን ''የእግዚአብሔር መንፈስ'' ወይም ''የጌታ መንፈስ'' ተብሎ ለተጻፈው መተኪያ ነው። በሐዋርያት ሥራ እንደተቀመጠው መንፈስ ቅዱስ በሃምሣኛው ቀን በሐዋርያቱ ላይ ሰፈፈ የሚል ሆኖ በምንባቡ ላይ በግልጽ ሠፍሮ ይነበባል። የነቢዩ ዩኤል ትንቢት መፈጸምን ''የእግዚአብሔር /የእኔ/ መንፈስ'' በሐዋርያቱ ላይ ፈሰሰ ሲል ጴጥሮስ ገልጾታል። እንደገናም ሉቃስ በ4፡1 ላይ ኢየሱስ ''በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ'' ከዮርዳኖስ ተመለሰ ይላል እንዲሁም በቀጣዮቹ ምዕራፎች ላይ ኢየሱስ የኢሳያስ ትንቢት 6፡1 መፈጸምን

''የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ'' ከእኔ ላይ አለ ማለቱን ይናገራል።

በሚከተሉት ምንባቦች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋት ገጎን ለጎን እንዴት እንደሚራመድ ደግሞ አስተውል።

''...መንፈስ ቅዱስ በአንቺ /በማርያም/ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኃይል ይፀልልሻል''

/ሉቃስ 1:35/

''...የመንፈስ ቅዱስ...ክርስቶስ በቃልና በሥራ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል

በመንፈስ ቅዱስም ኃይል /ሮሜ 15:13 19/

''...እነሆ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ። እናንተ ግን ከላይ ኃይል

እስክትለብሱ ድርስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።'' /ሉቃስ 24:19/

''...በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው።'' የሐዋ ሥ 10:38 ኢየሱስ ራሱን።

...ጳውሎስ ስለእግዚአብሔር ኃይል የሰበከውን መተማመኛ ሲሰጥ ''ቃሌም ስብከቴም መንፈስንና ኃይልን በመግለጥ ነበር እንጂ'' /1 ቆረንቶስ 2:4/ ያለውን ይናገራል።

## 2.2 የሚያነሣሣ መንፈስ

ስለእግዚአብሔር መንፈስ ትርጊሜ ስንገልጽ መንፈሱ ስለሚያከናውነው ኃይሉ፣ አስተሳሰቡ፣ ፍላጎቱና ተግባራቱ አመላካች መሆናቸውን ከላይ አስቀምጠናል። እንዲሁም እንዴት የእግዚአብሔር መንፈስ በዓለም ፈጠራ ላይ እንደሚሠራ ከላይ ገልጸልናል። ''በመንፈሱ ሰማያትን አገኘ'' /ኢዮብ 26፡13/ ሲል የእግዚአብሔር መንፈስ ያለውን የዓለም ፍጥረት ለማምጣት በውሃዎች ላይ አሳረፈ'' /ዘፍጥረት 1፡2/ ይላል። እንዲሁም ዓለም የተፈጠረው በጌታ ቃል መሆኑን ለማሳየት ዘፍጥረት ላይ ''እግዚአብሔር አለ'' ዓለምም በዚሁ መልኩ ተሠራ በማለት አስቀምጦታል። /መዝ 33፡6/ ስለዚህ የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ የሚያንፀባርቅ እንዲሁም የውስጥ ስሜታችንና ፍላጎታችንን ቃሎቻችን የሚገልጹ መሆኑንም በእውነት ያለነውን ''የእኛን/ በትክክል እናስተውላለን። ኢየሱስ በዐዋቂነት ያመለከተውም '' በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና'' /ማቴ 12፡34/ ሲል ጠ ቁሟል። ስለዚህ፣ የምንናገራቸውን ቃላት ለመቆጣጠር የመጀመሪያ በአስተሳሰቦቻችን መሥራት ይኖርብናል። የእግዚአብሔርም ቃል እንዲሁ የእርሱ መንፈስ፣ አስተሳሰብ ነፀብራቆች ናቸው። የእግዚአብሔርን መንፈስና አዕምሮ ለመረዳት እንድንችል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የእግዚአብሔር ቃሎች ሠፍረው ማግኘታችን ራሱ መባረክ ነው። እግዚአብሔር መንፈሱን በተጻፉ ቃላት እንዲገለገሉ የሚያደርግበት ሂደት ''በመንፈስ'' ዙሪያ ባለው ''በመንፈስ

መነሣሣት'' /'Inspiration-- IN SPIRIT - ATION"/ በሚለው ነው።

''መንፈስ'' ማለት ''እስትንፋስ'' "Inspiration" ማለት ደግሞ''

IN-SPIRATION"' ማለት ይሆናል። ሰዎች በመንፈስ በእግዚአብሔር ተነሣሥተው የጻፉቸው እንደመሆናቸው መጠን የእግዚአብሔር መንፈስ ቃሎች ናቸው ማለት ነው። ጳውሎስ የጢሞትዎስ ሶዎችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ካለው ቅርበት /ትስስር/ የተነሣ የእግዚአብሔር መንፈስ የፈጠራቸው አስደናቂ ዕውነታ መሁኑን እንዳይረሳና በዚሁም እውነተኛ የእግዚአብሔር ዕውቀት እንዲኖረን የሚያሻን መሆኑን እንዲየያገናዝቡ አበረታቲል።

''...ከህፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን

የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን

አውቀሃል፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ

ለትምህርትና ለተግሣፅ ልብህን ለማቅላት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።'' /2 ጢሞ 3፡15...17/

ከላይ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንደዘሁ ያለ የዕውቀት መሟላትን የሚሠእ ከሆነ የእግዚአብሔርን ዕውነታ የሚያሳይ ሌላ ውስጣዊ መብራት አያሻንም። ሆኖም አሕዛብ ስለእግዚአብሔር ያላቸውን ዕውቀት ከተግል ስሜቶቻቸውነና ልምደዶቻቻቸው አንፃር ስንት ጊዜ ይነናገራሉ በክርስት ሕይወት አንድን ሰው በተሚላ መልኩ ለመዘጋጀት በእግዚአብሔር የሚያነሣሣ መንፈሳዊ ቃል መቀበል ከሆነ ሌላ የጽድቅነት ኃይል ለሕይወታችን አያሻንም። እንደዚህ የሚፈለግ ነገር ካለ የእግዚአብሔር ቃልም ሙሉ በሙሉ ካላዘጋጀን ጳውሎስ ቃል እንደጻፈው እንደዚሁ ይሆናል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን በእጃችን ለመያዝና በእውነትም የእግዚአብሔር መንፈስ ቃል መሆኑን አምኖ ለመቀበል እምንት ይጠይቃል። የእስራኤል ልጆች የእግዚአብሔር ምን ለማለት እንደፈለገ በጎ ፍላጎት አሳይተዋል። ዛሬ ብዙ ''ክርስትያኖች'' እንዳሉ ይታያልና። የጳውሎስ መልዕክት በ4፡2 ላይ የሠፈረውን እንመልከት..

> ''... ለእነዚያ ደግሞ እንደተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናልና ጻሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚወዎቹ ጋር በእምነት ካልተወዋሃደ አልጠቀማቸውም'' ይላል።

በእግዚአብሔር መንፈስ /ቃል/ ፍጹም ዕምነት ለማግኘት ወደላይ ከመውጣት አጭር መንፈሳዊ መንገድ መያዝ የበለጠ ማራኪ ነው። የፅድቅ ኃይል በድንገት በላያችን ያርፋል በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ። ደግሞም ለእግዚአብሔር ቃል ያለንን ታማኝነት ለማቀራረብ አላስፈላጊ ችግር በንቃት ህሊናችን ከመፍጠር ብሎም የእግዚአብሔር መንፈስ በዕውነት ልባችንን ከሚያሳምነው ይልቅ በእግዚአብሔር ቃል ተመርተው አያሌ ''ክርስቲያኖች'' በመጽሐፍ ቅዱስ የተካተተው ቃል ሁሊ በእግዚአብሔር መንፈስ የመነጨ ነው ወይስ ያጠያትቃል የሚለውን ግዙፍ

መንፈሳዊ ኃይል ለመቀበል ባለመፈለግ በመጻሕፍቱ ያነበብነው የአዋቂ አባቶች የግል አስተያየቶች የተካተቱበት ነው የሚሉም አሉ፡፡ ሆኖም ጴጥሮስ ይህን አስተያየት በማቃለል እንደዚህ ብሏል፡፡

’’... ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፡፡
ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስክወጣ ድረስ ሰው በጨለማ ሥፍራ የሚያበራውን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ፡፡
በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም
አልፈቅድም፡፡ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና
ጻኑ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ
ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡’’ /2 ጴጥሮስ 1፡19...21/
መጽሐፍ ቅዱስ ’’ከሁሉ በላይ’’ በመንፈስ ተነሣሽነት የተጻፈ መሆኑን ማመን አለብን፡፡

## የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሓፊዎች

መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ በመንፈስ መነሣሣት አኪያ የሚኖረን ጠንካራ ዕምነት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ መጻሕፍቱን የጻፉት ሰዎች በመንፈስ ተነሣተውና ተገፋፍተው መሆኑንና የእነርሱም ቃላትም የእነርሱ ቃላት መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም እውነት /ዮሐንስ 17፡17/ በመሆኑና መሠረዝና ማረምም /2ጢሞ 3፡16..17/ እንደማይቻል እየታወቀ በብዙ አሕዛብ ዘንድ የሚዋጥ አለመሆኑ አያስገርምም፡፡ እውነት ቅር ያሰኛልና፡፡ እግዚአብሔር በመንፈስ አነሳሥቶት የእግዚአብሔርን ቃል

በድፍረት በመናገሩ ነቢዩ ኤርምያስ ብዙ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ ይህ በመሆኑ የተሰጠውን ቃላት ሁሉ ከማተም፣ ከመጻፍ /ከመመዝገብ/ ተቆጥቧል፡፡ ሆኖም የእግዚአብሔር ቃሉ መጻፍ የእርሱ ፈቃድ ውጤት እንጂ የሰው ልጆች ፍላጎት ባለመሆኑ ''በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ'' ከማድረግ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፡፡

> ''...ቀኑን ሙሉ መሣቂያ ሆኛለሁ ሁሉም ያላግጡ ብኛለ፡፡
> በተናገርሁ ቁጥር...እናም አልሁኝ ስሙን አልጠራም በስሙም
> ከዚህ በኂላ ምንም አልልም፤ ግን የእርሱ ቃል ግን በአጥንቴ
> ውስጥ እንደተጻፈነ የሚያቃጥል እሳት በልቤ ውስጥ ነበር፡፡
> ያንን ለመሸከም ደክሜ ስለነበር መግፋት /መቆየት/ ሳልችል
> ቀርቻለሁ፡፡'' ይላል /ኤርምያስ 20፡7...9/

እነዚህ ሰዎች በከፊል ብቻ በመንፈስ ተነሣሥተው ቢሆን ኖሮ ወደእውነተኛው ቃል ወይም ውደ እግዚአብሔር መንፈስ ማለፊያ አይኖራቸውም፡፡ የተጻፉት በእርግጥ የእግዚአብሔር ቃል ከሆኑ በእግዚአብሔር መንፈስ በመነሣሣት ወቅት የተፈጸሙ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙሉ በሙሉ ያከናወናቸው ያ ባይሆን ኖሮ ጥርት ያለው የእግዚአብሔር ቃል ውጤት ነው ማለት ባልተቻለ ነበርና፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ የእርሱ መሆኑን መቀበል ለማንበብና ትዕዛዛቱን ለመፈጸም የበለጠ ይገፋፋል፡፡

> ''...የእርሱ ቃክ በጣም የተጣራ ነው፡፡ ስለሆነም
> ባሪያዎቹ ቃሉን ይወዱታል፡፡'' /መዝ 119፡140/

ከዚህም አኳያ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሠራው እንጂ ሰዎች የጻፉት ሥነ ጽሁፍ አይደለም። ከዚህ አባባል እውነታ ለመማየት በሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደሚገልጸው እንመልከት...የማተ7ወዎስ ወንጌል በ2:5 እንዴት እንደተጻፈ ሲነናገር''...በነቢየያት አማከካይነት ተጻፈ''... እግዚአብሐ2ር በእነርሱ በኩልይጽፉ ነበር ብሏል። ''...
መንፈስ ቅዱስ በዳዊት አፍ ተናገረ'' /ሐዋ 1:16/ 16/ ይህ እንዴት ጴጥሮስ ከመዝሙረ ዳዊት /እብራ 3:7/ የጠቀሰው ነው።

ለክርስትና እምነት ተከታዮች የመጻሕፍት ደራሲ ሰዎች ባአንጻራዋ መልኩ ይህን ያህል ጠቃሚዎች አይደሉም። እውነታው የእነርሱ ቃላት በእግዚአብሔር ተነሣሥተው መሆኑ ነው ዋናው ጉዳይ።

የእግዚአብሔር ኃይለ...ቃል

የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያመላክተው ወደ እርሱ አዕምሮ ብቻ ሳይሆን አስተሳሰቦቹን ለመግለጽ ወደሚያመላክተው ኃይሉ ጭምር ነው። የእርሱ መንፈስ /ቃል/ ከአዕምሮ የሚወጠጣውን መግለጫ ብቻ አይደለም። በዚያ ቃል የያለውን ወደፊፊት የመሚያራምድ ኃይል ጭምር እንጂ ለዚያ ኃይል ያለን እውነተኛ አድናቆት እንድንጠ ቀምበት ሊያጊጊ ይገባል። እንደዚህ በማድረግ የእፍረት ስሜቶች ካሉ ለእግዚአብሔር ቃል በአለን ታማዕነትና ከዚያም በምናገኘው ኃይል እውቀት መኩራራት ከሕይወታችን ትናንሽ ነገሮችም ወጥተን ወደፊት ለመግፋት ወደድኀነት ለመገስገስ ባለን ጽኑ አቂም መበረታታት ይገባናል። ካለው ሰፊ ተሞክሮ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል።

> ''.. በክርስቶስ ወንጌል አላፍርም። ለድኀነት
> የእግዚአብሔር ኃይል ነውና.. /ሮሜ 1:16/

ሉቃስም በ3:37 እንዲሁ በተመሳሳይ '' አንድን የእግዚአብሔር ቃል /ከእግዚአብሔር/ ኃይል /መንፈስ/ የሌለበት ሊሆን አይችልም።'' ይላል።
ስለዚህ የመጽሸፍ ቅዱስ ጥናት በዕለት በዕለት ሕይወታችን መተግበር ራሱን በራሱ ወደፊት የመግፈፋት ሂደት ነው። ከመጻሕፍቱ አንደዳንድ ምንበባቦች ከሚጠቃቅሱልን ግን ለመረደዳት፣ ለመተግበር ጥረት የማያደርጉ አንዳንድ የኃይማኖት ምሁራንና የብዙ አብያተ ክትስቲያናት ሰዎች አሉ። ጥሩ እንዲሰማን ብቻ ክርስቲያንነትን የሚያራምዱ ቀዝቃዛ አካዳሚሺያንን ግን ይህ ፈጽሞ አይመለከታቸውም።
''የእግዚአብሔር ቃል ፈጣን /ሕያው/ና ኃይለኛ ነው'' ''የእርሱ /የእግዚአብሔር/ ኃይል ደግሞ ቃል ነው።'' /ዕዝራ 4:12፣1:3/ ''የእግዚአብሔር ቃል... በአንተ በምታምነው በሚገባ ይሠራል።'' /1ሑልቀ 2:13/ በየሰዓቱ በቃሉ አማካይነት እግዚአብሔር በዕውነተኛ አማኞቹ አዕምሮ በንቃት ሥራውን ይሠራል። እየተማርህ ያለኸው ወንጌል መሠረታዊ መልዕክቱ ስለእውነተኛው የእግዚአብሔር ኃይል ነው። እንደዚህ ማድረግ ከፈቀድህ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ሕይወትህ እንዲለወጥ ያደርገኃል። የእግዚአብሔር መንፈስ /አዕምሮ/ በተወሰነ ደረጃ በሕይወትህ ለላት ለውጥ በማምጣት ክርስቶስ እንደገና በሚመለስበት ጊዜ /2ጴጥሮስ 1:4/ለሚጠ ብቅህ የእግዚአብሼር መንፈሳዊ ተፈጥሮ ያሸጋግርሃል። ያዘጋጅሃል። የጳውሎስ ስብከትም ''የእግዚአብሔርን'' መንፈስና ኃይል በመግለጽ /በአስረጂነት/'' ነበር። /1ቆረንቶስ 1:4/

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ ግግሽ እምነት በያዙ ሰዎች የታጠርን ነን፤ ምንም እንኳን ለክርስትስ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን የሰጡ መሆናቸውን እንደሚያምኑ ቢናገሩም በተመሳሳዩም በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ ይናገራሉ ግን እግዚአብሔር አካላዊ መሁኑን ለመቀበል አልቻሉም። መጻሕፍቱ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ መነሣሣት

የተጻፉ መሆናቸውን በመካድ እንዲሁም ከግላዊስ ሚታቸውና ከጽኑ እምነቶቻቸው በመንፈስ በመነሣሣት መጻፉ የበላይነት ያለው መሆኑንም ባለመቀበል የእግዚአብሔርን ኃይል ይክዳሉ።

''...የአምልኮት መልክ አላቸው። ኃይሉን ግን ክደዋል።''
/ጢሞት 3፡5/ ሲል የወህጌል ኃይለ ቃል ማመላከቱ ነው።

መሠረታዊነታችን በዓለም እየተላገጠበት ነው። ስለዚህም ጳውሎስና ሰባኪዎቹ ''የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና'' ብለዋል። /1 ቆረን 1፡18/

ይህን ሁሉ በአዕምሮአችን በመያዝ እያንዳንዳችን ምንጊዜም ከዚህ በበለጠ አክብሮት በእጃችን መያዝና ከምንጊዜውም የበለጠ ይገባን ዘንድና ትዕዛዛቱን ለመቀበል በጉጉት ለመንበብ አንችልምን?

## ለቃሉ የእግዚአብሔር ሰዎች አስተያየት /አኪኗን/

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን ስናገላብጥ የምንረዳው ፀሐፊዎች በመንፈስ ተነሣሥተው መጻፋቸውን ብቻ ሳይሆን ሌሎች አጋር ጸሐፊዎችም በመንፈስ ተነሣሥተው እንደጻፉ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። ጌታ ኢየሱስ ደግሞ በዚህ የላቀ ነው። ኢየሱስ ከመዝሙረ ዳዊት እየጠቀሰ ባስተማረበት ጊዜ ይህን ''ዳዊት በመንፈስ'' /ማቴ 22፡43/ በሚል ቃል ደጋግሞ ገልጾታል። ይህ የሚያሳየው ዳዊት በመንፈስ እየተነሣሣ መናገሩን ነው። ኢየሱስ ስለሙሴ ''ጽሑፎች'' /ዮሐንስ 5፡45..47/ ሲናገር ሙሴ ፔንታቴኡህ መጻፉን አመላክቷል። ከፍተኛ ጥልቀት ያላቸው ክርስትያኖች ዳዊት ይህን መጻፉን በጥርጣሬ ነው የሚቀበሉት። የክርስቶስ አባባል ደግሞ የእርሱን አቀራረብ ይቃረናል። ክርስቶስ የሙሴን ጽሑፎች

''የእግዚአብሔር ትዕዛዝ'' /ማርቆስ 7:8.9/ ብሎ ይጠራዋል። እነዚያ እምነት የጎደላቸው ተጠራጣሪዎች አብዛኃኙ ብሉይ ኪዳን አፈ ታሪክ እንደሆነ ይናገራሉ እንጂ ኢየሱስና ጳውሎስ ግን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደሆነ አጥብቀው ሰብከዋል። ኢየሱስ ስለንግሥተ ሳባ የተናገረውም ተቀባይነት ያለው ታሪካዊ ዕውነታ እንደሆነ /ማቴ 12:42/ እንጂ ተረት አይደለም።

የሐዋርያቱ መንፈስ ከጌታ ጋር አንድ ዓይነት ነበር። በጴጥሮስ ተመስሎ የክርስቶስን ቃሎች በጆሮዎቹ እንደመሳቱ የግል ተሞክሮውን ገልጿል። ይህም ''የትንቢያ ቃልን በበለጠ እርግጠኛ'' መሆኑ ላይ አጥሎበታል። /ጴጥሮስ 1:19..21/ የጳውሎስ ድብዳበረዎች ''ዝንደሌሎቹ መጻሕፍት ሁሉ'' መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑንም ጴጥሮስ አምኗል። የጳውሎስ ደብዳቤዎች እንደቢሉይ ኪዳን ሥልጣን /ምስክርነት/ የተሰጣቸው ናቸውና በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ ብዙ የሚነኩ ነገሮች አሉ። ስለወንጌል ራዕይና መልዕክት /ደብዳቤ/ በተጨባጭነት የሚገልጹ መሆናቸውን በሚነሣሣ ተመሳሳይ መንፈስ ብቻ ሳይሆን ወንጌል ላይ የተመዘገበውም በአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች መሆኑ ሊታመንበት የግድ ነው። የጳውሎስ መልዕክት ወደጢሞትዎስ ሰዎች የላከው ከተለያዩ የብሉይ ኪዳን ተወስደው በሐዲስ ኪዳን ተቀርፀዋል። 1 ጢሞ 5:18 ሲጠቅስ በዘሁልቁ 25:4 በሉቃስ ወንጌል 10:7 ይነበባል። ጳውሎስ መልዕክቱ ከክርስትስ የተሰጠ እንጂ ከራሱ አይደለም ብሏል /ገላትያ 1:11..12/ ይህን አባባሉን ሌሎች ሐዋርያት ይናገሩታል።

እግዚአብሔር ለእኛ በክርስቶስ ተናግሮዋል። /እብራ 1:2/ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነሣው ለሌሎች በመንፈሱ የተነሣሱ ጽሑፎችን /ለምሣሌ የጃሲር መጽሐፍ የናታን ጽሑፍ፣ የኤልዳስ ጽሑፍ፣ የጳውሎስ መልዕክት ወደቆረንቶስ ሰዎችና የዮሐንስ ሦስተኛ መልዕክት።/ ይህም የሚያመለክተን ዮሐንስ በሙሉ ስሜት ለቤተክርስቲያን የጻፈው፤ ግን ዲዮትሬፌስ አልፈጸመም እንዳለው።

አንዳንድ ጊዜ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቀስ በቀስ በመንፈስ መነሣሣቱን ይቀበላል፤ ግን ሐዋርያቱ ርስ በርሳቸዉ የአንዱ ጽሑፍ የሌላውን
በመንፈስ በመነሣሣት ነው የማለት ሐቁ ይህን አለማረጋገጡ ነው:: በመጽሐፍ ውስጥ ያሉት ደብዳቤዎችና ቃላቱ ማለትም በመንፈስ በመነሣሣት
ከሆነ ታምራዊ የመንፈስ ተሰጥዖ ስጦታ አለ ማለት ያስችላል:: /ቆረንቶስ 14:37፣ ዮሐንስ 4:1 ራዕይ 2:2/ ይህ ማለት ደግሞ በመንፈስ የተጻፉ ደብዳቤዎች ወዲያውኑ በመንፈስ ተነሣስቶ የተጻፈ ነው ብሎ መቀበል ማለት ነው:: አንዳንድ አግጣጨአ ያልያዙ መጽሐፉን የሰው ምርጫዎች የሚገቡበት ከሆነ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን የለውም ማለት ነው::

## 2.3 የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰዎች ባለው ግንኙነት ሥልጣኑን፣ ኃይሉን የመንፈስ ቅዱሱን/ ይጠቀምበት ዘንድ ሰዎችን ሥልጣን ሰጥቲቸዋል:: ይህ ማለት ግን የፈለጉትን እንዲያደርጉ አይደለም:: ሁልጊዜም መንፈስ ቅዱስን መጠቀም የምቻለው ለተወሰነ ዓላማ ይሆናል:: ያልሆነ ነገር በሚፈጸምበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተመልሶ ይወሰዳል:: የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሠራበት መንገድ የሚያመራው እግዚአብሔር በአዕምሮው ውስጥ ያለው በሚተገበርበት ጊዜ ብቻ መሆኑን ማስተዋል ይገባናል:: የእግዚአብሔር የኑቅ ዓላማ ይፈጸም ዘንድ ዓላማው ብዙ ጊዜ ሰዎች በሕይዎታቸው ለጊዜው ሲቃይ ሊቀበሉ ይችላሉ:: ስለሆነም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የሰዎች ዓለማዊ ስቃይ እንዲያጠፋላቸው አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል:: እንደዚህ ላለ ስቃይ ፈውስ አለማግኘቱ ደግሞ ከፍ ወደሚል ዓላማ እንድንሸጋገር እግዚአብሔር ስለፈለገ ነው::

ይህ ዛሬ የብዙ ክርስትያኖችን ፍላጎት ይቃረናል፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመራው በክርስቶስ ማመን ዋጋ ያለው ለአካላዊ ድህንነት ለምሣሌ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከህመም መፈወስ ይበጃል እንደማለት ነው፡፡ በእርስ በርስ ጦርነት በሚታመሱት እንደኡጋንዳ ባሉ ሀገሮች በመንፈስቅዱስ ስም የመፈወስ ስጦታዎች እንዳሏቸው በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎች ዘንድ መታመኑና መሠራቱ ይህን ያረጋግጣል፡፡ እንደዚህ ዓይነት አካሄዶች የሚያዘወትሩት ሰዎች በችግር ውስጥ ሲሆኑና የመፈወስ ፍላጎታቸው በከፍተኛ ደረጃ በሚከሰትበት ወቅትና ቦታ ነው፡፡ ይህ በራሱ ደግሞ በወቅቱ የተፈጠረውን የሰው ልጆች በከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸው ከዚያ ስቃይ ለመውጣት በመንፈስ ቅዱስ አካላዊ መፈወስን ይሻሉ፡

አያሌ ክርስቲያኖች ዛሬ ታምራዊ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዳላቸው ይናገራሉ፤ ይክክለኛ ዓላማችሁ ምንድን ነው ተብለው ሲጠየቁ ግን እርግጠኝነት የላቸውም፡፡ እግዚአብሔር ምንጊዜም መንፈሱን የሚልከው የተወሰኑ፣ የታወቁ ተግባራት እንዲፈጸሙ ሲፈልግ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የመንፈስ ስጦታዎች ተቀብለናል የሚሉ ሰዎች የተቀበሉትን የትኞቹ ጥቅሞች ላይ እንደሚያውሉ በእርግጠ ኝነት ዐውቀዋል፡፡ የሥራቸው መቃናት /መሳካት/ ሙሉ በሙሉ እንጂ በከፊል አይደለም፡፡ ብዙ አለመሳካትና ከፊል ፈውሶች የማግኘቱ ጉዳይ የማዳን መንፈሳዊ ሰጦታዎች አለን ለሚሉት የተቃረነ ነው የሚሆነው፡፡

የተለዩ ምክንያቶችና ዓላማዎች ከመንፈሳዊ ስጦታዎች በስተጀርባ መሆናቸውን በሚከተሉት ምሣሌዎች ያመላክታሉ፡፡ በአንዳቸውም ምክንያት ስጦታዎችን የመያዝ ጉዳይ በአዕምሮአችን ብቻ ያለ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስጦታዎች ተቀባዮችም መንፈስን በፈለጉት ሁሉ ማዋል አይችሉም፡፡ ስለእገዚአብሔር መንፈስ በምንናገርበት ጊዜ ሰዎች በፈለጉት አግጣጫ በመምራት የመጠቀም ሁኔታ በፍጹም የሚያሰብ

አይሆንም። ለጊዜው መጠቀሚያነት ከማሰብ ይልቅ የተሰጣቸው መንፈስ እግዚአብሔር በሚገልገው መንገድና ልዩ ፍላጎት ላይ ማዋሉ የመስጠቱ ዓላማና ምስጢር ነው። /ኢሳያስ 40፡13/

በእስራኤል የቆየ ታሪክ ድንኳን ይሠሩ ዘንድ ታዝዘዋል /ተነግሯቸዋል/ የመስዋዕት ማቅረቢያውንና ሌሎች ቅዱስ ዕቃዎችን ያስቀምጥበት ዘንድ እግዚአብሔርን የሚያመል ኩባቸውን
አስፍላጊ ዕቃዎች ሁሉ እንዲያዘጋጁ ዝርዝር ትዕዛዘት ተሰጥቲቸዋል።
ይህን ለመፈጸም እንዲመራቸው እግዚአብሔር መንፈሱን ለአንዳንድ
ሰዎች ሰጥቲል።
''በዕውቀት መንፈስ ተሞልተዋል የአሮንን አልባሳት ወዘተ ይሠራ ዘንድ'' /ዘሁልቁ 28፡3/
ከእነዚህም ሰዎች አንዱ ቤዛሊል'' በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም፣ በማስተዋልም፣ በዕውቀትም የእግዚአብሔር መንፈስ ተሞላበት፤ የጥበብን ሥራ ያስተውል ዘንድ በወርቅና በብር በንሐስም ይሠራ ዘንድ ለፈርጥ የሚሆነውን የዕንቁ ድንግት ይቀርጽ ዘንድ፣ እንጨቱንም ይፀርብ ዘንድ ሥራውንም
ሁሉ ይሠራ ዘንድ /ዘፀአት 31፡3..5/

ለሙሴ ተሰጥቶ የነበረው መንፈስ /ኃይል/ ከእርሱ ተወስዶ ለሽማግሌዎችና ለአለቆች መሰጠቱ በዘሁልቅ 11፡14...17 ላይ ተመዝግቧል። በሙሴ ያለውን መንፈስ ወስዶ በነሱ ላይማድረጉ
በሙሴ ላይ ያለውን ግፊት ለመቀነስና ሽማግሌዎችም በትክክል
እንዲፈርዱ መንፈስ ከሙሴ ተወስዶ ለእነርሱ ተሰጥቲቸዋል። ልክ ሙሴ ከመሞቱ በፊት የእግዚአብሔር የመንፈስ ስጦታ ወደዮሽዋ ተላልፏል። የሹዋም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ሕዝብ

በትክክል ይመራ ዘንድ:: /ኦሪት ዘጻግም 34:9/

የእስራኤል ሕዝብ ወደሀጋረቸው ከመግባታቸው በፊትና የመጀመሪያ ንጉሣቸው /ሳዑል/ እስከሚነግሥበት ጊዜ ድረስ የሚተዳደሩት ''ዳኞች'' ተብለው በሚጠሩት ነበር:: በዚህ ጊዜም በጠላቶቻቸው ብዙ ግፍ ይደርስባቸው ነበር:: ሆኖም የእግዚአብሔር መንፈስ በዳኞች በማደሩ ታምራዊ በሆነ መልኩ ኦትንኤልን፡ ጌዴዎንን፣ ጀፍዛህን፣ ከመሳሰሉ ወራሪዎች መዳናቸው ይህን ያረጋግጣል:: /መሣ 3:10፣ መሣ 6:34፣ 11:29/

ሣምሶን የሚባለው ሌላ ዳኛም አንበሳ ሊገድል የበቃው በመንፈስ ኃይል ነው::: /መሣ 14:5..5/፣ እንዲሁም ሣምሶን
30 ሰዎችን ሊገድልና /መሣ 14:19/ የታሰረበትን ገመድ በጣጥሶ
ለመጣል የቻለውም /መሣ 15:14/ በመንፈስ ኃይል ነው::
እንደዚህ ያለ መንፈስ ለሣምሶን የተሰጠው ለሁልጊዜ በተከታታይ
ሳይሆን በሚያስፈልግበት ጊዜ ተሰጠው:: በማይፈልግበት ጊዜ ደግሞ ተወሰደበት::

ከዚህ ማረጋገጥ ሚቻለው ማንም የመንፈስ ስጦታ የሚሰጠው
ለተወሰነ የእግዚአብሔር ዓላማና ጊዜ እንጂ

- የድነነት ዋስትና
- አንድ ሰው በሕይወቱ ሁሉ የሚሰጠው ነገር
- በእነርሱ ውስጥ ያለ ረቂቅ ጉልበትና
- ለሚያስፈነድቅ ተሞክሮ አይደለም::

ስለመንፈስ ስጦታዎች አሳማኝነት የመደብዘዙ ሁኔታ እንዳለ መነገር

አለበት። ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ። አንዳንድ ሰባኪዎችም የእግዚአብሔርን የመንፈስ ስጦታዎች ኢየሱስን ከመቀበላቸው ያስቀድማሉ። ጥያቄው መሆን ያለበት የትኞቹን ስጦታዎች? ሰዎች የትኛው የመንፈስ ስጦታ እንዳላቸው በትክክል አያውቁም ማለት አይታሰብም።

ሣምሶን እንዲገድል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶታል። /መሣ 14:5..6/ የሚያጊራው አንበሳ በፊቱ ቆሞ ባለበት ጊዜ የተሰጠው መንፈስ ለምን እንደሆነ በትክክል አውቂል። በአዕምሮው ምንም ዓይነት ጥርጣሬ አልነበረውም። ዛሬ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለን ምንም ልዩ ተግባር ግን ልናደርግ አልቻልንም፤ የሚሉ ሰዎችን አካሂድ ይቃረናል። ምን ዓይነት የመንፈስ ስጦታ ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑንም አናውቅም የሚሉይንም ይጸረራል።

በመጀመሪያው መቶኛ ዘመን የስጦታዎች መከሰት ምክንያቶች

በዓለም ወንጌልን እንዲሰብኩ ለሐዋርያቱ ተሰጠው የመጨረሻ ትዕዛዝ ነበር። /ማርቆስ 16:15..16/ ይህን አደረጉ የክርስቶስን ሞትና እንደገና ወደሰማይ ወደላከው አባቱ ማረጉን ነበር የመጀመሪያው ዋና ትምህርታቸው። እንደምናውቀው ሐዲስ ኪዳን በዚያን ጊዜ አለመኖሩ ይታወሳል። ስለናዝራዊው ኢየሱስ በገቢያ ቦታዎች በምኩራብ ቆመው ተናግረዋል። የሚናገሩት ታሪክ ሁሉ ከእስራኤል አናጢ ግን ፍጹም ከነበረ ብሉይ ኪዳንን ለመፈፀም መሞቱንና ደግሞም መነሣቱን መስበክ ግራ የሚያጋባ ይመስላል። እናም ኢየሱስ ተጠምቀው የእርሱን እንዲከተሉ በዚህን ጊዜ አዝዟቸዋል። በነዚያ ቀናት ደግሞ ሌሎችም ሰዎች አምልኮ ተከታዮች እንዲስፋፉ ሞክረዋል። በክርስቲያኖች የሚሰበከው መልዕክት ሁሉ ከራሱ ከእግዚአብሔር መሆኑን ለዓለም የሚረጋገጥበት የሆነ መንገድ መኖር ነበረበት። የተወሰኑ ዓሣ አጥማጆች የሰሜን እስራኤል ሰዎች ፍልስፍና ነው ከማለት ይልቅ።

መልዕክቶቹ ከእግዚአብሔር መሆናቸውን ለማረጋገጥ በሐዲስ ኪዳን የተመዘገበው የኢየሱስ ትምህርትና ሥራ በጊዜያችን ልንመረምር ይገባል፤ ግን በነዚያ ቀናት ከመጻፉና ጽሑፉ ከመውጣቱ በፊት በርሱ መንፈስ ቅዱስ እንዲጠቀሙ እግዚአብሔር ለሰባኪዎች ፈቅዷል። ይኸውም የሚናገራቸው ሁለ እውነቶች መሆናቸውን ሲያስምርበት ነው። በዓለም ዓይን የስጦታዎች ጥቅም የተለየ ክምያት ነበረው። የተጻፈ የሐዲስ ኪዳን አለመኖርም አዲስ አማኞች በእምነታቸው እንዳይገፉ አሐስቺጋሪ አድርጎት ይሆናል። ከመካከላቸው የወጣ ግልጽ የሆነ መፍትሔ እንዳይኖራቸው ከተለሰቱ አያሌ ተጨባጭ ችግሮች አንፃር በክርስቶስ ያላቸውን እምነት አጎልብተው በዚያ እየተመሩ የሚጓዙበት መንገድ የለም። በነዚህ ምክንያቶች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የቀድሞዎቹ አማኞች በመንፈስ እየተነሣሱ የሚመሩበት መመሪያ ነበር። ይኸውም መልዕክቶቹ በሐዲስ ኪዳን እስከተቀረፁበትና የኢየሱስም ትምህርት የጽፎ እስለሚሰራጭበት ጊዜ ነበር።

> እንደማንኛውም ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ መሰጠት ምክንያቶች ግልጽና ሰፊ ናቸው።
>
> «ወደላይ /ኢየሱስ/ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማርኮ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ» ይላል። ወደምድር ታችና ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው?
> ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላው ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው። እርሱም አንዳንዶች ሐዋርያት
> ሌሎችም ነቢያት ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።» /ኤፌሶን 4፡8..12/
>
> እንዲሁም ጳውሎስ ለሮም አማኞች እንዲህ ሲል ጻፈ።

«ትፀኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና ይህን ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ
እምነት አብረን በናንተ እንድጽናና ነው» /ሮሜ 1፡11..12/

የስጦታዎች ጥቅም ከወንጌል ስብከት ጋር መጣጣሙን በሚመለከት የሚከተለውን እናነባለን፡፡

«...ወንጌላችን በኃልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደእናንተ አልመጣምና በእናንተ ዘንድ ስለእናንተ እንዴት እንደነበርን ታውቃላችሁ፡፡»
/1 ተሰሎንቄ 1፡5፣ ቆረንቶስ 1፡5..6/

ጳዉሎስ ሊናገር ተቻለውም «...አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ
በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሰጠው በቀር ልናገር አልችልም፡፡»
/ሮሜ 15፡18..19/

ወንጌል ሰባኪዎችን በሚመለከት የሚከተለውን እናነባለን፡፡

«...የሰሙትም ለእኛ አጸኑት እግዚአብሔርም እንደራሱ ፈቃድ
በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ያምራትም መንፈስ ቅዱስንም በማከፋፈል አብሮ መሰከረለት፡፡» /ዕብራ 2፡4/

ቆጵሮስ ውስጥ የወንጌል ስብከት ዘመቻ በተካሄደበት ወቅት ስብከቱ በታምራት የተደረገ ነበር፡፡

«...በዚያን ጊዜ አገር ገዡ የተደረገው ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ፡፡» /ሐዋ 13፡12/
ስለሆነም

የሚሰጠውን ትምህርት ከልቡ እንዲያከብር በታምራቱ ተመርቷል።

በሐናንያም እንደዚሁ «... ምልክትና ድንቅ በእጃቸው ይደረግ
ዘንድ እየሰጠ ለፀጋው ቃል ስለመሰከረው ስለጌታ ገልጠ ው እየተናገሩ ተጅም ወራት ተቀመጡ።» /ሐዋ 14፡3/

ይህ ሁሉ ሐዋርያቱ በታማኝነት እንዲሰብኩ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለማጠቃለል ነው። «...እነርሱም ወጥተው በየሥፍራው
ሁሉ ሰበኩ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያፀና ነበር። /ማርቆስ 16፡20/

## ልዩ /የተወሰኑ/ ነገሮች በልዩ /የተወሰኑ/ ጊዜያት

ከእነዚህ የመንፈስ ስጦታዎች የተሰጡ ለተወሰኑ ነገሮች በተወሰኑ ጊዜያት ነው። ታምራዊ የመንፈስ ስጦታ ባለቤት ነኝ ብሎ ማሰብ ስህተት በአንድ ሰው ሙሉ ሕይወት ሁሉ ያለ ቋሚ ተሞክሮ መሆኑን ያሳያል። ኢየሱስ ከአረፈበት ጊዜ ወዲያውኑ በሃምሣኛው /ጴንጤቆስጤ ቀን/ በዓል ላይ ሐዋርያቱ ጴጥሮስም ጭምር «በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር» /ሐዋ 2፡4/ በመንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሣኖች ይናገሩ ጀመር። የክርስትናን ወንጌል በአስደናቂ መንገድ ይሰብኩ ዘንድ አለቆች ሊያሰሯቸው በሞከሩ ጊዜ«...ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ...» /ሐዋ 4፡8/ በሚያሳምን መልኩ መለሰላቸው ። ከእስር ሲለቀቁ በመንፈስ ስጦታዎች ተሞልተው ስብከታቸውን ገፉበት። «በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ ተናገሩ።» /ሐዋ 4፡31/

ጠንቃቃ አንባቢ አስቀድሞ በመንፈስ ተሞልተው እነዚያን ነገሮች አከናወኑ አይልም። የተወሰኑ ነገሮችን ለመከናወን ብአ ነበር በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት፤ ሆኖም በእግዚአብሔር ዕቅድ አኪያ ተከታዩን የእግዚአብሔር ሥራ ለመሥራት እንደገና ይሞላሉ። ጳውሎስም እንደዚሁ ሲጠመቅ «በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ» ነበር፤ ሆኖም ከዓመታት በኋላ እንደገና «በመንፈስ ቅዱስ መሞላት»ነበረበት ክፉውን /ግፈኛውን/ ሰው በማሳወር ለመቅጣት ሐዋ 9፡17፣ 13፡9/

ታምራዊ ስጦታዎችን በተመለከተ በሚናገርበት ጊዜ ጳውሎስ ስለቀፍሞዎቹ አማኞች «እንደክርስቶስ ስጦታ ተሰፍሮ ለእያንዳንዳችን ፀጋ ተሰጠን ብሏል። በግሪክ ቋንቋ «መንፈስ» ለሚለው ቃል «የተወሰነ ክፍል» ማለት ነው። «እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና /ዮሐ 3.34/

በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የታየው የመንፈስ ባለቤትነት ብዙ የተጠቀሰ ስለሆነ አሁን እንተረጉማለን።

## የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንፈስ ስጦታዎች

### ትንቢያ

በግሪክ ቋንቋ «ነቢይ» የሚለው ቃል ሲተረጎም የወደፊቱን /የመጪውን/ የእግዚአብሔር ቃል የሚናገር ..ማለትም የእግዚአብሔርን ቃሎች ይናገሩ ዘንድ በመንፈስ የተነሣሡ በየጊዜውም መጪው ጊዜ የሚያመጣቸውን ድርግቶች የሚናገሩ ናቸው። /2 ጴጥ 19፡21/ ስለዚህ፣ «ነቢያት»..የመተንበይ ስጦታ አላቸው «ከኢየሩሳለም ወደ አንፆኪያ ወረዱ፤ ከእነርሱም አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ርሃብ ሊሆን እንደሚችል በመንፈሱ አመለከተ። ይህመ በቄላውዴዎስ የቄሳር ዘመን ሆነ። /ሐዋ 11፡27..29/ እንደዚህ ዓይነት ከፍተኛና ልዩ

ትንቢያ ያም በአጭር ዓመታት የመፈጸም የግልጽ ባህርይ ያላቸው የመተንበይ ተሰጥዖ ተቀብለናል ከሚሉት ውስጥ የለም። እንዲሁም የጥንት ቤ/ክርስቲያን የመንፈስ ስጦታ በእርግጠኝነት ተላብሰው ስለነበር ከተተነበየ መከራ ለመጠበቅ ጊዜያቸውንና ሐብታቸውን ለዚሁ አውለዋል። «በመንፈስ የተሞሉ» እየተባሉ ዛሬ በሚጠሩት ቤ/ክርስቲያናት እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንደሚገኙ ጥቂት ምሣሌዎች አሉ።

## ፈውስ

ሐዋርያት እግዚአብሔር በመሬት ፍጹምነት መንግስቱ መቃረቡን በሚታይበት ሁኔታ ታምራትን በመስራት መልዕክቶቻቸው በዚያን ጊዜ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ በማጣጣም ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።
«በዚያን ጊዜ የዕውሮች ዓይን ይገለጣል የደንቆሮዎችም ጆሮ ይከፈታል። በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደሚዳቆ ይዘላል የድካም ምላስ ይዘምራል በምድረ በዳም ውሃ በበረሃም ፈሳሽ ይፈልቃልና።»

ስለእግዚአብሔር መንግሥት ሁኔታዎች የበለጠ ለመየት ጥናት 9.5 ይመልከቱ። የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ይመሠረት ዘንድ በግማሽ መስፈርት እነዚህ ቃል ኪዳኖች አይሟሉም። መንግሥቱም እዚህ ይሁን አይሁን አሻሚ አይሆንም። ስለዚህ የእግዚአብሔር የመልዕክቱ ታምራዊነት ማረጋገጫ የማያጠራጥና እርግጠኛ ቅርፅ መያዙ ነው። በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ ፈውሶች በቀደምት አማኞች እይታ ውስጥ ያሉ ናቸው። በቤተ መቅደሱ ደጅ ላይ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት ተቀምጦ ይለምን የነበረውን አንካሳ ለማኝ ጴጥሮስ መፈወሱ ዓይነተኛ ምሣሌ ነው። የሐዋ ሥራ 3.2 ይህን ይጠቅሳል።

« ወደመቅደሱም ከሚገቡት ምፅዋት ይለምን ዘንድ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሏት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ የስቀምጠ

-ት የነበሩ ከእናቱ መህፀን ጀምሮ አንካሳ የነበረ አንድ ሰው ነበረ»

«በቀኝ እጁም ይዞ አነሣው በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭሚቱ ፀና ወደላይ ዘሎም ቆመ፡፡ ይመላለስም ጀመር፡፡ እየተመላለሰም እተዘለለም እግዚብሔርን እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት መልካምም በሚሏት በመቅደስ ደጅ ስለ ምፅዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደሆነ አወቁት በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው፡፡
የሐዋ 3.7-11

ጴጥሮስ ወዲያውኑ ስለክርስቶስ መነሓት የሠበኩት ዜናውን በአየር ላይ የዋለው፡፡ የማያጠያይቅ ፡ የመያስተባብል ማስረጃ ይኸውም የተፈወሰውም ለማኝ ከፊታቸውም ስለሚያዩት የጰጥሮስ ቃሎች የእግዚብሔር ቃሎች መሆናቸውን በእርግጠ ኝነት አመኑ፡፡ የመቅደሱ ደጅ «በፀሎት ሰዓት» ሐዋ 3.1

በህዝብ ተጨናንቀው ነበር ፡፡ ቅዳሜ ጠዋት ሰዎች በሚጨናነቁበት የገበያ ቦታ ላይ ነበር የእግዚአብሔር ተአምራት በመስራት ስብከት የሚካሔደው፡፡ በተመሣሣይ በሐዋ ሥራ 5፡12 እንዲህ ይላል፣ « በሓዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው» ጴንጤቆስጣዊ ፈዋሾች የፈውስማ ተስብከት ሥራዎችን የሚያከናውኑት በመንገዶች ሳይሆን በቤተክርስቲያናት ከተሰበሰቡት አማኞች ብቻ ነው የታምራት ሥራዎችን በጉጉት የሚጠብቁት፡፡

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በቂ ተመክሮ ስለአለው መንፈስ ተቀብለናል ስለሚሉት ምስክርነት ስለሚሰጠ ው ይመረምራል፡፡
ስለፈውስ ፣ ስለከፊል ማዳን አይቼ እንደሆነ የግል ምስክርነቴ ማብራሪያ አያስፈልገውም፡፡ ታማኝ የእነዚህ በ/ክርሰቲያናት

አባላትይህ በየጊዜው እንደሚከናወን ያምናሉ። በብዙ አጋጣሚዎች አንዳንድ ጴስጤቆስጤ ጓደኞች ስለፈወስ አወያይቻቸዋለሁ። እነዚህ የመፈወስ ሃይሎች ስለመቀበላችሁ ላለማመን አልፈልግም። ግን እግዚአብሔር ኃይሉ ማን እንዳለው ማን እንደሌለው በግልጽ አሳይቷል። ስለዚህ እውነታውን እንድታሳዩኝ መጠየቁ ምክንያት የሌለው አይደለም። ከዚህ በኋላ ትምህርቱን ወደመቀበል አደላለሁ። እስከዚያው ከመጽሐፍቱ ጋር ይህነ ለማስታረቅ አልችለም። ግልጽ ያለ የመንፈስና የኃይል መቀበል ለእኔ ተሰጥቶኝ አያውቅምና። በአንጻሩ የመጀመሪያው መቶ ዘመን አርቶዶክስ አይሁዳውያን ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው የእግዚአብሔር ታአምራዊ ስጦታዎችን መቀበል እይፈልጉም። «ይህ ሰው ብዙ መልዕክቶች ያደርጋልና» ዮሐ 11፡ 47 የሚለውን ገና አልተቀበሉትም።

«በእነዚህ ሰዎች ምን እንስራ? የታወቀ ምልክት በእነርሱ እጅ
እንደተደረገ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ተገልጦአልና» አንሸሽገውም ዘንድ አንችልም ነበር» ሐዋ 4፡ 16
እንዲሁም ሐዋርያት በምላሶቻቸው ሲናገሩ የሰሙትም ሁሉ «የሚሉትን አጡ» ሐዋ 2፡ 6 ዛሬ ያ አይነቱ የለም። ጴንጠ ቆስጤዎች ቢጠየቁም ምላሽ አያገኙም። የጴንጤቆስጤ ቤተክርስቲያናት አካሄድ ለመለወጥ የሚነሱ አንዳንድ አባላት ይህን የመፈወስ ኃይል መቀበልን ተግባር አለማመናቸው እዚህ ላይ የሚነሳና ለክርክር የሚጋብዝ ነው። አንድ ተአምር በኢየሩሳሌም መደረጉ ዋና ዜና ቢሆን በሎንዶን ትራፍላርጋር አደባባይ ወይም በናይሮቢ ኔሐሩር ፓርክ እንዲሁ እውነተኛ ተአምር ቢፈጠር የእግዚአብሔር ታምራዊ የመንፈስ ስጦታዎች መኖር ያኔ በዓለም ተቀባይነት ያገኛል።

ጴንጤቆስጣዊ /ባለአምሳ/ ፈውስ ስሜታዊና ሥነ-ልቦናዊ እንጂ የእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥራ አይደለም። በአንፃሩም

«ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወሳክ ያኖራቸው ነበር»። ሐዋ 5፡ 15
«በዚያን ጊዜ አገር ገባሮው የተደረገውን በየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር ከጳፉ ተነስቶ የድንፍልያ ወደምትሆን ወደጴርጌን ወጣ። ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ሐዋ 3፡12-15
እንዲሁም በልስጥራ ከተማ የሚኖሩትም ብዙዎቹ አረመኔዎች ተቀበሉ ሐዋ 14፡ 8-13 ከመንፈሳዊ ስጦታዎች ባህርይና ተፈጥሮ የተነሣም እነዚህ የሚደረጉት በህዝብ ፊት ነው። ሌላ ትንተና የማያስፈልገው ፣ ችላ ተብሎም የማይታለፍ የእግዚአብሔር ኃይል በአሽከሮቹ በግልጽ መፈፀም ነው። ከክርስቶስ የፈውስ ተአምራት የአንዱ ውጤት ከላይ ካነሳነው ተመሣሣይ ውጤት ነበር።

« ተነስቶ ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁለት ፊት ወጣ። ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ ማር 2፡ 12

### ልሣኖች.. ሌሎች ቋንቋዎች .C

ጥቂቶቹ አክራሪ ሐዋርያት ዓሣ አጥማጆች ነበሩ.. ወንጌልን ለፍጥረታት ሁሉ በዓለም ለመስበክ ይችሉ ዘንድ ትልቅ ሥልጣን ተቀበሉ። /ማር 16፡15..16/ ምናልባትም የመጀመሪያ ስሚታቸው «ግን ቋንቋዎቹን አላወቋቸውም» ነበር። ለእነርሱ «በትምህርት ቤት ቋንቋ ጥሩ ውጤት እንኳን አልነበረኝም።» በትምህርት ቤት አልተማርሁምና። በሁሉም ዘንድ ተጽፎ የነበረው «መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደሆኑ አስተውለው አደነቁ።» /ሐዋ 4፡13 በጣም

ለተማሩ ሰባኪዎች /እንደጳውሎስ ያሉ/ እንኳን ቋንቋው መለኪያ አስገራሚ ነበር፡፡ የአዲስ ኃይማኖት መቀበል /መለወጥ/ በሚደረግበት ጊዜ አንዱ ሌላውን ያለመስማቱ ጉዳይ በጣም ችግር ነበረበት፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት በሌሎች ቋንቋዎች /ሣኖች/ የመናገር ስጦታና ትርጉሙንም ለመረዳት የሚያስችል ተሰጥዖም ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ «በልሣኖች» በመናገርና በብዙ «እንደገና በመወለድን በሚያራምዱ ክርስቲያኖች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡ «እንደገና መወለድን» የሚከተሉ ክርስቲያኖች በስሜት፣ በፍንጥዝያ ፈሊጥ ግን የተለየው ባዶ ጩኸትን «በልሣኖች» እንደተናገሩ ማስመሰል ተቀባይነት የሌለው ነውና፡፡ ይህ ማምታታት ጥርት ብሎ እንዲታይ በመጽሐፍ የተጻፈው «የሣኖች ትርጉም» በወጭ ቋንቋዎች» ማለት እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል፡፡

በአምሳኛው ቀን የአይሁዶች በዓል .. የክርስቶስ ወደሰማይ ማረጉን ተከትሎ ሐዋርያቱ «በመንፈስ ቅዱስ ሁሉም ተሞልተው ነበር፤ እናም

> በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ፡፡ ቁጥር ስፍር የሌላቸው
>
> በአንድነት መጡ፡፡ ተጨናነቁ እያንዳንዱ ሰው የሚናገረውም

ሌሎች በሚያውቁት እነርሱ ግን በማይረዱት ነበርና ሁሉም

እርስ በርሳቸው ተደነቁ።

እንዲህ በማለት «በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ

እንደሰጣቸው በሌላ ልሣኖች ይናገሩ ጀመር። ከሰማይም

በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በፀሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም

ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምጽ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ

እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን?

እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት

እንሰማለን? የጳርቴና የሜድ የኢላሜጤም ሰዎች በሁለት

ወንዝም መካከል በይሁዳም… የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ

በልሣኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ሁሉም ተገረሙና

አመንትተው እርስ በርሳቸው እንጃ ይህ ምን ይሆን? አሉ።..

/ሐዋ 2፡4...12/

ዛሬ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተቀብለናል እያሉ የሚቀበጣጥሩትን የሰሙ በሆኑ ኖሮ ያ በሌሎች ልሣኖች በእውነትም ለሚናገሩት የነበራቸው መደነቅ እጥፍ ድርብ በሆነ ተጋኖ ባልተቀበሉትም ነበር። ትርጉም ስለማትሰጠው መቀበጣጠር ፌዝ እንጂ አድናቆት አይገባውምና።

በሐዋርያት ሥራ 2፡4..11 እንደተቀመጠው «በልሣኖች መናገርና» «በቋንቋዎች መናገር» መካከል ያለውን ይልጽ ተዛማጅነት በሐዲስ ኪዳን በሌሎች ክፍሎች ላይ በአስረጂነት «ቋንቋዎች» እየተባሉ ተገልጸዋል። በዮሐንስ ራዕይ «ሕዝቦች፣ ሐገሮች፣ ልሣኖች» እየተባሉ ከአምስት ጊዜያት በላይ ተገልጸዋል። /ራዕይ 7፡9፣ 10፡11፣ 11፡19፣ 13፡7፣ 17፡15/

1 ቆሮንቶስ 14 በልሣኖች የመናገር ስጦታ ትዕዛዝ በተመለከተ ቁጥር 21 ነቢዩ ኢሳያስ 28፡11 ባይሁዳውያን አንጻር ምሥክርነት መስጠታቸውን በመጥቀስ ሲያትት

«በሌሎች ልሣኖችና በሌሎች ከንፈሮች ለሕዝቡ

እንዲናገሩ እንደማድረግ በህግ ተጽፎአል።» ብሏል።

ኢሳያስ 28፡11 ላይ ሲናገር «እስራኤልን የወረሩት በሌሎች ቋንቋዎች

በሌሎች ልሣኖች መናገራቸውን አያውቁም ነበር ብሏል፡፡

«ልሣኖች»ና «ከንፈሮች» መካከል ያለው ልዩነት «ልሣኖች»

የወጭ ቋንቋዎች ለማለት እንደሆነ ሲገልጽ መጻሕፍት እንደ

1 ቆሮን 14 በመሳሰሉት «ልሣኖች» የምንላቸው የሌሎች ቋንቋዎችን እንደሚያመለክቱ በሰፊው ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ በመጀመሪያዎቹ አብያተክርስቲያናት የመንፈስ ስጦታዎች ያልተሰጣቸው እንደተሰጣቸው እያስመሰሉ መናገራቸውን በመኮነን ጳውሎስ በመንፈስ ተነሣሥቶ ክፉኛ ይነቅፋቸው ነበር፡፡ ጳውሎስም «ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ ቢመስለው ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትዕዛዝ እንደሆነች ይወቅ» ብሏል፡፡ /1ቆረን 14:37/

የመንፈስ ስጦታዎች አለኝ የሚል ካለ መሰጠቱ ከእግዚአብሔር ትዕዛዛት የመጡና በመንፈስ መነሣሣትን የሚጠይቅ መሆኑን ሊቀበል ይገባል፡፡

ዛሬ እነዚህን ትዕዛዛት የሚክድ ማንም የእግዚአብሔርን ቃላት እያጠላላ መሆኑን መቀበል ይኖርበታል፡፡

«እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ

እሆናለሁ። የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል።

እንዲሁ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ

የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤ/ክርስትያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ

ፈልጉ። ስለዚህ በሥልጣን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ

በልሣን ቢጸልይ መንፈሴ ይጸልያል፤ አዕምሮዬ ይህን ያለፍሬ

ነው። እንግዲህ ምንድን ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ

በአዕምሮም ደግሞ እጸልያለሁ። በመንፈስመ እዘምራለሁ።

እንዲያማ ካልሆነ አንተ በመንፈስህ ብትባርክ ባልተማሩት

ሥራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ እንዴት አድርጎ

ለምሥጋናህ አሜን ይላል? አንተማ መልካም ታመሰግናለህ።

ሌላው ግን አይታነጽበትም።» /1 ቆሮን 14፡11...17/

በቤ/ክርስቲያኑ የተሰበሰቡት የማይረዱትን መናገር እርባና የለውም። «አሜን» በየፀሎት መጨረሻ ላይ የሚሰማው እውነተኛ ካልሆነስ ምን ጥቅም ይኖተዋል? «አሜን» ማለት

«እንዲህ ይሁን» ማለት እስከሆነ ድረስ «በዚህ ጸሎት የተባለውን እስማማበታለሁ» ማለት እስከሆነ ድረስ። ወንድሞችህ የማትረዱትን ቋንቋ መናገር አያንጻቸውምና ጳውሎስ ይላል....

«ነገር ግን ሌሎች ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ

ቃላት በልሣን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአዕምሮዬ

ልናገር እወዳለሁ። /1 ቆሮን 14፡19/

ይህ በጣም ግልጽ ነው። ስለኢየሱስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አጭር ዐረፍተ ነገር ብዙ ሰዓት በሌላ ቋንቋ ከሚሰበክልኝ የተሻለ ስሜት ይሰጠኛል። ጳውሎስ ከዚህ አኳያ እንዲህ ብሏል...

«እንግዲያውስ በልሣኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው

እንጂ ለሚያምኑ አይደለም። ትንቢት ግን ከሚያምኑ እንጂ

ለማያምኑ አይደለም። /1 ቆሮን 14፡22/

ስለዚህ በልሣን የመናገር አስፈላጊነት ወንጌልን ለመስበክ ለወጡት ነበር፤ ግን ዛሬ «ልሣን» ለአማኞች በቡድን፡ በየግል

ተሞክሮ የተሰጠ እንደሆነ አድርገው የሚያዩ ብዙዎች ናቸው። በሌሎች ቋንቋዎች ታምራዊ በሆነ መንገድ ወንጌልን ለመስፋፋት የሚነሱ ሰዎች እንዳሉ ስናፈላልግ የዚህ ተግባር ፈጻሚ ምሣሌዎች ለማግኘት እንኳን ከፍተኛ ጥረት መኖሩን እንረዳለን። በ1990 ዓ/ም መግቢያ ስለክርስቶስ በምሥራቅ አውሮጳ ለመስበክ የነበረውን አጋጣመሚ በመጠቀም ወንጌላውያን ማኅበራትሥነ.ጽሑፋቸውን ለመስፋፋት የቋንቋ ችግር ስለነበረባቸው በእንግሊዝኛ እንዲጠቀሙ ተገደዋል። የልሣን ስጦታዎች ቢኖሩ ኖረሮ ለዚህ እናውለው ነበርና።

«እንግዲህ ማኅበሩ ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም

በልሣኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች

ቢገቡ አብደዋል አይሏቸውምን? /1 ቆሮን 14፡23/

ይህ ነው በትክክል የሆነው። በምዕራብ አፍሪካ እስላሞችማ አረመኔዎች የተሳለቁብንም በዚህ ልሣን የመናገር ስጦታዎች ተቀብለናል በሚሉ አስቂኝ ባህርይ ባላቸው ነበር። ባለአምሳ /ጴንጤቆስጤ/ ማኅበር /ስብሰባ/ ሥራውን ወደ ጥግ አድርጎ አባካቱን በዚያ ሁኔታ ሲያያቸው አብደዋል ወይስ እንዴት ነው ብሎ መደናገሩ አይቀርም።

«በልሣን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው

በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም የሚተረጉም ባይኖር

ግን በማህበር መካከል ዝም ይበል።» / 1ቆሮን 14፡27/

በማንኛውም የፀሎት ጊዜ በልሣን የሚናገሩ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ ያስፈልጉ ነበር። ከሦስት በላይ በልሣን የሚናገር የተገኘበት አንዳችም ስብሰባ ስለመኖሩ ያጠራጥራል። በማኝከለላዊ ሎንደን እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች ያሉበት ደግሞም ጥቂት ፈረንሣይኛና ጀርመንኛ የሚናገሩ ቱሪስቶች የሚገኙበት ስብሰባ ላይ በልሣኖች የመናገር ስጦታ ያሏቸው ሰዎች ካሉ ተናጋሪዎቹ ሰባኪ

እንዴት አመሻችሁ?

የመጀመሪያው በልሣን ተናጋሪ.. በፈረንሣይኛ ይህንኑ

የሁለተኛው በልሣን ተናጋሪ.. በጀርመንኛ እንዲሁ ምናልባት ይሹም ነበር። ነገር ግን በየተራ መናገር ይገባቸዋል። በየተራ ካልሆነ ሁሉም ባንድ ጊዜ ከተናገሩ ውዥንብር ይፈጠራል። ነገር ግን ዛሬ ዛሬ የሚናገሩት በስሜት ስለሆነ «በልሣን መነናገር» ከብዙወዎቹ በአንድ ጊዜ የመጮህ ባህርይ እየያዘ መጥተቷል። አንድ ሰው ሲጀምር ለሎችም በፍጥነት ለመናገር

ሲጣደፉ አስተውያለሁ።

በልሣን መናገርና መተንበይ አብዛኛውን ጊዜ ሳይነጣጠሉ በአንድነት ተጠቅመው ይሆናል። በእግዚአብሔር መንፈስ የመሚነሣሣ በልሣን የመናገር መዕክት ወደፊት የሚመጣውን ይናገራልና። ሁለቱንም ስጦታዎች የመጠቀም ምሣሌ በሐዋርያት ሥራ 19፡6 ይገኛል። ያም ሆነ ይህ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚገኙበት በሎንደን ስብሰባ ላይ የተገኙት የፈረንሣይ ሀገር ነብኻዎች ብዛት ቢኖራቸው ተናጋሪው በፈረንሣይኛ ቋንቋ ቢናገር የተገኙት የእንግሊዝ ሰዎች «አይታነፁም» ነበር። ስለዚህ ሁሉም ይገባው ዘንድ በልሣን የሚነገረውን የሚተረጉም መኖር ይኖርበታል። በዚህ ምሣሌ ከፈረንሣይኛ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የመተርጎም ብቃት የመተርጎምን ችግር ለማቃለል አስፈላፊ ነውና።

> «አንዱ ይተርጉም የሚተረጉም ባይኖር ግን በማህበር
>
> መካከል ዝም ይበል።» /1 ቆሮን 14፡27/

በልሣኖች ሌሎች ቋንቋዎችን እንናገራለን፣ ግን የምንናገረው የሚረዳ ማንም የለ የሚሉ ዘመናውያን ተርጓሚ እስከሌለ ድረስ ትዕዛዛቱን በልሣን የመናገር ስጦታን ያለአግባብ መጠቀም /ማጭበርበር/ ይሆናል።

> «…እና ነቢያት መንፈሶች የነቢያት ተጠሪዎች ናቸው
>
> እግዚአብሔር የውዥንብር ደራሲ ሳይሆን የሰላም
>
> እንጂ የቅዱሳን ማህበራትም ሁሉ እንዲሁ።

/1 ቆሮን 14:32..33/

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንድን ሰው ከዘወትር ንቃት ሕሌና አውጥቶ ይወስደዋል ከሚል ተሞክሮ ጋር አይያያዝም። መንፈስ በተጠቃሚው ቁጥጥር ሥር የሚውል እንጅ ያለፈቃዳቸው በደመ.ነፍስ በመንፈስ ይናገሩ ዘንድ ወደላይ የሚያወጣቸው ኃይል አለ ማለት አይደለም። ክፉ መናፍስት «ያልዳኑትን» ይይዟቸዋል የሚያሰኝ ሃሳብ ስህተት ነው፤ ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ አማኞቹን በመንፈስ ይሞላቸዋል። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተቀበሉት አቀጥጥር ሥሩ የሚውልና ለተወሰነ ዓላማ ተፈጻሚነት ብቻ የሚሰጥ ነው።

«በማህበራችሁ ያሉ ሴቶቻችሁ ዝም ይበሉ

እነርሱ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።

ነገር ግን ትዕዛዙን እንዲጠብቁ ታዝዘዋል

ሕጉም ደግሞ እንደዚህ ይላልና።» /1ቆሮን 14:34/

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመጠቀም በተመለከተ ሴት በማህበሩ አገልግሎት ጊዜ እነዚህን መጠቀም እንደሌለባት በማይካድ መልኩ ተቀምጧል። ይህ በአሁኑ ጊዜ በሚታየው ቅብጥርጥረሮሽ ፊት እንዲህ ያለውን ሌላው በስሜት ተቀብሎ ስለሚያስተጋባ ከዚህ ይኩረት አልተሰጠ ውም። ማን ምን እንደተናገረ ሁሉም በአንድ ጊዜ በሚናገሩበት ሁኔታ ይህን መቀበል ከቶ አመቺ አይደለምና።

ሴቶች እንዲሁ ክጆች ማንኛውም በስብሰባው ላይ የተገኘ አዕምሮው በፈቀደ ነፍንጥዝያ የሚናገረው ሁሉ በልሣን ከመናገር የራቀ ነው።

ሴቶች በልሣን መናገር «መተንበይ» እንደሚችሉ አስመስሎ በዘመናውያን ማኅበራት ማስተጋባቱ ከላይ የተጠ ቀሰውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ጋር ተቃርኖ አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ ሴት የሚጠላ ስለነበረ ነው የሚለው የሚያሳዝንና የሚያስቅ ነው። እንደገና መጻሕፍትን እንይ።

«ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስልው ይህች

የጻፍኩላችሁ የጌታ ትዕዛዝ እንደሆነች ይወቅ» /1ቆሮን 14፡37/

## 2.4 የስጦታዎች መሰረዝ /መወሰድ/

ዓለም አሁን ያለበችን ለመለወጥ ክርስቶስ ከተመለሰ በኋላ ታምርአዊ የእግዚአብሔር መንፈስ ስጦታዎች አማኞች እንደገና ይገለገሉባቸዋል። ስለሆነም፣ ስጦታዎች «አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን የሚያየውን ስጦታ

የቀመሱትን በመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን

መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን

የዓለምን ኃይል የቀመሱትን» /ዕብራ 6፡4..5/

ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ምዕመናን እነዚህ ስጦታዎች ይሰጧቸው የሚለው ዕውነታ አሁን ለማንም ላለመሰጠቱ በቂ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡ ማንም አዕምሮውን ከፍቶ የዓለምን ነባሪ ሁኔታ ለሚያስተውል የክርስቶስ መመለሻ ጊዜ መቃረቡን ይረዳል፡፡

የመንፈስ ስጦታዎች በተሰጡበት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመንና በሁለተኛው የክርስቶስ መመለስ መካከል ባለው ወቅት ስጦታዎች ተወስደዋል፡፡

«....ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ትንቢት ቢሆን

ግን ይሻራል፡፡ ልሣኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፡፡ ዕውቀትም

ቢሆን ይሻራል፡፡ ከዕውቀት ከፍለን እናውቃለንና

ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና ፍጹም የሆነው

ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል፡፡» /1 ቆረን 13፡8..10»

ስጦታዎች ቋሚ ሳይሆኑ ጊዜያዊ ናቸውና፡፡

በመጀመሪያው መቶኛ ክፍለ ዘመን ተልከው የመንፈስ ስጦታዎች ተመልሰው መወሰድ የነበረባቸው «ፍጹም የሆነው

እግዚአብሔር በመጣበት ጊዜ» ይህ ደግሞ እንደዳግሚያ የክርስቶስ መምጣት ሊሆን አይችልም።

የተሟላው ነገር የመተንብይ ስጦታዎች የነበሯቸውን የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች ከፊል ዕውቀት የሚተካ ነው። የእግዚአብሔርን ከመንፈሳዊ ቃላት ተነሣሽነት መተንበይ የወደፊቱን የመናገር ስጦታ አስታውስ።

በመጀመሪያው መቶኛ ዓመት እንደምናውቀው አማካኙ አማኝ ስለሐዲስ ኪዳን የሚያውቀው ትንሽ ነበር። ስለአንዳንድ ተጨባጭ ጉዳዮች የሰማቸውም አንዳንድ የትንበያ ቃሎች ከማኅበሩ ሽማግሌዎች ሊሆን ይችላል። የሰማው ወይም ያወቀው ጥቂት ስለክርስቶስ ሕይወትና ስለጳውሎስ ደብዳቤዎች ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር የትንበያ ቃሎች ተሟልተው ከተሰራጩ በኋላ ግን በመተንበይ ቃሎች መሞላት አስፈላጊ አልነበረም። ይህ በሐዲስ ኪዳን ተሟልቷል…

«እርሱ /ኢየሱስ/ ወደላይ /ወደሰማይ/ ሲያርግ ለሰዎች

በመንፈስ መሞላት ሰጣቸው፤ በክርስቶስ አካል ይታነፅ

ዘንድ፤ በዕምነት አንድነት ሁላችንም እስክንምጣ ድረስ

የእግዚአብሔር ልጅ ዕውቀት ወደፍጹማን ሰዎች እስኪደርስ

ወደዚያና ወደዚህ የምንወዛወዝ በእያንዳንዱ የትምህርት ነፋስ

ልጆች አይደለንም። /ኤፌሶን 4፡8..14/

በመጀመሪያ መቶኛ ዘመን በመንፈስ መሞላት ስጦታዎች ፍጹም እስኪሆኑ ወይም የበሰሉ ሰዎች እስኪሆኑ ድረስ ተሰጥተዋል። ስለዚህም 2 ጢሞ 3፡16..17 ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል።

«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ

ያለበት ሁሉ.....» /2 ጢሞ 3፡16...17/

ኮል 1፡28 እንዲሁ «ፍጹምነት የሚመጣው ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ ከመስጠት ነው ።» ሲል ያስተምራል።

አንድ ጊዜ መጻሕፍቱን በሙሉ ካገኘን በኋላ በተለያዩ ሌሎች ትምህርቶች በየማህበራት ቢሰጡ መደነቅና መደናገር አይኖርብንም ያለው አንድ መጽሐፍ ብቻ ነውና።

«...በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ ዕውነት ነው»

/ዮሐንስ 17፡17/ የመጽሐፉን የተለያዩ ገጾችን እያገላበጥን በምናጠናበት ጊዜ «የእምንት አንድነት» እናገኛለን። አንዱ ዕምነት ኤፌ 4፡13 ላይ የሚነበበው» እውነተኛ ክርስቲያኖች ያንን አንድ እምንት ለመያዝ ይደርሳሉ። በዚያ ስሜት ፍጹማን ይሆናሉ» ይላል።

ኤፌሶን 4፡14 ታምራዊ የተሰጥዖዎች ትምህርት መቀበልን እንዴት ከመንፈሳዊ ልጅነት ትንበያ ጋርም እንዴት እነዚህ ተሰጥዖዎች ተመልሰው እንደሚወሰዱም እንደገለጸ አስተውል። የመንፈስ ተሰጥዖዎችን ስለመቀበል ያለው ትርምስ የመንፈስ ብስለት ምልክት አይደለምና። 1 ቆረን 13፡11 የሚለው ይህንኑ ነው። ይህን ጽሑፍ በማስተዋል እያነበበ የመጣ ሰው ስለእግዚአብሔር ቃል የተጻፈውን በጥልቅ ማድንቅና በዚያ በኩልም እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ገልጦ ፍጹም በተሟላ መልኩ መምጣቱ የሰጣቸው ቃሎች ፍጹምነት ያላቸው መሆናቸውን በደስታ መቀበልና ትህትና በተሞላበት ታማኝነት ምላሽ መስጠት ይገባናል።

# ጥናት 2 ጥያቄዎች

«መንፈስ» ለሚለው ቃል ከሚከተሉት ውስጥ .1
የትኛው ትርጉም ይሆናል?

ሀ/ ኃይል ሐ/ ቅዱስ

ለ/ እስትንፋስ መ/ አቧራ

2/ መንፈስ ቅዱስ ምንድን ነው?

ሀ/ አንድ ግለሰብ
ለ/ ኃይል

ሐ/ የእግዚአብሔር ኃይል

መ/ የሥላሴ አካል

3/ መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ?

ሀ/ ሰዎች የራሳቸውን የግል ሀሳቦች ነው የጻፉት

ለ/ እግዚአብሔር ያለው የመሰላቸውን ሰዎች ጻፉት

ሐ/ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነሣሱ /የተሞሉ/ ሰዎች የጻፉት

መ/ አንዳንዶቹ ክፍሎች በመንፈስ መሞላት ሌሎች ባለመሞላት

4/ በእግዚአብሔር ታምራዊ ስጦታዎች መሞላት ከሚከተሉት ውስጥ የትኞቹ ምክንያቶች ናቸው?

ሀ/ በቃል ወንጌልን መስበክ ለመደገፍ

ለ/ የመጀመሪያዎቹን አብያተ ክርስቲያናት /ማህበራት/

ሐ/ ሕዝቦች ጻድቅ ይሆኑ ዘንድ ለማስገደድ

መ/ ሰብአዊ ችግሮች ሐዋርያቱን ለማዳን

5/ የእግዚአብሔርን ዕውነታ ከየት መማር እንችላለን?

ሀ/ ከፊሉን ከመጽሐፍ ቅዱስ ከፊሉን ከራሳችን አስተሳሰብ

ለ/ ነገሮችን በቀጥታ ከሚነገረን ከመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን

ከማንበብ ሌላ

ሐ/ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ

መ/ ከኃይማኖት አስተማሪዎች /ቀሳውስት/

# 3. የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች

# 3.1 የእግዘ1አብሔር ቃል ኪዳኖች .. መግቢያ

ጥናታችን አሁን በደረሰበት ነጥብ ስለእገዚአብሔርና እንዴትም እንደሚሠራ መግባባት ላይ ደርሰናል። ይህን ማድረጋችን አያሌ የተለመዱ አለመግባባቶችን

አስወግደናል። አሁን እግዚአብሔር «ለወደዱት ቃል የገባላቸውን» ነገሮች በአሉታዊ መልኩ ማየት ያስፈልገናል። ይኸውም «የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመጠበቅ»። /ዮሐንስ 14፡15/

በብሉይ ኪዳን የተገለጹት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች የዕውነተኛ ክርስቲያን ተስፋ የያዘ ነው። ለሕይወቱ ፈተና /ፍርድ/ ላይ በነበረበት ሰዓት መጭውን ሽልማት በመጠበቅ ጳውሎስ ያሉትን ነገሮች ሁሉ ለማጣት ተዘጋጅቷል።

> «አሁንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአባቶቻችን ስለተሰጠ ው
>
> ስለተስፋ ቃል አለኝታ ልፋረድ ቆሜአለሁ። ወደዚህ ወደተስፋ
>
> ቃል አሥራ ሁለቱ ወገኖቻችን ሌሊትና ቀን በትጋት ያመለኩ

ይደርሰ3 ዘንድ አለኝታ አለባቸው፡፡ ስለዚህ አለኝታ ንጉሥ

አግርጳ ሆይ ከአይሁድ እከሰሳለሁ» /ሐዋ 26፡6..7/

ከሕይወቱ አብዛኛውን ያውለው የነበረው በስብከት በነር፡፡

«እኛንም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፍ የምሥራቹን ለእናንተ

እንሰብካለን፡፡ ይህን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር

ደግሞ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደተጻፈ»

/ሐዋ 13፡32..33/

ከሙታን ተለይቶ የመነሳት ያለን ተስፋ ለፍርድ ኢየሱስ ዳግም እንዲመጣና የእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚመጣ ጳውሎስ እምነቱ መሆኑን አብራርቷል፡፡

/ሐዋ 25፡25፣ 28፡20...31/

ይህ ሁሉ የሚያሽቆለቁለን ብሉይ ኪዳን ስለዘለዓለማዊ ሕይወት ወደሚያመራው ተራ የእስራኤል ታሪክ ብቻ ሆኖ ወደሚቀር አፈ ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ከ2000 ዓ/ም በፊት በኢየሱስ አማካይነት ዘለዓላማዊ ሕይወት እንደሚሰጠን በድንገት አልወሰነም። ከእርሱ ጋር ከመጀመሪያው ጀምሮ ዓላማው...

> «የዘለዓለማዊ ሕይወት ተስፋ ያም የማይዋሸው እግዚአብሔር
>
> ዓለም ሳይፈጠር የሰጠው ተስፋ፤ ነገር ግን በሂደት ቃሉን
>
> የገለጸው በስብከት ነበር። /ጢሞ 1፡2..3/
>
> «ከአባቱ ጋር ተነበረው ወደእኛው የተገለጸው ዘለዓለማዊ
>
> ሕይወት ነው።» /ዮሐ 1፡2/

ለሕዝቦቹ የሰጠው ዘለዓለማዊ ሕይወት ከመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ የእርሱ /የእግዚአብሔር/ ፍላጎት እንደነበረ ስታይ እንደዚሁ በብሉይ ኪዳን እንደሰፈረው

ከሰዎች ጋር በነበረው ግንኙነት 4000 ዓመታት ሙሉ ዝም አይልም ነበር። በእርግጥ ብሉይ ኪዳን በትንቢያና በተስፋ የተሞላ ነው። ያም እያንጻንጹ እግዚአብሐሔር ለሕዝቡ ያዘጋጀውን ይህነ ተስፍ በበለጠ ትንተና የሰጥቷል። ለዚህም ነው ለድነነታችን ጠቃሚ የሆነው እግዚአብሔር

ለአይሁዳውያን አባቶች የሰጠው ተስፋ ልንረዳ የሚገባን:: ይህን ያህል ካልን ጳውሎስ በኤፌሶን ያሉትን አማኞች ያስታወሳቸው እነዚህን ከማወቃቸው አስቀድሞ እነርሱ «ያለክርስቶስ ነበሩ ከእስራኤል ውጭ ሆነው፣ ቃል ኪዳን ከተሰጣቸው የተለዩ ባዕዶች ተስፋ የሌላቸው በዓለም ላይ ያለእግዚአብሔር» ይላቸዋል:: /ኤፌ 2፡12/

የቀድሞው አረመኒያዊ እምነቶቻቸው ጥቂት ተስፋ ስለእግዚአብሔር ዕውቀት እንደሰጣቸው ያለጥርጣሬ ቢረዱም እንኳን ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከእግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋዎች የአለማወቅን ከባድነት ያመለክታል:: ይህ ማለት በተጨባጭ «ተስፋ አለመኖርና በዓለም ውስጥ ያለእግዚአብሔር» ማለት ነው:: ጳውሎስ እንዴት ክርስቲያናዊ ተስፋን እንደገለጸው አስታውሱ:: «ከእግዚአብሔር ዘንድ /ለአይሁዳውያን/ አባቶቻችን ስለተአጠ ው ስለተስፋ ቃል አለኝታ ክፉረድ ቆሜአለሁ» /ሐዋ 26፡6/

ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ናቸው በዚህ በብሉይ ኪዳን ክፍሎች ክብደት የሚሠጡት:: «ክርስትያንነት» በሐዲስ ኪዳን ላይ የተመሠረተ ኃይማኖተትነት እያወረዱት መጥተዋል:: ያኤም ጥቂት ቁጥሮች ከመጽሐፍ ጠቅሷለ:: ኢየሱስ በተገቢው መንገድ ክብደት የሚገባውን በግልጽ እህዲህ ሲል አስቀምጧል::

«...ንሠሓ ይገባሉ አለ ሙሴንና ነቢያትንም የማትሰሙ ከሆነ

ከሙታንም እንኳን አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።»

/ሉቃስ 16፡31/

ኢየሱስ ከሙታን ተለይቶ መነሣተን ማመን ይበቃል ብሎ ተፈጥሮአዊ አዕምሮአችን ሊያስብ ይችላል። /ሉቃ 16፡30/ ነገር ግን ኢየሱስ አለ ያለ ብሉይ ኪዳን ጠንካራ ግንዛቤ ይህ በተሟላ መልኩ የሚቻል አይሆንም ነበር። የጌታን ስቅለት ተከትሎ የደቀመዛመረቱ እምነት መንኮታኮት ተሚያሳየው ለብሉይ ኪዳን የነበራቸው ጥንቃቄ የተሞላበት እይት መጓደል ነው።

«እነርሱም እናንተ የሚያስተሉ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ

ልባችሁ ከማመን የዘገየ ክርስቶስ ይህንን መከራ ይቀበል ዘንድና

ወደክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን አላቸው። ከሙሴና

ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለእርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን

ተረጎመላቸው።» /ሉቃስ 25፡25..27/

ብሉይ ኪዳን በሙሉ ስለእርሱ እንዴት ትኩረት ሰጥቶ እንደተናገረ አስተውሉ። ስለብሉይ ኪዳን የተጻፉትን ቃላት ደቀመዛሙርቱ አላነበቡትም፣አልሰሙትም አልነበረም፤ ይልቁንም በትክክል ስለአልተገነዘቡት /ስለአልተረዱት/ በእውነት አላመኑባቸውም እንጂ. ስለዚህ ትክክልኛ የእግዚአብሔር ቃል ግንዛቤ ለመግኘት እንደዚሁ እርሱን ዝም ብሎ ከማንበብ ይልቅ እውነተኛ እምነትን ማበልጸግ አስፈላጊ ነው። አይሁዳውያን ብሉይ ኪዳንን ዓይናቸውን ሸፍነው በማንበብ የታወቁ ነበሩ፣ ሆኖም ስለኢየሱስና ስለወንጌሉ የተባለውን ስለአልተረዱ በእርግጠኝነት ያነበቡትን አገናዝበው አላመኑበትም። ኢየሱስም እንደዚህ ብሎ ነገራቸው..

«.. ሙሴን ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ

ስለእኔ ጽፎልና መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን

እንዴት ታምናላችሁ?» /ዮሐ 5፡46...47/

ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስን ቢያነቡም ቅሉ ስለኢየሱስ ትክክለኛውን መልዕክት አያዩም ነበር፤ ምንም እንኳን ስለድኅነት እትግጸኞች ቢመስላቸውም።

ኢየሱስም ለእነዚህ እንደዚህ መንገር ነበረበት...

«ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ /ሐዋ 17፡11/

ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ። እናንተ በመጻሕፍት

የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን

ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው»

/ዮሐ 5፡39/

የብሉይ ኪዳን ጥቂት ትምህርቶችና አጋጣሚ ዕውቀት ያላቸው ብዙ ሰዎች ይኖራሉ። ይህ ድንገተኛ አጋጣሚዎች ዕውቀት ከዚየዘም ከዚያም የለቃቀሟቸው ናቸው። የክርስቶስ አስደናቂ መልዕክትና ተእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ስብከት ይጠ ፋቸዋል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ዋና ዋና የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳኖችን ትክክለኛ ትርጉም በማሳየት ከዚያ ዓይነት አቋም እንዲያላቅቅ ማድረግ ነው።

- በኤደን የአትክልት ቦታ
- ለኖህ
- ለአብርሀም
- ለዳዊት

ለእነዚህ መግለጫ /መረጃ/ በአምስቱ የመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት /ዘፍጥረት..ዘዳግም/ ላይ በሙሴና በብሉይ ኪዳን ነቢያት ተጽፎ ተጽፎ ይገኛል። የክርስቲያናዊ ወንጌል መሠረታዊ ነገሮች ሁሉ እዚያ ይገኛሉ። ጳውሎስ የወንጌል ስብከቱ እዚያ እንደሚገኙ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል።

»... ነቢያትና ሙሴ ይሆን ዘንድ ያለውን ክርስቶስ መከራ

እንዲቀበል በሙታንም ትንሣኤ ለሕዝብ ብርሃንን

በመጀመሪያ ሲሰብክ እንዳለው ከተናገሩት በቀር አንድ ስንኳ

የተናገርኩት የለም።» /ሐዋ 26፡22...23/

እናም በመጨረሻዎቹ ቀናትም ዝግሬው ያው ተመሳሳይ ሆኖ ቀረ።

«.... ስለእግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ስለ

ኢየሱስም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ እያስረዳቸው

ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ ድረስ ትገልጥላቸው ነበር።

/ሐዋ 28፡23/

የጳውሎስ ተስፋ እኛንም የሚያነቃቃ ተስፋ መሆን ይኖርበታል። የሕይወቱ እጹብ ድንቅ ብርሃን ነበር። ይህም ኮስታራ /ምራቁን የዋጠ/ ለሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ መሆን ይኖርበታል። በመነቃቃቱ ተኩራርተን መጻሕፍትን መመርመር አሁን እንችላለን።

## 3.2 ቃል ኪዳን በኤዴን

የሰው ልጅ ውድቀት አሳዛኝ ታሪክ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላት ተጽፎ ይገኛል። የእግዚአብሔርን ቃል ያለአግባብ

ሔዋንንም ትዕዛዙን እንድትሽር በማሳሳቱ እባቡ ተረግሟል። እምነት በማጉደላቸው ሰውዬውና ሴቲቱ አይቀጡ ቅጣት ተቀጡ። እግዚአብሔር ለእባቡ የሚከተለውን ባለበት ወቅት የተስፋ ጮራ ፈነጠቀ።

> «...በአንተ በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከከል
>
> ጠላትነትንም አደርጋለሁ። እርሱ ራስህን ይቀጠ ቅጣል።
>
> አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።» /ዘፍጥ 3፡15/

ይህ ጥቅስ /ቁጥር/ ጠቅለል ያለ ስለሆነ በዚህ ውስጥ የተካተቱት ልዩ ልዩ ነገሮች በጥንቃቄ መተርጎም ያስፈልገናል። «ዘር» ማለት ወራሽ ወይም «ልጅ» ማለት ይሆናል፤ ግን ከልዩ ዘር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሕዝቦች ማመላከት ሊሆን ይችላል። የአብርሃን «ዘር» ኢየሱስ መሆኑን ቆየት ብለን እናየዋለን። /ገላት 3፡27..29/ «ዘር» የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው ወደ ወንድ ዘር ነው /1 ጴጥ 1፡23/ እውነተኛ ዘር የአባቱን ባህርያት /መለያዎች/ 23/ እውነተኛ ዘር የአባቱን ባህርያት /መለያዎች/ 23/ እውነተኛ ዘር የአባቱን ባህርያት /መለያዎች/ ይይዛልና።

የእባቡ ዘር ተሚያመለክተው እባቡን የመሰለ ቤተሰብን ሁሉ ይሆናል።

.. የእግዚአብሔርን ቃል ማወላገድ

.. መዋሸት

.. ሌሎቹን ወደኃጢአት ማምራት

በጥናት 6 ይህን የሚያደርግ ሰው እንደማይኖርና በእኛ ውስጥ

«... ከእንግዲህ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌ ሰዎችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን የሞተስ ከኃጢአት ጸድቋልና።»

.. «ለፍጥረታት ሰው» /ቆሮን 2፡14/

.. «ፍተኛ ኑሮአችሁን እያሰበሰችሁ እንደሚያታልል ሞኞች የሚጠላውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ።» /ኤፌ 4፡22/

.. «አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር... /ኮል 3፡9/

እንደሚኖር እናያለን።

በእኛ ውስጥ ይህ የኃጢአት «ሰው» የእባብ ዘሩ በመጥሐፍ «ዲያብሎስ» የሚባለው ነው። የሴቲቱ ዘር የተለየ ግለሰብ መሆኑ ነውና። «በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ። እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል።» /ዘፍጥ 3፡15/

ይህ ሰው የእባቡን ዘር /ኃጢአትን/ በቋሚነት መቀጥቀጥ ነበረበት። እባቡን ራሱ ላይ መቀጥቀጥ አዕምሮው ራሱ ላይ እንደመሆኑ ጭንቅላቱን /አዕምሮውን/ የሚያመላክት ነው።

> «... ከዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠን አሁን
>
> ግን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ታይቷል።
>
> አርሱ ሞትን ሽሮአልና። እኔ ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም
>
> አስተማሪ እንድንሆን በተሾምኩበት ጊዜ በወንጌል ሕይወትንና
>
> አለመጥፋትን ወደብርሃን አውጥቶአል።» /2 ጢሞ 1፡10/

ሴቲተ ዘር ተመራጭ ሊሆን የሚችለው ብቸኛ ሰው ጌታ ኢየሱስ ነው።

«እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሣሌ

በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጓልና እንደመንፈስ

ፈቃድ እንጂ እንደሥጋ  ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ

የሕግ ትዕዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኮነነ፡፡»

/ሮሜ 8፡3/ ይኸውም መጽሐፍ ዲያብሎስ ተብሎ የሚጻፈው

የእባቧ ዘር ነው፡፡  ኢየሱስ «እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ

እንደተገለጠ ታውቃላችሁ» /ዮሐ 3፡5/

«ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ /ትርጉሙም «አዳኝ»/ እርሱ ሕዝቡን

ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል፡፡ /ማቴ 1፡2/

ኢየሱስ በጥሬ ትርጉሙ «ከሴት የተወለደ» /ገላ 4፡4/ የማርያም ልጅ ነበር፤  ምንም እንኳን አባቱ እግዚአብሔር ቢሆንም፡፡  ስለዚህ በዚህ ስሜት የሴት ዘር ነበት ማለት ነው፡፡  እግዚአብሐር ለሌሎች የሴት ዘሮች ግን ባልሰጠው መንገድ የተፈጸመ ይህ የሴት ዘር በጊዜያዊ ኃጢአት የቆሰለ ነበር፡፡  የእባቧ ዘር ነውና፡፡  «ሰኮናውን ትቀጠቅጠዋለህ» /ዘፍጥ 3፡15/ ባለው መሠረት ሰኮናው ላይ በእባብ መነከስ ጊዜያዊ መቁሰል ሲሆን በአንጻሩ እባቧን ራስ ራሱን መቀጥቀጥ ግን ቋሚ መቁሰል ነው፡፡

የኃጢአት /የእባቧን ዘር/ በዋነኛነት ማውገዝ በክርስቶስ መስቀል ላት መዋል አማካይነት ታይቷል። ከላይ የተጠቀሱት ምዕራፎች ቁጥሮች ክርስቶስ ኃጢአትን ድል የነሣበት መሆን እንዴት እንደሚናገር እናስተውል። ኢየሱስ ሰኮናው ላይ ለጊዜው በመቁሰሉ የሦስት ቀናት ሞቱን ያመላከታል እንደገና ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ደግሞ የሚያረጋግጠው ጊዜያዊ ቁስለትን ነው። በተለይ ኃጢአት ከሰው ሞት ጋር ሲነፃጸር የመጽሐፍ ቅዱስ ያልሆኑ ታሪክ መዛግብት የመስቀል ባለዕፃዎች በሰኮናቸው በምስማር መቸንከራቸውን ማመልከቱ ደስ የሚል ነው። ስለዚህ ኢየሱስ መሞቱ «ሰኮናው ላት መቁሰሉን» ትገልጻል።፡ /ኢሳ 53:4..5/ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱ ደግሞ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ሰንበር ያወጣ መሆኑን ያመላክታል። ይህ በቀላሉ የሚያመራን የነበረው ክርስቶስ በእባቧ ዘር የመቀጥቀጡን ትንቢያ ነበር።

/ዘፍጥ 3:15/ ለማንኛውም በመጨረሻ ክርስቶስ ፊት ለፊቱ የተጋፈጠው እግዚአብሔር በክፋት አድርጎ ነው። እዚህ የተገለጸው ቅጥቀጣውን እርሱ እንዳደረገው ሆኖ /ኢሳ 53:10/ የእርሱን እጅ የቀጠቀጡትን የክፋት ኃይሎች በመቆጣጠር ነው። እና እንዲሁም እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ልጆቹ የሚሠራው በክፋት ተሞክሮዎች አማካይነት /በኩል/ ነው።

## ዛሬ ያለው ግጭት

«ኢየሱስ ኃጢአትንና ሞትን /የእባቧን ዘር/ ከአጠፋ እነዚያ ነገሮች እስከዛሬ ድረስ አሉ? የሚል በአዕምሮህ

የሚመጣ ጥያቄ ይኖር ይሆናል፡፡ መልሱም በራሱ ውስጥ ያለውን ኃጢአት በመስቀል ላይ ሲውል አጥፍቷል.. በዘፍጥ 3፡15 የሚተነተነው በዋነኝነት በኢየሱስና በኃጢአት መካከል ያለውን ፍጭት ነው፡፡ አሁን ይኸ ማለት እርሱ የእርሱን ድል አድራጊነት እንድንጋራው ስለጋበዘን የኋላ ኋላ እኛም ኃጢአትንና ሞትን ማሸነፍ እንችላለን፡፡ እነዚያ ድልን ለመጋራት ያልተጋበዙ ወይም ግብዣውን ያላከበሩ ኃጢአትንና ሞትን በእርግጥ እንድለማመዱ ይሆናሉ፡፡ ምንም እንኳን ሞትንና ኃጢአትን በሴቲቱ ዘር በክርስቶስ መጠመቅ ጋር ባለው ቁርኝት ምክንያት እውነተኛ አማኞች ቢፈታተናቸው ለኃጢአታቸው ይቅርታ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ እናም በመጨረሻም የኃጢአት ውጤት ከሆነው ከሞት ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ ለወደፊቱ ኢየሱስ በመስቀል ሞትን አስወግዷል /2 ጢሞ 1፡10 ምንም እንኳን እግዚአብሔር ስለምድር ያለው ዓላማ በመጨረሻይቱ ሺኛ ዘመን አሕዛብ በእርግጥ መሞት እስኪያቆሙ ድረስ ሞት እንደገና በምድር ላይ እስከማይመሰከርበት ጊዜ....

> «...ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድርስ
>
> /በእግዚአብሔር መንግሥት በመጀመሪያው ክፍል/
>
> ሊነግሥ ይገባዋል የመጨረሻ ጠላት የሆነው ሞት
>
> ይደመሰሳል» /1 ቆሬን 15፡25..26/

«በክርስቶስ ከተጠመቅን» ስለኢየሱስ የተሰጡት ቃል ኪዳኖች በዘፍጥረት 3፡15 እንደተጻፈው ለራሳችን የግል

ይሆናል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ከእንግዲህ እንዲሁ ደስ የሚሉ ክፍሎች አይሆኑም ለእኛ በቀጥታ የተሠሩ ትንቢቶችና ቃልኪዳኖች ናቸው እንጂ፡፡ እንደሴቲቱ ዘር እኛም የኃጢአት በእኛ ላት አቸናፍነት ለአጭር ጊዜ የምንለማመደው ይሆናል፡፡ በእኛ የሕይወት ዘመን ጌታችን ካልረመለሰ እኛም ሽኮናችንን እንደኢየሱስ ሁሉ እንቀጠቀጣለን በዚያም እኛም እንሞታለን፡፡ ነገር ግን በእርግጥ የሴቲቱ ዘር ጀሆነ ያ «ቁስለት» ጊዜያዊ ብቻ ይሆናል፡፡ ውኃ ውስጥ በመጥለቅ በክርስቶስ በአግባቡ ከተጠመቅን ከዝርሱ ከኢየሱስ ሞትና ትንሣዔ ጋር ራሳቸውን አንድ ያደርጋሉ፡፡

የሴቲቱ እውነተኛ ዘር ከሆን ሕይወታችን ዘፍጥረት 3፡15 ላይ የተጻፈውን በእኛ ውስጥ በትክክልና በስህተት መካከል የሚሰማንን ጦርነት ያመለክታል፡፡ ታላቁ ጳውሎስ በእርሱና በኃጢአት መካከል ያለውን በአንድ ሰው ውስጥ ብዙ ሰዎች ግጭት በውሰጡ ይረብሸው እንደነበር ይናገራል፡፡

በክርስቶስ ጥምቀት በኋላ ከኃጢአት ጋር ያለው ትግል መጨመር ይኖራል፡፡ ይህም በየቀኑ እንደዚሁ በማድረግ ይቀጥላል፡፡ ለነገሩ አስቸጋሪ ነው፡፡ የኃጢአት ኃይሉ ብርቱ ነውና በሌላ በኩል ግን አይደለም፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ራሳችንን ስናጸና ክርስቶስም ተዋግቶ ትንንቁን /ትግሉን/ አቸንፏልና፡፡ አማኞች እንዴት ሴት ተብለው እንደተገለጹ አስተውል፡፡ /ኤፌ 5፡23..32/

የሴቲቱ ዘር ኢየሱስንና የእርሱን ገጸ ባህርያት ለነያዝ የሚሞክሩትን በሚወክሉበት ተመሳሳይ መንገድ እንዲሁ የእባቧ ዘር ስለኃጢአትና /በመጽሐፉ ዲያብሎስ/ የኃጢአትንና የእባቢቱን ገጸ ባህርያት የሚያሳይ መሆኑን ይናገራል። ይህም ወደ ኃጢአት እፍረት ከእግዚአብሔር መነጠልን ያመጣባቸዋል። አዳምና ሔዋን እንደደረሰባቸው ሁሉ። ኢየሱስን ለሞት የዳረጉት በትክክል አይሁዳውያን መሆናቸው ሲታይ ማለትም የሴቲቱን ዘር ሸኮናው ላይ መቀጥቀጡ የእባቢቱ ዘር ዋነኛ ምሣሌዎች መሆናችው የሚጠበቅ ይሆናል።

ይህ ደግሞ በመጥመቁ ዮሐንስና ኢየሱስ ተረጋግጧል ...

«...እርሱ /ዮሐንስ ፈሪሳውያንንና ሰዱቃውያንን

/ኢየሱስን ያወገዙት የአይሁዳውያን ቡድን/ ብዙዎች

ወደጥምቀቱ ሲመጡ ባዬ ጊዜ እንዲህ አላቸው

እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ

ማን አመለከታችሁ?» /ማቴ 3፡7/

«ኢየሱስ የእነርሱን /የፈሪሳውያንን/ ሃሳቦች ዐወቀ።

እንዲህም አላቸው፡ እናንተ የእፉኝት ልጆች እንዴት ክፉ

ሆናችሁ ጥሩ ነገሮች ልትናገሩ ትችላላችሁ?» /ማቴ 12፡25..34/

ዓለም..ኃይማኖተኛ ዓለም ሳይቀር..ይኸው የእባቧ ባህርያት አለው፡፡ በክርስቶስ የተጠመቁት ብቻ ናቸው ከሴቲቱ ዘር ጋርየሚተባበሩት /የሚቆሙት/ ሌሎች ሁሉም በተለያዩ ደረጃዎች ይሁን እንጂ የእባቧ ዘሮች ናቸው፡፡ ኢየሱስ የእባቧ ዘር የሆኑትን እንዴት እንደሚያስተናግዳቸው ምሣሌያችን ሊሆን ይገባዋል፡፡

. .በፍቅር መንፈስና በእውነተኛ ጭንቀት እርሱ ሰበከላቸው

.. የእርሱ መንገዱችና አስተሳሰብ በእርሱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድር

አልፈቀደም፡፡ እንዲሁም

.. የእግዚአብሔርን የመውደድ ባህርይ በአኗኗር አሳያቸው፡፡

ያም ሆኖ ለዚህ ሁሉ እርሱን ጠሉት፡፡ ለእግዚአብሔር ባሳየው ታማኝነት ድካም እንዲመቀኙት አደረጋቸው፡፡ ቤተሰቦቹ ሳይቀሩ /ዮሐ 7፡5፣ ማር 3፡21/ እንዲሁም የቅርብ ወዳጆቹ /ዮሐ 6፡66/ መሰናክሎች አቆሙበት አንዳንዶም በአካል እንኳን ከእርሱ ራቁ፡፡ ጳውሎስ እንዲሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ወደቀ፣ ይኸውም ከእርሱ ጎን በአንድ ወቅት ቆመው ስለነበሩት ስለሸሹት ሰዎች ጳውሎስ አዘነ /አለቀሰ/፡፡

«እንኪያስ እውነቱን ስለነገርኋችሁ ጠላት ሆንኩባችሁን?»

/ገላትያ 4፡16..17/

እውነት ተዛምቶ አያውቅምና እውነትን ማወቅ ከእውነታ ጋር መኖር ለእኛ የሆነ ችግር ሁልጊዜ ይፈጥራል፡፡

«...እንደሥጋ የተወለደው እንደመንፈስ የተወለደውን በዚያን

ጊዜ እንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው፡፡» /ገላት 4፡፡29/

በእውነት ከክርስቶስ ጋር ከተዋሃድን ከእርሱ ስቃዮች /መከራ/ ጥቂት መቅመስ ይገባናል፡፡ ክቡር ከሆነው ኸልማቱ ይደርሰን ዘንድ ጳውሎስ ወደር የሌለው ምሣሌ ይሰጠናል፡፡ እንዲህ ሲል..

«....ይህ ታማኝ አባባል ነው.. ከእርሱ /ከክርስቶስ/ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን፡፡

ብንፀና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፡፡ ብንክደው

እርሱ ደግሞ ይክደናል፡፡» /2 ጢሞ 2፡10..12/

«...እኔን /ኢየሱስ/ አሳደውኝ እንደሆኑ እናንተን ደግሞ

ያሳዳጿችኋል፡፡ ቃሌን ጠብቀው እንደሆኑ ቃላችሁን ደግሞ

ይጠብቃሉ ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህንን ሁሉ ስለስሜ

ያደርጉባችኋል፡፡» /ዮሐ 15፡20..21/

ማለትም፣

«በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቀናልና.../ሐዋ 2፡38/

እንደነዚህ ያሉ ምዕራፍና ቁጥሮች «ከኢየሱስ ጋር የሚያያዘው የሴቲቱ ዘር የሚባለው ሁሉ ከሆነ «ከእርሱ ጋር አንድ ናካደርግ ይመረጣል» የሚለው ምክንያት የሚፈታተን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ልንደርስበት የማንችል ከሆነ ምንም ነገር ማድረግ ፍጹም አይጠበቅብንም፡፡

በተሟላ መልኩ እራሳችን በእርግጠኝነት ከክርስቶስ ጋር ለማዋሃድ ከፈለግን ራሳችንን መስዋዕት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ራሳችንን ከእርሱ ጋር አንድ ከማድረግ ክብር ያለው ሽልማት እናገኛለን፡፡ ይኸውም «የዛሬው የዚህ ዓለም መከራ ሁሉ በኋላ በእኔ ውስጥ ከሚገለጸው ክብር ጋር ሲነጻጸር ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ እናም አሁን እንኳን የክርስቶስ መስዋዕትነት በዚህ ዓለም የሕይወት ጠባሳዎች በኩል ጸሎቶቻችን በእግዚአብሔር ኃይል እንዲረዱን ያስችልናል፡፡ የሚከተሉትን ክብር የሚያሳጡ ዋስትና ከመጻሕፍት እንደ...

«ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም

ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ትልቅ ትፈተኑ ዘንድ የሚፈቅድ

እግዚአብሔር የታመነ ነው። ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ

ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።

/1 ቆሮን 10፡13/

«በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ

በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ

ዓለምን አቸንፌአለሁና» /ዮሐ 16፡33/

«...እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ

ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» /ሮሜ 8፡31/

## 3.3 ለኖኅ የተሰጠው ቃል ኪዳን

ከአዳምና ሔዋን ጊዜ በኋላ የሰው ልጅ ታርክም እየተራመደ ሲመጣ ሰው በይበልጥ ክፉ /ጨካኝ/ ሆነ ሥልጣኔም ሞራላዊ ዝቅጠት እያሳየ የመጣበት ደረጃ ሲያይ እግዚአብሔር ኖኅንና ቤተሰቡን አስቀርቶ ሌላውን ነገር ሁሉ ለማጥፋት ወሰነ:: /ዘፍጥ 6:5..8/ እግዚአብሔር ኖኅ መርከብ ሠርቶ ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ከእንስሳት ከአራዊት ሁሉ አንዳንድ ለዘር አስቀርቶ ሁሉንም በጎርፍ እንድጠፉ አደረገ:: ክፉው የሰው ልጅ እንጂ ምድር አለመጥፋቱን እናስተውል:: «በምድር ላይ ሥጋ ያለው የሚንቀሳቀሰው ሁሉ ጠፉም እንስሳውም ራዊቱም በምድር ላይ የሚርመሰመሰውም ተንቀሳቃሾችም ሁሉ ሰውም ሁሉ ጠፉ:: /ዘፍጥ 7:21/ ኢየሱስና ጴጥሮስ ሁለቱም በኖኅ ዓለም የተፈረደው ፍርድ ከክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ጋር የሚኖረውን ተመሳሳይነት አዩ:: በኖኅ ዘመን የሰውን ልጅ አሳዛኝ ክፋት ከዛሬው ዓለም ክፋት ጋር የሚገጥም ነው ይህም በክርስቶስ መመለስ የሚቀጣበት ይሆናል::

የሰው ልጅ በኃጢአት በመለወሱና ይህች ዓለምም ራሷን ለማጥፋት በያዘችው መርሃ ግብር በክርስቲያኖችም ሳይቀር በሁሉም ዘንድ ያለው እምነት ምድር እንድትጠፋ ነው:: እግዚአብሔር የምድራችንን ጉዳዮች በጥሞና እያየ መሆኑንና በቅርብ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ወደዚህ ዓለም አንደሚመለስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላለው መሠረታዊ መልክት አለመስተዋሉን ያመለክታል:: የሰው ልጅ ይህን ዓለም በራሱ ሊያጠፋት ከፈቀደ እነዚህ ቃል ኪዳኖች ሁሉ አይጠበቁም:: የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንደሚመሠረት በቂ ማስረጃዎች እንዳሉ በጥናታዊ ጽሑፉ 4.7 እና በጥናት 5 ላይ ሠፍሯል:: ለጊዜው የሚከተሉት አስረጂዎች ምድርና ፀሐይ እንደማይጠፉ በቂ ናቸው::

«ለዘላዐለም ምድርን መሠረታት» /መዝ 78:69/

«ምድር ለዘለዓለም ትኖራለች» /ተግሣፅ 1:4/

ፀሐይና ጨረቃ፣ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ ሰማየ

ሰማያት..አዝዟለና ተፈጠሩም...ለዘለዓለም ዓለም

አቆማቸው ትዕዛዝን ሰጠ አያልፉምም» /መዝ 148፡3..6/

«... ውኃ ባህርን እንደሚከድን ምድር እግዚአብሔርን

በማወቅ ትሞላለችና።» /ኢሳ 11፡9/

ዘሁልቁ 14፡21..አስቸጋሪ እግዚአብሔር ምድር ራሷን

እንድታጠፋ ከፈቀደ ይህ ቃል ኪዳን ገና አልተሟላም።

«ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱም ምድርን

የሠራና ያደረገ ያጸናትም ልትሆን እንጂ ለከንቱ

እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላል።»

/ኢሳ 45፡18/

እግዚአብሔር ምድርን የሠራት ስትጠፋ ለማየት ከሆነ

የእርሱ ሥራ በከንቱ ነው።

ወደዘፍጥረት ስንመለስ እግዚአብሔር ለኖኅ ይህን ሁሉ ቃል ገብቶለት እንደነበር እናያለን። ኖኅ ምድር ከጥፋት ውኃ በኋላ የሚኖርባት አዲስ ዓለም ኖኅ አጠቃላይ ጥፋት ምናልባት ይመጣ ይሆናል ብሎ ፈርቶ ነበር። ከጎርፉ ማዕበል ጥፋት በኋላ በዘነበ ቁጥር አዕምሮው ሳይጨነቅ አልቀረም። እናም እግዚአብሔር እንደገና እንደማይደርስ ቃል ኪዳኑን ሰጠ …

«… እኔ እነሆ ከእናንተ በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ

## ጋር እቆማለሁ። ከእናንተ ጋር ሳሉትም ህያው ነፍስ

ላላቸው ሁሉ ከእናንተ ጋት ከመርከብ ለወጡት ለወፎች ለእንስሳትም ለምድር አራዊትም ሁሉ

ለመንኛውም ለምድር አራዊት ሁሉ ይሆናል።

ቃል ኪዳኔንም ለእናንተ አቆማለሁ። ሥጋ .D

ያለውም

ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም። ምድርንም

ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም።»

/ዘፍጥ 9፡9...12/

ይህ ቃል ኪዳን በቀስተ ደመናው ተረጋግጧል፡፡

«...በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ

በደመናው ትታያለች በእኔና በእናንተ መካከል ህያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ያለውንም ሁሉ ያጠ ፋ ዘንድ ዳግመኛ የጥፋት

ውኃ አይሆንም፡፡ ቀስቲቱም በደመና ትሆናለች፡፡

በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው ያው ነፍስ ሁሉ

መካከል ያለውን የዘለዓለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ፡፡ እግዚአብሔር ኖኅን በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው ሁሉ መካከል ያቆምኩት ቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው አለው፡፡ /ዘፍጥ 9፡13...17/

በእግዚአብሔር በሰው ልጅ እንዲሁም በምድር ላይ በሚኖሩት እንስሳት መካከል ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን ስላለ ምድር ላይ ሰዎችና እንስሳት ለዘለዓለም ይኖራሉ፡፡ ስለዚህም ነው የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማት ሰማያት እንደሆነ ሁሉ በምድር የሚሆነው ለኖኅ የተሰሠው ቃል ኪዳን ስለእግዚአብሔር መንግሥት የሚሰበከው ወንጌል መሠረት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር ስለምድር ያለውን ትኩረትና ከእርሱ ጋር ያለውን ዘለዓለማዊ ዓላማ ነው፡፡ በአጠቃላይ ምህረትን

ያስታውሳል /ሐብ 3፡2/ እና እንዲሁም በፍቅሩ ለፍጡራን እንስሶቹ እንኳን ይገደዋል። /1 ቆሮን 9፡9/

# 3.4 ለአብርሃም የተሰጠ ቃል ኪዳን

በኢየሱስና በሐዋርያቱ የተሰበከው ወንጌል አብርሃም ከተረዳው መሠረታዊ ልዩነት አልነበረውም። እግዚአብሔር በመጻሕፍቱ አማካይነት «በእናንተ አህዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ ጴጥሮስ ወንጌልን ለእነርሱ መስበክ መጀመሩና መጨረሱ እጅግ ወሳኝ ነበር። /ሐዋ 3፡13..25/ አብርሃም የተማረውን ከተረዳን የክርስቲያናዊ ወንጌልን ዋነኛ ስዕል አገኘን ማለት ነው። «ወንጌልን» ልክ በኢየሱስ ጊዜ የተጀመረ ነገር ለመሆኑን የሚያመላክቱ ሌሎች ምልክቶች አሉ።...

> «...እኛም ለአባቶች የተሰጠው ተስፋ የምሥራች
> ለእናንተ እንሰብካለን። ይህን ተስፋ እግዚአብሔር
> በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ አንተ ልጅ ነህ እኔ
> ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስን አስነስቶ
> ለእኛ ለልጆቻቸው ጽፎአልና።» /ሐዋ 13፡32..33/
> «የእግዚአብሔር ወንጌል በነቢያቱ ፊት /ለምሣሌ
> አብርሃም/ ቃል የተገባው በቅዱሳን መጻሕፍት /ሮሜ 1፡1..2/

«...እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈርድባቸው በመንፈስ ግን

እንደእግዚአብሔር እንዲኖሩ ስለዚህ ምክንያት ወንጌል

ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና».. /1 ጴጥሮ 4፡6/

ይህም ከመጀሪያው መቶኛ ክፍለ ዘመን የኖሩና የሞቱ።

«...ለእነዚያ ደግሞ እንደተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናልና»

እብራ 4፡2/ ይህም እስራኤል በጠፍ በረሃ /ጫካ/ ውስጥ ለአብርሃም የተገቡ ቃል ኪዳኖች ሁለት መሠረታዊ መልዕክቶች አሏቸው፡፡

1/ ስለአብርሃም ዘር /ልዩ ትውልድና/

2/ ለአብርሃም ቃል የተገባለት ምድር ናቸው

እነዚህ ቃል ኪዳኖች በሐዲስ ኪዳን አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ መጽሐፍ ራሱ የሚናገር መሆን እንዳለበት የምናራምዳቸውን ፖሊሲ በማገናዘብ የሁለቱም ቃል ኪዳናት የተሰጠውን ትምህርት ለአብርሃም ጋር የተገባውን ቃል ሙሉ ስዕል ይሰጠናል፡፡

አብርሃም በመጀመሪያ ትኖር የነበረው በኡር.. ዛሬ ኢራቅ በሚባለው ሀገር የበለጸገች ከተማ ነበር፡፡ ዘመናዊ አርኬዎሎጂ በአሐበረሃም ጊዜ የነበረውን ከፍተኛ ሥልጣኔ ያሳያል፡፡ የባንክ አሠራር የመንግሥት ሥራና ተዛማጅ መሠረተ ልማት ነበር፡፡ አብርሃም በዚህች ከተማ ኖረ፡፡ ከዚህ የተለየ አይታወቅም፡፡ እስከምንረዳው ድረስ አብርሃም የዓለም ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ያልተለመደ ከእግዚአብሔር ለአብርሃም ጥሪ መጣ.. ከዚያ ከየሚላ ኑሮ ወደቃል የተገባላት ከተማ ጉዞ እንዲያደርግ በእርግጥ ወዴት በእርግጥ ምን እንደሆነ ግልጽ አልነበረም፡፡ ጉዞው 1.500 ማይል እንደሆነ ታወቀ ምድሯ ከነዓን ..ዘመናዊ እስራኤል... ነበረች፡፡

አልፎ አልፎ ለአብርሃም እግዚአብሔር እየተገለጸ ቃል ኪዳኑን ደጋግሞና አስፋፍቶ ይነግረው ነበር። እነዚያ ቃክ ኪዳኖች የክርስቶስ የምሥራች መሠረቶች ናቸው። እነዚያ የአብርሃም ጥሪዎች ለትክክለኛ ክርስትያኖች ዛሬም ይመጣልና። ይኸውም በዚህ ዓለም ያሉ አላፊ ነገሮችን ትተን በእምነት የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንዳለ በመቀበልና በመለወጥ በቃሉም በመኖር። በጉዞው አብርሃም የተሰጠው ቃል ኪዳን ምን ሲያወጣ ሲያወርድ እንደነበር ለመገመት ይቻላል።

«አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወደአለው

ሥፍራ /ከነዓን/ በዕምነት ታዘዘ። ወዴትም እንደሚሄድ

ሳይታወቅ ወጣ /ከኡር/

የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ በምናስብብበት ጊዜ እኛም እንዲሁ ለእግዚአብሔር መንግሥት ቃል ኪዳን የተሰጠበት ስፍራ በትክክል ምን እንደሚመስል አናውቅም። በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ያለን እምነት ግን እኛ ደግሞ በጉጉት የምንጠብቀው መሆን ይኖርበታል። አብርሃም ተዘዋዋሪ ዘላን አልነበረም። በቃል ኪዳኖች ያገኘውን ዕጣ ፈንታ ከማድረግ የተሻለ አማራጭ አልነበረውም። አብርሃም የተጋፈጠው ውስብስብና አስጨናቂ ውሣኔዎች የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳኖች ለመጠበቅና ለመተግበር ፊት ለፊት ከሚገጥሙን ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ነበሩ።

ይህም ከሥራ ባልደረቦቻችን እንዲሁም ከጎረቤቶቻችን የሚገጥሙን ዞር ያለ ሽሙጥ ለአብርሃም ሳይገጥሙት አልቀሩም፡፡ ይህን ሁሉ አልፎ እንዲወጣ ያገዘው ማነቃቂያ የሚያስገርም መሆን ይኖርበታል፡፡ አብርሃም ያን የጉዞ ዓመታት ሁሉ እንደገፋበት ያነሣሣው ብቸኛ ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነበር፡፡ እነዚያን ቃሎች በቃሉ አጥንቶ ቃሎችም ምን ለእርሱ ማለት እንደሆነ በየቀኑ በአንክሮ እያሰበ መሆን አለበት፡፡

ተመሳሳይ እምነት በማሳየት በመተግበርም አብርሃም የተሰጠውን ክብር ለእኛም ሊሰጠን ይችላል፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔር ወዳጆች ተብለን ልንጠራ እንችላለን፡፡ /ኢሳ 41፡ 8/ የእግዚአብሔር ዕውቀት ለማግኘት /ዘፍጥ 18፡17/ እንዲሁም በእግዚአብሔር መንግሥት ዘለዓለማዊ ሕይወት ለማግኘት ያለውን አስተማማኝ ተስፋ ለመጨበጥ የክርስቶስ ወንጌል የተመሠረተው በእነዚህ ለአብርሃም በተሰጡ ቃል ኪዳኖች መሆኑን እንደገና አጥብቀን እንናገራለን፡፡ በክርስቲያናዊ መልዕክት ከልብ ለማመን እኛም ለአብርሃም የተሰጡትን የተስፋ ቃል ኪዳኖች ደግሞ በጥብቅ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ያለእነዚህ የእኛ እምነት እምነት አይደለም፡፡ ስለዚህም በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል የነበረውን ንግግር መልሰን መላልሰን ማስተዋል ይኖርብናል፡፡

## ምድሩ

1/ «... ከሀገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ

ምድር ውጣ::»

2/ አብርሃም «በጉዞው ወደቤቴል /ዛሬ በማዕከለ እስራኤል/ በኩል ሄደ

እግዚአብሔር አብርሃምን አለው.. ዓይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ሥፍራ ወደሰሜንና ወደደቡብ ወደምሥራቅና ወደምዕራብ እይ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘለዓለም እሰጣለሁና... ተነሣ በምድር በርዝመትዋም በስፋትዋም ሂድ እርሱን ከአንተ

እሰጥሃለሁ» /ዘፍጥ 13፡3፣ 14..17/

3/ «እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ በሎ ቃል ኪዳን አደረገ... ከግብጽ

ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኦፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን

ምድር ለዘርህ ሰጥቻለሁ» /ዘፍጥ 15፡18/

4/ «በእንግድነት የምትኖርበትን ምድር የከነዓንን ምድር ሁሉ ለዘለዓለም

ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ካንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ።»

/ዘፍጥ 17፡8/

5/ «እርሱ /አብርሃም/ የምድር ወራሽ መሆን እንደሚገባው የተሰጠው

የተስፋ ቃል...» /ሮሜ 4፡13/

እኛ ለአብርሃም በየጊዜው የታየውን ራዕይ እንደሚከተለው እናያለን።

አንተ እንድትሄድ የምፈልገው ምድር አለ .1
አሁን አካባቢው ደርሰሃል። አንተ ልጆችህ ለዘለዓለም .2
እዚህ ትኖራላችሁ። የዘለዓለም ሕይወት የተስፋ ቃል ያለውብትና ያለመጋነን እንዴት በቀላሉ እንደተመዘገበ አስተውል። ሰብአዊ ደራሲ /ፀሐፊ/ ብዙ ዝባዝንኬ ትበዛ እንደነበር አያጠራጥርም።
የተስፋ ቃል ሥፍራ አካባቢ በበለጠ ልዩ ሆኖ ተብራርቷል። .3
አብርሃም ስለዚህ ዓለም ሕይወት የተስፋ ቃል .4
አልጠበቀም። ትልቁንም በዚህ ምድር «ባዕድ» ነበር ምንም እንኳን በኋላ ለዘለዓለም የምትኖርባት ቢሆን የዚህ አንድምታ እንደሚሞት በኋላም ይህ ቃል ኪዳን ይቀበል ዘንድ ከሞት እንደሚነሣ ነው።

ጳውሎስ በመንፈስ ተሞልቶ በአስረጂነት ለአብርሃም .5
የተሰጡት ቃል ኪዳኖች አየ። ይኸውም የምድር ሁሉ
ወራሽ መሆኑን።

መጽሐፍ ቅዱስ ከመሥመር ወጥቶ የሚያስታውሰን አብርሃም በሕይወት ዘመኑ የተስፋ ቃል ቃሎችን መፈጸም አለመቀበሉን ነው። «..ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ... እንደምፃተኛ በእምነት ተቀመጠ።» /ዕብራ 11፡9/

እንደምፃተኛ በምድሯ ኖረ። ስድስተኛ በሚሰማው ስሜት ዓይነት ከዘሩ ጋር በእራሱ በሚያውቁት ምድር አልኖረም። ከወራሾቹ ከይስሐቅና
ያዕቆብ /የተስፋ ቃል ተደጋግሞ የተነገረላቸው/ ጋር «በዕምነት ፀንቶ ሞተ፣ የተሰጣቸውንም የተስፋ ቃሎች አላገኙምና ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት። በምድሪቱም ችንግዶችና መፃተኞ እንደሆኑ ተመኑ።»

/ዕብራ 11፡13/

አራቱን ደረጃዎች አስተውል...

.. የተስፋ ቃሎቹን ማወቅ

.. በእነርሱ /በቃል ኪዳኖቹ/ መግባባቱ አብርሃምን ለማግባባት ይህን ያህል ከወሰደ ለእኛማ ምን ያህል የበለጠ ይሆን?

.. እነርሱም ማቀፍ አንድ መሆን በክርስቶስ አምኖ በመጠ መቅ

/ገላት 3:27..29/

.. ይህን ዓለም ዕውነተኛ ቤታችን አለመሆኑን በአኗኗራችን ተለይቶ የሚታይ መሆኑን ለዓለም መናዘዝ፡ ነገር ግን ያ በመጭው ዘመን ወደምድር የሚመጣን ተስፋ በማድረግ መኖር።

የእኛ ታላቁ ጀግናችን አብርሃም ምሣሌያችን ይሆናል። ይኸውም እነዚህን ነገሮች አክብረን ከተቀበልን። የቃል ኪዳኖች መፈጸም የሚመጣው ወደፊት መሆኑን ሊቀበል የቻለው የደከመው አሮጌ ሰው ምሽቱ ስትሞትበት ነበር። በእርግጥም ከተሰጠው ምድር ውስጥ ከፊሉን ገንዘብ ከፍሎ ምሽቱን መቅበር ነበረበት /ሐዋ 7:16/። እግዚአብሔር በዕውነትም «በዚህች የእግር ጫማ ስንኳ የሚያህል ርስት አልሰጠውም ነገር ግን ልጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው።» /ሐዋ 7:5/ የዛሬዎቹ የአብርሃም ዘሮች ንብረት ሲገዙና ሲከራዩ ይኸው ስሜት ይኖራቸው ይሆናል። ይህም ለእነርሱ ለየግላቸው ለዘለዓለም ይወርሱት ዘንድ በተሰጣቸው ምድር።

ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል ኪዳን ይጠ ብቃል፡፡ አብርሃምና ከእርሱ በኋላ ቃል ኪዳን የተሰጣቸው ተተኪዎች ሁሉ አንድ ቀን ይፈጸምላቸዋል፡፡

> «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፤ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል
>
> አላገኙምና እግዚአብሔር ስለእኛ አንዳች የሚመስል ነገርን
>
> አስቀድሞ አይቶ ነበርና ያለእኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ...»
>
> /ዕብራ 11፡13፡ 39፣40/

ሁሉም ዕውነተኛ አማኞች በተመሳሳይ ነጥብ አንድ ቀን ይሸለማሉ፡፡ ይኸውም በመጨረሻው የፍርድ ቀን፡፡ /2 ጢሞ 4፡1..8/ /ማቴ 25፡31...34/ / 1 ጴጥ5፡4/፡፡ በፍርድ ቀን ይዳኙ ዘንድ አብርሃምና ሌሎች በዚያች የፍርድ ቀን በፊት እንደገና ከሞት መነሣት እንዳለባቸው የተስፋ ቃሉን ያውቃሉ፡፡ አሁን እነዚያን ቃል ኪዳኖች ካልተቀበሉና የሚቀበሉይም ከተነሡና ክርቶስ ለፍርድ ቀን በተመለሰበት ጊዘረ ከሆነ አብርሃምን የሚመስሉትን መቀበል አማራጭ አይኖረውምና፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ለብዙ መቶ ዓመታት እነዚያን ሐሳቦች ለመቀበል መዝግብዋቸዋል፡፡ ከዚያ መስመር /አካሄድ/ ለመውጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገነባ ድፍረት ይኖርሃል፡፡

## ዘሩ

በጥናት 3.2 ቀደም ብለን እንደተገለጸው ስለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል ዋነኛነት ስለኢየሱስ የተባለ ነው። በሁለተኛ ደረጃም «በክርስቶስ» ላሉትና የአብርሃም ዘር እንደሆነ ደግሞ በሚቆጠሩት ነው።

«ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ እባርክሃለሁ ስምህንም .1
አከብረዋለሁ። ለበረከትህ ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ የሚረግምህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ።» /ዘፍጥ 12፡2..3/

«.. ዘርህንም እንደምድር አሸዋ አደርጋለሁ .2
የምድርን አሸዋ ይቆጥር ዘንድ የሚችል ሰው ቢኖር ዘርህ ደግሞ ይቆጠራል።» /ዘፍጥ 13፡15..16/

«... ወደሰማይ ተመልከት ከዋክብትንም .3
ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው። ዘርህ እንደዚሁ ይሆናል አለው። ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቻለሁ።» /ዘፍጥ 15፡5..18/

«...የከነዓንን ምድር ሁሉ ለዘለዓለም ግዛት ይሆንህ .4
ዘንድ ላንተና ካንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ።»

«...ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብት ባብህር ዳር .5
እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ። የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ ቃሌን ሰምተዋልና።» /ዘፍጥ 22፡17..18/

እንደገና ስለዘሩ የአብርሃም ግንዛቤ በየጊዜው ተስፋፍቷል።...

በመጀመሪያ ቁጥር ስፍር የሌለው ትውልድ .1
እንደሚኖረውና በዘሩም ምድር ሁሉ እንደምትባረክ
ተነግሮታል።
በኋላም ዘሩ ብዙ አሕዛብን እንደሚያካትት እነዚህ .2
አሕዛብም ከእርሱ ጋር በደረሰባት በከነዓን ምድር ዘለዓለማዊ
ሕይወታቸውን እንደሚያጠፉ ተነግሮታል።
ዘሩም እንደሰማይ ከዋክብት እንደሚበዙ ተነግሮያል .3
ይህም እርሱ ብዙ መንፈሳዊ ወራሾች /የሰማይ ከዋክብት/
እንዲሁም ተፈጥሮአዊዎች /የምድር አቧራ/ ወደሚል ሃሳብ
መርቶት ይሆናል።
የዘሩ አካል የሚሆንና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት .4
የሚኖረው ብዙ አሕዛብ ቀደም ብሎ የተሰጠው የተስፋ ቃል
በላቀ ዋስትና መጠናከሩ ተሰምሮበታል።
ዘሩ ጠላቶቹ ላይ ድል አግኝቶ ይሆናል። .5

ዘሩ «የተመሰገነ» በምድር ሁሉ ለአሕዛብ መስጠት እንዳለበት አስተውል። በመ«ሐፍ ቅዱስ ምስጉንነት ለኃጢአት ይቅርታ ከማግኘት ጋር ብዙ ጊዜ ይያያዛል። ለነገሩ ይህ የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ሁሉ የሚፈልገው ታላቅ ምሥጉን ነው። ስለሆነም እንደዚህ ያሉ ነገሮች እናነባለን።...

> «...መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአትም የተከደነችለት ምሥጉን
>
> ነው።» /መዝ 32፡1/

«የምንባረከው» የበረከት ጽዋ» /ቆሮን 10፡16/ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው መሆኑንና ይቅርታ ማግኘትም እንዲቻል

ያመለክታል። በዓለም የያጧአት መሻርም ያስገዐልን ብቸኛ የአብርሃም ትውልድ በእርግጥ ኢየሱስ ነው። እናም ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል ሐዲስ ኪዳን ላይ ያለው አስተያየት ጠንካራ ድጋፍ…

«…/እግዚአብሔር/ ለዘሮቹም አይልም ስለአንድ እንደሚነገር

ግን ለዘርህም ይላል እርሱም ክርስቶስ ይህንም እላለሁ።»

«…እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር ለአብርሃም

በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ከአባቶቻችን

ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች ናችሁ። ለእናንተ አስቀድሞ

እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነስቶ እያንዳንዳችሁን ከክፋታ

ችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ ሰደደው።»

/ሐዋ 3፡24..26/

ጴጥሮስ እንዴት ዘፍጥረት 22፡18 እንደሚጠቅስና እንደሚተረጉም አስተውል።

- ዘሩ = ኢየሱስ
- በረከት = ለኃጢአተኞች ምህረት ማግኘት

ዘሩ ኢየሱስ በጠላቶቹ ላይ ድል የማድረጉ ቃል ኪዳን በኃጢአት ላይ ካገኘው ድል ጋር ተዛምዶ ሲነበብ የበለጠ ግልጽ ይላል... ይኸውም የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንዲሁም የኢየሱስ ታላቁ ጠላት ኃጢአት ነውና፡፡

## ዘሩን መቀላቀል

አሁን የክርስትና ወንጌል ዋና መሠረታዊ አካሎች /ክፍሎች/ አብርሃም እንደተገነዘባቸው ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጠቃሚ የተስፋ ቃሎች ለአብርሃምና ለዘሩ ለኢየሱስ የተገቡ ነበሩ ለሌላስ? የአብርሃም ልጅ የሆ እንኳን በቀጥታ የአብርሃም ልጅ በመሆኑ የዚያ የልዩ ዘር አካል ሊሆን አይችልም፡፡ /ዮሐ 8፡39፣ ሮሜ 9፡7/ በሆነ መንገድ የኢየሱስ የቅርብ አካል መሆን ይኖርብናል፡፡ ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል ተካፋይ እንሆን ዘንድ ይህም የሚሆነው በኢየሱስ ስም በመጠመቅ /ሮሜ 6፡3..5/ ብቻ ነው፡፡ /ገላትያ 3፡27..29/ ይህን ነጥብ የበለጠ እንዲህ ሲል ይገስጠዋል...

«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ

ሁሉ ክርስቶስ ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ

ሰው የለም። ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም። ወንድም

ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስትስ ኢየሱስ አንድ ሰው

ናችሁና። እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደተስፋውም ቃል

ወራሾች ናችሁ።» /ገላት 3፣27..29/

የእግዚአብሔር የምህረት በረከት በኢየሱስ አማካይነት ለመቀበል በምድር የዘለዓለም ሕይወት የተስፋ ቃልን ለማግኘት በክርስቶስ መጠመቅ ነው። እንኪያስ ወደ ሮሜ ሰዎች ጳውሎስ በጻፈው መልዕክት 8:17 ላት «ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» /ሮሜ 8:17/ ሲል በአጋርነት ይጠራናል።

በዘሩ አማካይነት በምድር ሁሉ ባሉ አሕዛብ በረከት እነደሚመጣ አስታውስ። ዘሩም በመላ ዓለም በሚገኙ አሕዛብ እንደ ባህር አሸዋ እንደሰማት ከዋክብት እንደሚሆን አስተውል። ይህም የሆነበት ምክንያት ዘሩን ይሆኑ ዘንድ በረከቱን በመጀመሪያ መቀበላቸው ነው። ስለሆነም አንዱ ብቸኛ ዘር የምትመጣው ትውልድ ለጌታ ትነግረዋለች።» /መዝ 22:30/

ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል በሁለት ዋና ዋና አንዶች ጠቅለል አድርገን ማየት እንችላለን።...

/1/ ምድሩ

አብርሃምና ዘሩ ኢየሱስና በእርሱም ያሉ የከነዓንን ምድር ብሎም ምድርን በሙሉ ይወርሳሉ። እዚያም ለዘለዓለም ይኖራሉ። በዚህ ዓለም ሕይወታቸው አይቀበሉትም፤ በመጨረሻው ቀን ኢየሱስ ሲመለስ ግን ይቀበሉታል።

/2/ ዘሩ

ይህ በመሠረቱ ኢየሱስ ነበር። በእርሱም አማካይነት የሰው ልጅ ኃጢአቶቹ /ጠላቶች/ ድል ይነሣሉ። የይቅርታ በረከት በዓለም ሁሉ ይሰፍን ዘንድ።

በኢየሱስ ስም እንጠመቅ የዘሩ ተካፋይ አካል እንሆናለን። እነዚህ ሁለት ምድርና ዘሩ በሐዲስ ኪዳን ሲሰበኩና በትምህርት መሰጠታቸውን ሲሰሙ ወዲያውኑ መጠ

መቃቸው ተመዝግቦ ይገኛል። በእነዚህ መንገዶች ነበር ነውም እነዚያ ቃል ኪዳኖች ለእኛ የተሰጡን አሁን የምንረዳው ሽማግሌው ሰው በሞት ፊት በቀረበበት ጊዜ ለምን ጳውሎስ የተስፋውን «የእስራኤል ተስፋ» /ሐዋ28፡20/ ሲል ያስቀመጠ ው። ይኸውም የእውነት የክርስቲያን ተስፋ የቀድሞ የአይሁድ ተስፋ ነውና። «ድነት የአይሁዳውያን ነው» /ዮሐ 4፡22/ የሚለው የክርስቶስ አስተያየት መንፈሳዊ አይሁድ መሆን እንደሚያሻ ማመልከት ይኖርበታል። ይኸውም በክርስቶስ አማካይነት ለአይሁዳውያን አባቶች የተሠሩትን የድነት ቃል ኪዳኖች ለመጠቀም እንችል ዘንድ ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የሰበኩትን እናነባለን...

/1/ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚመለከቱ ነገሮች

እና

/2/ «የኢየሱስ ክርስቶስ ስም» /ሐዋ 8፡12/ ትንሽ ለየት ባሉ አርዕስቶች እነዚህ ለአብርሀም የተብራሩለት ሁለቱ ዋነኛ ነገሮች ነበሩ...

ሀ/ ስለምድሩ የተሰጠው ቃል ኪዳኖች

ለ/ ስለዘሩ የተሰጠው ቃል ኪዳኖች

ስለመንግሥቱና ስለኢየሱስ የተባሉት «ነገሮች» «ኢየሱስን መስበክ» ተብለው መጠቃላለቸውን አስተውል። ይህ

ሁሉም ብዙውን ጊዜ «ኢየሱስ ይወድሃል» ለማለት የተወሰደ ነው፡፡ እርሱ ለአንተ መሞቱን እንደምታምን ተናገር አንተ የዳንህ ሰው ነህ፡፡ ነገር ግን «ክርስቶስ» የሚለው ሐረግ በግልጽ የሚያጠቃልለው ስለእርሱና ስለመንግሥቱ ብዙ ነገሮች መበሉን ትምህርት መእጠቱን ነው፡፡ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ለአብርሃም የተሰ0ው የምሥራች በመጀመሪያዎቹ የወንጌል ስብከት ዓመታት ትስቅ ሚና እንደተጫወተ ነው፡፡ በቆሮንቶስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን መንግሥት በተመለከተ ሦስት ወራት ሙሉ ሲከራከርና ሲያሳምን» ነበር፡፡ /ሐዋ 19፡8/ በኤፌሶንም በየቦያው እየተዘዋወረ «የእግዚአብሔርን መንግሥት ሰብኳል፡፡» /ሐዋ 20፡25/ እንዲሁም በየመሳሳይ በሮማ ከተማም «ስለእግዚአብሔር መንግሥት እየተመሰከረ ስለኢየሱስም እያስረዳቸው ... ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ» /ሐዋ 28፡23..31/ መሠረታዊ የወንጌል መልዕክት... ስለመንግሥቱና ስለኢየሱስ ብዙ የሚነገር መኖሩን የሚያመለክተው...

«በኢየሱስ እመኑ» ለማለት ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ለአብርሃም መገለጽ ከዚያ በበለጠ ተተንትኗል፡፡ ለእርሱም የተሰጡት የተስፋ ቃሎች የእውነተኛ የክርስቲያን ወንጌል መሠረቶች ናቸው፡፡

ጥምቀት /በኢየሱስ/ የዘሩ አካል እንደሚያደርገን ገልጾልናል፡፡ ጥምቀት ብቻውን ግን ድነነት ሊያስገኝልን በቂ አይደለም፡፡ በዘሩ ውስጥ በኢየሱስ መቆየት ይገባናል፡፡ ለዘሩ የተሰጠውን ቃል ኪዳን የምንቀበል ከሆነ፡፡

ስለዚህ ጥምቀት የመጀመሪያ ነገር ነው። ለመሮጥ የሚያስችለንን አስቀድሞ ውስጥ ገባን ማለት ነው። የአብርሃም ዘር መሆን ብቻ በእግዚአብሼር ዘንድ ተቀባይነት እንደሚያስገኝልን አትርሳ። በአንዳንድ መንገዶች እስራኤሎች የአብርሃም ዘሮች ናቸው። ይህ ግን ሳይጠመቁ ክርስቶስን ሳይቀበሉ የአብርሃምን አርአያ ሳትከተሉ /ሮሜ 9፡7..8/ ይሆናሉ ማለት አይደለም።

ኢየሱስ ለአይሁዶች እንዲህ ሲል ነገራቸው...

«እናንተ የአብርሃም ዘሮች እንደሆናችሁ አውቃለሁ።

ግን ልትገሉኝ ወደዳችሁ... የአብርሃም ልጆች ከሆናችሁ

እናንተ የአብርሃምን ሥራዎች ታደርጉ ነበር።»

/ዮሐ 8፡37..39/

ይህም በእግዚአብሔርና በኢየሱስ የእምነት ሕይወት ትኖሩ ነበርና።» / ዮሐ 6፡29/

«ዘሩ» የአያቶቹ ባህርያት ልትኖሩ ይገባል። ስለዚህም እርሱ «ለሚያምኑት ሁሉ አባት እንዲሆን ... የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው...» /ሮሜ 4፡11..12/

«እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ ዕወቁ /በልባችሁ ያዙ/» /ገላት 3፡7/

እውነተኛ እምነት በሆነ ዓይነት ተግባር መገለጽ ይኖርባቸዋል። ያለበለዚያስ በእግዚአብሔር ዓይን ይህ እምነት አይደለም /ጀምስ 2፡17/ በእነዚህ ቃል ኪዳኖች የታመንን መሆናችንን ለማሳየት መጀመሪያ መጠ መቅ እንደሚኖርብን በግል ሕይወታችን እንድንጠቀምባቸው ያስፈልጋል። /ገላት 3፡27..29/ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳኖች በእርግጥ ታምንባቸዋለህ? በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ሳይቋረጥ መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ነው።

# አሮጌውና አዲሱ የተስፋ ቃል

አሁን ለአብርሃም የተሰጡት ቃልኪዳኖች የክርስቶስ ወንጌል የሚያጠ ቃልሉ የተረጋገጠ ዕውነታ መሆን ይኖርበታል። ሌሎች ዋና ቃል ኪዳኖች በመሙሴ ሕግ እንደተገለጸው ለአይሁዳውያን የተሰመጠ ናቸው። እነዚህም የሚገልጹት አይሁዳውያን ለሕጉ ታዛዥ ቢሆኑ ኖሮ በዚህ ዓለም በአካላዊ ሕይወታቸው የተባረኩ ይሆኑ ነበር። /ዘዳግ 28/ ስለዘለዓለማዊ ሕይወት በቀጥታ የተሰጡ የቃል ኪዳን /የተስፋ ቃል/ አልነበረም። ስለዚህ ሁለት ደረጃ ያላቸው የተስፋ ቃሎች መሰጠታቸውን እናያለን።

ለአብርሃምና ለዘሩ ኢየሱስ ሲመለስ በእግዚአብሔር መንግሥት የሚኖረው የምህረት የዘላዓለማዊ ሕይወት ቃል ኪዳን ይህ ቃል ኪዳን ለኤደንና ለዳዊት ተሰጥቶ የነበረ ቃል ኪዳን ነው። .1

በሙሴ ዘመን ለአይሁድ ሕዝቦች የተሰጠ ይኸውም የቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ህግ ካመኑ ሰላምና ደስታ በዚሁ ባሉበት ሕይወት እንደሚሠጣቸው .2

እግዚአብሔር በመንግሥቱ ለአብርሃም ምህረትና ዘለዓለማዊ ሕይወት እንደሚሰጠው ቃል ሰጥቷል፣ ነገር ግን ሊሆን የቻለው በኢየሱስ መስዋዕትነት ነበር። በዚህ ምክንያት የኢየሱስ ስቅለት ለአብርሃም የተሰጠ ውን ቃል አረጋገጠ። /ገላት 3፡17፣ሮሜ 15፡8፣ ዳንኤ 9፡27፣ 2ቆሮን 1፣፡20/ ስለዚህ የክርስቶስ ደም «የሐዲስ ኪዳን ደም» ተብሎ ይጠራል። /ማቴ 26፡28/ ይህን እናስታውስ ዘንድ ነው ኢየሱስ በየጊዜው የወይን ጽዋ .. ደሙን የሚያመለክቱንን.. እንድንወስድ የበገረን። /1 ቆሮን 11፡25/ «ይህ ጽዋ ሐዲሱ ኪዳኔን በደሜ የምያስታውሱት ነው።» /ሉቃ 22፡20/ ክርስቶስንና ሥራውን በማስታወስ «የምንቆርሰው ዳቦ» እነዚህን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ካላስገባ ትርጉም አይኖረውም።

የኢየሱስ መስዋዕትነት በእግዚአብሔር መንግሥት ምሕረትና ዘለዓለማዊ ሕይወት ሊሆን ችሏል። ስለዚህም የአብርሃም ቃልኪዳኖችን አረጋገጠ። «ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኗል» /ዕብራ 7፡22/ የጳውሎስ መልዕክት ወደዕብራውያን 10፡9 ስለኢየሱስ እንዲህ ይላል...
«ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል።» /ዕብ 10፡9/ ይህ የሚያሳየው ለአብርሃም የተሰጡትን የተስፋ ቃሎች ኢየሱስ ማረጋገጡን ነው። በዚህም በሙሴ አማካይነት የተሰጡትን ቃልኪዳኖች መሠረዛቸውን ያረጋግጣል። ስለኢየሱስ ከመጻሕፍት የተጠቀሱት ምዕራፍና ቁጥሮች አዲስ ኪዳን በሞቱ መሰጠቱን ብቻ ሳይሆን አሮጌው ኪዳን መሰረዙን ይሆናል ማለት ነው። /ዕብራ 8፡13/

ይህ ማለት ደግሞ ክርስቶስን የሚመለከተው ኪዳን ምንም እንኳን የመጀመሪያ ቀቃል ኪዳን ቢሆንም እስከዕለተ ሞቱ ድረስ በተሟላ መልኩ በተግባር አልመጡም ነበር። ስለዚህም ይህ «ሐዲስ» ኪዳን ይባላል። «ብሉይ» ኪዳን በሙሴ አማካይነት የተሰጠው ወሰኢየሱስ ሥራዎች እንዲያመሩና ኢየሱስን የሚመለከቱት ቃልኪዳኖችን የዕምነት ጥቅም አጉልቶ ለማሳየት ነው። /ገላት 3፡19..21/ በግልባጩም በክርስተቶስ መታመን ለሙሴ የተሰጠው ሕግ እውነተኛ መሆኑን ያረገጋግጣል። /ሮሜ 3፡31/ ጳውሎስ አሳምሮ ሲያጠቃልል እንዲህ ይላል..ሽ

«...እንደዚህ በዕምነት እንጸድቅ ዘንድ ህግ ወደክርስቶስ
የሚያመጣ ሞግዝታችን ሆኗል።» /ገላት 3፡24/

በዚህም ምክንያት ነው ለሙሴ የተሰጠው ሕግ የተጠበቀውና እስካሁንም ለእኛ ጠቃሚ ሆኖ የምናገኘው።

እነዚህ ነገሮች መጀመሪያ ስናነባቸው በቀላሉ አይገቡንም፡፡ እንደሚከተለው ጠቅለል አድርገን ልናያቸው እንችላለን...

- ኢየሱስን የሚመለከቱ ለአብርሃም የተሠሩ የተስፋ ቃሎች..

ሐዲስ ኪዳን

- ለሙሴ የተሰጡ የሚዛመዱ የእስራኤል ቃልኪዳኖች

ብሉይ ኪዳን

- በኢየሱስ ሞት.. ሞት ብሉይ ኪዳንን ተፈጸመ /ኮል 2፡15..17/

የሐዲስ ኪዳን ሥራ ተጀመረ

በዚህም ምክንያት እንደቅዳሜን ማክበር ወዘተ... የብሉይ ኪዳን አካል የነበሩት አሁን አስፈላጊ አይደሉም፡፡ እስራኤላውያን ክርስቶስን አምነው ሲቀበሉ ሐዲስ ኪዳን ይሰጣቸዋል፡፡ /ኤርም 31፡31..32/ /ሮሜ 9፡26..27 ሕዝ 16፡62/
ሆኖም ማንም ይሁዲ በኢየሱስ ሐዲስ ኪዳንን ዛሬም ይቀበላል፡፡ /ገላት 3፡27..29/

በዕውነት እነዚህ ነገሮችን ከገናዘብን የእግዚአብሔር ቃል ኪደኖችን እርግጠ ኛነት እንቀበላለን፡፡ ተጠራጣሪዎች የመጀመሪያዎቹን የክርስትና ሰባኪዎች አወንታዊ መልዕክት አትሰጡም በማለት ያለአግባብ ከሰዋቸዋል፡፡
ጳውሎስም እንዲህ በማለት ይመልሳል...

> «...እግዚአብሔር ግን የታመነ ነው፡፡ ለእናንተም
> የምነግረው /ስብከታችን/ አዎንና አይደለም አይሆንም...
> በመካከላችን የተሰበከ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
> ክርስቶስ አዎንና አይደለም አልነበረም፡፡ ነገር ግን በእርሱ
> አዎን ሆኖአል እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ
> አዎን ማለት በእርሱ ነውና አሜን» /2 ቆሮን 1፡17..20/

# 3.5 ለዳዊት የተሰጠ የተስፋ ቃል

ዳዊት ልክ እንደአብርሃምና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች የተቀበሉት ሌሎች ብዙ ተቀባዮች ቀላል ሕይወት አልነበራቸውም፡፡ በትልቅ ቤተሰብ ውስጥ የመጨረሻ ሆኖ በእስራኤል 1000 ከክርስቶስ ልደት በፊት ተወልዶ አድጓል፡፡ እረኛ ሆኖ በጎችንና ፍየሎችን ለመጠበቅ ሲሯሯጥ በታላላቅ አለቅነት በሚሰማቸው ታላቅ ወንድሞች እየታዘዘ ያደገ ነበር፡፡ / 1ሳሙ 15፡17/ በዚህን ጊዜ ጥቂት ሰዎች ብቻ ያራምዱት የነበረውን የእግዚአብሔር እምነት ተማረ፡፡

የእስራኤል ወገን ከወራሪ ጎረቤቶቻቸው መፈታተን የሚገጥማቸው ቀን በደረሰ ጊዜ ከእስራኤል ወገን አንዱ ግዙፉን ጎልያድን ይገጥም ዘንድ ከተፎካካሪዎች ፈተና ቀረበላቸው፡፡ ግጥሚያውን የያሸነፈ ደግሞ በተሸናፊዎቹ ላይ የበላይነት አግኝቶ እንደሚገዛም ፈተናውን የሰጡት ግንዛቤ ውስጥ እንደቅድመ ሁኔታ አቀረቡት፡፡ በእግዚአብሔር እርዳታም ግዙፉን ጎልያድን እረኛው ምስኪኑ ዳዊት ገጥሞ በወንጭፍ ገደለውና ከእስራኤል ንጉሥ /ሳኦል/ የበለጠ ታዋቂነትን አገኘ፡፡ «ምቀኝነት እንደመቃብር ጨካኝ ነውና» /መዝ 8፡6/ በታዋቂነቱ የቀናው ንጉሥ ሳኦል ዳዊትን በመክሰስ ለ20 ዓመታት ከአገር አገር በየበረሃው አሳደደው፡፡

በመጨረሻውም ዳዊት ንጉሥ ሆነና እግዚአብሔር ለእርሱ በየበረሃው ሲሳደድ ላሳየው ፍቅር ምላሽ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማነጽ ወሰነ፡፡ ከእግዚአብሔር የመጣው መልስ ግን የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ቤተመቅደሱን እንደሚያንጽና እግዚአብሔርም የዳዊትን ቤት እንደሚያንጽ ነበር፡፡ /ሳሙ 7፡4..13/ ከዚያም ተከትሎ ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል የሚደጋግም ዝርዝር ቃል ነበር፡፡ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ዙሪያም

«..ዕድሜህም በተፈጸመ ጎዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ

ጊዜ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፡፡

መንግሥቱንም አፀናለሁ እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፡፡

የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘለዓለም አፀናለሁ፡፡ እኔም አባት

እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፡፡ ክፉ ነገርም ቢያደርግ

ሰው በሚቀጣበት በትር በሰው ልጆች መቀጫ እገስጸዋለሁ

ከፊቴም ከጣልሁት ከሳኦል እንደራቅሁ ምህረቴን ከእርሱ

አላርቅም ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘለዓለም

ይጠነክራል ዙፋንህንም ለዘላለም ይፀናል።

/2 ሳሙ 7፡12..16/

የእግዚአብሔር ልጅ /2 ሳሙ 7፡14/ ሲል የገለጸው የሚያረጋጠው ዘሩ ኢየሱስ መሆኑን ነው። በመጽሐፍ ሌሎች ክፍሎችም ይህን እንደተገለጸ እንመልከት...

- «ኢየሱስ አለ.. እኔ ተጻዊት ሥርና ዘር ነኝ» /ራዕይ 22፡16/
- «/ኢየሱስ/ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ ።» /ሮሜ 1፡3/
- «...ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደተስፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ።» /ሐዋ 13፡23/
- ልጅዋን ኢየሱስን በሚመለከት መልአኩ ለድንግል ማርያም እንዲህ አላት..

«...ጌታ አምላክ የአባቱን ተዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል... ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። /ሉቃ 1፡32..33/ 33/ ይህ የዳዊትን ዘር የኢየሱስን የተስፋ ቃል ይመለከታል። /2 ሳሙ 7፡13/

ዘሩ ከኢየሱስ ጋር በጥብቅ የሚተሳሰር እስከሆነ ድርስ አያሌ ዝርዝር ጉዳዮች አሁን ግምት የሚሰጣቸው ይሆናሉ። እነዚህም

ዘሩ .1

«...ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ... እኔም አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፡፡» «...ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ፡፡» /2 ሳሙ 7፡12..14/ /መዝ 132፡11..12/

ዘሩ ኢየሱስ በአካልም /በሆድም/ የዳዊት ዘር ነበር፡፡ እግዚአብሔርም አባቱ ነው፡፡ በሐዲስ ኪዳን እንደተገለጸው ይህ ሊሆን የቻለው ኢየሱስ የዳዊት ዘር ከሆነችው ከድንግል ማርያም በመወለዱ ነው፡፡ /ሉቃ 1፡32/ ነገር ግን የሰው ልጅ የሆነ አባት አልነበረውም፡፡ እግዚአብሔር በተአምራዊ ሥራው በድንግል ማርያም ማህፀን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ኢየሱስን ፀንሳዋለች፡፡ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይል ይፀልልሻል ስለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡» /ሉቃ 1፡35/ «ለዳዊት የተሰጠው የተስፋ ቃል በአግባቡ ይፈጸም ዘንድ «የድንግል ልደት» ብቸኛው መንገድ ነበር፡፡

## ቤቱ .2

«...እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፡፡» /2 ሳሙ 7፡13/ ያለው የሚየሳየው ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ቤተመቅደሱን /በአካላዊና በመንፈሳዊ መልኩ/ እንደሚያንጽ ነው፡፡ ትንቢተ ሕዝቅኤል 40..48 እንዴት በመጀመሪያው 1000 የእግዚአብሔር መንግሥት በኢየሱስ መመለስ እውን ከሆነ በኋላ በኢየሩሳሌም ከተማ ቤተመቅደስ የሚታነፅ እንደሚሆን ያሳያል፡፡ የእግዚአብሔር «ቤት» እርሱ ለመኖር የሚፈቅድ ቤት ነው፡፡ እንዲሁም ኢሳያስ 66፡1..2/ ላይ የሚነግረን ለቃሉ ትሁት በሆኑት ሰዎች ልብ ውስጥ ለመኖር እንደሚመጣ ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር መኖሪያ መንፈሳዊ ቤተመቅደስ በእውነተኛ አማኞች ላይ ያንፃል፡፡ ኢየሱስ

የእግዚአብሔር መቅድስ የመሠረት ድንጋይ /1 ጴጥ 2:4..8/ መሆኑንና ክርስቲያኖቹ የመቅድስ ድንጋዮች /1ጴጥ 2:5/ መሆናቸውን መግለጫዎች አስቀምጠውልናል።

## 3. ዙፋኑ

«... የመንግሥቱንም /የኢየሱስን/ ዙፋን ለዘለዓለም አጸናለሁ።
በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ ዙፋኑንም ለዘዓለሙ ይጠነክራል።»
/2 ሳሙ 7:13 ኢሳ 9:6..7/

የክርስቶስ መንግሥት በዳዊት የእስራኤል መንግሥት ላይ የመሠረታል ይህም ማለት የሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት የእስራኤል መንግሥትን እንደገና የሚያጠናክር ይሆናል ማለት ነው። ይህን ቃል ኪዳን ለማሟላትም በዳዊት «ዙፋን» ወይም የግዛት ቦታ ላይ መንገሥ ይኖርበታል። ይህም ኢየሩሳሌምን የሚያመለክት ነው። ቃልኪዳኖቹ ይፈጸሙ ዘንድ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር እንደሚቆም የሚያረጋግጥ ሌላ ማሥረጃ ነው።

## 4. መንግሥቱ

«...ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘዓለም ይጠነክራል
ዙፋንህም ለዘለዓለም ይፀናል።» /ሣሙ 6:16/ የሚለው የሚያመለክተው የክርስቶስን ዘለዓለማዊ መንግሥት መመሥረት ዳዊት በዓይኑ የሚያየው እንደሚሆን ነው። ክርቶስ ተመልሶ ሲመጣ ዳዊት ከሞት እንደሚነሣና በዓለም ሁሉ መንግሥቱ የኢየሱስ ንግሥ በኢየሩሳሌም ሲቋቋም በዓይኑ እንደሚያይ ነው።

እነዚህ ለዳዊት የተሰጡ የተስፋ ቃሎችን መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው። ዳዊት ስለእነዚህ ነገሮች እንዲህ ሲል በደስታ ተናግሯል...

«... ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን... ይህ ሁሉ የእኔ የድነነትና የእኔ ሙሉ ምኞት ነው» /2 ሳሙ 23:5/ እነዚህ የእኛን ድነነትም ያሳያሉ። ክርስቲያናዊነት እነዚህን ትምህርቶች ከማስተማር ይልቅ እነዚህን እውነታዎች የሚቃረን ከሆነ አሳዛኝ ይሆናል።

ኢየሱስ በአካል «ቀድሞ ከነበረ» ማለትም ከመወለዱ በፊት እንደሰው ሆኖ ኢየሱስ የዳዊት «ዘር» ወይም ተወላጅ ስለመሆኑ ለዳዊት የተሰጠው የተስፋ ቃል ከንቱ ያደርገዋል።

የእግዚአብሔር መንግሥትም በሰማየ ሰማያት የሚሆን ከሆነ ኢየሱስ በእስራኤል የዳዊትን መንግሥት እንደገና ሊያጠናክር አይችልም፤ ከዳዊት «ዙፋን» ላይም ሊነግሥ አይችልም። እነዚህ ነገሮች በተጨባጭ ምድር ላይ ነበር። ስለሆነም እንደገና መመሥረታቸውም በዚሁ ተመሳሳይ ቦታ መሆን ይኖርባቸዋል።

## በሰለሞን መፈጸም

የዳዊት ልጅ ሰለሞን ለዳዊት ከተሰጡት የተስፋ ቃሎች ጥቂት ክፍሎችን ፈጽሞአል። ለእግዚአብሔር በተጨባጭ መቅደሱን አንጸዋል። /1 ነግሥ 5:8/ የበለጸሀገም መንግሥትም ነበረው። ለሰለሞን ያሳቸውን አክብሮት ለመግለጽ ከዓለም ዙሪያ መንግሥታት ተወካዮቻቸውን ልከዋል። /1 ነገሥ 10/ ከመቅደሱም ተጠቃሚ በመሆን ታላቅ መንፈሳዊ በረከት ነበር። ስለዚህ የሰለሞን መንገሥ ይልቁንም ለዳዊት ተሰጥተው የነበሩት የተስፋ ቃሎች በላቀ ሁኔታ ተፈጽመዋል።

አንዳንዶቹ ለዳዊት የተሰጡ የተስፍ ቃሎች በሰለሞን ጊዜ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸሚ ይናገራሉ ይህ አባባል ግን እንዳልሆኑ በሚከተሉት ተሸረዋል...

... ሰፊ የሐዲስ ኪዳን ማስረጃዎች «ዘሩ» ኢየሱስ እንጂ ሰለሞን አለመሆኑን ያስረዳሉ።

... እግዚአብሔር ለእርሱ /ለዳዊት/ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ዳዊት የያዛቸው ለአብርሃም ከተሰጡት ጋር ይመሳሰላል /1 ቆሮን 17:27 ዘፍጥ 22:17..18/

... የ«ዘሩ» መንግሥት ዘለዓለማዊ መሆን ስለነበረበት ዘላለማዊ ካልሆነው ከሰሎሞን ጋር አይዛመድም።

... የተስፋ ቃሎቹ ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚመለከቱ መሆናቸውን ዳዊት ተገንዝቧል። ይህም የቅርብ ቤተሰብን ሊመለከት አይችልም። «ምንም እንኳን የእኔ ቤት ከእግዚአብሔር ጋር ባይሆንም ከእኔ ጋር ዘለዓለማዊ የተስፋ ቃሎች ሠርቷል።» /2 ሳሙ 23:5/

... የዳዊት ዘር አዳኙ አምላክ ከኃጢአት ያዳነው ነው። /ኢሳ 9:67፣ 22:22 ኤርም 33፣ 5፣65 ዮሐ 742/ ነገር ግን ሰሎሞን የኋላ ኋላ ለእግዚአብሔር ጀርባውን ሰጠ። / 1 ነገሥ 11:1..3፣ ነሒሚ 13:26/ ከእስራኤል ተስፋ ውጭ ከሆኑት በፈጸመው ጋብቻ ምክንያት።

# ጥናት 3 ጥያቄዎች

ከሚከተሉት የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ውስጥ በኃጢ .1
አትና በጽድቅ መካከል ያለውን የማያቋርጥ ትግል የትኛው
ነው?

ሀ/ ለኖኅ የተሰጠው የተስፋ ቃል

ለ/ በኤደን የተሰጠው የተስፋ ቃል

ሐ/ ለዳዊት የተሰጠው የተስፋ ቃል

መ/ ለአብርሃም የተሰጠው የተስፋ ቃል

2. በኤደን የተሰጠው የተስፋ ቃል በተመለከተ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኛው እውነት ነው?

ሀ/ የእባቧ ዘር ሉሲፈር ናት፡፡

ለ/ ክርስቶስና ጻድቁ የሴቲቱ ዘር ናቸው፡፡

ሐ/ የእባቧ ዘር ለጊዜያዊ በክርስቶስ ቆስሎ ነበር፡፡

መ/ የሴቲቱ ዘር በክርስቶስ ሞት ተቀጠቀጠ፡፡

3. የአብርሃን ዘ ለዘለዓለም የት ይኖራል?

ሀ/ በመንግሥተ ሰማያት

ለ/ በኢየሩሳሌም ከተማ

ሐ/ በምድር ላይ

መ/ ጥቂቶች በመንግሥተ ሰማያት ሌሎች በምድር

4. ለዳዊት የተሰጠው የተስፋ ቃል የትኛው ነበር?
ሀ/ የእርሱ ዘሮች /ተወላጆች/ ለዘለዓለም እንደሚነግሡ

ለ/ የእርሱ ዘር በሰማያት መንግሥት እንደሚኖራቸው

ሐ/ «ዘሩ» የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን

መ/ የእርሱ ዘር /ኢየሱስ/ በምድር ከመወለዱ በፊት በሰማያት እንደሚኖር

# 4. እግዚአብሔርና    ሞቱ

# 4.1 የሰው ተፈጥሮ

ከሰው ልጆች አብዛኛዎቹ ስለሞት የሚያወጡ የሚያወርዱበት ጊዜ አነስተኛ ይመስላስ። እንደዚህ ያለው ራስን አለመፈተሽ የሚያመራው ወደራስን አለማወቅ ነው እና ስለሆነም ሕዝቦች በየግል ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶቻቸው ተዘናግተው ውሣኔ በመስጠት በሕይወታቸው እንዲሁ ይንሳፈፋሉ። ሕይወት በጣም አጭር የሆነና አንድ ቀን እኛም የሞት ጽዋን እንደምንቀምስ የሚያመላክተውን የአለመቀበል ሁኔታ ይታያል።

«ሕይወትህ ምንድን ነው? ጤዛ ነው። ያውም ለትንሽ ጊዜ የሚታይና

ታይቶም ቶሎ የሚጠፋ» መሞት ይኖርብናል እናም መሬት ላይ

የተተፉ እንደገና ሊታፈስ የማይቻል እንደውኃ ያለን ነን።

«በማለዳ እንደሣር ያልፋል ማልዶ /የወጣትነት ጊዜ/ ያብባል

ያልፋልም። በሠርክም ጠውልጎና ደርቆ ይወድቃል።»

/ቶማስ 4፡14፣ 2 ሣሙ 14፡14 መዝ 90፣፡5..6/

እውነት አሳቢ የሆነው ሙሴ ይህን ተገንዝቧል። እናም እግዚአብሔርን እንዲህ ሲል ተማፀነ።

« በልብ ጥበብን እንድንማር ቀኝህን እንዲህ አስታውቀን።

/መዝ 90፡12/ ስለሆነም ከሕይወቶቻችን ማጠር አንፃር እውነተኛ

ብልሃትን /ጥበብን/ ለማግኘት ቁጥር አንድ ተቀዳሚ ተግባራችን

አድርገን መነሣት ይገባናል።

ሰዎች ስለሞት ያላቸው ምላሽ የተለያየ ነው። ጥቂት ባህሎች ሞትንና ተቀብር ሥነ..ሥርዓትን የሕይወታቸው አካል አድርገው ለማሳየት አብዛኞቹ በተለይ «የክርስትናን» ስም የያዙ ሰው «የማይሞት ለፍስ» ወይም ሞትን አሸንፎ የሚወጣ የማይሞት ነገር ከውጡ ያለው በኋላም ወደወሮታ መቀበያ ወይም ወደቅጣት ቦታ የሚሄድ ነው ብለው ድምዳሜ ላት ደርሰዋል። ሞት በሰው ልጅ ዘንድ መሠረታዊ ችግርና እጅግ አሳዛኝ ክስተት እንደመሆኑ መጠን የሰው አዕምሮ በአዕምሮው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ብዙ ልምምድ አድርጎበት /ተላምዶት/ ሞትንና የሰውን ተፈጥሮ በተመለከተ የተሳሳቱ አመለካከቶች ሲከሰቱ ማየት የሚጠበቅ ነው።

እንደሁልጊዜው እነዚህ እጅግ ጠቃሚ ርዕስት ጉዳዮች ከመጽሐፍ ቅዱስ አኳያ ተፈትነው እውነታው መገለጽ ያሻዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ተመዝግቦ እንደሚታየው የመጀመሪያው ቅጥፈት በኤደን አትክልት ቦታ ላይ ስለእባቧ የተነገረው መታወስ ይኖርበታል። ግልጽ ያለውን የእግዚአብሔር መግለጫ ማለትም ኃጢአት ከሠራ ሰው በእርግጥ ይሞታል። «/ዘፍጥ 2:17/ የሚለውን በመጻረር እባቧ ለሴቲቱ በእርግጥም አትሞችም» ብላለች። /ዘፍጥ 3.4/ የሰው መጨረሻው ሞት መሆኑን አለመቀበል የተሳሳቱ ኃይማኖቶች መግለጫ ባህርይ ሆኗል። በተለይ ይህ የሚያረጋግጥልን አንዱ የተሳሳተ ትምህርት ወደሌላው፣ ሌላው ደግሞ ወደሌላ እያመራ እንደሚሄድና በተቃራኒውም ትክክለኛው ትምህርት ወደ ሌላ ትክክልኛ ትምህርት ወዘተ እንደሚያመራ ነው። /ቆሮን 15:13..17/። እዚህ ላይ ጳውሎስ ከአንድ እውነታ ወደሌላ እውነት ዘሏል /«ቢሆን ቢሆን ...» የሚለውን አስተውል።/

የእኛን እውነተኛ ተፈጥሮ ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ስለሰው አገባጠር የሚለውን እናስብ... «...እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ከምድር ዐፈር አበጀው በአፍንጫውም የሕትወት እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ለፍስ ያለው ሆነ... ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስበት ድርስ አፈር ነህና ወደዐፈርም ትመለሳለህ።» /ዘፍጥ 2:7 ፣ 3:19/ ሰው በውስጡ የማይሞት መሆኑን የሚያመለክት ፍንጭ የለም። ከሞት በኋላ እንደሚኖር የሚያሳይ ክፍልም የለም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ሰው በመሠረቱ የተሠራው ለአፈር መሆኑን በማያሻማና ጉልህ በማድረግ ያሳያል። «እኛ ጭቃ ነን» /ኢሳ 64:8/ «ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው።» /ቆሮን 15:47/ የሰው መሠረቱ በትቢያ ውስጥ የሆነ ነው።» /ኢዮ 4:10/ «ሰው ወደአፈር ይመለሳል።» /ኢዮ 34:14..15/ አብርሃም «...አፈርና አመድ» /ዘፍጥ 18:27/ መሆኑን ተቀበለ። የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በኤደን መጣሱን ተከትሎ እግዚአብሔር «አዳምን አስወጣው... አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር...» /ዘፍጥ 3:22..24/። ሰው በተፈጥሮው ሕያውነት በውስጡ ቢኖረዉ ኖሮ ይህ አስፈላጊ ባልሆነ ነበር።

## ቅድመ ሁኔታዊ ሕያውነት

የማያቋርጥና ተደጋጋሚ የወንጌል መልዕክት ዘለዓለማዊ ሕይወትና ህያውነት በክርስቶስ ሥራ መንገድ ሊያገኝ ይችላል። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ብቸኛው የህያውነት መንገድ ነው። ይህም የሚያሳየው የዘላለማዊነት ሀሳብ መጥፎ በመሥራት የሰው ልጅ ስቃይ ውስጥ ወድቋል የሚለው አካሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተቀባይነት /ድጋፍ/ የለውም። ህያውነት ለማግኘት ያለው ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በማክበርና በሚያከብሩትም ሕይወታቸው ፍጹማዊ፣ ለጽድቅ የሚሰጠውን ዋጋ የሚቀበሉ ይሆናል።

የሚከተሉት ጥቅሶች ዘላለማዊነት ቅድመ ሁኔታ የሚጠይቅ ማረጋገጫና በተፈጥሮአችንም የያዝነው መሆኑን ያመላክታሉ።

«ክርስቶስ... በወንጌል ሕይወትንና ህያውነትን እንዳመጣ ተገለጠ።
/2ጢሞ 1፡10፣ 1ዮሐ 1፡2/
«... ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት /በውስጣችሁ ለማለት ነው/ የላችሁም። ሥጋዬንም የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው። እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ።» ይህን ዘለዓለማዊ ሕይወት ለመስጠት።
/ዮሐ 6፡53..54/

በዮሐንስ ምዕራፍ 6 ሁሉ ክርስቶስ የሚገልጸው «የሕይወት እንጀራ» መሆኑንና ለእርሱ ትክክለኛ ምላሽ በመስጠት ብቻ የሕያውነት ተስፋ ሊኖር እንደሚችል ነው።
/ዮሐ 6፡47 50፣51፣57፣58/

... «እግዚአብሔርም የዘለዓለምን ሕይወት እንዲሰጠን /አማኞቹ/ ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ» /ዮሐ 5፡11/ «በክርስቶስ» ያላመኑ የህያውነት ተስፋ ሊኖራቸው አይችልም።

«ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘለዓለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።»
/ዕብራ 5፡9/
የሰው ስጅ ሕያውነት ከአጀማመሩም ሊሆን የቻለው በክርስቶስ ሥራ ነው።
... እውነተኛ አማኝ ሕያውነትን ይፈልጋል። ለዚህም በዘለዓለማዊ ሕይወት ስጦታ ይቀበላል። ይህም በተፈጥሮው ያልያዘውን ነው።
/ሮሜ 2፡7፣ 6፡23/ /ዮሐ 10፡28/

ሚች አካላችን «የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።» /1 ቆሮን 15፡53/ ስለሆነም ህያውነት ቃል ኪዳን የተሰጠበት ነገር እንጂ በእጅ የተጨበጠ አይደለም። /ዮሐ 2፡25/

..እግዚአብሔር ብቻ ነው በውስጡ ህያውነት የያዘው። /1ጢሞ 6፡16/

# 4.2 **ነፍስ**

ከላይ እንደገለጽነው ሰው «/ሕያው ነፍስ» ያለው ወይም በውስጡ ህያው ሁነ ንጥረ ነገር በተፈጥሮው የታደለው ነው ብሎ መቀበል የማይታሰብ ነው። «ነፍስ» የሚለውን ቃል በተመለከተ ያለውን ውኀንብር ግልጽ ለማድረግ እንሞክራለን...

ነፍስ በእብራይስጥ «ኔፌሽ» በግሪክ «ፕሱኼ» ተብሎ በመጽሐፍ እንደሚከተለው ተተርጉሟል።

| | |
|---|---|
| አካል | እስትንፋስ |
| ፍጡር | ልብ |
| አዕምሮ | ግለሰው |
| እሱ ራሱ | |

ስለሆነም «ነፍስ» ሰውን፣ አካልን ወይም ራስን ያመለክታል በሚገባ የሚታወቀው «ነፍሳችንን አድን» /ኤስ ኦ ኤስ/ በግልጽ እኛን ከሞት አድነን» ማለት ነው፡፡ «ነፍስ» ስለዚህ «አንተ» ወይም ሰውን ሰው እንዲሆን ያደረጉት ነገሮች ሁሉ ድምር ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠራቸው እንስሳት «ተንቀሳቃሾች ሕያዋን ፍጥረታት እያንዳንዱ ሕያው ፍጥረት..» /ዘፍጥ 1፡20..21/ ተብለው ይጠራሉ፡፡ «...ሰውም ሕያው ነፍስ ያለውሆነ፡፡» /ዘፍጥ 2፡7/ እንዲሁም ሰው ነፍስ ነው እንስሳት ነፍሶች እንደሆኑ ሁሉ በሰው ልጅና በእንስሳት መካከል ያለው ብቸኛ ልዩነት ሰው በአዕምሮው ከእንስሳት በላይ መሆኑና በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው፡፡/ዘፍጥ 1፡26/ እንዲሁም ጥቂት ሰዎች ለእነርሱ ክፍት የሆነውን የህያውነት ተስፋ የሚያዩበትን ወንጌል ያውቁ ዘንድ መጠራታቸው ነው፡፡ /2 ጢሞ 1፡10/ መሠረታዊ ተፈጥሮአችንን የመሞታችንንም ተፈጥሮ በሚመለከት በሰዎችና በእንስሳት መካከል ልዩነት የለም፡፡

> «የሰው ልጆችና የእንስሳት ዕድል ፈንታ አንድ ነው፡፡ ድርሻቸውም ትክክል ነው አንዱ እንደሚሞት ሌላው እንዲሁ ይሞታል፡፡ የሁሉም
> እስትንፋስ አንድ ነው ሁሉም ከንቱ ነውና፡፡ ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም ሁሉም ወደአንድ ቦታ ይሄዳል /ሰውና እንስሳ ወደመቃብር/
> ሁሉም ከዐፈር ነው ሁሉም ወደ ዐፈር ይመለሳል፡፡» /መክብብ 3፡19..20/ በመንፈስ የተነሣሣው መጽሐፈ መክብብን የጻፈው የሰው
> ልጅ ይህን እውነታ ይቀበል ዘንድ ለእግዚአብሔር ፀለየ ይኸውም እንዲህ ሲል «እኔ በልቤ ስለሰው ልጆች እንደእንስሳ መሆናቸውን እንዲያዩ ይፈትናቸዋል አልሁ፡፡» /መክብብ 3፡18/

ብዙ ሰዎች ይህን ዕውነት ለመቀበል የሚከብዳቸው መሆኑ የሚጠበቅ ነው፡፡ በእርግጥም እኛ በተፈጥሮአችን እንስሳት ነን ብለን ለመቀበል ሊያሳፍረን ይችላል፡፡ ተመሳሳት ራስን ለመጠበቅ የሚያሳምነውን ደመ ነፍሳትና ጠ ንካሮች በደካሞች ላይ
ለመኖር ያለው ሂደት ስናገናዝብም እንዲሁ ሰው እንስሳ መሆኑን እንዲያይ ማድረጉም እግዚአብሔር ሰውን ሲፈትነው ነው ተብሎ ተጽፏል፡፡ ይህ ማለትም የእግዚአብሔር ታማኝ ትሁት ሰዎች የሆኑት ይህን እውነት ይቀበላሉ ይህን ፈተና ይወድቃሉ፡፡ የሰው ልጆች እጅግ ከፍተኛ ጥቅምና ዋጋ ያላቸው ናቸው የሚለውን ሃሳብ የሚያራምዱ ..የሰውነት ፍልስፍናን.. በ20ኛው መቶ ዘመን በዓለም ሁሉ ቀስ እያሉ ተሠራጭተዋል፡፡ በመዝሙረ ዳዊት 39፡5 ላይ የሠፈሩት ግልጽ ቃላት ይህን ያስረዳሉ... «ሰው በውቡ ሁኔታውም ሳይቀር በአንድነት ከንቱ ነው፡፡» «የሰው

መንገድ ከራሱ እንዳይደለ አውቃለሁ። አካሄዱንም ለማቅናት ከሚራመድ ሰው አይደለም።» /ኤርም 10፡20/

እጅግ መሠረታዊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ የሰው ልጆች አካላት.. በእርግጥ ህያው የሆኑ ፍጥረታትም ሁሉ በመጨረሻ መሞታቸውን ማወቃችን ነው። «ነፍስ» ስለሆነም ይሞታል። ህያው ከሆነ ነገር ሁሉ ትክክለኛ ተቃራኒ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ሦስተኛው «ነፍስ» የሚለውን ቃል ከሞት ጋር አዛምዶ የነፍስን መጥፋት የሚገልጽ መሆኑ ሊያስደንቀን አይገባም። ለፍስ ስለሚለው ቃል እውነታው የሚያረጋግጥልን የማትጠፋና ህያው የሆነ ሊሆን የሚችል ነገር አለመሆኑን ነው።

.. «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ ትሞታለች» //ዘ 18፡4/
.. እግዚአብሔር ነፍስን ሊያጠፋት ይችላል። /ማቴ 10፡28/

ነፍሳት የሚጠፉ መሆናቸውን በተመለከተ ሌሎች ማሥረጃዎች
/ሕዝ 22፡27 ምሣሌ 6፡32 ሌቭ 23፡30/ ናቸው።

.. በሐዞር ከተማ ውስጥ የነበሩት «ነፍሳት» ሁሉ በጎራዴ ተገደሉ
/ዮሽ 11፡11፣ 10፡30..39/
.. «ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ» /ራዕ 16፡3 መዝ 78፡50/
.. የሙሴ ሕግ ደጋግሞ ያዘዘው አንዳንድ ሕጎችን የሚያከብር ነፍስ ሁሉ መገደል አለበት። /ሣሌ 25፡27..31/
.. ስለመታነቅ ወይም ስለማጥመድ የምንናገር ከሆነ ትርጉም የሚሰጠን ነፍስ
የምትሞት መሆኑን ከተረዳን ዘንድ ነው
/ምሣ 18፡7 22፡25 ኢዮ 7፡15/
.. «ነፍሱን በሕይወት ማቆየት የሚችል አንድም የለም።» /22፡29/
.. ክርስቶስ «ነፍሱን ስለኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ...» «ነፍሱን» ወይም ሕይወቱ ለኃጢአት መደምሰሻ ተብሎ የተሠራ ነው።
/ኢሳ 53፡ 10..12/

«ነፍስ» የሚያመለክተው ሰው ወይም አካል እንጂ በውስጣችን ያለ ሕያው ብልጭታ አይደለም። ለዚህም ጥቅት ግልጽ ምሣሌዎች አሉ..

.. «የነፍሳት ደም» /ኤርም 2፡34/
.. «..ማንም ሰው የሚያምለውን ቃል ቢሰማ ምስክር ሆኖም አንድ ነገር አይቶ እንደሆነ ወይም አውቆ እንደሆነ ባይናገር ኃጢአት መሥራቱ ነውና በደሉን ይሸከማል።

ማናቸውም ሰው ሳይታወቀው ርኩስ ነገር ቢነካ... እርኩስነቱን ሳያውቅ እርኩሱን ሰው ቢነካ በማናቸውም ርኩሰት ቢረክስ ቢሆን ነገሩ በታወቀው ጊዜ በደል ይሆንበታል፡፡
ማንናቸውም ሰው ሳያውቅ ክፉውን ወይም መልካሙን ያደርግ ዘንድ ያደርግ ዘንድ ሳያስብ በከንፈሩ ተናግሮ ቢምል ሳያስብ የማለው ስለማናቸውም ነገር ቢሆን በታወቀው ጊዜ ከዚህ ነገር በአንዱ በደለኛ ይሆናል፡፡»
/ዘሌዋ 5:1..4/
.. «ነፍሴ ሆይ ያ ሁዐ በውስጤ ነው ያለው እግሐዘአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን ምሥጋናውንም ሁሉ አትርሺ ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት» /መዝ 103፡፡1 2 5/
... «ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና ስለእኔ ስለወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል፡፡» /ማር 8:35/
ይህ «ነፍስ» በሰው ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ንጥረ ነገር እምደሚያመለክት በቂ ማሥረጃ ነው፡፡

## 4.3 የሰው መንፈስ

በብዙ ሰዎች አዕምሮ ዘንድ ነፍስና መንፈስ መካከል መምታት አለ፡፡ «ነፍስን» በመሠረታዊነት የሚገልጸው ሰው የተሠራበትን ሁሉ ነገር ሲሆን አልፎ አልፎ መንፈስም እንደተሠራ ነው፡፡ ለነገሩ በትርጉም ነፍስና መንፈስ ልዩነት እንዳላቸው በመጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ተገልጾአል፡፡ ነፍስና መንፈስ ሊከፋፈሉ የሚችሉ ናቸው፡፡ /ዕብ 4:12/

በእብራይስጥ «መንፈስ» ሩዋህ በግሪክ ፐኒዩማ በሚከተሉት መንገዶች ይተረጎማል፡፡

| | |
|---|---|
| ሕይወት | መንፈስ |
| አዕምሮ | ነፋስ |
| እስትንፋስ | |

እግዚአብሔር ፍጥረትን የሰውን ጭምር ለመጠበቅ የእርሱን መንፈስ የጠቀማል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ልጆች ውስጥ የሕይወት ኃይል ሆኖ የሚሠራ ነው፡፡ «የሰው አካል ያለመንፈስ ሙት ነው፡፡» /ቶማስ2:26/

«እግዚአብሔር በአፍንጫውም /አዳም/ የሕይወት እስትንፋስ
እፍ አለበት ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ» /ዘፍጥ 2.7/

ኢዮብ «የእግዚአብሔር መንፈስ» «በአፍንጫው ውስጥ» ያለ እንደሆነ ይናገራል። /ኢዮብ 27፡3 ኢሣ 2፡22/ በእኛ ውስጥ ያለ የሕይወት መንፈስ ስንወለድ ለእኛ የተሰጠን አካላችን እስካለ ድርስም በሕይወት አብሮን የሚቆይ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ከማንኛውም ነገር ሲነፍግ ወዲያውኑ ይጠፋል መንፈስ የሕይወት ኃይል ነውና እግዚአብሔር «... መንፈስና እስትንፋሱን ወደራሱ ቢሰበስብ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በአንድንት ይጠ ፋል። ሰውም ወደዐፈር ይመለሳል አስተዋይ ብትሆን ይህንን ስማ»
/ኢዮብ 34፡14..16/

በሞት ጊዜ የእርሱን /የእግዚአብሔርን/ መንፈስ ከእኛ እግዚአብሔር ወደዚያ ሲወስድ የእኛ አካል መሞት ብቻ ሳይሆን የእኛ ሙሉ ንቃተ ህሊና ያቆማል ዳዊት ይህን ማድነቁ ነበር እንደሰው ደካማ በሆነው በፍጡር ከማመን ይልቅ በእግዚአብሔር ወደማመን እንዲያመራ የሆነው።

መዝሙረ ዳዊት በ146፡3..5 ላይ ሰውነትን በተመለከተ ጠንካራ ተቃውሞ አለው ትወጣለች ወደመሬትም ይመለሳል። ያን ጊዜ ምክሩ ሁሉ ይጠፋል የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ ተስፋውም በአምላኩ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ምሥጉን ነው።» /መዝ 146፡3..5/

በሞት ጊዜ «ዐፈርም ወደነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደሰጠው ወደእግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ።» /መክ 12፡7/ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በየትኛው ሥፍራ እንደሚገኝ አሳይተናል። በዚህም ስሜት «እግዚአብሔር መንፈስ ነው።» /ዮሐ 4፡24/

ስንሞት «የመጨረሻ እስትንፋሳችንን» እንተነፍሳለን ይኸውም የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ ውስጥ ለቅቆ ይሄዳል ማለት ነው። መንፈስም በዙሪያችን ሁሉ ያለው ወደ እግዚአብሔር መንፈስ ይሳብና ስንሞት መንፈሱ ወደእግዚአብሔር ይመለሳል።

ፍጥረታትን ሁሉ የሚይዘው የእግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ይህ የሞት ሂደት በእንስሳትም ይፈጸማል። ሰዎችና እንስሳት አንድ ዓይነት መንፈስና የሕይወት ኃይል በውስጣቸው አለ።

«የሰው ልጆችና የእንስሳት ዕድል ፈንታ አንድ ነው ድርሻቸውም ትክክል ነው አንዱ እንደሚሞት ሌላው እንዲሁ ይሞታል። የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው። ሁሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም።» /መክ 3፡19/

ፀሐፊው የሰው ልጆች መንፈስና የእንስሳት መንፈስ በመጨረሻ የሚሄድባቸውን ማረፊያ በተመለከተ ይህ ነው የሚባል የሚታይ የተለየ ልዩነት የለም እስከማለት ይሄዳል። /መክ 3:21/ የሰው ልጅና እንስሳት አንድ ዓይነት መንፈስና አንድ ዓይነት አሟሟት እንዳላቸው መግለጽ እንዴት ሁለቱ የሰው ልጅና እንስሳት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መንፈስ አላቸው የሚባለውንና ሁለቱም በጎርፍ አንድ ዓይነት ሞት መሞታቸውን ወደኋላ የሚያነሣ ይሆናል። /ዘፍጥ 2:7፣ 7:15/ «በምድር ላይ ሥጋ ያለው የሚንቀሳቀሰው ሁሉ ወፉም እንስሰውም አራዊቱም በምድር ላይ የሚርመሰመሰው ተንቀሳቃሹም ሁሉ ሰውም ሁሉ ጠፉ። በየብስ የነበረው በአፍንጫው የሕይወት ነፍስ እስትንፋስ ያለው ሁሉ ሞተ በምድር ላይ የነበረው ከሰው ጀምሮ እስከእንስሳ ድረስ ተደመሰሰ።» /ዘፍጥ 7:21..23/ ባኦሪት ዘፍጥረት 7 ላይ የተመዘገበው በግልጽ የሚያሳየው የሰው ልጅ «እንደሁሉም ሥጋ ለባሽ እንደማንኛው ህያው ነገር» በአንድ ዓይነት ደረጃ ውስጥ መሆኑን ነው።

## 4.4 ሞት ራስን መሳት ነው

ስለነፍስና ስለመንፈስ እስካሁን ከተማርነው የምንረዳው የሞተ ሰው ሙሉ በሙሉ ራሱን የሳተ መሆኑን ነው። ይህን በተመለከተ ከሚከተሉት ግልጽ አባባሎች አንፃር ለመሟገት አስቸጋሪ ነው...

> ... «/የሰው ልጅ/ ነፍሱ ትወጣለች ወደመሬቱም ይመለሳል። ያን ጊዜ ምክሩ
>
> ሁሉ ይጠፋል።» /መዝ 146:4/

... «ሙታን ግን አንዳች አያውቁም... ፍቅራቸውና ጥላቸው ቅንዓታቸውም

በአንድነት ጠፍቶአል።» /መክ 9፡5..6/ «አንተ በምትሄድብት ዕውቀትና

ጥበብ አይገኝምና» /መክ 9፡10/ ማለት መቃብር። ማሰብ የለም ስለሆነም

ንቃተ ህሊና የለም።

... ኢዮብ ይላል.. በሞት ጊዜ «እንዳልነበረ» /ኢዮብ 10፡18/ 18/ ይሆናል።

ሞት ራስን መሳት መርሳትና አለመኖር እንዲሁም ከመወለዳችን በፊት

የነበረ እንደሆነ ኢዮብ አስተውሏል።

... የሰው ልጅ እንደእንስሳት ሁሉ ይሞታል /መክ 3፡18/ የሰው ልጅ ሞትን

አቸንፎ አንድ ቦታ የሚኖር ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሳይንስ ስለዚህ

ያሉት ነገር ባይኖርም ፀጥ ቢሉም እንስሳትም ይገባቸዋል።

... «እግዚአብሔር እኛ አፈር እንደሆንን አሰበ ሰውስ ዘመኑ እንደሣር

ነው እንደዱር አባበ እንዲሁ ያብባል ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ያልፋልና

ስፍራውንም ደግሞ አያውቅምና» /መዝ 103፡14..16/

ሞት በእውነትም ለጻድቃን እንኳን ሳይቀር ራስን መሳት በመሆኑ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሁሉ ከለሞት በኋላ ለመመስገንና ለመዳን እንደማይችሉ በሚገባ ስለሚረዱ የዚህ ዓለም ዕድሜያቸው ይረዝም ዘንድ እግዚአብሔርን ደጋግመው ሲማፀኑ ይታያሉ። ሕዝቅኤል /ኢሣ 38፡17..19/ ና ዳዊት /መዝ 6፡4..5፣ 30፡9 39፡13 115፡17/ ለዚህ ጥሩ ምሣሌዎች ናቸው። ሞት ለጻድቃንም ሆነ ለኃጢአን እንቅልፍ ወይም ዕረፍት እንደሆነ ተደጋግሞ ይገለጻል /ኢዮብ 3፡11..17 ዳን 12፡13/

የሰው ልጅ በሞተ ጊዜ በቀጥታ ጻድቃን ወደመንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ የሚባለው በብዛት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው አባባል በመጽሐፍ ቅዱስ የተመለከተበት ቦታ የለም። ስለሞትና ስለሰው ተፈጥሮ ያለው እውነተኛ ትምህርት በውስጣችን ሰላምን የሚሰጥ ነው። ከዚህ ሁሉ የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ከሚቀበለው መከራና ስቃይ በኋላ መቃብር ፈጽሞ የመረሻ ቦታ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለማያውቁ ይህ መረሳት ለዘለዓለም ይቀጥላል። ይህ አሳዛኝና ያልተሟላ ተፈጥሮአዊ ሕይወት እንደገና ይነሣል ማለት የሰው ተፈጥሮአዊ አዕምሮ የፈጠረው በጣም ደካማ ተስፋና ፍራቻ የመነጨ ሊሆን የማይችል ነው።

በመጽሐፍ ጥናት ዕውነትን የማግኛ አካሄድ እንዳለ ሁሉ በሰው ኃይማኖታዊ አስተሳሰብ ስህተትም የሚፈጠርበት መጽሐፍ ቅዱስ በአንክሮ ባለመመልከት /ባለረዳት/ አካሄድም አለ። የሞትን መጨረሻ ለማወቅ በሚያደርገው ጥረት የሰው

ልጅ ህያው ነፍስ እንዳለው ወደማመን እያመራው ሄዷል:: በሰው ውስጥ ህያው ነፍስ አለ የሚለውን የተቀበለ ደግሞ ከሞት በኋላ ወደአንድ ቦታ መሄድ እንዳለ ማሰብ የግድ አስፈላጊ ይሆናል:: ይህ ደግሞ በፋንታው በሞት ጊዜ በጻድቃንና በኃጢአን መካከል ልዩነት መኖር እንዳለበት ወደሚያመራው አስተሳሰብ ይስበናል:: ይህን ለማቻቻል «ጥሩ ህያው ነፍስ» የምትሄድበት ቦታ እንዳለና ስሙም መንግሥተ ሰማያት እንደሆነ መጥፎ ህያው ነፍስ የምትሄድበት ቦታ እንዳለ ስሙም ገሃነም እንደሚባል መደምደሚያ ላይ ይደረሳል:: ቀደም ሲል «ህያው ነፍስ» የሚባል በመጽሐፍ ቅዱስ ዘንድ ፈጽሞ የማይቻል እንደሆነ አሳይተናል:: በብዙ ዘንድ እውነት እንደሆመ የሚነገርለትን የተሳሳተ አባባል አሁን በሚቀጥሉት ነጥቦች ጠቅለል አድርገን እናስቀምጣቸው::

በሕይወታችን ስለፈጸምነው በሞት ጊዜ ዋጋ ይሰጠ .1
ናል:: ዋጋውም
ህያው ነፍሳችን የሆነ ቦታ ይመደብለታል::

ጻድቃንና ኃጢአን በሞተ ጊዜ ይለያሉ:: .2
የጻድቃን ካሣ /ሽልማት/ ወደመንግሥተ ሰማያት .3
መሄድ ነው::
ማንኛውም ህያው ነፍስ ካለው ማንኛውም .4
ወደመንግሥተ ሰማያት
ወይም ወደ ገሃነም መሄዱ የግድ ይሆናል::

የኃጢአን ነፍሶች ገሃነም ወደሚባል የቅጣት ቦታ .5
ይሄዳሉ::

ይህ ትንታኒያችን እንዲሁ የአፍራሽነት ተግባር አይደለም፡፡ እነዚህን ነጥቦች በዝርዝር በማስቀመጥ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶችን ለመግለጽ ይቻላል ብለን ከማመን እንጂ፡፡

## 4.5 ትንሣዔው

የጻድቃን ካሣ በትንሣዔ .. ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ እንደሚፈጸም መጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ /1 ተሰላ 4፡16/ የሚተውን ማስነሣት ክርስቶስ የሚደርገው የመጀመሪያ ነገር ነው፡፡ ይህም የፍርድ ቀንን ያስከትላል፡፡ ነፍስ በሞት ጊዜ ወደመንግሥተ ሰማያት ገብቶ ከሆነ ደግሞ የትንሣዔ ቀን አስፈላጊ አይሆንም፡፡ የትንሣኔ ቀን ከሌለ ለእግዙአብሔር ታማኝነትን ትርጉም የሌለው እንደሚያደርገው ጳውሎስ ተናግሮአል፡፡ /1 ቆሮን 15፡32/ ጳውሎስ እርሱም በሞት ጊዜ «ነፍሱ» ወደመንግሥተ ሰማያት በመሄድ የምይካስ መሆኑን ቢያምን ኖሮ በእርግጥ እንደዚህ አይልም ነበር፡፡ የዚህ አንድምታም የአካላችን ትንሣዔ ብቸኛው የመካሻ መንገድ መሆኑን ጳውሎስ አምኗል የሚለው ይሆናል፡፡ አሁን በህይወት ላሉ አማኞች በትንሣዔ ቀን ዋጋ እንጠብቅ ዘንድ ክርስቶስ አደፋፍሮናል፡፡ /ሉቃ 14፡14/

ከአካላዊ ቅርጽ የተለየ ሌላ የመኖር ቅርጽ ስለመኖሩ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር እንደገና መነሣት ያለበት ነጥብ ነው፡፡ ይህ ቅርጽ እግዚአብሔር ክርስቶስ መላዕክቱ እና ሰው ልጅ ቅርጽ ላይ ይሠራል፡፡ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ «.. ሁሉን እንኳን ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል» /ፊል 3፡20..21/ አሁን ባለው ሰብዓዊ አካልና አካሉም ከደም ይልቅ በመንፈስ ንፁህ ኃይል የተሞላ በመሆኑ ተመሳሳይ ካሣ እንጋራለን፡፡ በፍርድ ቀን የዚህን ዓለም አካላዊ ሕይወታቸውን የኖሩ ሁሉ ወደአፈር ተመልሰው የሚበሰብሱ አሁን ከያዙት ከሟች አካላቸው ጋር ሲቀሩ የሥጋን ፍላጎት ለማቸነፍ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሆነው

የሞከሩት ደግሞ ከመንፈስ በተሞላ ሥጋዊ ቅርጽ የዘለዓለምን ሕይወት ያጭዳሉ።» /ገላ 6፡3/

ጻድቃን በአካላዊ ቅርጽ ዋጋ እንደሚቀበሉ ተጨማሪ አማግኝ አስረጂ አለ። ይህን ተቀባይነት ካገኘ የትንሣኤ ጠቃሚነት ግልጽ ይሆናል። አሁን ያለው አካላዊ ቅርጻችን በሞት ጊዜ ያከትነማል። ዘለዓለማዊ ሕይወትና በአካላዊ ቅርፅ ህያውነት መላመድ ብቻ ከቻልን ሞት ራስን የመሣት ሁኔታ መሆን ይኖርበታል ይኸውም አካላችን እንደገና እስከሚፈጠርና በኋላም የእግዚአብሔር ተፈጥሮ እስኪሰጠው ድረስ ነው።

1 ቆሮንቶስ 15 ስለትንሣዔው በዝርዝር ያትታል። በጥሞና በጥንቃቄ መነበብ ያለበት ነው። 1 ቆሮንቶስ 15፡35..44 ዘር ተዘርቶ ከመሬት በሕእግዚአብሔር አካላዊ ቅርጽ ተሰጥቶት እንደሚወጣ የሞተውም እንዴት በተመሳሳይ ቅርጽ ይዞ እንደሚነሣ ያትታል። ክርስቶስ ከመቃብር ተነሥቶ ሟቹ አካሉ ወደማይሞት አካሉ መለወጡ የእውነተኛ አማኝ ዋጋ ተምሣሌት መሆኑን ያሳያል። በጥምቀታችን ምክንያት ከክርስቶስ መሞትና መነሣት አንድ በመሆናችን ክርስቶስ ያገኘውን ዋጋ ሁሉ እንቀበላለን። ዛሬ ሥቃዩን እንደምንቀበል ሁሉ ሽልማቱንም እንጋራለን።

« የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንሠራለን።»
/ 2 ቆሮን 4፡10/

« ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወት ይሰጠዋል።/ /ሮሜ 8፡11/

በዚህ ተስፋ የምንጠብቀው «የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ..» /ሮሜ 8፡23/ በዚያም ሰውነት ህያው መሆንን ይሆናል። ይህ የሰውነት ተስፋ በመጀመሪያዎቹ የእግዚአብሔር አማኞች የታወቀ ነበር። አብርሃም በከነዓን ምድር እንዲመላለስበት ለሁልጊዜውም እንዲወርስ ቃል ተሰጥቶት ነበር። በዚያ ቃል ኪዳኖች የነበረው እምነት በሆነ መንገድ በመጭው ጊዜ ሰውነቱ ተነሥቶ ህያው ሊሆን እንደሚችል ነው።

ኢዮብ በግልጽ ያስቀመጠው ሲሞት በዘመሚት የሚበላው አካሉ አካሉ እንደገና በሰውነት እንዴት እንደሚመለስ ያለውን ግንዛቤ ነበር።

«እኔን ግን የሚበገፍኝ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቸ እግዚአብሔርን እንጻይ ዐውቃለሁ። እኔ ራሴ

አየዋለሁ:: ዓይኖቻም ይመለከቱታል:: ከእኔም ሌላ አይደለም ልቤ
በመናፈቅ ዝሎአል::» /ኢዮብ 19:2...7/
የኢሳያስም ተስፋ ተመሳሳይ ነበር:: «ሙታን ህያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሣሉ»
/ኢሳ 26:19/
የኢየሱስ ወዳጅ ስለነበረው ስለአልዓዛር ሞት ተመሳሳይ ቃላት ተብሏል:: በማጽናናት ፋንታ ጌታ ኢየሱስ ስለትንሣዔው ቀን ነው የነገራቸው:: «ወንድምሽ እንደገና ይነሣል» አላት:: የአልዓዛር እህት ማርታ ሰጺያውኑ የሰጠችው ምላሽ የሚያመለክተው ምን ያህል በቀድሞዎቹ ክርስቲያኖች አድናቆትን ያገኘ ነው::
«ማርታም በመጨረሻው ቀን በትንሣዔ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው::» /ዮሐ 11:24..24/ እንደኢዮብ ሁሉ ማርታም ሞት ወደህይወት በር ወደሆነው ገነት የሚያስተላልፍ አለመሆኑን በመረዳት ስለትንሣዔው ቀን ነው ወደፊት አራምዳ የተመለከተችው:: «በመጨረሻው ቀን» ስትል /ኢዮብ ግን «በኋለኛው ቀን» ብሎታል::/ ጌታችን «... እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል:: እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደእኔ ይመጣል» ሲል ቃል ሰጥቶኛል:: /ዮሐ 6:44..45/

# 4.6 የእግዚአብሔር ፍርድ /ብይን/

የአንድ እምነት መሠረታዊ መርሆው ማለትም ከጥምቀት በፊት ግልጽ ሊሆን የሚገባው መጽሐፍ ፍርድን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ነው::
/የሐዋ ሥ 24:25 ዕብራ 6:2/ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተደጋግሞ «ስለፍርድ ቀን» የምናገኘው /2 ጴጥ 2:29 3:7 1 ዮሐ 4:17/ የእግዚአብሔር ዕውቀት የተሰጣቸው ሽልማታቸው የሚቀበሉበት ቀን እንደሆነ ነው:: እነዚህ ሁሉ «በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት መቆም» ይኖርባቸዋል:: /2 ቆሮን 5:10/ በአካላዊ ቅርጽ በሕይወታችን የሚኖረንን ዋጋ ለመቀበል እንድንችል::

የክርስቶስን ዳግም መምጣት በተመለከተ የዳንዔል ዕይታ ከእነዚህ የፍርድ ወንበሮች አንዱ ዙፋን ወንበር እንደሚሆን ጽፎአል:: /ዳን 9:14/ አባባሉን ጌታቸው ተመልሶ አሽከሮችን ሰጥቷቸው የሃደውን ገንዘብ እንዴት በተገቢው መንገድ እንዳዋሉት ከመጠይቅ ጋር ያመሳስለዋል:: /ማቴ 13:47..49/ የአሣ አጥማጆች ተምሣሌት የወንጌል ጥሪ ከአሣ ማጥመጃ መረብ ያመሳስለዋል:: ብዙ ዓይነት ሰዎች ቢያስባስብም ጥሩውን ከመጥፎ

አሣ እንደሚለይ ሁሉ ሰዎችንም እንዲሁ ይለያያቸዋል፡፡ /ማቴ 13፡47..49/ ትርጓሜው ግልጽ ነው፡፡ «በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፡፡ መላልክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል፡፡»

እስካሁን ከየነው ከጌታ መመለስና ከትንሣዔ በኋላ ወደወንጌል የተጠሩት ሁሉ ክርስቶስን ያገኙ ዘንድ በተለየ ቦታና ጊዜ አንድ ላይ ይሰበሰባሉ፡፡ ጌታም ሰዎች በሠሩት ሥራ ተመዝነው ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ፈቃድና ዋጋ የሚቀበሉትን ከማይቀበሉት ይለያል፡፡ በዚህ ጊዜ ብቻ ነው ጻድቃን ዋጋ የሚቀበሉት፡፡ በበጎቹና በፍየሎቹ ተምሣሌነት በተጻፈው ይህ ሁሉ ተጠቃሎአል፡፡

« የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን / በዳዊት ዙፋን በኢየሩሳሌም/ ይቀመጣል፡፡ አህዛብም ከመላው ዓለም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፡፡ እረኛም በጎቹን በቀኙ ፍየሎቹን በግራው ያቆማቸዋል፡፡ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ፡፡» /ማቴ 25፡31..34/

የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ ለአብርሃም የተሰጠውን ቃል ኪዳን መቀበል የጻድቃን ሽልማት /ዋጋ/ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ከፍርድ ቀን በኋላ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከክርስቶስ መመለስ በፊት ቃል የተገባልንን የህያውነት አካል ሽልማትን መቀበል ፍጹም አይቻልም፡፡ ከዚህም በማጠቃለል ለማለት የሚቻለው ከሞት እስከ ትንሣዔ ባለው ጊዜ አማኙ ንቃተ ህሊና ያለው ኑሮ በፍጹም አይኖረውም፡፡ በማንኛውም አካል ባለው መልኩ ለመኖር አይቻልም፡፡

ክርስቶስ ሲመለስ እንጂ ከመመለሱ በፊት እንደማይሆን ተደጋግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ መርሆ ላይ የሠፈረ ነው፡፡

…«…የእረኞቹም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን
የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ፡፡» /1 ጴጥ 5፡4/
…« በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው
በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በመገለጡና በመንግሥቱም
እመክርሃለሁ፡፡ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል
ይህንም ጽድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል
ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ
አይደለም፡፡»
/2 ጢሞ 4፡1..8/
መሲሁ በሚመለስበት የመጨረሻ ቀን «በምድር ትቢያ ውስጥ
ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፡፡ እኩሌቶቹ ወደዘለዓለም ሕይወት

እኩሌቶቹም ወደእረፍትና ወደዘለዓለም ጉስቁልና» ይሄዳሉ
/ዳን 12፡2/
... ለፍርድ ክርስቶስ ሲመጣ እነዚያ «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁ
ን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፡፡ መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይመጣሉና በዚህ አታደንቁ፡፡» /ዮሐ 5፡25..29/

... «እነሆ እኔ /ክርስቶስ/ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡»
/ራዕይ 22፡12/
ዋጋ ለመግኘት ወደመንግሥተ ሰማያት አንሄድም ክርስቶስ
መንግሥተ ሰማያትን የመጣልናል እንጂ፡፡

ዋጋችንን ኢየሱስ ይመስልናል ስንል ለእኛ በመንግሥተ ሰማያት የተዘጋጀ ግን ዳግም ወደምድር ሲመለስ የሚያመጣልን ማለታችን ነው፡፡ ለአብርሃም እንደሚሰጥ ቃል የተገባለትን ምድር «እንወርሳለን» ስንል ደግሞ ተጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ይባረክ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይጋለጥ ዘንድ ለተዘጋጀው መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል፡፡» /1ጴጥ 1፡4..5/ ያለውን ማመላከታችን ነው፡፡

ይህን ከተገነዘብን የበለጠ ግልጽ ያልተረዳነውን ምንባብ ዮሐንስ መልዕክት ምዕራፍ 14፡2..3 ላይ የተመዘገበውን «... ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና ሄጄም ሥፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ፡፡ ወደእኤም እወስዳችኋለሁ፡፡» በትክክል ለመረዳት እንችላለን፡፡ ሌላ በተለይም ዋጋችንን ለመክፈል እንደገና እንደሚመለስ /ራዕይ 22፡12/ ና ያም ዋጋ የሚሰጠው በፍርድ ዙፋኑ ላይ ሆኖ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በዳዊት ዙፋን ላይ በኢየሩሳሌም ለዘላለም እንደሚነግሥ አይተናል፡፡ /ሉቃ 1፡32..33/
በምድር ላይ ዘላለማዊ ሕይወትን ያጠፉል ያም የእግዚአብሔርን መንግሥት መሰርት ነው፡፡ «ወደ እራሴ አንተን ለመቀበል» ሲል በፍርድ እርሱ እንደሚቀበለን ያመለክታል፡፡ ይህም የግድ ወደኢየሱስ በአካል መንቀሳቀስ ይሆናል ማለት አይደለም፡፡

ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት በፍርድ ጊዜ ዋጋ ይሰጣል የሚለው የሚያመላክተው እንድምት ሲሞቱ ጻድቃንም ኃጢአንም ወደአንድ ቦታ እንደሚሄዱ ነው፡፡ ይኸውም ወደመቃብር ነው ፡፡ በሞት ጊዜ ልዩነት አይፈጠርም፡፡ የሚከተሉት ጥቅሶች የዚህ አወንታዊ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

.. ዮናታን ጻድቅ ነበር፤ ግን ሣኦል ኃጢእ ነበት፤ ሆኖም «በሞታቸው አልተለያዩም።» 2 ሣሙ 1:23/

... ሣኦል፣ ዮናታንና ሣሙኤል በሞት ጊዜ ሁሉም ወደአንድ ዓይነት ቦታ ሂዱ።/1 ሣሙ 28:19/

... ፃስቁ አብርሃም በሞተ ጊዜ «ወደ ሕዝቦቹ ተሰባሰበ» ወይም ወደአያቶቹ አመነዛሬዎች ነበሩና። /ዘፍጥ 25:8 ፣ ዮሸዋ 24:2/

... በመንፈስ ብልጡና ሞኙ አንድ ዓይነት ሞት ይሞታሉ። /ዘሑ 2.15..16/

ይህ ሁሉ አባባል በክርስትና ዕምነት ተከታዮች ዘንድ ተቀባይነት ከአገኘው የተከመደ ግንዛቤ የተቃረነ ነው። በሞት ጊዜ ደግ የሠራው ጻድቅ ወደመንግሥተ ሰማያት ቀጥታ ይሂዳል የሚለው የተለመደ አመለካከት የትንሣዔንና የፍርድን ቀን አስገላጊነት ሙሉ በሙሉ ይደመስሰዋል። በእግዚአብሔር የመዳን ዕቅድና የወንጌል ትክክለኛ ስብከት የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ጠቃሚ መልዕክት እንደሆነ አይተናል። በሕዝብ የተለመደው ሃሳብ የሚያመለክተው አንድ ጻድቅ ሰው ስሞት ወደመንግሥተ ሰማይ በመሄድ ዋጋውን ይቀበሳል። በሚቀጥለው ቀን፣ወር፣ዓመት ደግሞ በሌሎቹ ተከታይነት ይኸው ያለመቋረጥ ይቀጥላል። ይህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ጻድቃን በአንድነት በአንድ ጊዜ ዋጋቸው ይከፈላቸዋል የሚለውን ይጻረራል።

... አንድ በአንድ በጎቹ ከፍየሎቹ በፍርድ ቀን ይለያሉ።
ፍርዱም እንዳለቀ ክርስቶስ በጎቹ ሁሉ በቀኙ በኩል
እንዲሰበሰቡ ይነግራቸዋል እንዲህም ይላቸዋል።
«እናንተ የአባቴ ብሩካን ኑ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ
ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ»
/ማቴ 25:14/
ስለሆነም ሁሉም በጎቹ መንግሥቱን በአንድ ጊዜ ይወርሳሉ።
/1 ቆሮን 15:52/
... በክርስቶስ መመለሻና በፍርድ «የመኸር» ጊዜ ወንጌልን
በመስበክ የደከሙ ሁሉ በአንድነት ይዘምራሉ /ይፈነድቃሉ/
/ዮሐ 4:35..36፣ ማቴ 13:39/
... በራዕይ 11:18 «... በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ
ለባሪያዎችህም፣ ለነቢያትና ለጻድቃን ስምህንም ለሚፈሩት
ለታናናሾቹና ለታላላቆቺም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ ምድርንም
የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ» ተገልጿል

/ራዕ 11፡18/ ማለትም ሁሉም አማኞች በአንድነት ነው፡፡
ወደ ዕብራውያን ምዕራፍ 11 የብሉይ ኪዳን የጻድቃንን ስሞች የሚጠቅስ ምዕራፍ ነው፡፡ ቁጥር 13 ላይ የተሰጠው አስተያየት እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባባት ስለሚገኘው ድነነት ለአብርሃም የተሰጠውን የተስፋ ቃል አልተቀበሉም የሚል ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በሞቱ ጊዜ አንድ በአንድ ዋጋቸውን ለመቀበል ወደመንግሥተ ሰማያት አመሩ ማለት መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ የሚሰጠው ምክንያት ደግሞ የተስፋውን ቃል አይደለም የተቀበሉት እግዚአብሔር ጥቂት የተወሰኑ ነገሮች ሰጥቶን እነርሱ ያለእኛ የተሟሉ /ፍጹም/ ሆነው ሊሠሩ አይችሉም የሚል ነው፡፡ /ዕብ 11፡39..40/ የተስፋውን ቃል እግዚአብሔር በዕቅዱ ማዘግየቱ አማኞች ሁሉ በአንድ ላይ ፍጹም ሆነው መሠራት ስላለባቸው ነው፡፡ ይህ የሚሆነው በክርስቶስ ዳግም መምጣትና በፍርድ ቀን ነው፡፡

## 4.7 የሽልማቱ ቦታ ሰማይ ወይስ ምድር?

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተለየ የእግዚአብሔር መንግሥት ማለትም የተስፋው ቃል ዋጋ የሚሰጥበት ቦታ መንግሥተ ሰማያት እንጂ ምድር አይደለም የሚል ስሜት እስካሁን ስሜት ያለው ማንም ሰው ሚከተሉትንም ነጥቦችም በተጨማሪ መግለጽ ይገባዋል፡፡

**የጌታ ፀሎት የእግዚአብሔር መንግሥት እንድትመጣ • /ማለትም ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣ ዘንድ የሚደረገው ፀሎት/ የእግዚአብሔር ፈቃድ አሁን በሰማይ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁ በምድር ይፈጸማል፡፡ /ማቴ 6፡10/ ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደምድር እንድትመጣ እንፀልያለን፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሳያስቡበት በየቀኑ እነዚህን ቃላት ይፀልያሉ፤ ይኸውም በሌላ በኩል የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማያት ተመስርቶ አልቆአል መሬትም ትጠፋለች ማለት እጅግ አሳዛኝ ነው፡፡**

«የዋሆች ብፁዓ ን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና» /ማቴ 5፡5/ • ነፍሶቻቸው ወደሰማይ ስለሚሄዱ አይደለም ይህም መዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 37 ሙሉ በሙሉ ትኩረት የሚሰጠው የጻድቃን የመጨረሻ ዋጋ የሚከፈለው ምድር ላይ መሆኑን ነው ክፉዎች ጊዜያዊ ብልጫ አግኝተው በሚቧርቁበት በዚያችው ተመሳሳይ ምድር ጻድቃኑ በዘላለማዊ ሕይወት ይካሳሉ ክፉዎች የበላይነር አግኝተው ይዘዋት የነበረችውን ምድር ይወርሳሉ፡፡ /መዝ 37፡34..35/ «ገሮች ምድርን ይወርሳሉ፡፡ በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል፡፡ እርሱን የሚባርኩት ምድርን ይወርሳሉና የሚረግሙት ግን ይጠፋሉ፡፡ ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፡፡ በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ፡፡» /መዝ 37፡11..29/፡፡ የተስፋ ቃል በተሰጠባት ምድር መኖር ማለት የሰማይ ዘላለማዊ ሕይወት ፈጽሞ የማይቻል ነው፡፡

«ዳዊት ሞቷል፡፡ ተቀብሯልም፡፡ ዳዊት ወደሰማያት • አላረገም» /ሐዋ 2፡29..34/ ይልቁንም ተስፋው ክርስቶስ ሲመለስ ከሞት እንደሚነሣ ነው፡፡ /ሐዋ 2፡22..36/

ምድር ለሰው ልጅ የእግዚአብሔር ሥራዎች የሚከናወኑበት • ቦታ ነች፡፡«የሰማያተ ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው፡፡ ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት፡፡» /መዝ 115፡16/

ራዕይ 5፡9.10 ጻድቃን ከፍርድ ዙፋኑ ዘንድ ተቀባይነት • እንዳገኙ ሲገለጽላቸው ምን እንደሚሉ ነው የሚያስረዳው፡፡ «ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና

ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው በምድርም ላይ ይነግሣሉ» ይላል።
የዳንኤል ትንቢያዎች በምዕራፍ 2:5..7 ይህንኑ ያጠ• ናክራሉ። «ለልዑል ቅዱሳን ሕዝብ ይሰጣል መንግሥቱም የዘላለም መንግሥት ነው።» /ዳን 7:27/። ስለዚህ ዋጋቸው በመንግሥቱ ዘላለማዊ ሕይወት በምድር ላይ ክርስቶስ ዳግም ሲመለስ እንደሚከፈል ነው።

## 4.8 የግዚአብሔር ተጠሪነት

ሰው የማይሞት ነፍስ በተፈጥሮው ካለው በሆነ ቦታ ማለትም የሽልማት ወይም የቅጣት ዘላለማዊ መዳረሻ ሊኖረው የግድ ይሆናል። የዚህ እንድምታ ማምን ሰው ተጠያቂነቱ ለእግዚአብሔር ነው። በአንፃሩም የሰው ተፈጥሮ ከእንስሳት እንደማይለይ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። የተወሰኑ ሰዎች በእግዚአብሔር መንግሥት የዘላለም ሕይወት እንደተሰጣቸው ተስፋ ተሰጥቷቸዋል። በዚህ ዓለም የኖሩ ሁሉ ትንሣዔ ያገኛሉ ማለትም እንጻልሁነ ግልጽ መሆን ይኖርበታል፤ እንደእንስሳት ሁሉ ሰዎች ይኖራሉ ወደዐፈርነት ይለወጣሉ። ይሞታሉ በፍርድ የሚወገዙና ዘላለማዊ ሕይወት የሚያገኙ ጥቂት ሰዎች ስለሚኖሩ ከሰው ልጆች መካከል ለፍርድና ለሽልማት ትንሣዔ የሚያገኙ ክፍሎች እንደሚኖሩ ማጠቃለል

እንችላለን። ፍርዱ የሚመለከታቸው መሆናቸውና አለመሆናቸው እንደኃላፊነታቸው ልዩነት ታይቶ መነሣት ያለበትና የሌለበት ይለያል። የፍርዳችን መሠረቱ እንዴት ለእግዚአብሔር ቃል ያለን ዕውቀት ነው። ክርስቶስ እንደገለጸው «የሚጥለኝ ቃሌንም የማትቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው። እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈረድበታል።» /ዮሐ 12፡48 የክርስቶስን ቃል ያልተረዱ ወይም ያላወቁ እና ስለሆነም ለመቀበልና ለመጣል ዕድል ያልነበራቸው በፍርዱ ቀን ተጠያቂ አይደሉም።

> «ያለሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለሕግ ፈግሞ ይጠፋሉ። ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈርድባቸዋል» /ሮሜ 2፡12/ በዚህም እግዚአብሔር የሚፈልጋቸውን ያላወቁ እንደእንስሳት ይጠፋሉ፤ እያወቁ የእግዚአብሔርን ህግ የሚጥሱ ግን ፍርድን ለመቀበል ከሞት ይነሣሉ።

በእግዚአብሔር እይታ «ህግ በሌለበት ኃጢአት አይሠራም።» «ኃጢአት /የእግዚአብሔር/ ሕግ መተላለፍ ነው።» «ሕግ ነው የኃጢአት መገለጫው» «//ሕግ እስኪወጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበርና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቀጠርም።» /ሮሜ 5፡13፣ 1 ዮሐ 3፡4 ሮሜ 3፡20/ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕጎች ያላወቀ ኃጢአት አይቆጠርበትምና ፍርድም ትንሣዔም አያገኝም። የእግዚአብሔርን ቃል ያላወቁ ሁሉ እንደእንስሶችና እንደዛፎች ሁሉ ሞተው ይቀራሉ።

> «አዕምሮ የሌለው ክቡር ሰው እንደሚጠፉ እንስሶች መሠለ።» /መዝ 49፡20/
> «እንደበጎች ወደ ሲኦል የሚሄዱ ናቸው» /መዝ 49፡14/

የግዚአብሔርን መንገዶች ማወቃችን ለሥራዎቻችን ሁሉ ተጠያቂ ስለሚያደርገን ለትንሣዔያችንና ለፍርድ መቈረባችን ወሣኞች ራሳችን ነን፡፡ ስለዚህ ጻድቃን ወይም የተጠመቁ ብቻ የመሚነሡ አለመሆነናቸው ግልጽ ሊሆንልን ይገባል፡፡ የሚነሡት ስለእግዚአብሔር ያላቸው ዕውቀት ምክንያት ሆኖ ለእግዚአብሔር ተጠሪ የሆኑት ሁሉ እንጂ፡፡ ከመጽሐፍ እንጥቀስ ...

... ዮሐ 15፡22 የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ኃላፊነት ላይ እንደሚጥል ሲያሳይ

> «እኔ /ኢየሱስ/ መጥቸ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸው ነበር አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የለባቸውም» ይላል፡፡ ወደሮሜ 1፡20..21 እንዲሁ እግዚአብሔርን ማወቃቸው ሰዎችን ለሥራቸው

## ሁሉ ያለ አንዳች ምክንያት ይተዋቸዋል፡፡

**«ወደእኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡፡ እኔም በመጨረሻው ቀን**

**አስነሳዋለሁ፡፡ ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ**

**ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል፡፡ እንግድህ ከአብ የሰማ የተማረ**

**ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፡፡» /ዮሐ** 6፡44..45/

... በእርግጥ የእርሱን መንገዶች ባለማወቅ የሚሠሩትን ሁሉ እግዚአብሔር አያዘክርም፤ መንገዶችን የሚያውቁትን ግን ይከታተላቸዋል መልስም ለማግኘት ይጠብቃል፡፡ /ሐዋ 17፡30/

... «የጌታውንም ፈቃድ ዐውቆ ያልተዘጋጀ እንደፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፡፡ /ለሣሳሌ ሞቱ በመቅረት/ ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፡፡ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል፡፡» /ሉቃ 12፡47..48/

... «ስለሆነም ጥሩ ለማድረግ የሚያውቅ ግን ለማይፈጽመው ለእርሱ ኃጢአት ነው።» /ቶማ 4፡17/

... እርሱን በተመለከተ የእግዚአብሔር ራዕይ ለእስራኤሎች የተለየ የእግዚአብሔር ተጠሪነት ነበረባቸው።» /አሞ 3፡2/

... «ዕውቀት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትዕዛዝ ሲመለሱ የጻድቃን መንገድ ባላወቁት በተሻላቸው ነበርና።» /2ጴጥ 2፡21/ ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶችን ዮሐ 9፡41 3፡19፣ 1 ጢሞ 1፡13፣ ዳግ 1፡39 ይጨምራል።

እግዚአብሔርን ማወቃችን ለፍርዱ ዙፋን ተጠያቂ ይደርገናል። ከዚህም በመነሳት የእግዚአብሔር ዕውቀቱ የሌላቸው እንደማይኖራቸው ግልጽ ይሆናል። ይኸውም እንደሚጠፉት እንደአራዊት ተፈርጀው ፍርድ አይደረግላቸውም ማለት ነው። በምድር የኖሩት ሁሉ ትንሣዔ እንደማይሰጣቸው ግልጽ የሆኑ ምልክቶች አሉ...

... የባቢሎን ጥንታዊ ሕዝቦች ከሞቱ በኋላ «አይነሡም» ምክንያቱም
ስለእውነተኛው እግዚአብሔር ምንም ዕውቀት አልነበራቸውምና /ኤር 51፡39 ኢሣ 43፡17/

... ኢሳያስ ራሱን አበረታቶአል «አቤቱ አምላካችን ሆይ ካንተ በቀር ሌሎች ጌቶች ገዝተውናል። እነርሱም ሞተዋል በሕይወት
አይኖሩም። ጠፍተዋል። አይኮንኑም መታሰቢያቸውን ሁሉ ምንምን አድርገዋል።» /ኢሣ 26፡13..14/

እንደማይነሱ ሦስት ጊዜያት በመጥቀስ የተነገረውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። «እንደገና አይኖሩም» «አይነሱም» «መታሰቢያቸው ሁሉ ይጠፋል» ማለቱን።

በተቃራኒው የእስራኤል ሕዝቦች እግዚአብሔርን ያወቁ በመሆናቸው የትንሣዔ ተስፋ ተሰጥቷቸዋል። «ሙታንም /እስራኤሎች/ ሕያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሣሉ»

/ኢሣ 26፡19/

...የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆኑት እስራኤላውያን ስንናገር «ክርስቶስ

በሚመለስበት ጊዜ «በምድርም ትቢያ ውስጥ ከአንቀላፉት ብዙዎቹ

ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደእረፍትና

ወደ ዘላለም ጉስቁልና» ተብሎ ተጽፎአል። /ዳን 12፡2/ ስለዚህ

ሁሉም ባይሆኑ ብዙዎቹ አይሁዳውያን ይነሣሉ። የተመረጡ ሕዝቦች

ሆነው ለእግዚአብሔር ባላቸው ኃላፊነት እነዚያ ስለእውነተኛው

እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ እውሮች የሆኑት «ይወድቃሉ ደግሞም

አይነሱም።» /አሞ 8፡12..14/ «የእግዚአብሔርን ቃል ለመግኘት

አልታደሉምና»

አሁን የተማርነው

1/ የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ለእርሱ ተጠያቂነትን እንደሚያመጣ

2/ ተጠያቂነት ያላቸው ብቻ እንደሚነሡና ለፍርድ እንደሚቀርቡ

3/ እውነተኛውን እግዚአብሔርን የማያውቁ እንደእንስሳት ሁሉ ሞተው

እንደሚቀሩ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ማጠቃለያዎች የምንረዳው በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዛሬም በታሪክም ሁሉ ያለፉት እውነተኛውን ወንጌል ያላወቁ፣ አእምሮአቸው በፀና ታምሞ የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕድት ለመጠበቅ ያልቻሉ የወንጌልን መልዕክት ለመርዳት ዕድሜያቸው ያልደረሱ ህፃናት ወጣት ልጆች ሁሉ ስለእግዚአብሔር ዕውቀቱ ከሌለላቸውና ለእግዚአብሔርም ኃላፊነት ከሌላቸው ተመድበው ትንሣዔ አያገኙም ለፍርድም አይቀርቡም። ወላጆቻው መንፈሳውያን ቢሆኑም እንኳን ይህ ሰብአዊነትን፣ የተፈጥሮ ፍላጎትንና ስሜትን ይጻረራል። ስለመጨረሻው እውነት የእግዚአብሔርን ቃል ደግነትና በእኛ

ተፈጥሮ ውስጥ ያለደግነት ሀሳብ ሁሉ የዚህን ዕውነት ለመቀጠል ወደሚያስችለን ይመራናል። በሰብዓዊ ተፈጥሮአችን ያሉ ሐቆችን ስንመረምር ያውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን መመሪያ ሳናውቅ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ቡድኖች የወደፊት ሕይወት ተስፋ አይኖራቸውም ወደሚል መደምደምያ ያመራናል።

በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ የእግዚአብሔርን መንገዶች ስናስጠይቅ የሚያመራን መንገድን ወደመሳት ነው። «አንተ ሰው ሆይ ለእግዚአብሔር የምትመልል ማን ነህ?» /ሮሜ 9፡20/ እርግጥ እውቀታችን ውሡን ነው ነገር ግን እግዚአብሔር አድላዊ ነው ወይም ሐቀኛ አይደለም ብለን መክሰስ አያስችለንም። እግዚአብሔር በማንኛውም መንገድ የሰውን ልጅ እንደማያፈቅር ወይም በዚህ በዚህ ተሳስቷል የሚል አንድምት ኃያሉ ሁሉ የማትሳነው እግዚአብሔር አባታችንና ፈጣሪያችን ፍጥረታቱን ሁሉ ትክክል ባልሆነና አግማኝ ባልሆነ መንገድ እንደሚያስተናግደን ወደሚል ይወስደናል። ንጉሥ ዳዊት ልጁን ባጣበት ጊዜ የተናገረውን ማንበብ ይረዳናል። ዳዊት ልጁ በሕይወቱ በነበረበት ወቅት ለልጁ አጠንክሮ ፀልዮ ነበር። ነገር ግን የሞቱን እውነታ ተቀብሏል። «ህፃኑ ሕያው ሳለ እግዚአብሔር ይምረኝ ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደሆነ ማን ያውቃል? ብዬ ጾምሁ። አለቀስሁም፤ አሁን ግን ሞቶአል የምጾመው ስለምንድን ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደእርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደእኔ አይመለስም አለ።» / 2 ሣሙ 12፡15..24/ ከዚያም ምሽቱን አጽናናት ወዲያውም ሌላ ህፃን አገኙ።

በመጨረሻም ብዙ ሰዎች ይህንን በእግዚአብሔር ኃላፊነት መሸከም መርህ በመጨበጥ ስለእርሱ ተጨማሪ ዕውቀት ለመግኘት አለመፈለግ ሊኖር እንደሚችል ሊነግ ይችላል። ለእግዚአብሔር ተጠያቂነትና ለፍርድ መቅረብን በመፍራት ማለት ነው። ሆኖም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን እነዚህ ሰዎች ገና ድሮ በእግዚአብሔር ተጠያቂነትን ተረድተዋልና ከዚያ ሊያመልጡ አይችሉም እግዚአብሔር በዕለት ዕለት ህይወታቸው በመሥራቱ ግንኙነቱ ተፈጥሮአልና። «እግዚአብሔር ፍቅር» መሆኑን ማስታወስ ይገባል። እርሱ «ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም» እንዲሁም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወዷልና።» /ዮሐ 4፡8፣ 2 ጴጥ 3፡9 ዮሐ 3፡16/ እግዚአብሔር በመንግሥቱ እንድንሆን ይፈልጋል።

> እንደዚህ የመሰለ ክብርና መብት ኃላፊነት የግል ማምጣታቸው አይቀርም። እነዚህ በእኛ ላይ እንዲጫኑ የተፈጠሩ አይደሉም። እግዚአብሔርን ከልብ በእውነት ከወደድን ስለድኀነት የሰጠንን አክብረን መቀበልና መያዝ ይገባናል።

በቃሉ አማካይነት የእግዚአብሔር ጥሪ እየተገነዘብን ስንመጣ በሕዝብ መካከል ስንራመድ ሁሉ የምንገነዘበው ለፍቅሩና ለጥበቃው የምንሰጠውን ምላሽ በጉጉት ይጠባበቃል እንጂ በኃላፊነታችን ምክንያት እስክንወድቅ ድረስ አይደለም። እግዚአብሔር የፍቅር ዓይኑን ከእኛ አያነሳም። ለእርሱም ያለንን ዕውቀት ለመረሳት ወይም ለመለወጥ አንችልም። ከእግዚአብሔር ያለንን ልዩ ቅርበት አክብረን መያዝና በዚያም መደሰት ይገባናል። በፍቅሩ ታላቅነት አመኔታ ሊኖረን ይገባል። ለዚህም የበለጠ ለማወቅ እንጂ ያነሰ አያስፈልገንም። ለእግዚአዘብሔር መንገዶችና ፍላጎቶች ያለን የእግዚአብሔር ፍቅር የእርሱን ምሣሌነት እንድንከተል እንጂ የእርሱን ከፍተኛ ቅዱስነት በመፍራት አይደለም።

## 4.9 ሲኦል

የሲኦል ፅንሰ ሐሳብ የደከሙ የማይሞቱ ነፍሶች ከሞት በኋላ የሚቀጠ ብት ወይም ደግሞ በፍርድ ቀን የተወገዙ ሰዎች ቅጣት የሚቀበሉበት ቦታ

እንደሆነ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ሲኦል ሰዎች ሁሉ በሞቱ ጊዜ የሚሄዱበት መቃብር ነው።

**በእብራይስጥ ቋንቋ ቃሉ «ሺኦል» ሲተረጎም «ገሃነም» ወይም «ሲኦል» ማለት የተሸፈነ ቦታ ማለት ነው። ስለዚህ ሶኦል የሚለው ቃል ስናነብ በተሟላ የተተረጎመ ቃል መሆኑን አያብራራም። «ሄል ሜት» የሚለው የእንግሊዘኛ ቋንቋ የራስ ሽፋን ማለት ይሆናል። ከዚህ አኳያ ይህ የተሸፈነ ቦታ ወይም ሲኦል ሲተረጎም «መቃብር» ሊሆን ነው። በመጽሐፍ ላይ «ሺኦል» «መቃብር» መሆኑን ብዙ ጥቅሶች አስቀምጠውታል። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጽሑፎቹ ላይ «ሺኦል» በሚለው ፋንታ «መቃብር» እያሉ ጽፈው እናገኛለን። ጥቂት ጥቅሶች እንይ...**

**... ክፉወዎች በመቃብር /ሼኦል/ ውስጥ ፀጥ ይበሉ።»**

**... «እግዚአብሔር ይቀበለኛልና ነፍሴን ከሲኦል /መቃብር/**

**እጅ ይቤዠታል» /መዝ 49:15/ ማለትም የዳዊት ነፍስ**

**ወይም ሬሳ ከመቃብር ወይም ከ«ሲኦል» እንደሚነሳ ነው።**

**ሶኦል የክፉዎች የመቀመጫ ቦታ ነው የሚለው እምነት ፃድቃንም በኋላ ይነሳሉ እንጂ የሚሄዱበት ቦታ መሆኑንም ማጠቃለል ይኖርበታል። ሆሴዕ 13:14 ይህን በማረጋገጥ**

«ከሲኦል እጅ እታደጋቸዋለሁ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ።» ይላል። እንዲሁም ሁለተኛ መነሣትን በተመለከተ «ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ።» /ራዕይ 20፡13/ ሞት /መቃብር/ና ሲኦል እንዴት ጎን ለጎን እንደተቀመጡ ልብ በሉ።

የሐናህ ቃሎች በ 1 ሣሙኤል 2፡6 በግልጽ ተቀምጠዋል። «.. እግዚአብሔር ይገድላል፤ ያድናልም በትንሣዔ አማካይነት ወደሲኦል /መቃብር/ ያወርዳል። ያወጣል። ሲኦል መቃብር መሆኑን ስናይ ፃድቃን በትንሣኤ አማካይነት ዘላለማዊ ሕይወት በማግኘት ይድናሉ። ወደሲኦል /መቃብር/ መግባትና በኋላም በትንሣዔ አማካይነት ሲኦልን ለቅቆ መነሳት ይቻላል። የኢየሱስ ዋና ምሣሌነት ሊጠቀስ ይችላል። «... ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ።» /ሐዋ 231/ ምክንያቱም ትንሣዔ በማድረጉ ነው። የክርስቶስ «ነፍስ» ና «ሥጋው» ጎን ለጎን መቀመጣቸውን ይስተዋል። ሥጋው «በሲኦል አልተተወም» የሚለው የሚያመለክተው ለሦስት ቀናት ሥጋው በመቃብር መቆየቱን ነው። ክርስቶስ ወደሲኦል መሄዱ ክፉዎቹ ብቻ የሚሄዱበት አለመሆኑን በቂ ማሥረጃ ይሆናል። ጥሩም መጥፎም ሰዎች ወደ «ሲኦል» ማለትም ወደመቃብር ይሄዳሉ። ስለሆነም ኢየሱስ «መቃብሩን ከክፉዎች አደረገ» /ኢሣ 53፡9/። ያዕቆብም ስለልጁ ዮሴፍ ወደሙታን ሥፍራ እያዘንኩ እወርዳለሁ አለ። /ዘፍጥ 37፡35/

ለኃጢአት ቅጣቱ ሞት መሆኑን ከእግዚአብሔር መርሆዎች አንዱ ነው:: /ሮሜ 6:23፣ 8:13፣ ቶማ 1:15/ ኃጢአት ፍጹም ውድመትን እንጂ ዘላለማዊ ቅጣትን አይደለም የሚያስከትለው:: ልክ ሕዝቦች በጎርፍ እንደሚወድሙ ሁሉ:: /ማቴ 21:41 22:7፣ ማር 12:9፣ ቶማ 4:12፣ ሉቃ 17:27/ ልክ እስራኤላውያን በበረሃ እንደሞቱ ሁሉ /1 ቆሮን 10:10/ ስለዚህ ክፉዎች በንቃተ ሂሊና ውስጥ እያሉ ለዘላለሙ የሚቀጡ ወይም የሚሰቃዩ አድርጎ ማየቱ የሚያስኬድ አይሆንም::

ለቃሉ እንግዳ ከሆነ እግዚአብሔር ኃጢአትን አይጭንብንም፣ እየቆጠረም አይመዘግበንም:: /ሮሜ 5:13/ በዚህ ውስጥ ያሉ ሞተው ይቀራሉ:: ለኃጢአት ፍርዱ ሞት ስለሆነ ደካሞች ይህን ይቀበላሉ:: ከክርስቶስ የፍርድ ዙፋን ፊት ከቀረበ በኋላ ክፉዎች ቅጣታቸውን ይቀበላሉ፤ ሞተው ለመቅረትም እንደገና ይሞታሉ:: ይህም በራዕይ 2:11 የተነገረው «ሁለተኛው ሞት» የተባለው ነው:: በክርስቶስ መመለስ ከሞት ይነሣሉ:: ፍርድም ይሰጣቸዋል:: ከዚያም በሁለተኛው ሞት ይቀጣሉ:: ይህም ልክ እንደመጀመሪያው ሞት ሁለት ሙሉ በሙሉ ንቃተ ህሊና በሌለበትና ዘላለማዊ በሆነ ሁኔታ ይሆናል::

የኃጢአት ቅጣት ዘላለማዊ ስለሆነ በመሞታቸው ፍጻሜ አያገኙም:: ሞቶ ለዘላለም መቅረት ዘላለማዊ ቅጣት ነው:: እግዚአብሔር የፈርዖንን ሠራዊት በቀይ ባህር ለዘላለም ያጠፋው እንደገና ተነሥቶ እስራኤልን እንዳያጠቃ አስቦ ነው::

«በቀይ ባህር ውኃ እንዳሰጠማቸው እግዚአብሔርም እስከዛሬ ድረስ እንዳጠፋቸው።» /ዘዳ 11፡4/ ተጽፎአል።

በቀድሞው የቢሉይ ኪዳን ጊዜያት ክፉዎች ወደመቃብር ይመለሱ ዘንድ በመጨረሻዋ ቀን ትንሣኤ እንደሚኖር አማኞች ተገንዝበዋል። ኢዮብ በ21፡30..32 በግልጽ «ኃጢአተኛው በመቅሰፍት ቀን እንደተጠበቀ በቁጣው ቀን እንደሚድን እርሱን ግን ወደ መቃብር ይሸከሙታል።» /ኢዮብ 21፡30..32/ ስለክርስቶስ መመለስና ስለፍርድ ቀን ከተጻፉት ምሣሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ አንዱ ክፉዎች እያወቁ፣ እየሰሙ ይታረዳሉ ይላል። /ሉቃ 19፡27/ 27/ ይህ ሀሳብ ግን ክፉዎች እየሰሙ ግርፋት ባለማቋረጥ እንደሚቀበሉ ለዘላለም ይኖራሉ ከማለት ጋር አይጣጣምም። ለ70 ዓመታት ተግባር ዘላለማዊ ግርፋት ይቀበላሉ ብሎ ማሰብ በማንኛውም መለኪያ አሳማኝ አይደለም። እግዚአብሔር ክፉዎችን ሰዎች በመቅጣት ደስታ አያገኝምና። ስለሆነም ለዘላለሙ በቅጣቱ ውስጥ እንዲኖሩ እንደማይፈልግ የሚጠበቅ ነው። /ሕዝ 18፡23፣ 32፡33፣11፡2፣ 2 ጴጥ 3፡9/

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሲኦል /መቃብር/ ሲያስተምር «እንደበጎች ወደሲኦል የሚሄዱ ናቸው፤ እረኛቸውም ሞት ነው። ብሏል /መዝ 49፡14/። የክርስቶስ ነፍስ ወይም ሥጋ በሲኦል ለሦስት ቀናት ቢቆይም ስቃይ አልደረሰበትም። /ሐዋ 2፡31/ ሲኦል የእሳት ቦታ ቢሀሆን ኑሮ ይህ ሊሆን ባልቻለ ነበር። ሕዝ 32፡26..30 በሕያዋንም ምድር ኃያላኑን ያስፈሩ ነበርና መሣሪያቸውን ይዘው ወደሲኦል ከወረዱ ሰይፋቸውንም ከራሳቸው በታች ካደረጉ ኃጢአታቸውን በአጥንታቸው ላይ ከሆነ ጋር ከወደቁም ካልተገረዙ ኃያላን ጋር ይተኛሉ። አንተም ባልተገረዙት መካከል ትሰበራለህ በሰይፍም ከተገደሉት ጋተ ትተኛለህ ኤደምያስና ለገሥታቶቹ አለቆቿም ሁሉ በዚህ አሉ

በሰይፍ ከተገደሉት ጋር በኃይላቸው ተኝተዋል ካልተገረዙትና ወደጉድጓድ ከሚወርዱት ጋር ይተኛሉ የሰሚን አለቆች ሁሉ ፍዶንያውያንም ሁሉ ከተገደሉት ጋር ወርደው በዚያ አሉ። በኃይላቸውም ያስፈሩ በነበሩ ፍርሃት አፍረዋል። በሰይፍም ከተገደሉት ጋር ሳትገረዙ ተኝተዋል። ወደጉድጓድም ከሚወርዱት ጋር ዕፍረታቸውን ተሸክመዋል። በሰይፍ የተገደሉ ፈርዖንና ሠራዊቱ ሁሉ ያይዋቸዋል። ፈርዖንም ስለብዛቱ ሁሉ ይጽናናሉ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።» /ሕዝ 32፡26..30/ ይህ የሚያመለክተው ተዋጊዎች ከመሣሪያዎቻቸው ጋር እንደሚቀበሩና ከሬሳቸው ራስም ጋሻቸው እንደሚያርፍ ነው። ይህ የሲኦል /የመቃብር/ አገላለጽ ነው። ጴጥሮስ ለክፉ ሰው «የእግዚአብሔር ስጦታ ሀንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ገንዘቡም ከአንተ ጋር ይጠፋል።» ሲል ነግሮታል።/ሐዋ 8፡20/

በሕይወት እንዳለ በግዙፍ ዓሣ ሲዋጥ ዮናስ እንዲህ አለ። «ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደአምላኩ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ» /ዮናስ 2፡1..2/ የሲኦል ሆድ ከዓሣው ሆድ ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ነው። የዓሣው ሆድ የተሸፈነ ቦታ ነበርና የሲኦል ትክክለኛ ትርጉሙን ይይዛል። ሲኦል የእሳት ቦታ አለመሆኑንም በግልጽ ያሳያል። ዮናስም ከሲኦል ሆድ ለመውጣቱ በዓሣው መተፋቱ ያሳያል። ይህም የክርስቶስን ከገሃነም /ከመቃብር/ የሚነሣ መሆኑን አመላክቶ ነበር።

/ማቴ 12፡40 ላይ ተመልከት/

## እሳት

መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ የሚያስተምረው እግዚአብሔር በሰው ኃጠ
-አት ቁጣውን ለመግለጽ ዘላለማዊ እሳት እንደሚጠቀም ነው፡፡ ይህም ኃጠ
-አተኛው በመቃብር ውስጥ እንዳለ መጥፋትን ያስከትላል ነሠማለት ነው፡፡
ነዋሪዎቹ በሠሩት ክፋት ሰዶም በዘላለማዊ እሳት ተቀጥታለች፡፡ ዛሬ ያች
ከተማ ወድማ ከሙት ባህር በታች ተቀብራ ጠፍታ ቀርትለች፡፡ ዛሬ
በእሳት ላይ አትገኝም ይህም በዘላለማዊ እሳት ውስጥ አለመሆኗን
ያረጋግጣል፡፡ እነደዚሁም ኢየሩሳሌም በእስራኤል ኃጢአት እግዚአብሔር
ተቆጥቶ በዘላለማዊ እሳት እንደሚያጠፋት አስጠንቅቆ ነበር፡፡
«በእየሩሳሌም በሮች እንዳትገቡ የነገርኋችሁን ባትሰሙኝ በበሮችዋ ላይ
እሳትን አነድዳለሁ የኢየሩሳሌምም አዳራሾች ትበላለች አትጠፉም» /ኤር
17፡27/ ኢየሩሳሌም የመንግሥቱ ከተማ እንደምትሆን ቃል የተገባላት
ከተማ ቤቶች በእሳት ተበልተው ነበር፤ ሆኖም ያ እሳት ለዘላለሙ
አልቀጠለም፡፡
/2 ንግ 25፡9/

በተመሳሳይም የኢዱሚአ ከተማም እግዚአብሔር
በእሳት ቀጥቷታል፡፡ «.. በሌሊትና በቀንም አትጠፉም ጠ
-ስዋም ለዘላለም ይወጣል ከትውልድም እስከ ትውልድም ድረስ
ባድማ ሆኖ ትኖራለች ለዘለዓለም ምንም አያልፍባትም
ጭልፍትና ጃርት ግን ይወርሷታል በላይዋም የመንፈስ
ገመድና የባዶነት ቱንቢ ይዘረጋባታል፡፡ /ኢሳ 34፡9..15/ በጠ
ፋችዋ የአዱሜአ ከተማ እንስሳትና አትክልት እንደሚኖሩባት
ስናይ ተአላለማዊ እሳት ቋንቋ የእግዚአብሔርን ቁጣና ቦታውን
ሙሉ በሙሉ ማጥፋትን ለመግለጽ የተጠቀመበት ቋንቋ
መሆኑን እንጂ ቃሉን እንዳለ መውሰድ የለብንም፡፡

በኢየሩሳሌምና በእስራኤል ኃጢአት የእግዚአብሔር
ቁጣ ተደጋግሞ በእሳት ተመስሎ ይነገራል፡፡ «..እነሆ ቁጣዬና
መዓቴ በዚህ ሥፍራ ላይ በሰውና በእንስሳት ላይ በዱር

**በዛፎችና በምድር ፍሬ ላይ ይፈሳል፡፡ ይነድዳል አይጠፋምም» ይላል /ኤር 7፡20/**

እሳት ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በኃጢአት የእግዚአብሔር ፍርድ ጋርም ይያያዛል፡፡ «እነሆ እንደምድጃ እሳት የሚነድድ ቀን ይመጣል፡፡ትዕቢተኞችና ኃጢአትን የሚሠሩ ሁሉ ገለባ ይሆናሉ፤ የሚመጣውም ቀን ያቃጥላቸዋል ሥርንና ቅርንጫፍንም አይተውላቸውም፡፡» /ሚልክ 4፡1/ ገለባ ወይም የሰው ሬሳ ሲቃጠል ወደአመድነት ይመለሳል ማንኛውም ነገር ይልቁንም የሰው ሥጋ ለዘላለም ሲቃጠል ሊኖር አይችልም፡፡ የሚቃጠል ነገር ከሌለ ደግሞ እሳት ሲነድ አይኖርም፡፡ «ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ፡፡» /ራዕይ 20፡14/ ይህም ሲኦል ከእሳት ጋር የተለየ መሆኑን ያሳያል፡፡

## ገሃነም

ገሃነም ከኢየሩሳሌም ውጭ የቆሻሻ ቦታን ያመለክታል፡፡ ገሃነም በአረማይክ ቋንቋ ሲሆን በእብራይስጥ ደግሞ «ገቤን ሂኖን» የሚባለው ነው፡፡ ይህ ከኢየሩሳለም አቅራቢያ የሚገኝና ኢየሱስ በነበረበት ዘመን ቆሻሻ የሚደፋበት ቦታ የነበረ ነው፡፡ የወንጀለኛ አስከሬን የሚወረወርበት ባለመቋረጥ እሳት የሚነድበት የፍጹም ውድመትና መወርወሪያ ምልክት ነበር፡፡ «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና» /ዕብ 12፡29/ ይኸውም በፍርድ ቀን የቁጣ እሳቱ ኃጢአተኞችን ፈጽሞ ያጠፋቸዋል፡፡ ሕዝቦቹን እስራኤላውያንን ፍርዱ በባብሎናውያን እጅ ባለፈው በቀጣበት ጊዜ ገሃነም ከእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል በኃጠ ፡አተኞቹ ሬሳ ተሞልቶ ነበር፡፡ /ኤር 7፡32..33/

ዕልቅና ባለው መንገድ ጌታ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ሃሳቦች አንድ ላይ በማምጣት «ገሃነም» የምንለውን ቃል በቦታው ተጠቅሞበታል፡፡ በሚመለስበት ጊዜ በፍርድ ዙፋኑ ሆኖ የተኮነኑት የሚሄዱበትን ደጋግሞ ገልጿል፡፡ «...እሳቱም ወደማይጠ ፋበት ወደገሃነም ወደማይጠፋ እሳት ከመሄድ ጉንድሽ ሆነህ ወደሕይወት መግባት ይሻላል፡፡» ብሏል /ማቴ 9፡43..44/ በአይሁዶች አዕምሮ ገሃነምን ከሥጋ መወርወርና መጥፋት ጋር ያዛምዱታል፡፡ ዘላለማዊ እሳትን በኃጢአተኞች ላይ

የእግዚአብሔር ቁጣና የኃጢአተኞችም ሞት ዘላለማዊ ውድመት ጋር ያያይዙታል።

ከእግዚአብሔር ሰዎች መካከል ያሉት ክፉዎች ቀደም ሲል የተቀጠቡበት ቦታ ገሃነም ከሆነ ክርስቶስ ገሃነም የሚለውን የመጠቀሙን እውነታ ያሳያል።

# ጥናት 4 ጥያቄዎች

1/ ከሞት በኋላ ምን ይሆናል?

ሀ/ ነፍስ ወደመንግሥተ ሰማይ ትሄዳለች

ለ/ ንቃተ ህሊና ቢስ እንሆናለን

ሐ/ እስከፍርድ ድረስ ነፍስ አንድ ቦታ ትቀመጣለች /ትጠበቃለች/

መ/ ክፉ ነፍሶች ወደ ሲኦል ደግ ነፍሶች ወደመንግሥተ ሰማያት ይሄዳሉ።

2/ ነፍስ ምንድን ነች?

ሀ/ ከሰውነታችን የማይሞተው አካል

ለ/ ሥጋ፣ ሰው፣ ፍጡር ለሚለው ቃል ትርጉም

ሐ/ ልክ መንፈስ ከምንለው ጋር ተመሳሳይ

መ/ ከሞት በኋላ ወደመንግሥተ ሰማያት ወይም ወደሲኦል የሚሄድ አንድ

ነገር

3/ ሞት አዕምሮን የመሳት /ምንም ያለማወቅ/ ሁኔታ ነውን?

ሀ/ አዎ

ለ/ አይደለም

4/ ሲኦል ምንድን ነው?

ሀ/ የክፉ ሰዎች ቦታ

ለ/ የዚህ ዓለም ሕይወት ስቃይ

ሐ/ መቃብር

# 5. የእግዚአብሔር መንግሥት

## 5.1 መንግሥትነቱ ሲተረጎም

ቀደም ሲል በአስቀመጥናቸው ጥናታዊ ጽሑፎች ላይ እንዳመለከትነው ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ለአመኑት ዘላለማዊ ሕይወትን መስጠት የእግዚአብሔር ዋነኛ ዓላማ ነው፡፡ ይህም ዘላለማዊ ሕይወት በምድር ላይ የምናጠፋው ነው የሚሆነው፡፡ የእግዚአብሔር ተደጋጋሚ ቃል ኪዳን አማኞች ወደመንግሥት ሰማይ መሄድ ያለባቸው /የሚሄዱ/ መሆኑን የሚያመላክት አንዳችም አንድምት የለም፡፡

«...የመንግሥቱን ወንጌል...»/ማቴ 4፡32/ ስለምድራዊ የዘላለም ሕይወት እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ሰጥቷል፡፡ /ገላ 3፡8/፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት እነዚህ ቃልኪዳኖች የሚፈጸሙበት የክርስቶስ ዳግም የመምጣት ጊዜ ነው፡፡ ምንም እንኳን ዛሬም እግዚአብሔር በመጨረሻ የዚህ ሁሉ ፍጥረት ንጉሥ ቢሆን የሰው ልጅ እንዳሻው ዓለምን እንዲገዛና ሕይወቱን እንዲመራ ሰጥቶታል፡፡ ዛሬ የዚህ ዓለም «የሰዎች መንግሥት» /ዳንኤል 4፡14/ ያጠቃልላል፡፡

ክርስቶስ ዳግም ስመለስ «...የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች ለዘለዓለምም እስከዘላለም ይነግሣል» /ራዕይ 11፡15/፡፡ በኋላም የእግዚአብሔር ፈቃድና ፍላጎት ሙሉ በሙሉና በግልጽ ምድር ላይ ይከናወናል፡፡ ከዚህም አኳያ ኢየሱስ እኛን ያዘዘን ፀሎት «...መንግሥትህ ትምጣ ገቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፡፡» /ማቴ 6፡10/ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የ«እግዚአብሔር መንግሥት» የሚለው «የመንግሥተ ሰማያት መንግሥት» በሚል ሐረግ እየተተካ ተጽፎ እናገኛለን /ማቴ 13፡11 ማር 4፡11/ ፡፡ እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን በሰማይ ያለ መንግሥት የሚል ፈጽሞ እንዳላነበብን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ በሰማያቱ መላዕክት ታዛዥነት ስለሚከናወን /መዝ 103፡19..21/ መጪው የእግዚአብሔር መንግሥት ጻድቃን ብቻ የሚኖሩባት ምድርና «እንደመላዕክቱ እኩል በሚሆኑበት» /ሉቃ 20፡36/ በምድር ይሆናል፡፡

ክርስቶስ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት በዚህ ሕይዎታችን የክርስትና እምነት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፡፡ /ማቴ 25፡34 ሐዋ 14፡22/

ፊሊጶስ ስለክርስቶስ ሲሰብክ ያስተማረው «ስለእግዚአብሔር መንግሥትና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስም» /ሐዋ 8፡5..12/ በመተርጎም ነው። ጳውሎስ ስለ«እግዚአብሔር መንግሥት» ትኩረት ሰጥቶ በዋነኛነት መጻፉን በምንባቦቹ ሁሉ አካትቶ ጽፏል። ሰብኳል። /ሐዋ 19፡8 20፡25 28፡23..31/። ከዚህ አኳያ የእግዚአብሔርን መንግሥት ትምህርት አሟልተን እንረዳ ዘንድ እጅግ የወንጌል መልዕክት ዋናው ጠቃሚ አሳል ሆኖ ተጽፎ ይገኛል። «በብዙ መከራና ችግር ወደእግዚአብሔር ምንግሥት መግባት ይኖርብናል።» /የሐዋ 4፡22/

የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር የዓለምን መጪ ጊዜ ማወቅ ፈልጎ ነበር። የታላቅና የጥንካሬ ዕይታ የተሰጠው ከተለያዩ ብረቶች እንደተሠራ ያህል ይቆጠር ነበርና ዳንኢል ኢተረጉመው የወርቅ ራስ ሆኖ የባቢሎንን ንጉሥ እንደሚወክል አድርጎ ነው። /ዳን 2፡38/ ከእርሱ በኋላ በእስራኤል ዙሪያ አያሌ ግዛቶች መወራረስ መጥቶ ሁኔታው ሲገባደድ «...እግሪቹም እኩሉ ብረት፣ እኩሉ ሸክላ ነበር መንግሥቱ በከፊል ጠንካራ በከፊልም የተሰባበረ» /ዳን 2፡42/ ነበር።

የዛሬው የዓለም የኃይል ሚዛን በብዙ መንግሥታት የተከፋፈለ ሆኖ ጥቂቱ ጠንካራ ጥቂቱ ደካማ ነው። በኋላም ዳንኤል በመርከብ ያለውን ቅርጽ በትንሽ ድንጋይ መትቶ ሲያጠፋውና ራሱ ግን መላውን ምድር የሚሞላ ትልቅ ተራራ ሲሆን ታየው። /ዳን 2፡34..35/። ይህ ድንጋይ የተመሰለው ለኢየሱስ /ማቴ 21፡42 ሐዋ 4፡11 ኤፌ 2፡20 1ጴጥ 2፡4..8/ ነው። በዓለም ዙሪያ የሚፈጥረው ተራራ የተመሰለው ለዳግሚያ ትንሣኤ ለሚመሠረተው ለዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ይህ ትንቢት በራሱ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማይ ሳይሆን በምድር ላይ ስለመሆኑ አስረጂ ነው።

የእግዚአብሔር መንግሥት በእርግጥ በተሟላ የሚመሠረተው ክርስትስ ዳግም ተመልሶ ሲመጣ መሆኑን ሌሎች ማሥረጃዎች አሉ።

ኢየሱስ በሕያዋንና በሙታን ላይ እንደሚፈርድ ጳውሎስ «በጌታ በኢየሱስ ክርስትስ ፊት በመጋለጡና በመንግሥቱም» /2 ጢሞ 4፡1/ ተናግሯል፡፡ ሚክያስ በ4፡1 ላይ የዳንኤልን ሀሳብ በማንሣት የእግዚአብሔር መንግሥትን በግዙፍ ተራራ በተራሮች ራስ ላይ ፀንቶ ያቆማል ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ከፍ ይላል»/ሚከ 4፡1..4/
ያለው፡፡ እግዚአብሔር የዳዊትን ዙፋን ነኢየሩሳሌም ለኢየሱስ ይሰጠዋል፡፡ «...ለዘለዓለም ይነግሣል... ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡» /ሉቃ 1፡32..33/ ለዚህ አንድ አስተማማኝ ነጥብ መኖር ይኖርበታል፡፡ በዳዊት ዙፋን ኢየሱስ መንገሥ ይጀምራል መንግሥቱም ይጀመራል፡፡ ይህም የክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው፡፡ «ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም» የሚለው ከዳንኤል 2፡44 ጋር ይያያዛል፡፡ «የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል ለሌላ ሕዝብ የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፡፡» የዮሐንስ ራዕይ በቁጥር 11፡15 ስለክርስትስ ዳግም የሚገልጸው በተመሳሳይ ቋንቋ ነው፡፡ «በሰማይም የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች ለዘለዓለምም እስከዘለዓለም ይነግሣል፡፡» የክርስቶስ መንግሥት የሚመሠረትበት ቁርጥ ቀን መኖር አለበት፡፡ በምድርም ንግሡ የሚጀምርበት፡፡ ይህም የእርሱ ዳግም መምጣት /መመለሽያ/ ጊዜ ነው፡፡

## 5.2 መንግሥቱ አሁን ገና አልተመሠረተም

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን በተሟላ ሁኔታ እንዳለ ያለው አመለካከት በስፋት እንደሆነ በዛሬዎቹ አማኞች ቤተ ክርስቶያን የሚታይ ነው፡፡ ወደፊት አውነተኛ አማኞች የሚድኑበት ከመንግሥቱ ቦታ የሚቀበሉበት ክርስቶስ አሁን ገና ባለመመለሱና መንግሥቱን ሙሉ በሙሉ የማንወርስበት መሆኑን ማንም አንዳችም ጥርጣሬ የለውም፡፡

እስካሁን ካየናቸው ጥናቶች በግልጽ እንደተረዳነው «..ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም» /1 ቆሮን 15፡50/፡፡ እኛ «...ለሚያፈቅራቸው ቃል የገባላቸውን መንግሥር ወራሾች» ነን /ቶማ 2፡5/ ጥምቀት ለአብርሃም ስለምግሥቱ በመሠረታዊው ወንጌል ላይ የተሰጠው

ቃል ኪዳን ወራሾች ያደርገናል። /ማቴ 4፡23 ገላ 3፡8 27..29/ ስለዚህ ለአብርሃም የተሰጠው ቃ ኪዳን ይፈጸም ዘንድ በክርስቶስ መመለስ መንግሥቱም የመውረስ ቃል ኪዳን እንደሚኖር ግልጽ ይሆናል። /ማቴ 25፡34 1ቆሮ 6፡9..10 15፡50 ገላ 5፡21 ኤፌ 5፡5/። ስለመጪው የመውረስ ቋንቋ የሚያመለክተው መንግሥቱ አሁን የዛሬዎቹ አማኞች የያኡት /የተቀበሉት/ አለመሆኑን ነው።

ኢየሱስ በምሳሌ አድርጎ እንዲህ ተናገረ «የእግዚአብሔር መንግሥት ፈጥኖ ተገለጠ ስለዚህም እንዲህ አላቸው። አንድ መኮንን ለራሱ መንግሥት ይዞ ሊመለስ ወደሩቅ አገር ሄደ። አሥር ባሮቹንም ጠርቶ አሥር ምናን ሰጣቸውና እስከመጣ ድረስ ነግዱ አላቸው መንግሥትንም ይዞ በተመለሰ ጊዜ ገንዘብ የሰጣቸውን እነዚህን ባሮች ነግደው ንም ያህል እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ እንዲስጡት አዘዘ።» እናም ፈረደላቸው። /ሉቃ 19፡11..27/

መኮንኑ የተመለሰው በፍርድ ተመልሶ ዳግም በሚመጣበት ቀን መንግሥቱን ለመቀበል «ከሩቅ ሀገር» የሚመጣውን የክርስቶስን ነው። ስለዚህም «ባሮች» አሁን ጌታ በሌለበት ጊዜ መንግሥቱን ሊወርሱ ፍጹም አይቻልም።

የሚከተሉት ተጨማሪ አስረጂዎች /ማረጋገጫዎች/ እነሆ...

... «መንግሥቴ ከዚህ ዓለን አይደለችም።» ሲል ኢየሱስ በግልጽ አስቀምጦታል።
/ዮሐ 17፡36/ ሆኖም በዚያን ጊዜ «እኔ ንጉሥ ነኝ» /ዮሐ 18፡37/ ማለት ይችል
ነበር። የክርስቶስን ያኔ ንግሥ መንግሥቱ አሁን አለመመሥረቱን ለማሳየት
የመጀመሪያዎቹ ክፍለ ዘመን አማኞች እንኳን «የእግዚአብሔርን መንግሥት»
/ማር 15፡43/ እንደሚጠብቁ ነው የተገለጸው።

... ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ከዚያ ወይን እንደገና እንደማይጠጣ ሲነግራቸው

«በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት

**እስከዚያ ቀን ድረስ» ብሏል። /ማቴ 26፡29/። ይህ በግልጽ የሚያሳየው**

መንግሥት ወደፊት የሚመጣ መሆኑን ነው። ሰዎች የክርስቶስን «ስለእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንገዱም ያልፍ ነበር» የሚለውን ትምህርት ተረዱ። /ሉቃ 8፡1/ «...በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው» ብሏልና /ሉቃ 14፡15/

... ሉቃስ በዚህ ባባል ላይ በመቀጠል «... አባቴ እኔን እንደሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ» /ሉቃ 22፡29..30/ ብሏል።

... ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን የሚያመለክቱ ምልክቶች እንዳሉ በገለጸ ጊዜ ያጠቃለለው «... እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔረ መንግሥት እንደቀረ ብቻ ዕወቁ» በሚል አስተያየት ነው።

/ሉቃ 21፡31/ 31/ ይህ ክርስቶስ ተመልሶ ከመምጣቱ በፊት መንግሥቱ አሁን አለ ብሎ ማመን ሞኝነት ነው

... «ወደእግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል»። /ሐዋ 14፡22/ ማንኛውም በሥቃይ ላይ ያለ አማኝ መንግሥቱ ፈጥና ትመጣ ዘንድ ቢጸልይ አያስገርምም። /ማቴ 6፡10/

... እግዚአብሔር «ወደመንግሥቱ ሲጠራን» /1 ተሰሎንቄ 2፡12/ በምላሹ ወደዚያ መንግሥት እንገባ ዘንድ አሁን በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ማለፍ ይኖርብናል።

## 5.3 የእእግዚአብሔር መንግሥት ባለፈው ዘመን

የእግዚአብሔር መንግሥት የአማኞች የመጪ ዘመን ዋጋ ነው። የክርስቶስን ምሣሌነት አጥብቀው በመያዝ አጭርና የጉስቁልና ሕይወት የሚኖሩ የሚነቃቁበት ዋና ምክንያትም ይኸ ነው። ለመንፈሳዊ ትግልና እንደአባታቸው ለሚያፈቅሩት ለእግዚአብሔር ሙሉ ዕወጃ መነቃቂያነቱ መጭው የእግዚአብሔር መንግሥትን በመጠባበቅ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ መንግሥቱ ምን መልክ እንዳለው ውስን ዝርዝር አስቀምጧል። ሆኖም ጥቂት ፍንጭ ለማግኘት በሕይወት ዘመንህ ሙሉ መድከም ይኖርብሃል። ሆኖም የምታገኘው በጣም ጥቂት ይሆናል። ስለመጪው መንግሥት መሠረታዊ መርሆዎችን ለመረዳት አንዱ መንገድ ባለፈው ጊዜ በእስራኤል ሕዝብ መልክ የነበረውን የእግዚአብሔርን መንግሥት መቀበል ነው። ይህም መንግሥት በክርስቶስ መመለስ እንደገና ይመሠረታል። በመጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤልን ሕዝብ በተመለከተ ብዙ ተጽፎ እናገኛለን።

እግዚአብሔር «የእስራኤል ንጉሥ /ኢሣ 44፡6፣ 41፡27፣ 43፡15፣ መዝ 48፡2፣89፡18፣149፡2/ ተደጋግሞ ተገልጿል። ከዚህም የእስራኤል ሕዝብ የእርሱ መንግሥት እንደነበሩ መረዳት ይቻላል። በቀይ ባህር አቋርጠው ከግብጽ በወጡበት ጊዜ ከእርሱ ጋር በሲናይ ተራራ ቃል ኪዳን በተገባላቸው ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት መሆን ጀምረዋልና። ይህን ቃል ኪዳን ጠብቀው ለመኖር ፈቃዳቸውን በገለጹበት ጊዜ «..እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ይሆኑልኛላችሁ።» /ዘፀዓት 19፡5..6/ ብሏል። ስለሆነም፣ «..እስራኤል ከግብጽ የያዕቆብም ቤት ከእንግዳ ሕዝብ በወጣ ጊዜ ይሁዳ መቅደሱ እስራኤልም ግዛቱ ሆነ።» /መዝ 114፡1..2/
ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ እስራኤላውያን የሲናይ በረሃን አቋርጠው ተስፋ ወደተገባላቸው የከንዓን ምድር ተጉዘው መኖሪያቸውን መሠረቱ።
እግዚአብሔር ንጉሣቸው ስለነበር ከነገሥታት ይልቅ በዳኞች /ምሣሌ ጌዴዎንና ሣምሶን/ ይተዳደሩ ነበር። እነዚህ ዳኞች በመለኮት እየተመሩ አንዳንድ የሀገሪቱን ክፍሎች ገዙ እንጂ መላ ምድሩን አልገዙም። ለአንዳንድ የተለዩ ተግባራት በእግዚአብሔር ተነሣሥተዋል። እስራኤላውያን ዳኛ ጌዴዎንን ንገሠሣቸው ንጉሣቸው እንዲሆን በጠየቁት ጊዜ «እኔ አልገዛችሁም ልጄም አይገዛችሁም እገዚአብሔር ይገዛችኋል አላቸው።» /መሣ 8፡23/

የመጨረሻው ዳኛ ሣሙኤል ነበር። በእርሱ ጊዜ እስራኤላውያን ልክ በአካባቢያቸው እንዳሉት ሕዝቦች እነርሱም የሰው ንጉሥ እንዲኖራቸው ጠየቁት። በታሪክ ሁሉ የእግዚአብሔር እውነተኛ ሕዝቦች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት መቀራረብ ክብደት እንዳይሰጡ ተፈትነዋል። በአካባቢያቸው ካሉት ሕዝቦች ጋር እንደሚመሳሰልላቸው ብቻ ከእግዚአብሔር መቀራረቡን መሥዋዕት አድርገውታል። ይህ ፈተና

በዛሬው ዓለም ብሶበታል። እግዚአብሔር ለሣሙኤል «በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁም» ብሎታል። /1 ሣሙ 8:7/ ያም ሆኖ እግዚአብሔር ከክፉው ሳኦል ጀምሮ ነገሥታት ሰጣቸው። ከእርሱም በኋላ ፃድቁ ደዊት ነገሠ። ከእርሱም የነገሥታቱ ዘሩን ውርስ መሥመር ተዘረጋ። የእግዚአብሔርን ንግሥ ባይቀበሉም መንፈሳዊ የሆኑት ነገሥታት እስራኤል የእግዚአብሔር መንግሥት መሆኗን ተገንዝበዋል። ስለዚህ እነርሱ እስራኤልን የሚገዙት በራሳቸው መብት ሳይሆን በእግዚአብሼር ተመርጠውና ተወክለው መሆኑን ተቀብለዋል።

ይህን መርሆ መገንዘብ የዳዊት ልጅ ሰሎሞን በነገሠበት ጊዜ የገለጸውን ለመገንዘብ ያስችለናል። «/የእግዚአብሔር/ ዙፋን ለጌታ በእግዚአብሔር ስም ንጉስ ሆንሁ።» /2 ዜና መዋዕል 9:8፡ 1 ዜና 28:5፣ 29:23/ የንጉሥ ሰሎሞን ንግሥ ዘመን ሰላምና ፀጋ የተሞላበት መሆኑ የሚያመላክተው መጭውን የእግዚአብሔርንም መንግሥት ነው። የሰሎሞን በእስራኤል ላይ እግዚአብሔርን በመወከል መንገሥ ክብደት የተሰጠውና በእግዚአብሔር ዙፋንም ኢየሱስ የእስራኤልለ ንጉሥ ሆኖ እንሚቀመጥ በመጽሐፍ /ማቴ 27:37..42፣ ዮሐ 1:49፣ 12:13/ የተገለጸውም ስለዚህ ነው።

## የእግዚአብሔር ፍርዱ

በሰሎሞን ክህደት የተነሣ የእስራኤል መንግሥት ለሁለት ተከፍሎ ነበር። የሰሎሞን ልጅ ሬሆቡአም። በይሁዳ፣ በኒያሚንና በማንአሲሕ ከፊል ነገዶች ነገሠ፤ ኤሮቦአም በሌሎች አሥር ነገዶች ላይ ነገሠ። እነዚህ አሥሩ ነገዶች እስራኤል ወይም ኤፍሬም ሲባሉ ሁለቱ ነገዶች ደግሞ ይሁዳ ተብለው ተጠሩ። የእነዚህ የሁሉም ነገዶች ሕዝቦች በአብዛኛው የሰሎሞንን መጥፎ ምሣሌነት ተከትለው በእውነተኛው በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ አስመስሎ በአንፃሩም በዚያኑ ጊዜ የአካባቢው ሌሎች ሕዝቦች እንደሚያደርጉት በጣዖታት አመለኩ። መልሰ መላልሶ በነቢያቱ አማካይነት ንስሐ ይገቡ ዘንድ ለመናቸው ግን አልሰሙም። በዚህም ምክንያት ከእስራኤል መንግሥት ወጥተው በጠላቶቻቸው መሬቶች ውስጥ እንዲገቡ አድርጎ ቀጣቸው። ይህ የሆነውም አሶራውያንና ባቢሎናውያን እስራኤልን ወርረው ምርኮኛ አድርገው ወስደአቸው። «ብዙ ዓመታት ታገሥካቸው በነቢያትም እጅ በመንፈስህ መሰከርክባቸው አላዳመጡህም። ስለዚህም በምድር አሕዛብ እጅ አሳልፈህ ሰጠሃቸው።» /ነህሚያ 9:30/

አሥሩ የእስራኤል ነገዶች በፍፁም ጥሩ ነገሥታት አልነበሯቸውም። ኤርቦአም ፣ ኢሓብ ፣ ኢሖሓዝ ወዘተ በጣአት አምለኪዎች እንደነበሩ በመጽሐፈ መሳፍንት ተመዝግበው እናገኛለን።

በመጨረሻው ንጉሣቸው በሖሺአ ጊዜም በሶሪያ እስራኤል ተሸንፋ አሥሩም ነገዶች ወደምርኮኝነት ተግዘዋል። /2 መግ 17/። ከዚያም አልተመለሱም።

ሁለቱ የይሁዳ ግዛቶች ምንም እንኳን አብዛኞቹ ነገሥታት ክፉዎች ቢሆኑም ጥቂት ጥሩ ነገሥታት ነበሯቸው። /ለምሣሌ ሕዝቅያስና ዩሲያህ/ በመጨረሻ በይሁዳ ግዛት በነገሠው በጼዴቅያህ ዘመን በሕዝቦቹ የተደጋገመ ኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔር የይሁዳን ግዛት ከእራሱ መንግሥትነት አውጥቶ ባድማ አደረጋት። ይኸ የሆነውም በባቢሎናውያን በመወረራቸውና ወደባቢሎን ማርከው በወሰዷቸው ጊዜ ነበር። /2 መግ 25/ ለ70 ዓመታት እዚያው በባቢሎን ውስጥ በባርነት ቆዩ። ከዚያም በኋላ በእዝራና በናሖሚያ አመራር ጊዜ ጥቂቶች ወደእስራኤል ተመለሱ። እንደገናም የራሳቸው ንጉሥ ሳትኖራቸው ቀረና በባቢሎናውያን፣ በግሪኮችና በሮማውያን ተገዙ። ኢየሱስም የተወለደው በሮማውያን አገዛዝ ዘመን ነው። እስራኤላውያን ኢየሱስን ባለመቀበላቸው በ70 ዓ/ም ተወርረው በዓለም ተበተኑ።
ካለፉት መቶ ዓመታት ወዲህ ብቻ ነው መመለስ የጀመሩት። ሕዝቅኤል 21:25..27 በሕዝበ እስራኤል እንደታየው የእግዚአብሔር መንግሥት መፈጸሙን ተንብዮአል።

> «... አንተም ቀንህ የደረሰብህ የኃጢአትህ ቀጠሮ ጊዜ የደረሰብህ ርኩስ ኃጢአተኛ የእስራኤል አለቃ ሆይ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
> ይላል። መጠምጠሚያውን አውልቅ ዘውዱንም አርቅ ይህ ይህ እንዲህ አይሆንም የተዋረደውን ከፍ አድርግ ከፍ ያለውንም አዋርድ
> ባድማ፣ ባድማ፣ ባድማ አደርጋታለሁ ፍርድ ያለው እስኪመጣ ድረስ
> ይህች ደግሞ አትሆንም ለእርሱም እሰጣታለሁ።
> /ሕዝቅኤል 21:25//27/

ሦስት ጊዜ ባድማ የሚለው የሚየታሳየው በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ሦስት ጊዜያት መወረሯን ነው። የዜዴቅያስ መንግሥት መወገድ የእግዚአብሔር መንግሥት መወገድ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥት የእስራኤል ቤት ሲሻር ይሆናል። «ከእስርኤልም ቤት መንግሥትን እሽራለሁና።»
/ሆሴዕ 1:4/ «የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል። ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም»
/ሉቃስ 1:32..33/ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ። ይህም የመንግሥቱ ተመልሶ የመቋቋሙ ጊዜ ሲፈጸም ይሆናል።

# የእስራኤል ተመልሶ መቋቋም

የክርስቶስ ደቀ መዝሙርት በደንብ ልብ ብለው የሰሚትና የጠየቁት «ጌታ አንተ በዚህ ጊዜ የእስራኤልን ምንግሥት እንደገና ትመልሳለህን? ማለትም ሕዝቅኤል 21፥27 ላይ የተጻፈው አሁን ይሚላልን? ብለው ነበር፡፡ ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡፡ ዳግመኛ የምመጣበት ትክክለኛ ቀኑን አራውቁትም□፡፡ ምንም እንኳን ወዲያውኑ አንድ ወቅት ላይ በእርግጥ እንደምመጣ ቢያረጋግጡላችሁም፡፡

የእግዚአብሔር /የእስራኤል/ መንግሥት ተመልሶ የሚቋቋመው ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ጴጥሮስ እግዚአብሔር «ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድልክላችሁ ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንሰሐ ግቡ ተመለሱም እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ጊዜ ድረስ፡፡» ሲል ሰብኮአል፡፡ /ሐዋ 3፥20..21/
ሁለተኛ መመለሱ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደገና ማቅናትና የጥንቱ የእስራኤል መንግሥት ተመልሶ መመሥረቱን የሁሉም /የእግዚአብሔር/ ቅዱሳን ነቢያት እውነተኛ መልዕክት ነው፡፡

… «ዙፋንም በምህረት ይቀናል በዚያም ላይ በዳዊት ድንኳን ፍርድን
የሚሻ ጽድቅንም የሚያፋጥን ፈራጅ በእውነት ይቀመጣል፡፡»
/ኢሣ 16፥5/
… «በዚያን ቀን የወደቀችውን የዳዊትን ድንኳን አነሣለሁ የተናደውንም
ቅጥሯን እጠግናለሁ የፈረሰውንም አድሳለሁ እንደቀድሞውም
ዘመን እሰራታለሁ፡፡» /አሞጽ 9፥11/
… /የእስራኤል ልጆቻቸውም እንደቀድሞ ይሆናሉ፡፡ ማኅበራቸውም በፊቴ
ፀንቶ ይኖራል፡፡» /ኤር 30፥20/
… «ጌታም ኢየሩሳሌምን ዳግመኛ ይመርጣል፡፡» /ዘካ 2፥12/ የዓለም
ዙሪያ መንህሥቱ ዋና ከተማ ያደርጋታል፡፡»
/መዝ 48፥2 ኢሣ 2፥2..4/
… «የይሁዳን ምርኮና የእስራኤልንም ምርኮ እመልሳለሁ እንደ ነበሩ
አድርጌ እስራቸዋለሁ፡፡ ይህችም ከተማ እኔ የምሠራላቸውን

በጎነትና ሰላም ሁሉ በሚፈሩና በሚደነግጡ አሕዛብ ሁሉ ፊት
ለደስታ ስም ለምሥጋናም ለክብርም ትሆናለች፡፡ መንጎቻቸውን
የሚያሳርፉት የእረኞች መኖሪያ ይሆናል፡፡» /ኤር 33፡7..13/

መንግሥቱን ለማቅናት የክርስቶስ መመለስ በእውነት የእስራኤል ተስፋ ነው፡፡ ለዚህ እኛም በጥምቀት አብረን መሆን ይገባናል፡፡

## 5.4 የእግዚአብሔር መንግሥት በመጭው ዘመን

ክፍል 1 እና ክፍል 3 ላት መንግሥቱ ምን እንደሚመስል በቂ መግለጫ እንደተሰጠበት ግልጽ ነው፡፡ አብርሃም በተሰጠው የተስፋ ቃል በዘሩ አማካይነት ዓለም በሙሉ እንደተባረከ አይተናል፡፡ በሮሜ 4፡13 በአብርሃም ዘር /በኢየሱስ/ ውስጥ ያለ ሁሉ ምድርን እምደሚወርሱ ተገልጿል፡፡ ዳንኤል ምዕራፍ 2 ላት ክርስቶስ እንደትንሽ ድንጋይ ይመለስና መንግሥቱ ቀስ በቀስ በዓለም እንደሚሠራጭ ይተነብያል፡፡ /መዝ 72፡8/ ይህ ማለት ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ብዙዎቹ እንደሚያምኑት ዝም ብሎ በኢየሩሳሌም ወይም በእስራኤል ምድር ትቆማለች ማለት አይደለም፡፡ በእርግጥ እነዚህ አካባቢዎች ማዕከለ ምድር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በዚህ ዓለም ክርስቶስን የሚከተሉ «ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፡፡ በምድርም ላይ ይነግሣሉ» /ራዕይ 5፡10/ የተለያዩ መጠንና ቁጥር ያላቸውን መንደሮች እንገዛለን፡፡ አንዱ አሥር የሠፈራ መንደሮችን ሌላው አምስት ሠፈራቸውን ያስተዳድራል፡፡ /ሉቃ 19፡17/ ክርስቶሐሰመ የምድርን ግዛት ከእኛ ይካፈላል፡፡ /ራዕይ 2፡27፣ 2 ጢሞ 2፡12/ «እነሆ ንጉሡም /ኢየሱስ/ በጽድቅ ይነግሣል፡፡ መሳፍንትም አማኞች በፍርድ ይገዛሉ፡፡» /ኢሣ 32፡1፣ መዝ 45፡16/

ክርስቶስ እንደገና በሚቀናው በዳዊት ዙፋን ለዘለዓለሙ ይነግሣል፡፡ /ሉቃ 1፡32..33/ ማለትም የዳዊት ቦታና ሥልጣን ይዞ በኢየሩሳሌም ይነግሣል፡፡ ከኢየሩሳሌም ልሰሚነግሥ መጭው የእግዚአብሔር መንግሥት ዋና ከተማውን ከዚህ ያደርጋል፡፡ በዚህ አካባቢም ቤተ መቅደሱ ይታነፃል፡፡ /ሕዝ 40፡48/ በዓለም ሁሊ ያሉት ከያሉበት ሆነው እግዚአብሔርን ቢያመሰግኑም ቤተ መቅደሱ ዋና የትኩረት ማዕከል ይሆናል፡፡ /ሚልክያስ

1፡11/። በኢየሩሳሌም በቤተመቅደሱ ዙሪያ መንግሥታት «ለንጉሡ ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ይሰግዱ ዘንድ የዳስ በዓሉንም ያከብሩ ዘንድ በየዓመቱ ይወጣሉ። /ዘካ 14፡16/

ይህ ዓመታዊ ወደኢየሩሳሌም ጉዞ በኢሣያስ 2፡23 ላይ ተተንብዮአል።

> «በዘመኑም ፍጻሜ የእግዚአብሔር ቤት /ቤተመቅደስ ተራራ...
> በተራሮች ራስ ላት ፀንቶ ይቆማል ከኮረብቶችም በላይ ከፍ ይላል
> አሕዛብም ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ ሕግ ከጽዮን
> የእግዚአብሔርም
> ቃል ከኢየሩሳሌም ይወጣልና ብዙዎች አህዛብ ሄደው ኑ ወደ
> እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ አምላክ ቤት እንውጣ
> እርሱም መንገዱን ያስተምረናል። በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ።»
> /ኢሣ 2፡2..3/

ከጊዜያችን ግዙፍ የሰው አሳዛኝ ሁኔታዎች አንዱና ዋናው አሕዛብ እግዚአብሔርን ከፖለቲካ፣ ጀባህላዊና ከስሜታዊ ምክንያቶች የተነሣ እንጂ እግዚአብሔር አባታቸውና ፈጣሪያቸው መሆኑን በመሠረቱ ከልብ አገናዝበው አለመሆኑ ነው። የእግዚአብሔርን መንገዶች ለመማር አለም አቀፍ ፍላጎት በመንግሥቱ ወደፊት ይኖራል። አሕዛብ በዚህ ፍላጎት ተነቃቅተው ከሁሉም የዓለም ማዕዘን ወደኢየሩሳሌም ስለእግዚአብሔር የበለጠ ዕውቀት ከማግኘት እምደሚጓዙ አያጠራጥርም።

የሰው ልጅ በፈጠራቸው የሕግ ሥርዓት፣ የፍርድ አፈጻጸም ውኸንብሮችና ኢፍትሐዊ አካሄድ ጠፍተው በምትካቸው አንድ ዓለም አቀፍ ሕጋዊ ሥርዓት ዓለም እንደምትመራ ይጠበቃል። ይኸውም ሕግ የጌታ ቃል ሆኖ በክርስቶስ በኢየሩሳሌም እንደሚታወጅ ነው። አሕዛን ሁሉ ወደእነዚህ ትምህርቶች ጉባዔዎች በመጉረፍ እግዚአብሔርን በእውነት ለማወቅ የጋራ ፍላጎት ሆኖ በአሕዛብ መካከል፤ በግለሰቦች መካከል አሁን ያለውን የተፈጥሮ ሽኩቻና ግጭት ይህንን ዕውቀት በዚህ ሕይወታችን ለማግኘት ራሳቸውን ለዚህ ተግባር የሚያውሉ ግለሰቦች እንደሞኖሩ ነው።

አሕዛብ ሁሉ ወደኢየሩሳሌም እንደሚጎርፉ በኢሣያስ 60፡5 ዓይ ከተገለጸው አይሁዳውያን «በአንድ ላይ» አይሁዳውያን ካልሆኑ ጎን እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደኢየሩሳሌም ይጎርፋሉ ከሚለው ጋር ይመሳሰላል። ይህ የዘካርያስ ትንቢት ጋር ፍጹም ይያዛል።

> «በብዙ ከተሞች የሚቀመጡ አሕዛብ ገና ይመጣሉ በአንዲትም
> ከተማ የሚኖሩ ሰዎች እግዞአብሔርን እንለምን ዘንድ
> የሠራዊትንም
> ጌታ እግዝአብሔርንም እንፈልግ ዘንድ ኑ እንሂድ እኔም እሄዳለሁ

እያሉ ወደሌላ ከተማ ይሄዳሉ። ብዙ ወገኖችና ኃይለኞች አሕዛብ በኢየሩሳሌም የሠራዊትን ጌታ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ እግዚአብሔርንም ይለምኑ ዘንድ ይመጣሉ የሠራዊትም ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡.. በዚያን ዘመን ከአሕዛብ ቋንቋ ሁሉ አሥር ሰዎች የአንዱን አይሁዳዊ ሰው ልብስ ዘርፍ ይዘው እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እንዳለ ሰምተናልና ከእናንተ ጋር እንሂድ ይላሉ።» /ዘካ 8፡20..23/

ይህ አይሁዳውያንን የአሕዛብ ራስ እንጂ ጅራት እንዳላደረጋቸው መለከታል። ይኸውም ንሰሓ በመግባታቸውና ታማኝ ሆነው በመገኘታቸው ነው። /ዘዳ 28፡13/ ስለድኅነት የእግዚአብሔር ዕቅድ የአይሁዳውያንን መሠረትነት በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል። እነዚህን ጉዳዮች አሕዛብ ሁሉ ለአይሁዳውያን ይነግሯቸው ዘንድ በጉጉት ይወያዩበታል። «እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር መሆኑን ሰምተናል» እያሉ በመንፈሳዊ ነገሮች ዙሪያ ውይይቶች ይጎለብታሉ።

ክርስቶስ «በእግዚአብሔር መካከል ይፈርዳል በብዙ አሕዛብም ላይ ይበይናል።
ሰይፋቸውንም ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጠቀሉ። ሕዝብም በሕዝብም ላይ ሰይፍ አያነሣም ሰልፍም ከእንግዲህ አይማሩም።» /ኢሣ 2፡4/ ማለቱ አያስገርምም። የክርስቶስ ፍጹም ስልጣንና አለመግባባቶች በሰላም የሚዳኙበት ፍትሕ በአሕዛብ መካከል ተፈጥሮ ሀገሮች በፈቃዳቸው የጦር መሣሪያዎቻቸው አላስፈላጊ ሆነው ወደምርት/ማምረቻ/ መሣሪያነት እንዲቀየሩ ይደርጋል። ወታደራዊ ሥልጠናም ይቆማል። «በዘመኑ ጽድቅ ያብባል» /መዝ 72፡7/ የእግዚአብሔርን የፍቅር፣ የትምህርት፣ የፍትሕ ወዘተ ባህሪያት የሚያንፀባርቁ ይከበራሉ። ይህ የዛሬውን የትምክህተኞች፣ የራስ ወዳዶችና የስግብግብ ምቀኞች መኩራራት ይተካል ማለት ነው።

የኅራዴዎች ወደማረሻነት በፈቃድ የመቀየር ሁኔታን ተከትሎ ከምን ጊዜው የበለጠ በመሬት ላይ የሚመጣ የእርሻ ለውጥ ይመጣል። በአዳም ኃጢአት ምክንያት ምድሯ ተረገማ /ዘፍጥ 3፡17..19/ ከእርሷ ምግብ ለማግኘት በአሁኑ ጊዜ የላቀ ጥረት አስፈልጓል። በመንግሥቱ «ምድር በተራሮች ላይ መጠጊያ ይሆናል። ፍሬውም ከሊባኖስ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል። እንደምድር ሣር በከተማ ይበቅላል። ስሙ ለዘለዓለም ብሩክ ይሆናል።» /መዝ 72፡16/ «አራሹ አጫጁ ወይን ጠባቂውም ዘሪውን የሚያገኝበት ወራት ይመጣል ይላል። እግዚአብሔር ተራሮቹም በተኃውን የወይን ጠጅ ያንጠባጥባሉ ኮረብቶችም ይቀልጣሉ።» /አሞ 9፡13/ ካሁን የተሻሻለ የመሬት ምርታማነት ይኖራል። በኤደን የተነገረው የመሬት እርግማንም ይቀነሳል።

እንደዚህ ያለ ግዙፍ የእርሻ ድርጅት አያሌ አሕዛብን ያቀፈ ይሆናል። የመንግሥቱ ትንቢት አሕዛብ ራሳቸውን በበቂ ወደ ሚመግብ ምርት አባቃይነት አኗኗር ይመለሳሉ።

«...የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር አፍም ተናግሯልና ሰው እያንዳንዱ ከወይኑና ከበለሱ በታች ይቀመጣል። የሚያስፈ ራውም የለም።» /ሚክ 4፡4/

ሌሎችን ሀብታም ለማድረግ ሕይወትን ሙሉ በሥራ መጠመድ ጊዜ ያለፈበት ይሆናል።

«... ቤቶችንም ይሠራሉ ይቀመጡባቸውማል ወይኑንም ይተክላሉ ፍሬውንም ይበላሉ። ሌላ እንዲወመጥበት አይሠሩም ሌላም እንዲበላው አይተክሉም የሕዝቤ ዕድሜ እንደዛፌ ዕድሜ ይሆናልና እኔም የመረጥኳቸው በእጃቸው ሥራ ረጅም ዘመን ደስ ይላቸዋል በከንቱ አይደክሙም፣ ለጥፋትም አይወልዱም።» /ኢሣ 65፡21..23/

«...ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል በረሃውም ሀሴት ያደርጋል። እንደጽጌረዳም ያብናል፤ በምድረ በዳ ውኃ በበረሃም ፈሳሽ ይፈልቃልና ደረቂቱ ምድር ኩሬ የጠማት መሬት የውኃ ምንጭ ትሆናለች።» /ኢሣ 35፡1..7/

እንስሳት በመካከላቸው የሚያደርጉት ወረራ እንኳን ይወገዳል። «ተኩላና ጠቦት በአንድነት ይሰማራሉ።» ልጆችም ከአባብ ጋር ይጫወታሉ። /ኢሣ 65፡25፣11፡6..8/

በተመሳሳይ መንገድም በፍጥነት ላይ የተላለፈው ርግማን በሰፊው ይቀነሳል። በሰው ልጅ ላይ የተጣለውም ይቀነስ ዘንድ። የሰው የመኖር ዘመን እጅግ ይጨምራል። አንድ ሰው በመቶ ዓመቱ ቢሞት ልጅ እንደሞተ ይቆጠራል። /ኢሣ 65፡20/። ሴቲቾ ልጅ ለመውለድ የሚያምጡበት የጭንቅ ጊዜ እጅጉን ይቀንሳል። /ኢሳ 65፡23/

በዚያን ጊዜም የዕውሮች ዓይን ይገለጣል። የደንቆሮዎችም ጆሮ ይከፈታል በዚያን ጊዜ አንካሳ እንደሚደቋ ይዘላል የድዳም ምላስ ይዘምራል።» /ኢሣ 65፡23/

ይህም የሚሆነው ታምራዊ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንደገና እጅና ስከምናደርጋቸው ይሆናል። /ዕብራ 6፡5/

የእግዚአብሔር መንግሥት መሠረታዊ ዓላማ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ስለሆነ ምድር ለእግዚአብሔር ክብር እስክትሞላ ድረስ «ውኃ ባህርን እስከሚከድን» /ዕንቆባ 2፡14/ ይሆናል። ይኸ ነው

የእግዚአብሔር የመጨረሻ ዓላማ። «እኔ ሕያው ነኝና በእውነት የእግዚአብሔር ክብር ምድርን ሁሉ ይሞላል» /ዘሁልቁ 1421/ ለእግዚአብሔር ክብር ማለት የምድር ነዋሪዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያደንቃሉ። ያመሰግናሉ የጽድቅ ሥራውን ሁሉ ይከተላሉ /ይቀዳሉ/ ምክንያቱም ዓለም በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ስለምትሆን ምድር ይህን ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ ታንፀባርቃለች። «ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ። በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል።» /መዝ 37፡11/። እነዚያ በመንግሥቱ ውስጥ ሆነው ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ይጠግባሉና።» /ማቴ 5፡6/

በመንግሥቱ ዘለዓለማዊ ሕይወት የመቀበል ሀሳብ ራስ ብዙ ጊዜ አሽዛብ በክርስትና ፍላጎት እንዲፈጠሩ ማባበያ አድርገው እንደ «ካሮት» ይጠቀሙበታል። የዘለዓለማዊ ሕይወት መቀበል ምክንያቱ በመንግሥቱ መገኘትና እግዚአብሔርን ማክበር ነው። ከጥምቀት በኋላ በሚቀረን ዘመን ሁሉ ይህን ባለመቋረጥ እያዳበርን ማድነቅ ይኖርብናል።

ፀሓፊው ለአሥር ዓመታት በፍጹምነትና ከእግዚአብሔር ጋር በጥሩ ህሊና መቆየቱ የአጠቃላይ የጉስቁልና የዚህ ዓለም ሕይወትን የመቀበል ዋጋ ይሆናል።

በእግዚአብሔር መንግሥት መሆን የዓለሙን ጥቅሞችና ቁሳቁሶች /ጸሎት/ እንድንንቅ ዋናው መበረታቻ ነው። ለቅርቡ መጭ ብዙ በመጠ በብ ፋንታ ኢየሱስ «አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህ ሁሉ ይጨመርላችኋል» ያለውን ምክር ተቀብሎ መራመድ ይበጃል። /ማቴ 6፡30..34/ አሁን የምናስበውና የምንመኘው ማንኛውም ነገር በመጨረሻ በእግዚአብሔር መንግሥት መሆንን ከማሟላት ጋር አይነፃፀርም።

/የእግዚአብሔር/ «የጽድቅነት» መፈለግ ይኖርብናል። ማለትም የእግዚአብሔርን የፍቅር ባህርይ ለማበልጸግ መሞከር ማለት ነው። ጽድቅ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስለሚከበር እዝያ ውስጥ መሆን እንፈልጋለን። ከሞት ለማምለጥና ለዘላለሙ ቀላል ሕይወት ለመኖር ስንል ሳይሆን በሙሉና በግብረገብነት ፍጹማን ለመሆን ከመፈለግ ሊሆን ይገባል። ሁሉም በተደጋጋሚ የወብጌል ተስፋ የሰው ልጅ ራስ ወዳድነትን እንዲያጠፋ ይግባኝ የሚባልበትን መንገዶች ያመለከተ ነው። በመንግሥቱ ውስጥ ለመሆን ያለው ማነቃቃይ በግልጽ ከቀን ወደ ቀን ብዙ ይለያል። እዝህ ላይ የምንሰጠው ሐሳብ ተምኔታዊ ነው። ቅድሚያ የምንሰጠው ወንጌልን መማርና ለእግዚአብሔር ካለን የፍቅር ታማኝነት የተነሣ ለምንፈጽመው ለእምቀት ራሳችንን ስናቀርብ ይሆናል። እግዚአብሔር የሚሰጠንን ተስፋና የእኛም የመንግሥቱ ተካፋይ ለመሆን

ትክክለኛ ምክንያቶቻችን ከጥምቀታችን በኋላ የሚያድጉና የሚጠናከሩ ይሆናሉ፡፡

# 5.5 ሺኛው ዘመን

በመንግሥቱ ስለሚኖረው ሕይወት በጥናታችን ያመላከትአውን የሚያስተውል አንባቢ ጵየእግዚአብሔር መንግሥት የሰውን የመምሰል ሥዕል አያሳይምን? ብሎ ምናልባት ይጠይቅ ይሆናል፡፡ ሰዎች በመንግሥቱ ልጅ /ህፃናት/ አሁንም ይራባሉ፡፡ /ኢሣ 65፡23/ እናም እንኳን ይሞታሉ፡፡ /ኢሣ 65፡20/፡፡ እነዚህ ሰዎች ክርስቶስ የሚያጠፋው አሁንም በመንግሥቱ ውስጥ አለመግባባቶች ይኖርባቸዋል፡፡/ኢሣ 2፡4/ ምንም እንኳን አሁን ካለው የቀለለ ቢሆን ለመኖር አሁንም በምድር ላይ መሥራት ይኖራል፡፡ ይህ ሁሉ የሚመስለው ከተስፋ ቃሎቹ የመነጨ ጩኸሐሐተ ነው፡፡ ጻድቃን ዘላለማዊ ሕይወት እንደሚቀበሉ እንደእግዚአብሔር ያለ ተፈጥሮና ከመላዕክት የመስተካከል በዚህም ማግባትም ሆነ መራባት እንደማይኖር ካለው ግንዛቤ የተነሣ ነው፡፡ /ሉቃ 20፡35..36/ ሐቁና መልሱ የመጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግሥት ክፍል ለ1000 ዓመታት ለሚሊኒየም የሚቀጥል ከመሆኑ ጋር ያለው እውነታ ላይ ነው፡፡ /ራዕ 20፡2..7 ይመልከቱ/፡፡ በዚህ በሺው ዓመት በምድር ላይ ሁለት የአሕዛብ ቡድኖች ይኖራሉ፡፡

1. ቅዱሳን.. በዚህ ዓለም ክርስቶስን ተቀብለን ተከታዮቹ የሆን ሁሉ
በፍርዱ መቀመጫ ዘላለማዊ ሕይወት ሚሰአን «ቅዱስ» ማለት
የተጠራ ሰው ሲሆን ለማንኛውም ዕውነተኛ አማኝ ማለት
መሆኑን አስተውል፡፡
2. ተራ ሟች ክርስቶስ በተመለሰበት ጊዜ ወንጌልን ያላወቁ ማለትም
ለፍርድ ዙፋኑም ተጠያቂነት የሌላቸው አሕዛብ ናቸው፡፡
ክርስቶስ ሲመጣ ሁለት ሰዎች በሜዳው ላይ ይሆናሉ፤ አንዱ /ወደፍርዱ/ ይወሰዳል፤ ሌላው ይተዋል፡፡ /ሉቃ 17፡36/ የተተውት በሁለተኛው ቡድን ይመደባሉ፡፡

የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ ከፍርድ መቀመጫ የሚቀበሉት ቅዱሳኑ የሚሞቱም ሆነ የሚራቡ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በመንግሥቱ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን የሚያከናውኑት መገላጫዎች ሁለተኛውን ቡድን ይመለከታል፡፡ እነዚህም ክርስቶስ በሚመለስበት ጎዜ በሕይወት ያሉ ህን ደግሞ እግዚአብሔር ከእነርሱ የሚፈልገውን ያላወቁ ናቸው፡፡ የጻድቃኑ ዋጋ /ሽልማት/ «ንጉሥና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው በምድርም ላይ

ይነግሣሉ።» /ራልይ 5፡10/ ነገሥታት በአንድ ሰዉ ላይ መንግሥት ይኖርባቸዋል። ስለወንጌል ምንም የማያውቁትን በክርስቶስ ዳግም መምጣት በሕይወት ኑረው የሚጓዙ ይሆናሉ። ከክርስቶስ ጋር በመሆንም የእርሱን ሽልማት እንካፈላለን። የዓለም ንጉሥ እንሆናለን።

«ድል ለነሣውና እስከመጨረሻም ሥራዬን ለጠበቀው እኔ ደግሞ
ከአባቴ እንደተቀበልሁ በአሕዛብ ላይ ሥልጣንን እሰጠዋለሁ።
በብረትም በትር ይገዛቸዋል።» /ራዕይ 2፡26..27/

የእግዚአብሔር መንገዶች ዕውቀት በፍጥነት አይሠራጭም። ክርስቶስ በኢየሩሳሌም መንገሡ ይታወጃል። አሕዛብም ስለእርሱ የበለጠ ዕውቀት ለማግኘት ወደዚያ ይጓዛሉ። /ኢሣ 2፡2..3/ የዳን ተራራ /የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚወክለው/ እንዴት በምድር እንደተስፋፋም አስተውል። /ዳን 2፡35..44/ የእግዚአብሔርን ዕውቀት እንዲያም ሲል መንግሥቱን ማሠራጨት የቅዱሳን ተግባር ይሆናል።

እስራኤል ቀድሞ የእግዚአብሔር መንግሥት በነበረበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ዕውቀት ያስተማሩ ቀሳውስት ነበሩ /ሚልክ 2፡5..7/ ለዚህም ሲባል በመላ እስራኤል በተለያዩ ከተሞች ተመድበው ነበር። የላቀ ክብር ባለው ሁኔታ እንደገና መንግሥቱ በሚቆምበት ጊዜ የቀሳውስት ሚና በቅዱሳን ይያዛል። /ራዕይ 5፡፡10/

ዛሬ ክርስቶስ ቢመጣ

1/ በሕይወት ካሉ ግን በደግ ሥራቸው ተጠያቂነት ካለባቸው ጎን ተጠያቂ የሆኑት ማቾች ወደ ፍርድ ቦታ ይወሰዳሉ።

2/ በክፋት ተጠያቂነት ያለባቸው በሞት ይቀጣሉ፤ ጻድቃኑም ዘላለማዊ ሕይወት ይቀበላሉ። ክርስቶስን የሚቃወሙ አሕዛብ ደግሞ ወደ ፍርድ ይወሰዳሉ።

3/ ጻድቃ በሕይት ያኔ የነበሩትን ግን ለእግዚአብሔር ተጠያቂ ያልሆኑትን ይገዛሉ። «እንደ ነገሥታትና ክህናት» /ራዕ 5፡10 ሆነው ወንጌልን ያስተምራሉ።

4/ ይህም ለ1000 ዓመታት ይሆናል። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ተጠሪነት ያላቸው ሚች አሕዛብ ወንጌልን ይሰማሉ። እነዚህ ሰዎች ረዥም ዕድሜና የበለጠ የደስታ ሕይወት ይኖራቸዋል።

5/ በዚህ በሺኛው ዘመን መጨረሻ በክርስቶስና በቅዱሳን አንፃር አመፅ ይነሣሣል። እግዚአብሔርም አመጹን ያጠፋል። /ራዕይ 20፡8..9/

6/ በሺው ዓመት መጨረሻ የሞቱት ሁሉ በዚያን ጊዜ ይነሣሉ ለፍርድም ይቀርባሉ። /ራዕይ 20፡5 11..15/

7/ ከእነርሱ መካከል ክፉዎች ይደመሰሳሉ፤ ጻድቃንም የዘለዓለም ሕይወት በመያዝ ከእኛ ጋር ይቀላቀላሉ።

ስለምድር እግዚአብሔር የሚኖረው ዓላማም በዚህ ይፈጸማል፡፡ በህያውና በጻድቃን ትሞላለች፡፡ የእግዚአብሔር ስም «ያሃዌህ ኤሎሂም» /ትርግሙ ግርማ ሞገስ ባላቸው ቡድን የሚከሰት/ የሚለው ይሟላል፡፡ እንደገናም ኃጢአት ብሎም ሞት በምድር አይኖርም፡፡ ስለ እባቧ ዘር የተሰጠው የተስፈጋ ቃል ሙ በሙሉ ራሱን በመቀጥቀጥ ይጠፋል የሚለው ይፈጸማል፡፡ /ዘፍ 315/ በሺኛው ዘመንም ክርስቶስ «ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድርስ ሊነግሥ ይገባዋልና፡፡ የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፡፡ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና፡፡ ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል፡፡» /1 ቆሮ 15፡24/

ይህ «ኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሣልፎ በሰጠ ጊዜ» ነው፡፡ /1 ቆሮ 15፡24/፡፡ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ በሚሆንበት ጎዜ ምን እንደሚከተል አልተነገረም፡፡ የምናውቀው ዘላለማዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ባህርይ እንደሚኖረንና እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ለማክበር እንደምንኖር ነው፡፡

«የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል» መረዳት የእነዚህን ቃላት የሚያነብ ሁሉ ለድኅነቱ ወሳኝ ነው፡፡

እግዚአብሔር በመንግሥቱ እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ የእርሱ አጠቃላይ ዓላማ የተቀረጸው እኛ የገጣረነት ችሎታው አካል እንድንሆን ነው፡፡ ጥምቀት መንግሥቱን በተመለከተ ከተስፋ ቃሎቹ ጋር ያዛምዳቸዋል፡፡ ጥምቀትና ከዚያም ተከትሎ የእግዚአብሔርን ቃል በትህትና በታማኝነት ለጥቂት ዓመታት መጠበቅ ወደዚያ ወደ ክብርና ዘለዓለማዊ ዕድሜ መግቢያ ያስገኝልናል ብሎ ማመን ከባድ ነው፡፡ ያም ሆኖ በእግዚአብሔር ወሰን በሌለው ፍቅሩ ያለን ዕምነት ጽኑ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአጭር ጊዜ ችግሮቻችን ምንም ይሁኑ የወንጌልን ጥሪ የምንቃረንበት በእርግጥ ስሜት የሚሰጥ ምክንያት የለንም፡፡

> «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል» /ሮሜ 8፡31/
> «ለእኛ ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን ያሁኑ ዘመን ስቃይ ምንም እንዳይደል አስባለሁ፡፡» /ሮሜ 8፡18/
> «ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘለዓለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና የሚታየው የጊዜው ነውና የማይታየው ግን የዘለዓለም ነው፡፡» /2 ቆሮ 4፡17/

## ጥናት 5 ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር መንግሥት የሚቀናበት ጊዜ ከሚከተሉት የትኛው ነው?
   ሀ/ ሁልጊዜም ቢሆን የቀና ነው።
   ለ/ ክርስቶስ በሚመለስበት /በክርስቶስ መመለስ/
   ሐ/ በመጀመሪያው ክፍለ.ዘመን በሃምሳኛው ቀን
   መ/ በአማኞች ልብ በሚያምኑበት ጊዜ

2/ ሺህኛው ዘመን ምንድን ነው?
   ሀ/ ብፁዕነት በልባችን ሲነግሥ
   ለ/ የአማኞች የ1000 ዓመት በሰማያት የመንገሥ ዘመን
   ሐ/ የሰይጣን 1000 ዓመት በምድር የመንገሥ ዘመን
   መ/ በምድር የመጪው የእግዚአብሔር መንግሥት የመጀመሪያው የ1000 ዓመት

3/ በሺህኛው ዘመን የዛሬዎቹ አማኞች ምን ያደርጋሉ?
   ሀ/ በሟች አሕዛብ ላይ ገዢዎች ይሆናሉ
   ለ/ በሰማያት ገዢዎች ይሆናሉ
   ሐ/ አናውቅም
   መ/ በሌላ ፕላኔት ላይ ይኖራሉ።

4/ ስለእግዚአብሔር መንግሥት መልዕክቱ ተሰብኳል?
   ሀ/ በሃዲስ ኪዳን አዎ በትክክል
   ለ/ በኢየሱስና በሐዋሪያቱ አዎን በትክክል
   ሐ/ በሁለቱ በብሉይና በሐዲስ ኪዳኖች
   መ/ በብሉይ ኪዳን አዎን በትክክል

# 6. እግዚአብሔርና ክፉ ነገር

# 6.1 እግዚአብሔርና ክፉ ነገር

ብዙ የክርስትና ክፍሎች ከሌሎች ኃይማኖቶች ጎን በዚህ ዓለምና በእኛም

ውስጥ ያሉ ችግሮችን ሁሉ የፈጠረና ለምንሠራቸው .E
የኃጢአት ሥራዎች ሁሉ ተጠያቂ አንድ ነገር ወይም
አስፈሪ አካል እንዳለ ያምናሉ። ዲያብሎስ ወይም
ሰይጣን ብለውም ይጠሩታል። መጽሐፍ ቅዱስ
እግዚአብሔር በሁሉም ኃያል እንደሆነ በግልጽ
ያስተምራል። መላዕክት ኃጢአት እንደማይሠሩ
ቀደም ሲል በጥናት 1..4 አይተናል። እነዚህን
ነገሮች በዕውነት ካመን በዚህ ዓለም ሁሉ የማይሳነውን
እግዚአብሔርን የሚቃረን በሥራ ያለ ልዩ
ልዕለ..ተፈጥሮ ነገር ሊኖር አይችልም። እንደዚህ ያለ
ነገር አለ ካልን ደግሞ ሁሉ የማይሳነውን
የእግዚአብሔርን የበላይነት ጥያቄ ውስጥ አስገባነው
ማለት ይሆናል። የዲያብሎስ ወይም የሰይጣን
ትክክለኛ ግንዛቤ ካልጨበጥን የኢየሱስን ተፈጥሮ ሥራ
ልንረዳ አንችልም።

.F

በጥቅል ዓለም፣ በተለይ ደግሞ የክርስቲያን .G
ዓለም ብለን በምንጠራው መልካም ነገሮች

ከእግዚአብሔር መጥፎ ነገሮች ከዲያብሎስ ወይም ከሰይጣን እንደሚመጡ የሚያስተጋባው ሃሳብ አለ። ይህ አዲስ ሃሳብ አይደለም። ለክርስቲያኖች ብቻ የተወሰነ ሃሳብም አይደለም። ባቢሎናውያን ለምሳሌ ሁለት አምላኮች እንዳሉ ያምኑ ነበር .. አንዱ የጥሩና የብርሃን አምላክ፤ ሌላው የክፉና የጨለማ አምላክ ሆነው ሁለቱም እኔ አሸንፍ እኔ አሸንፍ እያሉ እየተዋጉ እንደሚኖሩ ይቀበሉ ነበር። የፋርስ ንጉሥ ሳይሩስ ይህን አምኗል። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ነገረው። «... እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ምንም የለም። ብርሃንን ሠራሁ ጨለማውንም ፈጠርሁ ደህንነትን እሰራለሁ ክፉትንም እፈጥራለሁ እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።» /ኢሣ 45፡5..7 ፣22/። እግዚአብሔር ሰላምን ይፈጥራል። እግዚአብሔር ክፉትን ወይም ጥፋትን ይፈጥራል። በዚህ ስሜት በ«ክፋት»ና በ«ኃጢአት» መካከል ልዩነት አለ። የኋለኛው የሚፈጠረው በሰው ስህተት ስለሆነ ወደዓለም የገባው በእግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ባመጣው ጣጣ ነው። /ሮሜ 5፡12/

.H

.I

እግዚአብሔር ለሳይሩስና ለባቢሎናውያን የሚነግራቸው «ከእኔ ጎን ሌላ እግዚአብሔር የለም» ነው። በእብራይስጥ ቋንቋ «ኢል» ሲተረጎም

«እግዚአብሔር» በመሠረቱ የጥንካሬ ወይም የኃይል ምንጭ ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ምንጭ የሆነ ኃይል በዚህ ዓለም የሚኖር ከእኔ በስተቀር የለም ነው የሚለን፡፡ ለዚህም ነው በእግዚአብሔር በዕውነት የሚያምን ልዕለ..ተፈጥሮ ያለው ዲያብሎስ ወይም ጭራቅ የሚባል ወይም ሌላ ኃይል የመኖሩን ሃሳብ ሊቀበል የማይችለው፡፡

.J

## እግዚአብሔር የመቅሰፍት ፈጣሪ .K

.L

መጽሐፍ ቅዱስ በሰዎች ሕይወትና በዚህ ዓለም .M
«ክፉ ነገሮች» የሚያመጣ እግዚአብሔር መሆኑን በልዩ ልዩ ምሣሌዎች ያስረዳል፡፡ አሞፅ በ3፡6 ላይ በአንድ ከተማ ላይ ክፉ ነገር ቢደርስ እግዚአብሔር ያመጣው መሆኑን ይናገራል፡፡ ለምሣሌ የመሬት መንቀጥቀጥ በአንድ ከተማ ላይ ሲደርስ ብዙ ጊዜ የዲያብሎስ ሥራ ሆኖ መዓቱን እንዳመጣው ይሰማናል፡፡ እውነተኛ አማኝ ግን ይህን መዓት ያመጣው እግዚአብሔር እንደሆነ ሊያምን ይገባል፡፡ ስለዚህም ሚክያስ በ1፡12 ላይ እንዲህ ይላል ...

«ክፉ ነገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለአለ .N
እየሩሳሌም በር ድረስ
ወርዷል»

በመጽሐፈ ኦዮብ ጻድቁ ሰው ኢዮብ በዚህ ዓለም .O
የሕይወት ዘመኑ የነበሩትን ነገሮች እንዴት እንዳጣቸው እናነባለን፡፡ መጽሐፉ በአንድ ሰው ሕይወት የክፋት ሥራ ለእግዚአብሔር ካለን ታማኝነትና ከሃዲነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ እንዳይደለ ያስተምረናል፡፡ ኢዮብ «እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሳ» /ኢዮብ 1፡21/ አለ እንጂ እግዚአብሔር ሰጠ ሰይጣን ነሳ አላለም፡፡ ለሚስቱም እንዲህ ሲል ጠይቋታል «ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀበልን ክፉ ነገርስ አንቀበልምን? /ኢዮ 2፡10/ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ «እግዚአብሔርም ከመጣበት ክፉ ነገር ሁሉ አጽናኑት /ወዳጆቹ/» ይላል /ኢዮብ 42፡11/

ስለሆነም፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚከሰቱት .P
ችግሮች እንደደረሱ ዋናው ፈቃጅ ስለሆነ የክፉ ነገር ምንጩ እርሱ ነው፡፡

«ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና የሚቀበለውንም .Q
ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል
ቅጣት ሁሉ ለጊዜዉ የሚያሳዝን እንጂ ደስ .R
የሚያሰኝ አይመስልም
ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም .S
ጽድቅን ያፈራላቸ
ዋል፡፡ /ዕብራ 12፡6..11/፡፡ .T

.U

ይህ እግዚአብሔር የሚሰጠን ፈተናዎች በመጨረሻ .V
ወደመንፈሳዊ ዕድገት እንደሚያመሩን ያሳያል፡፡
ስለዲያብሎስ ያለን አክራሪ ሀሳብ እዚህ ላይ ከባድ ፈተና ውስጥ እየገባ ነው፡፡ በተለይ የዚህ ከባድነቱ ሰውን ወደኃጠ ‐አት የሚመራውን ይኸውም «መንፈስ ይጠበቅ ዘንድ ወይም መንፈሱ ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋዉ ጥፋት ለሠይጣን እንዲሰጥ ፍርዱ ነው፡፡» የሚናገረው ምንባብ ላይ ነው፡፡ /1 ቆሮ 5፡3 ፣ 1 ጢሞ 1፡20/ ሰይጣን በእርግጥ ሰዎች ኃጢአት እንዲሠሩ ያለ ነገር ከሆነና በሰዎች ላይ አሉታዊ የመንፈስ ተጽዕኖ ያለው ከሆነ ለምን እነዚህ ጥቅሶች ስለሰይጣንም በአወንታዊ ብርሃን ያነሡታል? መልሱ ያለው ተፎፎካካሪው «ሠይጣን» ወይም በሕይወት ውስጥ ያለው እግር አወንታዊ መንፈሳዊ ውጤት በአማኞች ሕይወት ላይ ብዙ ጊዜ ያስከትላል፡፡

.W

ክፉ ነገር ከእግዚአብሔር እንደሚታዘዝ .X
ከተቀበልን ስለአሉብን ችግሮች አንድ ነገር እንዲያደርግልን ለምሣሌ እንዲያስወግድልን ለእግዚአብሔር መጸለይ እንችላለን፡፡ ካላስወገደልን ለመልካም መንፈሳችን ሲል ከእግዚአብሔር የተላኩ መሆናቸውን እናውቃለን፡፡ አሁን ለችግሮቻችን ምክንያት አንድ ክፉ ነገር ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ ተብሎ የሚጠራ አለ ብለን ካመን ከእነዚህ ክፉ ነገሮች ጋር የመስማማት መንገድ አይኖርም፡፡ አካለ ስንኩልነት ህመም፣ የድንገተኛ አደጋ መኖር ወይም መዓት እንዲሁ እንደመጥፎ ዕድል ተደርገው መወሰድ ሊኖርባችው ነው፡፡ ዲያብሎስ እንደዚህ ኃይለኛ ኃጢአተኛ መልዓክ ከሆነ ከእኛ በጣም የላቀ ኃይለኛ ስለሚሆን በእርሱ እጅ ከመሰቃየት ወጭ ምርጫ አይኖረንም፡፡ በተቃራኒው በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስለሆን እንጽናናለን፡፡ «ነገሮች ሁሉ /በሕይወት/ ለበጎ በአንድነት ይሠራሉ፡፡» /ሮሜ 8፡28/፡፡ ስለዚህም በአማኝ ሕይወት ውስጥ «ዕድል» የሚባል ነገር የለም፡፡

.Y

## የኃጢአት መነሻ .Z

.AA

ኃጢአት ከእኛ ውስጥ እንደሚመጣ .BB
ጎልቶ መታወቅ አለበት፡፡ ኃጢአት መሥራት የእኛ ስህተት ነው፡፡ በእርግጥ መሥራታችን የእኛ ስህተት አይደለም ብሎ ማመን ጥሩ ነበር፡፡ በነፃነት ኃጢአት ፈጽመን የዲያብሎስ

ስህተት ነው ብሎ መጽናናቱ ማመካኘቱ ይቀል ነበር፡፡ የኃጠ
-አታችንን ስህተት በዲያብሎስ አመካኝቶ እርሱን መውቀስም
መልካም ነበር፡፡ በሰፊው የክፉት ባህርይ ውስጥ የሚገኙ
ሰዎች በዚያን ጊዜ በሠይጣን ተሸፍነው የፈጸሙት በደል
እንደሆነ አድርጎ አጥፊዎች ምህረትን መለመናቸው
ያልተለመደ አይደለም፤ ነገር ግን በትክክለኛው ሲታይ
ደካማ ምክንያቶች /የይቅርታ ጥያቄዎች/ ፈጽሞ አሳማኝነት
/ተቀባይነት/ እንደሌላቸው ይገመገማሉ፡፡ በመሆኑም
ግለሰቡ/ቦች/ ይፈረድበታል/ቸዋል/፡፡

«የኃጢአት ደመወዙ ሞት ነው፡፡» /ሮሜ 6፡23/ የሚለውን ማስታወስ ይገባናል፡፡ ኃጢአት ወደ ሞት ይመራል፡፡ ኃጢአት መሥራታችን የእኛ ስህተት ሳይሆን የዲያብሎስ ከሆነ ትክክለኛው እግዚአብሔር ዲያብሎስን ነው መቅጣት ያለበት፡፡ እኛን አይደለም፡፡ ነገር ግን ለራሳችን ኃጢአት እኛ የመዳኘታችን ሀቅ ለኃጢአቶታችን እኛው ተጠ
ያቂዎች መሆናችንን ነው የሚያሳየው፡፡ ዲያብሎስ በእኛ ውስጥ ያለ የኃጢአት መርሆ ሳይሆን ከእኛ ውጭ ያለ አንድ ልዩ አካል /ፍጥረት/ አድርገን የመውሰዳችን ሀሳብ ለኃጠ
-አቶቻችን ከኃላፊነት ራሳችንን ለማራቅ የምናደርገው ሙከራ ነው፡፡ ይህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎች ተፈጥሮ ማለትም በመሠረቱ ኃጢአተኛ ስለመሆናቸው ከሚያስተምረው ጋር አለመታረቃቸውን የሚያሳይ ሌላው ምሣሌ ነው፡፡

«ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጭ

የሚገባውስ ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም። ከውስጥ ከሰው

ልብ የሚወጣው ክፉ ሀሳብ፣ ዝሙት፣መስረቅ፣መግደል፣ምንዝርነት፣

መጎምጀት፣ ክፋት፣ተንኮል፣መዳራት... ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ

ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል።» /ማር 7፡15..23/

ከውጭ ካለው ልብ ነው እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ የሚመጡት። ለዚህም ነው በጎርፍ ጊዜ እግዚአብሔር «የሰው ልብ ሃሳብ ከትንሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና» /ዘፍጥ 8፡21/ ሲል ያሰበው። ቶማስ 1፡14 ላይም እንዴት እንደተፈተን እንዲህ ሲል ይነግረናል። « እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ክፉ ፍላጎት እንዲላቀቅ ይፈተናል» /ቶማ 1፡14/። እኛ የምንፈተነው በራሳችን ክፉ ችግርና ፍላጎት እንጂ በሌላ ከውጭ በሚመጣ ኃይል አይደለም። ቶማስ «ከየት ነው በመካከላችሁ ጦርነትና ግጭቶች የሚመጣው»? ሲል ይጠይቃል እያንዳንዳችን የተወሰኑ የራሳችን ግላዊ ፈተናዎች አሉብን። የግልም ስለሆኑ ከራሳችን ክፉ ፍላጎቶች የሚነሡና የሚካሄዱ ናቸው። በትክክል እንደሚባለው እኛ ለራሳችን የመጨረሻ መጥፎ ጠላቶች ነን።

መጽሐፈ ሮማውያን በአብዛኃኙ ኃጢአትን፣ የኃጢአትን መነሻና እንዴት ለማሸነፍ እንደሚቻል በተመለከተ የተጻፈ ነው። በዚህ መጽሐፍ ስለዲያብሎስና ሰይጣን የተጠቀሰ ነገር እንደሌለ ማገንሳቱ እጅግ አስፈላጊ ነው። ማለትም ስለኃጢአት መነሻ ምክንያት ጳውሎስ ዲያብሎስን ወይም ሰይጣንን አያነሳም። በተመሳሳይ መንገድ «ዲያብሎስ» የሃዲስ ኪዳን ፅንሰ ሃሳብ ነው። ኃጢአት እንሠራ ዘንድ የሚያደርገን ነገር ውጫዊ ኃይል ቢሆን ኖሮ በእርግጥ በብሉይ ኪዳን በሰፊው ይጠቀስ ነበር። ሆኖም ምንም ይኽ ነው እዚህ ላይ ተነስቶአል የሚባል ምልክት እንኳን የለም። በዘመነ መሣፍንት እስራኤላውያን በበረሃ በነበሩበት ጊዜ የተጻፈው የሚያሳየው በሰፊው ኃጢአት እየሰሩ እንደነበር እንጂ ኃይለኛ ልዕለ ተፈጥሮ ያለው

ነገር ወይም ኃይል ኖሮ እየገባ ኃጢአት እንደሚያሠራቸው እግዚአብሔር ያስጠነቀቀበት ሁኔታ የለም። ይልቁንም ቃሉን ይጠብቁና በሥጋቸው ፍላጎት እንዳይወድቁ አበረታታቸው እንጂ። /ምሣሌ ዘዳግ 27፡9..10 የሽዋ 22፡5/

> «በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር ዐውቃለሁና የማልወደውን
> ክፉውን ነገር አደርጋለሁ። ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን የማደርገው አሁን
> እኔ አይደለሁም በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ» ይላል ጳውሎስ
> /ሮሜ 7፡18..21/

እዚህ ላይ ኃጢአተኛነቱን ዲያብሎስ በሚባል ውጫዊ ኃይል አያመካኝም። የራሱን የግል ክፉ ተፈጥሮ የኃጢአቱ ትክክለኛው ምንጭ መሆኑን እንጂ። «የማደርገውን አላውቅምና የምጠላውን ያን አደርጋለሁና የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደሆነ እመሰክራለሁ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና» /ሮሜ 7፡15..21/ ሌላው ያለጥርጥር ጻድቅ የሆነው ዳዊት እንደዚሁ የተፈጥሮውን ኃጢአተኛነት ሲገልጽ «..እነሆ በአመፃ ተፀነስሁ እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።» /መዝ 51፡5/

ስለዋናው ክፉ የሰው ተፈጥሮ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልጽ ያለ ነው። ይህን ከተቀበልን ሃሳባዊ ሰው በሃሳብ ፈጥሮ ለኃጢአታችን ኃላፊነት መውሰድ ከሚኖርባቸው የሰው ተፈጥሮዎች ውጭ ማድረግ አስፈላጊ አይሆንም። ኤርምያስ በ17፡9 ላይ የሰው ልብ ተስፋ በሚያስቆርጥ ሁኔታ ደካማና አታላይ ነው ብሏል። ኢየሱስም እንደዚሁ የሰውን ተፈጥሮ በሚክያስ 7፡11 ላይ ከክፋት ጋር ያቀናጀዋል። «የሰው ልጆች ልብ ክፋትን ትሞላለች» /መክ 9፡3/ ኤፌሶን 4፡18 የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከእግዚአብሔር የመለየቱን ምክንያት ይሰጣል። እንዲህ ሲል «እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ ልቦናቸው ጨለመ።» በአላዋቂ ልቦቻችንና በመንፈስ በመታወራችን ምክንያት በውስጣችን ባለው የክፋት መንገድና አስተሳሰብ ከእግዚአብሔር እንድንርቅ ሆነናል። በዚህ መሥመርም ስለኃጢአታችን ወደገላትያ ሰዎች 5፡19 ላይ «የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው» ይላል። የእኛ ሥጋ፣ የእኛ ማንነትና ተፈጥሮ ነው ኃጢአት የሚያሠራን። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ በእኛ ውስጥ ያለው ኃጢአት ምንጩ ዲያብሎስ በእኛ ውስጥ ያስቀመጠው ስለመሆኑ የተጻፈ አናገኝም። የኃጢአተኛነት አዝማሚያዎች ከተወለድንበት ቀን ጀምሮ አብሮን የተፈጠረ ነገር ነው። ሰው የተሠራበት ዋና አካል ነው።

## 6.2 ዲያብሎስና ሰይጣን

አልፎ አልፎ በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ቃላት ሳይተረጎሙ እንዳሉ ተትተዋል፡፡ «ሰይጣን» የሚለው ያልተተረጎመው የእብራይስጥ ቃል ሲሆን ተቀናቃኝ ማለት ነው «ዲያብሎስ» የሚለው ቃል «ዲያቦሎስ» ከሚለዉ የግሪክ ቃል የተወሰደና ትርጓሜውም «ውሸታም» ጠላት ወይም «የውሸት ከሣሽ» ማለት ነው፡፡ ለኃጢአታችን ኃላፊነት ያለባቸው ከእኛ ውጭ የሆኑት ሰይጣንና ዲያብሎስ ናቸው ብለን የምናምን ከሆነ እነዚህ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲያጋጥሙን ይህን ክፉ ሰው እንዲያመላክቱ ማድረግ ነበረብን፡፡ የእነዚህ ቃላት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠ ቃቀም የሚያሳየው ተራ የተራውን ሰው ገላጮች አድርገን መጠቀም እንደምንችል ነው፡፡ ሰይጣንና ዲያብሎስ የሚባሉት ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስንጠቀምባቸው በራሳቸው ከሰው ውጭ ሆነው የክፉ ሰው ወይም ፍጡር መገለጫ ናቸው ብሎ ምክንያት ለመስጠት እንደማይቻል ይህ ሐቅ ያሳያል፡፡

ሰይጣን የሚባለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀሪያው መጽሐፈ ነገሥት 11:14 ላይ የተመዘገበው «እግዚአብሔር የኤዶምያስን ሰው ሀዳድን ጠላት አድርጎ በሰሎሞን ላይ አስነሣው» ይላል፡፡ እና «እግዚአብሔር ሬዞንን ሌላ ጠላት /ሌላ ሰይጣን/ አድርጎ አስነሣበት በሰሎሞን ዘመን ሁሉ የእስራኤል ጠላት ነበር፡፡» /1 ነገሥ 11:23..25/ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮ ያለው ሰው ወይም መልአክ የሰሎሞን ጠላት /ሰይጣን/ አድርጎ አስነሳበት ማለት አይደለም፡፡ ተራ ሰዎች አስነሣበት ማለት እንጂ፡፡ በማቴዎስ በ16:22..23 ሌላ ምሣሌ ይሰጣል፡፡ ጴጥሮስ ኢየሱስ ለመሞት ወደኢየሩሳሌም እንዳይሄድ ለማግባባት በሞከረበት ጊዜ ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ዞወር ብሎ እንዲህ ብሎታል «..ወደኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና እንቅፋት ሆነህብኛል፡፡» /ማቴ 16:22..23/፡፡ ጴጥሮስ ሰይጣን ተብሎ ነበር፡፡ ክርስቶስ እነዚያን ቃላት ሲናገር ለመልአክ ወይም ለሆነ አስፈሪ ነገር አልነበረም፤ ለጴጥሮስ ነበር እንጂ፡፡

ሰይጣን የሚለው ቃል ጠላት ማለት ስለነበረ መልካም ሰው እንዲያውም እግዚአብሔር ራሱ ሰይጣን ተብሎ ስያሜ ሊሰጠው ችሏል፡፡ ጠለቅ ብሎ ሲታይ ቃሉ በራሱ ኃጢአተኛ የግድ የሚያደርገው አንዳችም ነገር የለም፡፡
እግዚአብሔር ራሱ በሕይወታችን ላይ ፈተና በማምጣት ሰይጣን ሊሆን ይችላል፡፡ የተሳሳተ መንገድና እርምጃ በምንወስድበት በመቆምም እንደዚሁ ሰይጣን ሊሆን
ይችላል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር «ሰይጣን» ተብሎ ሊጠራ ይችላል ብንልም እርሱ በራሱ ኃጢአተኛ ነው ማለት አይደለም፡፡

የሣሙኤልና መዋዕለ ዜና መጻሕፍት ለነዚህ ተመሳሳይ አጋጣሚዎች ተዛማጅ መግለጫዎች ይሰጣሉ፡፡

«... እግዚአብሔር... ዳዊትንም ሂድ እስራኤልንና ይሁዳን ቁጠር ብሎ በላያቸው አስነሣው፡፡» /2 ሣሙ 24፡1/፡፡ እንዲሁም «.. ሰይጣን በእስራኤል ላይ ተነሣ... ዳዊትንም አንቀሳቀሰው፡፡» /2 መዋ ዜና 21፡1/ የሕዝብ ቆጠራ እንዲያደርግ፡፡

በአንድ ምንም መፈታተኑን የሚያደርገው እግዚአብሔር ሲሆን ሌላውን ሰይጣን ነው ማለት እግዚአብሔር ለዳዊት እንደሰይጣን ወይም ጠ ላት አደረገ ወደሚለው ብቸኛ መደምደሚያ ላይ ነው የሚያደርሰው፡፡ ለኢዮብ በሕይወቱ ውስጥ ፈተናዎች በማድረሱ ኢዮብ ስለእግዚአብሔር እንዲህ ብሏል «ተመልሰህ ጨካኝ ሆንህብኝ በእጅህም ብርታት አስጨነቅኸኝ፡፡» /ኢዮብ 30፡21/፡፡ በመሠረቱ ኢዮብ ይለው የነበረው በሌላ አነጋገር «በእኔ አንፃር አንተ እንደሰይጣን ትሆንብኛለህ» ነበር፡፡

## በመጽሐፍ ቅዱስ «ዲያብሎስ» የሚለው ቃል

ኢየሱስ ስለያስቆሮቱ ይሁዳ ሲናገር «እናንተን 12 ሐዋርያቴ አድርጌ አልመረጥኋችሁምን? እንዲሁም አንዳችሁ ዲያብሎስ አይደለምን?» /1 ጢሞ 3፡11 ይሁዳ ተራ ሟች ሰው ነበር እንጂ ሌላ ፍጡር አልነበረም፡፡ ዲያብሎስ የሚለው ቃል የገለጸው ክፉን ሰው ነው፡፡ ጳውሎስ ጢጦስን ባልቴት ሴቶች ሃሰተኛ ከሳሾች ወይም ዲያብሎስ መሆን እንደሌለባቸው አስጠንቅቋቸዋል፡፡ /ጢጦ 2፡3/፡፡ እንዲሁም ለጢሞትዎስ እንዲህ ብሎታል፡፡» በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደመጣ ይህን ዕወቅ... ሰዎች ሃሰተኛ ከሣሶች /ዲያብሎሶች/ ይሆናሉ /2 ጢሞ 3፡1..3/ ይህ ማለት የሰው ልጆች ወደልዕለ ሰውነት ይለወጣሉ ማለት ሳይሆን ክፋታቸው ግን የበለጠ እየጨመረ ይሄዳል ለማለት ነው፡፡ ከዚህ ግልጽ መሆን ያለበት ሰይጣን ወይም ዲያብሎስ የሚሉት ቃሎች የወደቀ መልዓክ ወይም ከእኛ ውጭ የሆነ ኃጢአተኛ ፍጡርን እንደማያመላክት ነው፡፡

## ኃጢአት፣ ሰይጣንና ዲያብሎስ

ሰይጣንና ዲያብሎስ የሚባሉት ቃላት ኃጢአት ለመሥራት በውስጣችን ያሉትን አዝማሚያዎች ለመግለጽ መሆኑን በጥናት 6.1 ላይ አይተናል፡፡ «ሰይጣን» የእኛ ዋና ጠላት ነው፡፡ ለእነዚህ ደግሞ የሰው አምሳል ሰጥተናቸዋል፡፡ በዚህም «ዲያብሎስ» ለእኛ ጠላት የእውነት ጠ ላት ብለን መናገር እንችላለን፡፡ ይህ የእኛ ተፈጥሮአዊ ሰው የሚመስለው

ዋናው ዲያብሎስ ነው፡፡ በዲያብሎስና በውስጣችን ባለው በክፉ ፍላጎቶች መካከል ያለው ትስስር በብዙ ምንባቦች ላይ በግልጽ ሠፍሮአል፡፡

> «...እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት
> ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው፡፡ /ዕብራ 2፡14/

ዲያብሎስ ለሞት ዋና ተጠያቂ እንደሆነ ተገልጾአል፡፡ ነገር ግን «የኃጠ ‹አት ደመወዝ ሞት ነው» ይላል /ሮሜ 623/፡፡ ስለሆነም፣ ኃጢአትና ዲያብሎስ ጎን ለጎን መሆን አለባቸው፡፡ በተመሳሳይም፣ ቶማስ 1፡14 ላይ ክፉ ፍላጎቶችን ይፈታተኑናል፤ ይኸውም ወደኃጢአትና ብሎም ወደሞት ይመሩናል ይላል፤ ሆኖም ወደ እብራውያን ሰዎች 2፡14 ዲያብሎስ ሞትን ያስከትላል /ያመጣል/ ይላል፡፡ ያው ቁጥር ኢየሱስ ዲያብሎስን ያጠፋ ዘንድ የእኛ ተፈጥሮ ነበረው ይላል፡፡ ይህን ወደሮሜ ሰዎች 8፡3 ላይ ከተጻፈው ጋር ሲነጻጸር «..እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ /ማለትም በሰብአዊ ተፈጥሮአችን/ ምሣሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጓልና» ይላል፡፡ ይህም ዲያብሎስና በሰብአዊ ተፈጥሮአችን ውስጥ በሚመነጨው በኃጢአት አዝማሚያዎች መካከል ልዩነት እንደሌለ ያሳያል፡፡ ኢየሱስም ልክ እንደእኛ ተፈትኖ እንደነበር ማገናዘቡ በጣም ጠ ቃሚ ነው፡፡ የዲያብሎስን ትምህርት በትክክል አለመረዳት ማለት የኢየሱስን ተፈጥሮና ሥራ በትክክል ለመረዳት አለመቻል ነው፡፡ ኢየሱስ የእኛ የሰው ተፈጥሮ ነበረውና በእርሱ ውስጥ ዲያብሎስ በመኖሩም የድኅነት ተስፋ ሊኖረን ብቸኛው ምክንያት ሆነ፡፡
የራሱን የግል ተፈጥሮአዊ ፍላጎቶች በማሸነፉ ኢየሱስ ዲያብሎስን በመስቀል ሊያጠፋው ችሎአል፡፡ /ዕብራ 2፡14/፡፡ ዲያብሎስ ሰብአዊ ፍጡር ቢሆን ኑሮ እስካሁን ሊኖር ባልቻለም ነበር፡፡ ወደ እብራውያን ሰዎች 9፡26 «ራሱን በመሰዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል፡፡» ይላል፡፡ ይኸው ምዕራፍ ላይ በቁጥር 14 ከዚሁ ጋር በመግጠም በሞቱ ክርስቶስ በውስጡ ያለውን ዲያብሎስ አጠፋ ይለዋል፡፡ በሞቱ ኢየሱስ ለወደፊቱ የ/ኃጢአትን ሥጋ» አጠፋ /ሮሜ 6፡6/ ይህም ማለት ሰብአዊ ተፈጥሮ በሥጋዎቻችን ፍላጎቶች የሚገለጸውን ኃጢአት ነው፡፡

«...ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፡፡» /1 ዮሐንስ 3፡8/ ምክንያቱም ኃጢአት የራሳችን ተፈጥሮአዊ ክፉ ፍላጎቶች መንገድ የመስጠት ውጤት ነውና፡፡ «... ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ፡፡» /1 ዮሐ 3፡8/፡፡ ዲያብሎስ የእኛ ክፉ ፍላጎቶች ስንል ትክክል ከሆነ የክፋት ፍላጎቶች ማለትም የሚያስከትለው ኃጢአቶቻችንን ነው፡፡ ይህ 1 ዮሐ 3፡5 ላይ ተረጋግጧል፡፡ «እርሱ /ኢየሱስ/ ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ፡፡» «ኃጠ ‹አቶቻችን»ና «የዲያብሎስ ሥራዎች» አንድ ዓይነት መሆናቸውን ይህ

ያረጋግጣል። ጴጥሮስ ለአናናውያን «ሰለምን ሰይጣን በልብህ ሞላ?» ይላል። በኋላም በቁጥር 4 ጴጥሮስ «ስለምን በልብህ ይህን ነገር ያዝህ?» ይላል። መጥፎ ነገር በልባችን ማርገዝና /መያዝና/ ሰይጣን ልባችንን መሙላት አንድ ነው። እኛው ራሳችን አንድ ነገር ካረገዝን /ለምሣሌ የኃጢአት ዕቅድ/ በውስጣችን መፈጠርና ማደግ ይጀምራል። አንዲት ሴት ልጅ የምታረግዘው በውስጧ እንጂ ከውጭ አይደለም ። መዝሙረ ዳዊት ኃጢአተኛው ሰው ከሰይጣን ጎን ለጎን በ109፡6 ላይ «... በላዩ ኃጢአትን ሹም ሰይጣንም በቀኙ ይቁም» ሲል ያስቀምጠዋል።

## ከፖለቲካ አኳያ «ዲያብሎስና ሰይጣን»

የምንኖርበትን ክፉና ኃጢአት የተሞላበት የዓለም ሥርዓት ለመግለጽ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚሉትን ቃላት እንጠቀማለን። የሰው ልጅን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ የሥልጣን ተዋረዶች ለመግለጽ «ዲያብሎስ» የሚለውን ቃል እንገለገልበታለን። የአይሁዳውያንንና የሮማውያንን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ለመግለጽ በሐዲስ ኪዳን ላይ «ዲያብሎስና» «ሰይጣን» ተመልክተዋል።
አማኞችን ወደወህኒ ቤት ለማውረድ ሮማውያን ባለሥልጣኖች ዲያብሎስ የሚለውን ቃል ተጠቅመዋል። /ራዕይ 2፡10/። በዚህም ጽሑፍ የሰይጣን መቀመጫ ወይም ዙፋን በሚገኝበት በፔረሞስ ቤ/ክርስቲያን .. በፔርጋሞስ ማለትም የአማኞች ቡድን በነበረበትና በሮማ ቅኝ ግዛት በነበረው አገዛዝ የነበረውን እናነባለን። ሠይጣን በራሱ ቢኖር እንኳን በአካል በፔርጋሞስ ዙፋን ነበረው ለማለት አንችልም።

የእያንዳንዱ የተናጠል ኃጢአት ሲተረጎም የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ማለት ነው። /ዮሐ 3፡4/ ነገር ግን ኃጢአት በጅምላ እግዚአብሔርን በመቃረን እንደፖለቲካዊና ማኅበራዊ ኃይል ሲገለጽ ከተናጠል የላቀ ኃይልኛ ኃይል ነው። ይህ የጅምላ ኃይል ነው። አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ኃይል ያለው መልክ ሰጥተን ዲያብሎስ ብለን የምንጠራው። ለዚህም ነው ኢራንና ሌሎች እስላማዊ ኃይሎች አሜርካንን «ትልቁ ሰይጣን» ማለትም ለእነርሱ በፖለቲካዊና በኃይማኖታዊ ቃሎች ለአቋማቸው ትልቅ ጠላት ለማለት በዚያ የጠሩት። በመጽሐፍም ሰይጣንና ዲያብሎስ የተገለጡበት መንገድም ያው ነው።

በመደምደሚያም በጥቂት ቁጥሮች ሰፊ ትምህርታዊ ትንተናዎች ከመስጠት ይልቅ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱሱ ሚዛናዊ አስተያየት ላይ የተመሠረተ ከማንኛውም ሌላ ጉዳይ የላቀ ግንዛቤ መውሰዱ ይበጃልና ዲያብሎስን በተመለከተ የጋራ እምነቶች ልንይዝ ይገባል። እነዚያ ቃላት

እንደተራ ገላጮች ወይም በአንዳንድ ቦታዎች በሰብአዊ ተፈጥሮአችን ውስጥ የሚመነጩ ኃጢአትን ይመለከታሉ።

ከእኛ የመደምደሚያ ሀሳቦች ጋር ችግሮች ያሉባቸው ሁሉ ራሳቸውን መጠየቅና መመለስ የሚኖርባቸው ...

1. ኃጢአት ተምሳሌ ነውን? በግልጽ ነው።
2. ሰይጣን ልክ እንደገላጭ ሊያገለግለን መቻሉ እውነት ነውን? አዎ ነው። ስለዚህ ኃጢአት በጠላታችን ለሰይጣን የተመሰለ መሆኑን በመቀበላችን ምን ተጨባጭ ችግር ሊኖር ይችላል? ዓለም ብዙ ጊዜ በዮሐንስ ደብዳቤዎችና በወንጌል ምሣሌ ይመሰላል። ከሰይጣን ወይም ከዲያብሎስ ለዚህ በምን በተሻለ ርዕስ /ስያሜ/ ይመሰላል።

## 6.3 መናፍስት /አጋንንት/

በቀድሞዎቹ ክፍሎች ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ሰብአዊ ፍጥረቶች ወይም ጭራቅ ናቸው ብለን ለምን እንደማናምን ገልጸናል። እንደዚህ የሚባል ነገር እንደሌለ ከተቀበልን የዲያብሎስ ባሪያዎች የሆኑት አጋንንት በእርግጠኝነት አይኖሩም ማለት ነው። ብዙ አሕዛብ እግዚአብሔር በሕይወት ያሉትን መልካም ነገሮች ሁሉ ይሰጠናል። ዲያብሎስና የእርሱ አጋንንት መጥፎ ነገሮችን ይሰጡናል እግዚአብሔር የሚሰጠንን መልካም ነገሮች ደግሞ ይነጥቁናል ብለን የምናምን ይመስላል። እግዚአብሔር የሁሉም ኃይል ምንጭ እንደሆነና በሕይወታችን ለሚያጋጥሙን መልካምና መጥፎ ነገሮች ሁሉ ኃላፊነቱ የእግዚአብሔር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል /ኢሳ 45፡7/። ስለዚህ፣ ፈተናዎች በሚደርሱብን ጊዜ ዲያብሎስን ወይም አጋንንትን ከመውቀስ /ከማመካኘት/ ይልቅ ከእግዚአብሔር እንደሚመጡ መቀበል ይኖርብናል። ኢዮብ እንደተገነዘበው «እግዚአአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።» ይላል /ኢዮ 1፡21/

ሕዝቦቹ በሌሎች አማልክት ማመን ሲጀምሩ እግዚአብሔር ይቀናል፡፡ እነርሱ ለእግዚአብሔር አንተ ታላቅ ኃያል እግዚአብሔር ነህ፣ ሆኖም ከአንተ ጎን አንዳንድ ሌሎች አማልክት አሉ እንደአንተም ኃይለኛ ባይሆኑም ቢሉት ይቀናል፡፡ ስለዚህም ነው እንደእውነተኛው እግዚአብሔር ሳይሆን መናፍስትም ሆኑ ዲያብሎስ ይኖራሉ ብለን ልናምን አንችልም፡፡ የምንለው እስራኤል የሠራችው ስህተት ልክ ይኸው ነው፡፡ በእግዚአብሔርና በሌሎች አማልዕክት በማመናቸው እስራኤል እግዚአብሔርን እንዴት እንዳሳዘኑት ለማሳየት ነው ብሉይ ኪዳን በአብዛኛው የጻፈው፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናየውም አሕዛብ ዛሬ በአጋንንት እንደሚያምኑ ሁሉ ልክ እስራኤልም በሃሰተኛ ጣዖቶች ያኔ ያምኑ እንደነበር ነው፡፡

## መናፍስት ጣዖታት ናቸው

### በመጀመሪያይቱ ቆሮንቶስ ጳውሎስ ክርስቲያኖች በጣዖታትና በመሳሰሉት ለምን ማመን እንደሌለባቸው ይገልጻል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን አሕዛብ መናፍስት ትናንሽ አማልዕክት አድርገው በመውሰድ በሕይወታቸው ችግሮች እንዳይመጡ በእነርሱ ያምኑ ነበር፡፡ ስለዚህም ልክ እንደጣዖታት ሁሉ የመናፍስት ልዩ ልዩ ቅርጾች በመሥራት ያምኑባቸው ነበር፡፡ ይህ ለምን ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ እየለዋወጠ አንዴ መናፍስት ሌላ ጊዜ ጣዖታት እያለ ይጠ ቀም እንደነበር ይገልጻል፡፡ «አሕዛብ የሚሰውት ለአጋንንት እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሰው እላለሁ፡፡ አጋንንትም ጋር ማህበርተኞች

እንድትሆኑ አልወድም። ማንም ግን ይህ ለጣዖት የተሰዋ ነው ብላችሁ ከዚያ ካስታወቃችሁ ከሀሊና የተነሣ አትበሉ።» 1 ቆሮ 10፡20..28/ ስለዚህ፣ ጣዖታትና አጋንንት በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው። ጳውሎስ እንዴት እነርሱ /የቆሮንቶስ ሰዎች/ «ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋንንት /ለጣዖታት/» መሥዋዕት እንዳደረጉ የገለጸውን አስተውል። አጋንንት እግዚአብሔር አልነበሩም። እኛም አንድ እግዚአብሔር ብቻ ስላለ አጋንንት በፍጹም እውነተኛ ኃይል የላቸውምና አማልክት አይደሉም።

«መቸም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ

ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ ለእኛስ

ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ

አብ አለን... ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእረሱ በኩል

የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ አለን።» /1 ቆሮ 8፡5..6/

«ለጣዖታት የተሰዋውን ሥጋ ስለመብላት ጣዖት ሆሉ በዓለም

ከንቱ እንደሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናው

ቃለን።» /1 ቆሮ 8፡4/

ወደ ብሉይ ኪዳን እንመለስም «አጋንንት»ና «ጣዖታት» ተመሳሳይ ስለመሆናቸው የበለጠ አስረጅ አለው። የግሪክ ብሉይ ኪዳን በተለይ ሁለቱን ቃላት እየለዋወጠ ተጠቅሟል።

/ዘጸግ 32:17፣ መዝ 106:37/ መዝሙረ ዳዊት 106:36..39 የእስራኤልን ስህተት የከነዓናውያንን ጣዖታት ከአጋንንት ጋር አመሳስሎታል:.. «..ለጣዖቶቻቸው ተገዙ፣ አጥመድም ሆኑባቸው ወንዶች ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሰው የወንዶች ልጆቻቸውን የሴቶች ልጆቻቸውን ደም ለጀነላን ጣዖቶች የሠውአቸውን ንፁሕ ደም አፈሰሱ።»

/መዝ 106:36..39/

## የሐዲስ ኪዳን አጋንንት

ነገር ግን «በግልጽ ስለአጋንንት የሚናገሩት የሀዲስ ኪዳን ምንባቦች ሁሉ እንዴት ነው?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። አንድ ነገር ግልጽ ማድረግ አለብን። የሁሉም የማይሳነው እግዚአብሔር ቃል ስለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ርስ በርስ አይጋጩም። እግዚአብሔር ችግሮችን ሁሉ የሚያመጣብን ስለመሆኑ የሁሉም ኃይል ምንጭ እርሱ ስለመሆኑ በግልጽ ተነግሮን ከሆነ ያው መጽሐፍ ቅዱስ ትናንሽ አማልክቱ.. አጋንንት..እግዚአብሔርን በመቃወም በእኛ ላይ እነዚህን ነገሮች ያመጡብናል ብለን ደግሞ ማመን አንችልም። በብሉይ ኪዳን «አጋንንት» የሚለው ቃል የጣዖት አምልኮን በመግለጽ አራት ጊዜ ብቻ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። በወንጌል ግን ብዙ ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። የዚህ ምክንያቱ ወንጌል በተጻፈበት ዘመን ማንኛውም ያልታወቀ በሽታ በአጋንንት ስህተት ነው የሚፈጠረው ብሎ መቀበሉ የወቅቱ ቋንቋ ስለነበረ ነው የሚል አስተሳሰብ አለ። በእርግጥ አጋንንት ካሉና ለችግሮቻችንና ለህመሞቻችን ተጠያቂ ከነበሩ በብሉይ ኪዳን

**ላይ ስለእነርሱ ብዙ ቦታዎች ላይ ተጽፈው ማግኘት ነበረብን፡፡ ሆኖም ይህን በተመለከተ በፍጹም ምንም አልተጻፈም፡፡**

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩት አሕዛብ ያልተረዱዋቸውን ነገሮች ሁሉ አጋንንት ብለው በጠሯቸው ሃሳባዊ ፍጥረታት እንደሚፈጠሩ ያሳብቡ ነበር፡፡ በህክምና ዕውቀት ደረጃዎቻቸው ሊረዷቸው የከበዷችውን የአዕምሮ ህመሞች ሁሉ አጋንንት ከአደረባአቸው ጋር አቆራኝተው አሕዛብ እዲቀበሏቸው አድርጓል፡፡ በብሉይ ኪዳን ጊዜያት ክፉት ወይም ያዳደፈ መንፈስ ያስከተለው የተረበሸ የአዕምሮ ሁኔታ እየተደረገ ይወሰድ ነበር፡፡/ይሁ 9፡23፣ 1 ሣሙ 16፡14 18፡10/፡፡ በሀዲስ ኪዳን ጊዜያት የክፉ መንፈስ /አጋንንት መለከፍ/ ቋንቋ በአዕምሮ ህመም የሚሰቃዩትን እየገለጸ መጥቶ እንደነበረ ይስተዋላል፡፡
በአጋንንተና በህመም መካከል ያለው ተዛምዶ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> «... አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎቹን ወደእርሱ /ኢየሱስ/ አመጡ በነቢዩ በኢሳያስ እርሱ ድካማችንን ተቀበለ፡፡ ህመማችንንም ተሸከመ
> የተባለው ይፈጸም ዘንድ መናፍስትን በቃሉ አወጣ፡፡ የታመሙትንም
> ሁሉ ፈወሰ፡፡» /ማቴ 8፡16..17/

ስለዚህ፣ የሰው ድካሞችና ህመሞች «በአጋንንት»ና በክፉ መናፍስት ከመያዝ ጋር አንድ ናቸው፡፡ ሲድኑ ደግሞ በአጋንንት ከተለከፉበት ወደ ትክክለኛ አዕምሮ ተመለሱ ይባላል፡፡ /ማር 5፡15፣ሉቃ 8፡35/፡፡ ይህ በአጋንንት መለከፍ ማለት አዕምሮው ደህና አለመሆኑን መግለጽ ነው፡፡ እነዚያ አጋንንት ያደረባቸው ተፈወሱ ወይም ዳኑ የሚለው የሚያሳየው በአጋንንት መያዝ ሌላው የህመም መግለጫ መንገድ መሆኑን ነው፡፡ /ማቴ 4፡24፣ 12፡12፣ 17፡18/

# ጥናት 6 ጥያቄዎች

1. ለችግሮቻችንና ለፈተናዎቻችን የመጨረሻው ኃላፊነት ያለበት /ተጠ ያቂ/ ማነው?

ሀ/ እግዚአብሔር

ለ/ ዕድል

ሐ/ ሰይጣን የተባለው ኃጢአተኛ ፍጡር

መ/ አጋንንት የሚባሉት ኃጢአተኛ ፍጥረታት

በኃጢአት ለሚደርስብን ፈተና ምንድነው ተጠያቂው .2
ምክንያት?

ሀ/ የእኛው የራሳችን ሰብአዊ ተፈጥሮአችን

ለ/ እግዚአብሔር

ሐ/ ክፉ መናፍስት

መ/ ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው ኃጢአተኛ
ፍጡር

3/ በቃልነቱ የ«ዲያብሎስ» ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ/ ኃጢአት

ለ/ እባቢ

ሐ/ የሀሰት ከሳሽ

መ/ ሉሲፈር

4/ በቃልነቱ የ«ሰይጣን» ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ/ ኃጢአተኛ

ለ/ አስፈሪ አውሬ

ሐ/ ጠላት ወይም ተቀናቃኝ

መ/ የአጋንንት ንጉሥ

5/ «ሰይጣን» እና «ዲያብሎስ» በዘይቤ ምንን ያመለክታሉ?

ሀ/ ኃጢአትና ፈተናን

ለ/ በውጫዊው ህዋ ያሉትን ክፉ ኃይሎች

ሐ/ ድራጎን

# 7. የኢየሱስ ባህርይ

# 7.1 ስለኢየሱስ የብሉይ ኪዳን ትንቢት

በጥናት 3 ላይ የእግዚአብሔር ድኅነት ዓላማ በኢየሱስ ክርስቶስ ዙሪያ የሚያጠነጥን መሆኑ ተገልጿል። ለሄዋን፣ ለአብርሃምና ለዳዊት እግዚአብሔር የገባላቸው ቃል ኪዳኖች ኢየሱስ ከእነርሱ ቀጥተኛ ዘር እንደሚሆን ነበር። በእውነቱ ብሉይ ኪዳን ከሞላ ጎደል በሁሉም የሚያመለክተውና የሚተነበየው ስለክርስቶስ ነው። ከክርስቶስ በፊት እስራኤል እንድትጠብቀው የተሰጣት የሙሴ ህግ ስለኢየሱስ ነበር። «እንደዚህ በዕምነት እንፀድቅ ዘንድ ሕግ ወደክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል።» /ገላ 3:24/። ስለዚህም ፍጹም በሆነ ሁኔታ አንድ ጠቦት በፋሲካ በዓል መገደል ነበረበት። /ዘፀዓት 12:3..6/ ይህ የኢየሱስን መስዋዕትነት ያመላክታል። «..የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ይለዋል። /ዮሐ 1:29/። የእንስሳት መስዋዕትነት የአስፈለገበት ሁኔታም ወደፊት የሚያመላክተውን የኢየሱስን ፍጹምነት ነው። /ጴጥ 1:10/

መዝሙረ ዳዊትና የብሉይ ኪዳን ነቢያት በሙሉ መሲሁ ምን እንደሚመስል ቁጥር ስፍር የሌላቸው ትንበያዎች ጽፈዋል። በተለይ ትኩረት የሰጡትም እንዴት እንደሚሞት ነበር። ስለሚሞተው የመሲህ ሀሳብ አይሁዳውያን አሻፈረኝ ያሉበት ብቸኛ ምክንያት ለነዚህ ትንበያዎች ትኩረት ባለመስጠታቸው ነው። ጥቆቶቹም አሁን እንደሚከተለው ተመልክተዋል።

| የብሉይ ኪዳን ትንቢት | በክርስቶስ መፈጸም |
|---|---|
| ..አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?» /መዝ 22:1/ | ..እነዚህ ኢየሱስ በመንቀል ላይ በዋለበት ጊዜ የተናገራቸው ቃላት ነበሩ። |
| ..«እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም | ..እስራኤል ኢየሱስን ናቀ /ሉቃ |

አይደለሁም የሰው ማላገጫ፣በሕዝብም ዘንድ የሚያ ፉኝ ሁሉ ያላግጥብኛል ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ በእግዚአብሔር ተማመነ እርሱንም ያድነው» /መዝ 22:6..8/

23:35/ ቀለዱበትም /ማቴ 27:39/ ራሳቸውን ነቀነቁና እንዲህም አሉ እርሱ በመስቀል ሲሰቀል /ማቴ 27:43/

..«በጉረሮዬም ምላሴ ተጠጋ:: እጆቹንና እግሪቹን ቸነከሩ» /መዝ 22:15.16/

..ክርስቶስ በመቀል ሲጠማ ተፈጸመ:: /ዮሐ19:28/ የእግሮቹንና የእጆቹን መቸንከር አካላዊ የስቅላት ዘዴውን ያመላክታል::

..«ልብሶቸን ለራሳቸው ተከፋፈሉ በቀሚ ም ለይ ዕጣ ተጣጣሉ /መዝ 22:18/

..የዚህን መፈጸም በአጭሩ በማቴዎስ ወንጌል 27:35 ይገኛል::

መዝሙረ ዳዊት 22:22 ስለኢየሱስ ንደሚያመላክት በዕብራውያን 2:12 ላይ በተለይ መጠቀሱን ልብ እንበል::

..«ለወንደሞች እንደሌላ ለእናቴ ልጆችም ከቤ እንደእንግዳ ሆንኩባቸው የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና::»/መዝ 69:8.9/

..ይህ ከአይሁዳዊ ወገኖቹና ተሰቦቹ ክርስቶስ መገለሉን የሚገልጽ ስሜት ነው:: /ዮሐ 7:3.5፣ማቴ 12:47.49 ዮሐ 2:17 ላይ ተጠቅሶአል/

..ለመብሌ ሐሞት ሰጠ ኝ፣ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠ ጡኝ /መዝ 69:21/

ክርስቶስ በመስቀል በነበረበት ጊዜ ነበር ይህ የሆነው:: /ማቴ 27:34/

በትንቢተ ኢሳያስ 53 በሙሉ የተገለጸው ስለክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እያንዳንዱ ቁጥርም ምንም ስህተት የማይታይበት መፈጸምን የሚያመላክት ነው::

ሁለት ምሣሌዎች ብቻ እንዲሁ እንይ...

..ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላዮቹም ዘንድ ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም::»/ኢሳ 53:7/

..የእግዚአብሔር ጠቦት ክርስ ቶስ በፈተናው ጊዜ ዝም ብሎ ቀረ /ማቴ 27:12..14/

..«ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረገ ከባለጠጎቹም ጋር በሞቱ../ኢሳ 53፡9/

..ከክፉ ወንጀለኞች ጎን ኢየሱ ስ ተሰቀለ፤ሆኖም በባለጠጎቹ የመቃብር ቦታ ተቀበረ፡፡ /ማቴ 27፡57..60/

የብሉይ ኪዳን «ሕግና ትንቢቶች» ስለክርስቶስ ላለን ግንዛቤ መሠረት መሆናቸውን ሐዲስ ኪዳን ቢያስታውሰን የሚያስገርም አይሆንም፡፡ /ሐዋ 26፡22፣ 28፡23 ሮሜ 1፡23፣ 16፡25..26/ «ሙሴንና ነቢያትን» በትክክል ሳልተረዳን እርሱን ልንረዳ እንደማንችል ራሱ አስጠንቅቋልና፡፡ /ሉቃ 16፡31፣ ዮሐ 5፡46..47/

የክርስቶስ ከመወለዱም በፊት በአካል ቀድሞም ነበር የሚለው የተሳሳተ ትምህርት ነው፡፡ ከልደቱ በፊት ከነበረ ከሄዋን፣ ከአብርሃምና ከዳዊት ዘር ይወለዳል የሚለው ተደጋግሞ የተገባው ቃል ትርጉም ያጣ ይሆናል፡፡ በነዚህ የቃል ኪዳኖች ጊዜ በሰማይ ከነበረ እግዚአብሔር ከእነርሱ ትውልድ መሲህ እንደሚወለድ የሰጠው ቃል ስህተት ይሆን ነበር፡፡

ክርስቶስን አስመልክቶ ለዳዊት የተሰጠው ተስፋ በተስፋ ቃሉ ጊዜ ክርስቶስ በአካል አለመኖሩን ያመለክታል፡፡ «ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሳዋለሁ፡፡ መንግሥቱንም አፀናለሁ፡፡ እኔም አባት እሆነዋለሁ፡፡ እርሱም ልጄ ይሆነኛል፡፡» ይላል /2 ሣሙ 7፡12..14/፡፡ ይህ ጥቅስ የመጭ ጊዜን የሚያመላክት መሆኑን እናስተውል፡፡ እግዚአብሔር የክርስቶስ አባት እንደሚሆን ሲገለጽ ቃል ኪዳኑ በተሠራበት ጊዜ በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ በአካል ነበረ ማለት አይቻልም፡፡ «እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይፀፀትም እንዲህ ብሎ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ፡፡» /መዝ 132፡11/

የመጀመሪያው የቃል ኪዳን ፈጻሚ ሰሎሞን ነበር፣ ሆኖም በዚህ ቃል ኪዳን ጊዜ በአካል ይኖር ስለነበር /2 ሣሙ

5፡14/ የእግዚአብሔር ልጅ የዳዊት አካላዊ ትውልድ ስለመሆኑ ዋናው የቃል ኪዳን መፈጸምን የሚያመላክተው ስለክርስቶስ ነበር፡፡ /ሉቃ 1፡31..33/ «..ለዳዊት ጻድቅ ቁጥቋጦ የማስነሰቃበት ዘመን ይመጣል፡፡» /ኤር 23፡5/ ...ይኸው መሲህ ነው፡፡

ክርስቶስን በተመለከተ ተመሳሳይ የመጭን ጊዜ የሚያሳዩ ሌሎችን ትንቢያዎች ተገልግለዋል፡፡ «..እንደአንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ፡፡» /ዘዳ 18፡18/ ሐዋሪያ የተባለው የሚለው ኢየሱስ እንደሆነ በሐዋሪያት ሥራ 3፡22..23 ተጠ ቅሰዋል፡፡ «እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ይላል /ኢሣ 7፡14/፡፡ ይህ በክርስቶስ ልደት በግልጽ ተፈጽሟል፡፡ /ማቴ 1፡23/

## 7.2 የድንግል ልደት

የክርስቶስ መጸነስና መወለድ ከዞያ በፊት በአካል ነበረ ለማለት አያስከለደንም፡፡ ስለሥላሴ የተሳሳተ ትምህርት ያላቸው በአንድ ወቅት ሦስት በሰማዕት ነበሩ ከእነርሱም አንዱ ጠፋና ሁለቱን በሰማዕቱ ትቶ በማርያም ማህፀን ተፀነሰ የሚል ድምዳሜ ይሰጣሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እምዳየነው በዓለም ያለ ፍጡር /ነገር/ ሁሉ አካላዊ ቅርጽ የያዘ ነው፡፡
ስለዚህ ከቅድመ ሕይወት /መኖር/ ጽንሰ ሃሳብ ስንነሳ ክርስቶስ በሆነ መንገድ ከሰማዕት ወርዶ ከድንግል ማርያም ማሕፀን ውስጥ ገባ እያልን ነው፡፡ ይህ ውስብስብ የመጽሐፍ ትምህርት ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በጣም የወጣ ነው፡፡ የክርስቶስ መነሻ በምንም ምክንያት ብናስበው በአካል ሰማዕትን ትቶ ድንግል ማርያም ማሕፀን ገባ ለማለሐት አያስኬደንም፡፡ በሥላሴ ትምህርት ለዚህ ማሥረጃ አለመኖሩ ዋናው ጉድለት ነው፡፡

መልዓኩ ገብርኤል ለማርያም ተገልጾ ያስተላለፈው መልዕክት ስናይ
«..እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ
ይሠትይዋለሽ እርሱ ታላቅ ነው፤ የልዑል ልጅም ይባላል።
ማርያምም መልዐኩን ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?
/ድንግል ስለነበረች/ አለችው። መልዐኩም መልሶ እንዲህ አላት
መንፈስ ቅዱስም ባንቺ ላይ ይመጣል የልዑል ኃይል ይፀልልሻል።
ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ
ይባላል።» /ሉቃ 1፡31..35/ የሚል እናነባለን።

ኢየሱስ ሲወለድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሁለቴ ተሠምሮበታል። ይህም የሚያስረዳው የእግዚአብሔር ልጅ ከልደቱ በፊት አለመኖሩን ነው። እንደገና ብዙዎቹ ዐረፍተ ነገሮች የመጭ ጊዜን የሚያመለክቱ መሆናቸው መስተዋል አለበት ለምሣሌ «እርሱ ታላቅ ይሆናል» የሚለውን ስናይ ቀድሞ ከነበረ ቀድሞውንም ታላቅ ነበረ ማለት ይሆን ነበር። ኢየሱስ የዳዊት ዘር ነበር። /ራዕይ 22፡16/ «ጄኔስ» የሚለው የግሪክ ቃል ኢየሱስ ከዳዊት ትውልድ የሚሆን መሆኑን ይጠቁማል።

## የኢየሱስ መፀነስ

መንፈስ ቅዱስ /የእግዚአብሔር እስትንፋስ/ኃይል/ በእርሷ ላይ በማደሩ እመቤታችን ማርያም ያለዘርዓ ብዕሲ ኢየሱስን ለመጸነስ በቅታለች። ስለዚህ ዮሴፍ የኢየሱስ እውነተኛ አባቱ አልነበረም። መንፈስ ቅዱስ ሰው አለመሆኑ /በጥናት ሁለት/ ልንረዳ ይገባል። በድንግል ማርያም ላይ

የእግዚአብሔር መንፈስ አድሮ «እናም እግዚአብሔር አንዲያ ልጁ ከእነርሱ የተወለደ «የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎም ተጠራ /ሉቃ 1፡35/

ኢየሱስ በድንግል ማርያም ማህፀን «ተፀንሶ» ነበር /ሉቃ 1፡31/ የሚለው እርሱ ከዚያ ጊዜ በፊት በአካል ሊኖር እንደማይችል ያስረዳል፡፡ ሃሳብ ካረገዝን /በውስጣችን ከያዝን/ በእኛ ውስጥ ይጀምራል፡፡ እንደዚሁም ኢየሱስ በማርያም ማህፀን ተጸነሰ፡፡ እንደማንኛውም የሰው ፍጡር ሁሉ ሽሉ በማሕፀኗ ተጀመረ፡፡ በዮሐንስ 3፡16 በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በጣም የታወቀው ቁጥር እግዚአብሔር «አንድያ ልጁን ኢየሱስን ወለደ» ብሎ መዝግቧል፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ይህን የሚጠቅሱ ሰዎች ምንም ማለት እንደሆነ በሚገባ በጥልቀት ተረድተው ለማስረዳት ይቸገራሉ፡፡ እግዚአብሔር /እንደአባቱ/ ኢየሱስን ወለደ ካልን አባቱ ከልጁ በዕድሜ የገፋ ነው፣ ማለታችንና እግዚአብሔርም መነሻ የለውም ካልን ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም ማለታችን ነው፡፡

እግዚአብሔር አዳምን በመጀመሪያ እንደፈጠረ ሳይሆን እግዚአብሔር ኢየሱስን አባት ሆኖ ወለደው ማለታችን የሚስተዋል ነው፡፡ እግዚአብሔር ከኢየሱስ ጋር ያለውን የዝምድና ቅርበት ይህ የሚቀጥለው ጥቅስ ይገልጸዋል፡፡ «እግዚአብሔርም በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከእርሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፡፡» /2 ቆሮ 5፡19/ ከዐፈር የተፈጠረ ሳይሆን ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የተወለደ በመሆኑ የእግዚአብሔርን የአባቱን መንገዶች የተፈጥሮ ችሎታው አድርጎ ይዟል፡፡

የዓለም ብርሃን ክርስቶስን በተመለከተ የኢሣያስ ትንቢት 49፡5..6፣ ትንቢቱ መፈጸሙን ደግሞ በዮሐንስ 8፡12 ላይ ተጽፎአል፡፡ በመንፈስ ቅዱሱ ኃይል አማካይነት በድንግል ማርያም ማሕፀን ክርስቶስ ስለዚህ ተመሥርቷል፡፡ የክርስቶስ አካላዊ ውጥን በድንግል ማሕፀን በእርግጥ ነው ማለት ነው፡፡

በጥናት 7.1 ላይ እንዳየነው መዝሙረ ዳዊት 22 ላይ በመስቀል እንዳለ ክርስቶስ ያሰባቸውን በትንቢት ይናገራል። ስለእግዚአብሔር «...አንተ ግን ከሆድ አውጥተኸኛልና በእናቴ ጡት ሳለሁም በአንተ ታመንሁ ከማህፀን ጀምሮ በአንተ ላይ ተጣልኩ። ከእናቴ ሆድ ጀምረህ አንተ አምላኬ ነህ።» /መዝ 22፡9..10/ ሲል ዳዊት አንፀባርቋል። በሚሞትባትም ሰዓት ክርስቶስ ወደመሠረተ አመጣጡ ማለትም በእግዚአብሔር ኃይል ወደተመሠረተው ወደ እናቱ ድንግል ማርያም ማህፀን ዙሮ ተመልክቷል። በወንጌል የክርስቶስ እናት ስለሆነችው ስለድንግል የተገለጸው በራሱ ከድንግል ከመወለዱ በፊት ነበረ የሚለውን አስተሳሰብ ይሠርዘዋል። ድንግል እንደማንኛውም ሰው እንደነበረችና በዚያም ተራውን ሰው መጥምቁ ዮሐንስን የወለደችው አክስት እንደነበረች እርግጥ ነው። ድንግል ማርያም እንደማንኛውም ተራ ሰው የሰው ፍጡር አልነበረችም የሚለው የሮማን ካቶሊክ ሃሳብ የሚነግው ከተራ ሰው ክርስቶስ የሰው ልጅና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሊመጣ አይችልም ከሚል የተሣሣተ እምነት ነው።

ክርስቶስ ከሰው ፍጡር እናቱ በመወለዱ የሰው ልጅ ሲያሰኘው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር በድንግል ማህፀን እንዲፀነስ በማድረጉ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ያሰኘዋል። /ሉቃ 1፡35/ ትርጉም እግዚአብሔር አባቱ ነበር ማለት ነው።

> «...ከእርኩስ ነገር ንፁሕ ሊያወጣ ማን ይችላል? አንድ እንኳ
> የሚችል የለም ንፁሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድነው? ፃድቅስ
> ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድነው?»/ኢዮ 14፡4፣15፡14/

ድንግል ማርያም «ከሴት የተወለደች» ወላጆቿም ተራ ሰዎች የሆኑ በሰው ያሉ ሁሉ ባህርይ ያላቸው ናቸው። ከሴት

በመወለዱም የሰው ባህርያት ወደኢየሱስ የተላለፈ ነው፡፡ /ገላ 4፡4/

ወንጌል ደጋግሞ የድንግል ማርያምን ሰውነት ያመላክታል፡፡ ክርስቶስ ድንግልን ሦስት ጊዜያት ስለመንፈሳዊ አስተሳሰብ እጦት ቆጣ እያለ ተናግሯታል፡፡ /ሉቃ 2፡49፣ ዮሐ 2፡4/፡፡ የሚላቸውን ነገሮች ሁሉ ለመረዳት ይሳናትም ነበር፡፡ /ሉቃ 2፡50/፡፡ ልጇ የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም ቅሉ የሰው ተፈጥሮ ካላት ሴት ደግሞ ይህ የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም፣ የሰው ተፈጥሮን የሚጋራ ቢሆንም እንኳን ቅሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነውና መንፈሳዊ አስተሳሰቡ የላቀ ጥልቀት ያለው በቀላሉ ለመረዳት ደግሞ ከባድ መሆኑ የግድ ይሆናል፡፡ ድንግል ማርያም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ዮሴፍን አግብታ ልጅ ወልዳለች፡፡ /ማቴ 1፡25/

በማቴዎስ ወንጌል 12፡46.47 «ስለእናቱና ወንድሞቹ» የተጠቀሰው ማርያም ከኢየሱስ በኋላ ሌሎች ልጆች እንደነበሯት የሚጠቁም ነው፡፡ ኢየሱስ የመጀመሪያ ልጇ ነበር፡፡ ማርያም ድንግል እንደሆነች ቀርታለች ከዚያም ወደ ሰማዕት አርጋለች የሚለው የካቶሊኮችና የኦርቶዶክሶች ትምህርት ፈጽሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ የሌለው ነው፡፡ እንደሰው የሚችነት ባህርይ ሁሉ ስለነበራት ድንግል ማርያምም እንደሰው በዕድሜ መግፋት ከዚያም መሞት በነረባት፡፡ ከዚህም ሌላ በዮሐንስ ወንጌል 3፡13 «ወደሰማይ ተወጣ ማንም የለም፡፡» /ዮሐ 3፡13/ ማለቱን አንርሳ፡፡ ክርስቶስ የሰው ተፈጥሮ አለው ስንል ከእናቱ በኩል ማለታችን ነው እንጂ ከአባቱ ከእግዚአብሔር ማለታችን አይደለም፡፡ /እብራ 2፡14..18፣ ሮሜ 8፡3 ይመልከቱ/

## 7.3 በእግዚአብሔር ዕቅድ የክርስቶስ ሥፍራ

ፍጥረት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር የተሟላ ዕቅድ አስቀምጧል። /ዮሐ 1፡1/ ልጅ ይኖረው ዘንድ ፍላጎቱ ከመጀመሪያውም የነበረው ዕቅድ ነው። ሙሉ በሙሉ ብሉይ ኪዳን ስለተለያዩ የድኅነት ዕቅዶች በክርስቶስ እንደነበረው እግዚአብሔር ገልጿል። እግዚአብሔር ልጅ እንዲኖረው ያደረገው በጥበቡ ዓለምን በፈጠረበትጊዜ ነው። /ዕብራ 1፡1..2/ የሰው ልጅ የዓመታት ታሪክ በክርስተቶስ ተጀምሮ የተጠቃለለ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ከመጀመሪያውም ያቀደው ነበር /ዕብ1፡2/። ለዓመታት የእግዚአብሔር መኖር ለሰው ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ለመሆኑና ይህም ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ አማካይነት /የሚመለከት/ ስለመሆኑ በብሉይ ኪዳን ተመዝግቦ ይገኛል።

የክርስቶስን ታላቅነት፣ ግዙፍና መሠረታዊነት ለእግዚአብሔር ያለውን ቦታም አጠቃልሎ ለመረዳት በጣም ያስቸግረናል። ስለሆነም ምንም እንኳን በአካል ከእመቤታችን የተወለደው ቆይቶ ቢሆንም ክርስቶስ በእግዚአብሔር አዕምሮና ዕቅድ ውስጥ ከመጀመሪያው ጀምሮ ነበረ ማለት ትክክል ይሆናል። እብራውያን 1፡4..7 13፣14፣ ክርስቶስ መልአክ እንዳልነበረ፣ በሚችነት ሕይወቱም ከመላዕክት ያነሰ መሆኑን /እብ 2፡7/ ሆኖም የእግዚአብሔር «አንድያ ልጁ» በመሆኑ ከመላዕክት እጅግ የላቀ ክብርና ሞገስ ያለው ነው /ዮሐ 3፡16/። ክርስቶስ እንደሁሉም ሰው ከመወለዱ በፊት በመንፈስም አልነበረም። «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ ስለእናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ።» /1 ጴጥ 1፡20/

ኢየሱስ ለወንጌል መሠረትነና ማዕከል ነው። «በነቢያት አፍ በቅዱሰሳን መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ለተሰጠው ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ። ይህም ወንጌል በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ እንደቅድስናው መንፈስ ግን ከሙታን መነሣት

የተነሣ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለተገለጠው ስለልጁ ነው።»
/ሮሜ 1፡1..4/

ይህ የክርስቶስን ታሪክ ያጠቃልላል። ይኸውም...

1/ በብሉይ ኪዳን ተስፋ ተሰጠ..ማለትም በእግዚአብሔር ዕቅድ ነበረ
2/ የዳዊት ዘር ሆኖ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በአካል ሰው ሆኖ ተፈጠረ።
3/ ፍጹም በሆነው ባህርይ /በቅዱስ መንፈሱ/ የሚችነት ሕይወቱ ታየ።
4/ ትንሳዔ አደረገ። እናም እንደገና በመንፈሳዊነት በተሞሉት ሐዋርያቱ ስብከት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በዓለም ሕዝብ ፊት ታወጀ።

## የእግዚአብሔር የቅድሚያ ዕውቀት

እግዚአብሔር ወደፊት ስለሚመጡት /ስለሚደረጉት/ ነገሮች ሁሉ በቅድሚያ ያውቃል። ስለሆነም ስለወደፊቱ ዕቅድ አውጥቷል። ፍጹም የሆነ የቅድሚያ ዕውቀት አለውና። እግዚአብሔር ስለሌሉ ነገሮች እንዳሉ አድርጎ መናገርና ማሰብ ይችላል። ስለወደፊት እፍዚአብሔር ያለው ዕውቀት ፍጹም ነው። እግዚአብሔር «የሌሉትን ነገሮች እንዳሉ ሁሉ ይጠራቸዋል።» /ሮሜ 4:17/ ስለሆነም እግዚአብሔር «በመጀመሪያ መጨረሻውም ከጥንትም ያልተደረገውን እነግራለሁ። ምክሬ ትፀናለች ፈቃዴንም ሁሉ እፈጽማለሁ እላለሁ።» ሲል ያውጃል። /ኢሣ 46፡10/። በዚህም ምንክያትእግዚአብሔር የሞቱትን በሕይወት እንዳሉና ከልደታቸው በፊት ሰዎች በሕይወት እንዳሉ አድርጎ መናገር ይችላል።

ከመጀመሪያውም ክርስቶስን የእግዚአብሔር ቃል በትንቦት ተናግሮታል። ክርስቶስ ሁልጊዜም በሃሳብ፣

በዓላማው እንደነበረ ነውአአ። በእርግጥም በአንድ ወቅት ክርስቶስ በአካልም እንደሚወለድ እንዲሁ ከመጀመሪያው ዕቅዱ ውስጥ ይዞት የነበረ ስለመሆኑ በመጽሐፍ ተጽፏል። በክርስቶስ ያስቀመጠውን ዕቅድ እግዚአብሔር አሚልቷል። የእግዚአብሔር የቅድሚያ ዕውቀት እርግጠኝነት ማረጋገጫው በቃሉ መጠበቅና መፈፀም ይንፀባረቃል። ስለዚህም ዳዊት እንዲህ ብሏል። «ይህ የእግዚአብሔር ቤት ነው።» /1 መ ዜና 22፡1/ ይህን ያለው ግን ገና የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሳይሰራ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል እንደተሰጠ ነበር። ዳዊት በዕምነቱ ከብቃቱ የተነሣ ስለወደፊቱ አሁን እንዳለ አድርጎ የሚገልጸውም ለዚህ ነበር። ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ እንደሚያሟላ እግዚአብሔር እርግጠኛ ነበርና እንዲህ ብሎታል። «ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቻለሁ።» /ዘፍ 15፡18/ ይህም አብርሃም ገና ዘር እንኳን ሳይኖረው ነበር። ዘሩ /ይስሐቅ/ ክርስቶስ ከመወለዱ በፊትም እግዚአብሔር በተጨማሪም እንዲህ የሚል የተስፋ ቃል ሰጥቷል። «ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁ» /ዘፍ 17፡5/ ከዚህ አኳያ በዚያን ጊዜ ሁኔታው እንደዚያ ባይሆንም ክርስቶስ ባስተማረበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት «ሁሉንም በእጁ /በክርስቶስ/ እንደሰጠ» ተናግሯል። /ዮሐ 3፡35/

> «…ሁሉን ከእርሱ /ከክርስቶስ/ በታች ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም።» /ዕብ 2፡8/

እግዞአብሔር በኢየሱስ አማካይነት ስለድኅነት ዕቅዱ «ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ ተናገረ።» /ሉቃ 1፡70/ ምክንያቱም እነርሱ ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር የቀረበ ትስስር ነበራቸውና እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያውም በዚያን ጊዜ በእርግጥ በአካል ባይኖሩም እንደነበሩ ተደርጎ ተነግሯል። ይልቁንም ነቢያት ከመጀመሪያውም በእግዚአብሔር ሀሳብና ዕቅድ ውስጥ ነበረ ለማለት እንችላለን። ኤርምያስ ተጨባጭ ምሣሌ ነው። ለነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ነገረው። «በሆድ ሳልሠራህ

ዐውቄሃለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።» /ኤር 1፡5/
ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር ስለኤርምያስ ከመፈጠሩ በፊት ሁሉን ነገር ማወቁን ነው። ስለፋርስ ንጉስ ሳይሩስም እንዲሁ ስለሌላ ሰው የተገለጸው ጥሩ አሥረጂ ምሣሌ ነው።

ስለእውነተኛ አማኞችም በአካል ሳይኖር በእግዚአብሔር አዕምሮ እንዳሉ ተናግሮዋል። «... ያዳነን በቅዱስም አጠራሩ የጠራን እግዚአብሔር ነውና ይህም እንደራሱ ሃሳብና ፀጋ መጠን ነው እንጂ እንደሥራችን መጠን አይደለም። ይህም ፀጋ ከዘለዓለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ የሰጠን» /2 ጢሞ 1፡9/። «...ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱስንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ ክርስቶስ መረጠን በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነ።» /ኤፌ 1፡4..5/ ግለሰቦች ከመጀመሪያው በአካል ከመወለዳቸው በፊት በእግዚአብሔር በቅድሚያ ታውቀው ለድኅነት ተለይተው ይያዛሉ የሚለው ሃሳብ ግለሰቦች ከመጀመሪያውም በእግዚአብሔር አዕምሮ /ሃሳብ/ ውስጥ ነሆናቸውን የሚያመላክት ነው። /ሮሜ 8፡27፣ 9፡23/

በዚህ ሁሉ ምክንያት የእግዚአብሔር የፍጥረት ምክያት ማዕከልና ማጠቃለያ ስለሆነው ስለክርስቶስ በአካል ከመወለዱ በፊት በእግዚአብሔር ሐሳብና እቅድ ውስጥ ከመጀመሪያ የነበረ ስለመሆኑ ሀቅ ስንናገር ልንጠራጠርም ሆነ ልንገረም አይገባም።

«..ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት /ክርስቶስ/ ነበር ሲል /ራዕይ 13፡8/ የተመለከተው ቀጥተኛ ትርጉሙ ከጊዜ አንፃር ሲታይ አያስኬድም። ኢየሱስ ያኔ አልሞተም ነበርና። እረሱ «የእግዚአብሔር በግ» በመስቀል የተሰቀለው ከ4000 ዓመታት በኋላ ነበር። /ዮሐ 1፡29፣ 1 ቆሮ 5፡7/። በተመሳሳይ መንገድ ክርስቶስ ከመጀመሪያ እንደተመረጠ ሁሉ /1ጴጥ 1፡20/ አማኞችም እንዲሁ ተመርጠ ዋል። /ኤፌ 1፡4/ 4/ ይህን ለመረዳት በሰውነታችን ያለብን

የመረዳት ችግር ከጊዜ ዕንሰ ሃሳብ ውጭ እግዚአብሔር እንዴት እምደሚሠራ ለማወቅ ካለን የዕውቀት ውሱንነት የሚመነጭ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር አመለካከት አኳያ ከግዜ ዕንሰ ሀሳብ ውጭ /ያለ ጊዜ ዕንሰ.ሐሳብ/ ነገሮችን ለማየት ያለው የሰው ችሎታ «እምነት» ብቻ ይሆናል፡፡

## 7.4 «በመጀመሪያ ቃል ነበር» የዮሐንስ ወንጌል 1፡1.3

«... በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ፡፡ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡» /1 ዮሐ 1፡1..3/

ይህ ጥቅስ ክርስቶስ ከልደቱ በፊት በሰማያት እንደነበረ አድርጎ ለማስተማር በስፋት የሚጠቀስ ለተሳሳተ ግንዛቤ አንዱ ዋነኛ ምንባብ ሆኗል፡፡ የዚህን ጥቅስ ትክክለኛ ትርጉም ለመረዳት «ቃል» የተባለው ሰውን በቀጥታ አለማመልከቱን ማየት ያስፈልጋል፡፡ ይኸውም ሰው በአንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋርና እግዚአብሔርም መሆን አይችልምና፡፡ «ቃል» በራሱ «ኢየሱስ» ማለት አይደለም፡፡

### «በመጀመሪያ»

የእግዚአብሔር መንፈስ ውስጣዊ አስተሳሰቡን ወደተግባር እንዴት እንደሚያመጣቸው ማለትም በመንፈሱና በቃሉ መካከል ያለውን ግንኙነት በክፍል 2.2 ላይ አሳይተናል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሰዎች ጋር ያለውን ዕቅድ ከመጀመሪያውም በጽሑፍ የሰፈረውን ቃልም በመንፈስ እንደሞላው የሚያሳየው የክርስቶስን አሠራርና ቃልን ሲያገናኝ ነው፡፡

ክርስቶስ የእግዚአብሔር /ሎጎስ የሚለው የግሪክ ቃል ትርጉሙ ሌሎች ውስጣዊ አስተሳሰብ በውጫዊ ቃላትና ኮሚኒኬሽኖችን ነው/ «ሎጎስ» ነበርና የእግዚአብሔር መንፈስ ስለክርስቶስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ከሁሉም አሠራሮች ጋር ገልጿል፡፡ ለዚህም ነው በብዙዎች የብሉይ ኪዳን ስለክርስቶስ በሰፊው ያሰፈሩት፡፡ ለማንኛውም ክርስቶስ በሰውነቱ «ቃል» እንዳልነበረ በጣም መጋነን የለበትም፡፡ ይልቁንም በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔር የድኅነት ዕቅድ ይኸውም «ቃል» ነበረ ማለት ነው፡፡ «ሎጎስ» /«ቃል»/ የሚለውን ወንጌለ ክርስቶስን በተመለከተ ብዙ ቦታ ላይ ተጠቅመዋል፡፡ ለምሣሌም «የክርስቶስ ቃል» /ማተ 13፡19 ፣ዮሐ 5፡24፣ የሐዋ 19፡10፣ ተሰሎ 1፡18 ወዘተ/ ክርስቶስ ሲወለድ ቃል ወደ ሥጋና ደም ተለወጠ .. «ቃልም ሥጋ ሆነ» /ዮሐ 1፡14/፡፡ ኢየሱስ በሰውነቱ «ቃል ሥጋ ሆነ» ቃል በመሆን ፋንታ እርሱ በሰውነቱ በሌላ ቀደም ባለ ጊዜ ሳይሆን ከድንግል ማርያም በተወለደበት ጊዜ «ቃል» ሆነ፡፡

ስለክርስቶስ የእግዚአብሔር ዕቅዱ ወይም መልዕክቱ ከመጀመሪያውም ነበረ፤ ሆኖም በግልጽ የታየው በክርሰቶስ ሰው መሆንና በመጀመሪያው መቶኛ ዘመን ስለእርሱ ወንጌል መሰበኩ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ፣ በክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔር ቃሉን ተናገረ፡፡ /ዕብ 1፡1..2/ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ቃሎች መናገሩንና እግዚአብሔርን ለእኛ ለመግለጽ ሲል በእግዚአብሔር የትዕዛዝ ቃል ያምራት አድርጓል፡፡ /ዮሐ 2፡22፣3፡34፣7፡16፣10፡32 38፣14፡10..24/ የክርስቶስ ወንጌልን «ለሁሉም ዓለም» ለመስበክ ጳውሎስ የክርስቶስን ትዕዛዝ ተቀብሎ ታዘዘ፡፡ «ስለኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን የወሰነውን ተሰውሮም የነበረውን የእግዞአብሔርን ጥበብ በምስጢር እንናገራለን፡፡» /1 ቆሮ 2፡7/ ለሰው ለዘለዓለማዊ ሕይወት ሊሠራ የቻለው በክርስቶስ ሥራ አማካይነት ነው፡፡ /ዮሐ 3፡16፣ 6፡53/ ይህም ለሰው ዘላለማዊ ሕይወት የመስጠት የእግዚአብሔር ዕቅድ ከመጀመሪያው ነበር፡፡ ይኸውም ክርስቶስ የሚያደርገው መሥዋዕትነትን አስቀድሞ ያውቅ ነበርና፡፡

የዚያ የመስጠት ዕቅድ ሊገለጽ የቻለው ግን ኢየሱስ ከተወለደና ከሞተ በኋላ ብቻ ነበር።

«በዘለዓለም ሕይወት ተስፋ እንደአምልኮት ያለውን እውነት
እንዲያውቁ የተላከ ስለዚህ ሕይወት የማይዋሽ እግዚአብሔር
ከዘለዓለም ዘመናት በፊት ተስፋ ሰጠ። በዘመኑም ጊዜ መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ ለእኔ አደራ በተሰጠኝ
ስብከት ቃሉን ገለጠ።» /ጢጦስ 1:2.3/

የተናገሩበት «ቃል» ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር ስለነበረ ከዚያ ስሜት አኳያ የእግዚአብሔር ነቢያት ሁልጊዜም እንደነበሩ መነገሩን አይተናል። /ሉቃ 1:70/

ኢየሱስ ከእነዚህ ነገሮች ስለብዙዎቹ በምሣሌ እያደረገ ገልጿል። ስለሆነም ራሱን በሚመለከት ትንቢቱን አሟልቷል። «በምሣሌ አፌን እከፍታለሁ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ የተባለውም ይፈጸም ዘንድ «ማቴ 13:35/ ከዚህም ስሜት የተነሣም ነው «በመጀመሪያም ..ቃሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ «በኋላም በክርስቶስ ልደት ቃሉ ሥጋ የሆነው»።

## ቃሉ እግዚአብሔር ነበረ

አሁን «ቃሉ እግዚአብሔር ነበረ» ስንል በምን ስሜት እንደሆነ ለማብራራት የምንችልበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። እግዚአብሔር ስለክርስቶስ የነበረው ዕቅድ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊገናዘብ ይችላል። «/ሰው/ በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና» /ምሣ 23:7/ ። እግዚአብሔር እንዳለም እርሱም እንደዚሁ ነው። ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል ወይም አስትሳሰብ ራሱ እግዚአብሔር ነው። «ቃሉ እግዚአብሔር ነበረ»። በዚህም ምክንያት በእግዚአብሔርና በቃሉ መካከል ቅርብ ትስስር አለ። «...የእግዚአብሔር ድምፅ ምድር በዳውያን ያናውጣል።»

/መዝ 29፡8/ «… ለእናንተ ጉዳት እንደሆን በእጃችሁ ሥራ ታስቆጡኝ ዘንድ አልሰማችሁኝም ይላል እግዚአብሔር፡፡» /ኤር 25፡7/ የመሳሰሉት በነቢያት የተለመዱ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ማለት በቀጥታ በነቢያት የተነገሩትን የእኔን ቃላት አልሰማችሁም ማለት ነው፡፡ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቃላት እንደፋኖስና መብራት በመነወሰዱ /መዝ 119፡105/ የሚከተለውን አባባል አንፀባርቋል፡፡ «አቤቱ አንተ መብራቴ ነህና እግዚአብሔርም ጨለማውን ያጠራል፡፡» /2 ሣሙ 22፡29/ ይህም በእግዚአብሔርና በቃሉ መካከል ያለውን ተጋሪነት ለማሳየት ነው፡፡ ስለሆነም የእግዚአብሔር ቃል እንደራሱ የሰውነት አካል መልበሱ ግልጽ ይሆናል፤ ማለትም ሰው ያልሆነው ሰው እንደሆነ ተደርጎ ተገልጿል፡፡

እግዚአብሔር በራሱ እውነታ ነው /ዮሐ 3፡33፣ 8፡26፣ 1 ዮሐ 5፡10/ ከዚህም አኳያ የእግዚአብሔርም ቃል እውነታ ነው፡፡ /ዮሐ 17፡17/ በተመሳሳይ መንገድም ኢየሱስ ራሱን ከቃላቱ ጋር አቆራኝቶ ስለሚያይ ቃሉን ሰው አድርጎ ይወስደዋል፡፡ «… የሚነግረኝ ቃሌንም የማትቀበል እርሱ የሚፈርድበት አለው፡፡ እኔ የተናገርሁት እርሱ በመጨረሻው 2ቀን ይፈረድበታል፡፡» ይላል /ዮሐ 12፡48/

ኢየሱስ ቃሉ ትክክለኛ ሰው ራሱ ማለት ነው.. አድርጎ ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ እንደሰው ሰው ሆኖዋል፡.. ማለት እግዚአብሔር ራሱ /ዮሐ 1፡1..3/፡፡ ስለሆነም ቃሉን በሚመለከት «..ሁሉ በእርሱ ሆነ» /ዮሐ 1፡3/ ተብሎ ተነግሮአል፡፡ ለማንኛውም ቀደም ሲል በትዕዛዛተ ቃሉ ሁሉንም ነገሮች «እግዚአብሔር ፈጠረ» /ዘፍጥ 1፡1/ የሚለውን አይተናል፡፡ በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ተናግሮአል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የእግዚአብሔር ቃል በልባችን በመኖሩ እግዚአብሔር ለእኛ በጣም ቅርብ መሆኑን ነው፡፡

ከኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ የሆነው በክርስቶስ ሳይሆን በቃሉ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ሁሉንም ነገሮች የሠራ ቃሉ እንጂ ክርስቶስ በእርሱነቱ አለመሆኑ ተገልጿል። /ዮሐ 1:1..3/
«..በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ። ሠራዊታቸውም ሁሉ /ከዋክብት/ በአፉ እስትንፋስ እርሱ ተናገሮአልና ሆኑም። እርሱ አዘዘ። ፀኑም።» /መዝ 33:6..9/። ዛሬም ተፈጥሮአዊ ዓለም የምትሠራው በቃሉ ነው። «ነገሩን ወደ ምድር ይሰድዳል ቃሉም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል።... ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል። ነፋሱን ያነፍሳል ውሆችንም ያፈስሳል።» /መዝ 147:15..18/

የእግዚአብሔር ቃል የመፍጠር ኃይሉ በመሆኑ ከድንግል ማህፀን ለወለደው ለአንድያ ልጁ ለኢየሱስ ተጠ ቅሞበታል። ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሥራ ላይ የዋለው የእግዚአብሔር ዕቅድ የክርስቶስን መፀነስ አስመልክቷል። /ሉቃ 1:35/ ስለክርስቶስ የወደፊት መፀነስ ዜና ድንግል መልስ በሰጠችበት ጊዜ ተገንዝባ «እንደቃልህ ይሁንልኝ» ብላለች። /ሉቃ 1:38/

በብሉይ ኪዳን ሁሉ የተገለጸው ዓላማውን የሚያንፀባርቅ የእግዚአብሔር ቃል /መንፈስ/ መሆኑን አይተናል። የዚህ እውነታ በሐዋርያት ሥራ ተገልጸዋል። «..በየሰንበቱ የሚነበቡትን የነቢያትን ድምፆች /አይሁዳውያን/ ስላላወቁ በፍርዳቸው ፈጽመዋልና..» /የሐዋ 13:27/። በመንፈስ ተሞልቶ ሐዋርያው ዮሐንስ ሐዋርያቱ በተጨባጭ ሊያዩትና ሊሠሩት ስለቻሉት ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዴት በክርስቶስ እንደተገለጸ አብስሮአል። ክርስቶስን በአካል ባናየውም እኛም ስለእርሱ በሚኖረን አውነተኛ ግንዛቤ እንደምናየው ቆጥረን ልንደሰት እንችላለን። በዚህም በእኛ ያለውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በቅርብ በማወቅ ስለዘለዓለማዊ ሕይወት እርግጠኞች እንሆናለን። /1 ጴጥ 1:8.9/
በእርግጥ ክርስቶስ ዐውቀዋለሁን? የሚለውን ጥያቄ ለራሳችን ማቅረብ አለብን። ኢየሱስ የሚባል አንድ ጥሩ ሰው በአንድ ወቅት ነበር የሚለው በቂ አይደለም። በፀሎት የታጀለ መጽሐፍ ቅዱስ ተከታታይ ጥናት በማድረግ የአንተ የግል

አዳኝ እንደሆነ በማቀበልና በጥምቀትም ራስህን ከእርሱ ጋር አንድ በማድረግ እርሱን በቶሎ ለመረዳት ትችላለህ።

# ጥናት 7 ጥያቄዎች

1/ ከመወለዱ በፊት ኢየሱስ በአካል ነበርን?

ሀ/ አዎ ነበረ
ለ/ የለም አልነበረም

2/ በምን መንፈስ ነው ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ነበረ ሊባል የሚችለው?

ሀ/ እንደመልአክ
ለ/ ከሥላሴ እንደ አንዱ አካል
ሐ/ እንደመንፈስ
መ/ በእግዚአብሔር አዕምሮ /ሐሳብ/ና ዓላማ ብቻ

3/ ስለድንግል ማርያም ከሚከተሉት የትኛው ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኞቹ እውነት ናቸው?

ሀ/ ኃጢአት የሌለባት ፍጹም ሴት ነበረች
ለ/ እንደማንኛውም ሴት ነበረች
ሐ/ በመንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን እንድታረግዝ ሆነች
መ/ አሁን ፀሎታችንን ለኢየሱስ ታቀርባለች

4/ ምድርን የፈጠረ ኦየሲስ ነውን?

ሀ/ አዎ
ለ/ አይደለም

# 8. የኢየሱስ ባህርይ /ተፈጥሮ/

## 8.1 የኢየሱስ ባህርይ /ተፈጥሮ/ መግቢያ

ፍጹም በሆነው ባህርይ አማካይነት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን ድል በማድረጉ መቀበል የሚገባውን ክብርና አድናቀቆት አለማግኘቱ በክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ታላቅ ከሚባሉት አሳዘዛኝ ነገሮች አንዱ መሆን አለበት፡፡ በሰፊው በተያዘው የሥላሴ ትምህርት ኢየሱስን እግዚአብሔር ራሱን ያደርገዋል፡፡ እግዚአብሔር ሊፈተን እንደማይችል /ቶማስ 1፡13/ ና ኃጢአት የመሥራት ሁኔታውም እንደሌለ ስናይ ክርስቶስ ከኃጢአት አንፃር ጦርነት በእርግጥ አልነበረውም ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ በምድር የክርስቶስ ሕይወትና ሰብአዊ ልምዱ የሰው ልጅ አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ውጥረት አልነበረበትም፡፡ ይኸውም በግላዊ ሕይወቱ እንደሰው የኑሮ ውጣ ውረድ ተፅዕኖ አልደረሰበትምና፡፡

በሌላው አክራሪ ጫፍ ደግሞ እምደሞርሞኖችና ጀሆባዎች ያሉ ቡድኖች የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ክርስቶስን አስገራሚ ሥራውን በአግባቡ አይረዱም፡፡ አያደንቁም፡፡ መልአክ ወይም የየሴፍ ልጅ አልነበረምና፡፡ ጥቆቶች በሕይወት ዘመኑ ከመውደቁ በፊት በነበረበት ልክ እንደነበረው አዳም የተፈጥሮ ሕይወት ክርስቶስ ነበረው የሚል ሐሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ ለዚህ አስተሳሰብ የመጽሐፍ ቅዱስ አሥረጂ ካለመኖሩም በተጨማሪ አዳን ከእግዚአብሔር ከዐፈር /ከትቢያ/ የተፈጠረ ሰሆን ኢየሱስ ግን በድንግል ማርያም ማህፀን እንዲፀነስ በእግዚአብሔር ልጅነት የተፈጠረ ነው፡፡ ኢየሱስ በእርግጥ አባቱ ሰው ካለመሆኑ በስተቀር በሌሎች መንገዶች እንደሰው የተፀነሰና የተወለደ ነው፡፡ የእኛ ኃጢአተኛ

ተፈጥሮ ያለው ሰው ፍጹም ባህርይ ሊኖረው እንደሚችል ብዙ አሕዛብ አይቀበሉም። በክርስቶስ እውነተኛ እምነት እንዳይኖር መሰናክል የሆነውም ይህ ሐቅ ነው።

ኢየሱስ የእኛ ባህርይ ኖሮትም ምንጊዜም ፈተናን እያቸነፈ በባህርዩ ኃጢአት የሌለበት እንደነበር ማመኑ ቀላል አይደለም። በወንጌል ስለእረሱ ፍጹምነት ግን እግዚአብሔር ግንላ ለመሆኑ የተመዘገበውን ማንበብ መረዳት ይጠይቃል። ኢየሱስ ፍጹም ባህርይ አለው ለማለት እግዚአብሔር ራሱ ነው ብሎ ማመን ይቀላልና ያ አስተያየት ኢየሱስ ሰብአዊ ተፈጥሮን /ባህርይን/ና ኃጢአትን ድል የማድረጉን ታላቅነት ያጠፋዋል።

የሰው ተፈጥሮ ነበረው። የእያንዳንዳችንን የኃጢአትነት ባህርያት ይዞም ነበር። /ዕብራ 4:15/ ሆኖም የእግዚአብሔርን መንገዶች ለመያዝ በነበረው ቁርጠኝነትና ኃጢአትን ለማቸነፍ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ በመሻቱ በኃጢአት ላይ ድል ተጎናጽፎአል። ለዚህም እግዚአብሔር በፈቃዱ እስከመስጠት የደረሰው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከእርሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና /በልጁ አማካይነት/ ነው። /2 ቆሮ 5:19/

## 8.2 በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያሉት ልዩነቶች

«እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ነበር» በሚለው የኢየሱስን ሰውነት በሚገልጸው መካከል ያለውን ሚዛን ከመጠበቅ አኳያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉ ምንባቦች ይገኛሉ:: የኢየሱስን ሰውነት የሚገልጹት ምንባቦች ኢየሱስ እግዚአብሔር ራሱ ማለት ነው የሚለውን የተሳሳተ የሦስቱ ሥላሴ ትምህርት ሃሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደማያስኬድ የሚያደርገው ነው:: /በ325 ዓ/ም በኒኮሲያ በተደረገው የዓለም ክርስቲያናት ምክር ቤት ጉባዔ የእግዚአብሔር ሃሳብና ሥላሴ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው፤ ከዚያ በፊት በነበሩት የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያናት ፈጽሞ ግን የማይታወቀው/ :: ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም የለም:: ቀጣዩ ጥናት 9 ክርስትስ በኃጢአት ላይ ፍጹም ድል ማግኘቱንና ለዚህም የእግዚአብሔርን ሚና በበለጠ ይመለከተዋል:: እነዚህን ጥናቶች በምንጀምርበት ወቅት ድኅነት በትክክለኛና ሐቀኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እናስታውስ:: /ዮሐ 3:36፣ 6:53፣ 17:3/ 3/ ይህን ግንዛቤ በትክክል ለመጨበጣችን እርግጠኞች ከሆን ድኅነቱን ለመጋራት በእርሱ መጠበቅ እንችላለን::

በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለውን ዝምድና ከሚገልጹት ግልጽ ማጠቃለያዎች አንዱ «..አንድ እግዚአብሔር አለና በሰዉም መካከል ያለው እርሱም ሰው ሆነ ክርስቶስ ነው::» የሚለው /1ጢሞ 2:5/ ላይ የተጻፈው ነው:: እዚህ ላይ ከተጠቀሱት ቃላት በዋነኛነት ያሉት በስሩት ሲተነተኑ ወደሚቀጥሉት ማጠቃለያዎች ያደርሳሉ ...

... አንድ እግዚአብሔር ብቻ በመኖሩ ኢየሱስ እግዚአብሔር ሊሆን

አይችልም:: አብ እግዚአብሔር ከሆነ ኢየሱስም ደግሞ እግዚአብሔር

ከሆነ ሁለት እግዚአብሔሮች አሉ ማለት ነው፡፡ «...ለእርሲ የሆንን

አንድ አምላክ አብ አለን፡፡» /1 ቆሮ 8፡6/፡፡ አብ እግዚአብሔር ብቸኛ

እግዚአብሔር ነው፡፡ ለዚህም አንፃር የተሳሳተው የሥላሴ ትምህርት

የሚያውጀው ወልድ እግዚአብሔር የሚባል ልዩ አካል ሊኖር አይች

ልም፡፡ ብሉይ ኪዳን እንዲሁ አንዱ እግዚአብሔር እግዞአብሔር አብ

መሆኑን ያስተምራል፡፡ /ምሳሌ ኢሣ 63፡16፣ 64፡8/

... ከዚህ አንድ አምላክ እግዚአብሔር በተጨማሪ በሰውና በእግዚአብሔር

መካከል ያለው ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ አለ፡፡ «እንዲሁም አንድ

አስታራቂ» ከሚለው ሀረግ ውስጥ «እንዲሁም» የሚለው ቃል በእግዚ

አብሔርና በክርስቶስ መካከል ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡

... የክርስቶስ «አስታራቂ» መሆን ማለት በኃጢአተኛው በሰውና ኃጢአት

በሌለበት በእግዚአብሔር መካከል ማለት እስከሆነ ድረስ ራሱ ኃጢአት

የሌሽ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። የኃጢአተኛነት የሰው ተፈጥሮ

ያለው ግን ኃጢአት የሌለው ሰው ማለት እንጂ። «ሰው ኢየሱስ ክርስ

ቶስ የሚለው አባባል ተገለጻችንን ትክክለኛነት ያንፀባርቃል። ምንም

እንኳን ከክርስቶስ ትንሣዔ በኋላ ቢሆንም ጳውሎስ «እግዚአብሔር

ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ አልጻፈም።

እግዚአብሔር ሰው አይደለም የሚለው ቃል ብዘ3 ገዜያት እንደተገለጸ እናስታውሰሳለን። /ዘናል 23:19/ በአንፃሩ ኢየሱስ «የሰው ልጅ» ስለመሆኑ በሃዲስ ኪዳን በግልፅ ተቀምጧል። ክርስቶስ «የልዑል ልጅ» ነበር /ሉቃ 1:32/። ልዑል እግዚአብሔር መባል እርሱ ብቻ የመጨረሻ ልዕልና /የበላይነት/ እንዳለው ያረጋግጣል። ኢየሱስ ደግሞ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ መባሉ በራሱ በኢየሱስ እግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል ያሳያል። ስለእግዚአብሔርና ኢየሱስ የሚገልጸው የአባትና የልጅነት ቃል ራሱ አንድ አለመሆናቸውን ግልጽ ያደርገዋል። ምንም እንኳን ልጅ

ከአባቱ ጋር አንዳንድ የሚመሳሰልባቸው ሁኔታዎች ቢኖሩም አንድ ሰውና አንድ ዕድሜ ሊሆኑ አይችሉም።

ከዚህ አኳያም፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር ራሱ ሊሆን እንደማይችልና በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ብዙ ግልጽ ልዩነቶች መኖሩን በዝርዝርና በንጽጽር እንመልከት ...

| እግዚአብሔር | ኢየሱስ |
| --- | --- |
| ...እግዚአብሔር ሊፈተን አይችልም /ቶማ 1፡13/ | ክርስቶስ «ልክ እንደኛ ሁሉ በሁሉ አግጣጫዎች /ነጥቦች/ተፈትኗል።» /እብ 4፡15/ |
| ...እግዚአብሔር አይሞትም። በባህርይ | ክርስቶስ ለሦስት ቀናት ሞቶ ነበር |
| የማይሞት ነው። /መዝ 90፡2፣1ጢሞ | /ማቴ 12፡40፣16፡21/ |
| ...እግዘአብሔር በሰዎች ሊታይ አይችልም። | ...ሰዎች ኢየሱስን አይተውታል። |
| /1ጢሞ 6፡16፣ዘፀአት 33፡20/ | አብረውትም ኖረዋል። |
| | /1 ዮሐ 1፡1 በበለጠ ይገልጸዋል/ |

ፊቱን በሚደርስብን ሰዓት በኃጢአትና እግዚአብሔርን በመታዘዝ መካከል እንድንመርጥ እንገደዳለን፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንመርጣለን፡፡ ክርስቶስ ተመሳሳይ ምርጫዎች ነበሩት ሆኖም በእግዚአብሔር ትዕዛዛት መታመንን መርጧል፡፡ ኃጢአተኛ የመሆን አማራጭም ነበረው፤ አላደረገን እንጂ እግዚአብሔር ግን ኃጢአተኛ ተሚሆንበት መንገድ ግን ፍጹም የሚታሰብ አይደለም፡፡ የዳዊት ዘር ተብሎ በ2 ሣሙኤል 7፡12..16 ላይ ቃል የተገባለት በእርግጥ ክርስቶስ እንደነበረ አሳይተናል፡፡ ቁጥር 14 ስለክርስቶስ ለኃጢአት የነበረበትን አማራጭ «..ክፉ ነገር ቢያደርግ ሰው ሰው በሚቀጣበትና በሰው ልጆች መቀጫ እገስጸዋለሁ፡፡» ሲል ይናገራል፡፡

## 8.3 የኢየሱስ ባህርይ /ተፈጥሮ/

«ባህርይ» የሚለው ቃል በተፈጥሮ በመሠረታዊነት ማንነታችንን ያመላክታል፡፡ በጥናት 1 ላይ ሁለት ባህርያት /ተፈጥሮ/ ማለትም የእግዚአብሔርና የሰው ባህርያት እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ በባህርዩ እግዙአሕብሔር እንደማይሞት በኃጢአት እንደማይፈተን ወዘተ፡፡ ክርስቶስ ግን በሕይወት ዘመኑ የእግዚአብሔር ባህርይ እንዳልነበረው እርግጥ ነው፡፡ ከዚህ አኳያም ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ የሰው ተፈጥሮ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ከላይ ለተፈጥሮ /ባህርይ/ ከሰጠነው ትርጉም ስናየውም ክርስቶስ የሰውና የእግዚአብሔር ባህርያት በአንድነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በኃጢአት ላይ በፍጹም ድል አድራጊነት ለእኛ ይቅርታን ያስገኘልን ዘንድ ክርስቶስ መፈተኑ እጅግ ወሳኝ ነበር፡፡ /እብራ 4፡15/፡፡ ከውስጣዊ ሰብዓዊ ባህርያችን የሚነሱ የመፈተናችን መሠረት የሆኑር የተሳሳቱ ፍላጎቶቻችን ከውስጣችን የሚመጡ ናቸው፡፡ /ማር 7፡15..23/፡፡ ስለዚህም መፈታተንን ግብ ግብ ይገጥም ዘንድ ድልም ይነሣ ዘንድ ክርስቶስ ሰብዓዊ ባህርይ ሊኖረው የግድ አስፈላጊ ነበር፡፡

የዕብራውያን 2፡14..18 ይህን ሁሉ በብዙ ቃላት እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል፡፡

«...እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ

በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ

ነው፡፡ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ

የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ፡፡

የአብርሃምንም ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላዕክትን አይደለም

ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ ለእግዚአብሔር በሆነው

ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ

ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው፡፡ እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን

ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና፡፡»/ዕብ 2፡14..18/

ይህ ምንባብ ኢየሱስ ሰብዓዊ ባህርይ ያለው ስለነሆኑ ሐቅ ልዩ በሆነ አገላለጽ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ የአብርሃም ዘር ለሚሆኑ ድኅነት እንዲመጣላቸው ለሚያስፈልጋቸው እጅግ ብዙ አማኞች የአብርሃም ዘር የነበር ክርስቶስ የመላዕክት ባህርይ እንዳልነበረው እብራውያን 2፡16 በሚገባ አስቀምጦታል፡፡ በዚህም ምክንያት ክርስቶስ የሰው ባህርይ እንዲኖረው አስገላጊ ነበር፡፡ ኢየሱስ በሙሉ የሰው ተፈጥሮ /ባህርይ/ ያልነበረው አድርጎ ማሰብ የክርስቶስ ታላቅ የምሥራች /ዜና/ ምንም አለመረዳት ነው፡፡

የተጠመቁ አማኞች ኃጢአት በሠሩ ቁጥር ኃጢአታቸውን በክርስቶስ በኩል በፀሎት ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ወደእግዚአብሔር መምጣት ይችላሉ፡፡/1ዮሐ 1፡9/፡፡ ክርስቶስ ልክ እንደእነርሱ ሁሉ ለኃጢአት መፈተኑን ግን ፍጹም ስለነበር ፈተናውን ሁሉ ድል በማድረጉ በአቸናፊነት መውጣቱን እግዚአብሔር ያውቀዋል፡፡

ከዚህም የተነሣ «እግዚአብሔር ስለኢየሱስ ሲል» ይቅር ይለናል /ኤፌ 4፡32/ በባህርዩ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» /ዮሐ 4፡24/ እንዲሁም ምንም እንኳን ቁሳዊ አካል ቢኖረውም እንደ «መንፈስ» ደምና አጥንት የለውም፡፡ ክርስቶስ በአንፃሩ በሕይወት ዘመኑ «ሥጋ ለባሽ» ባህርይ ስለነበረው በምንም መንገድ የእግዚአብሔር ባህርይ አልነበረውም፡፡

ከክርስቶስ ልደት በፊት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠበቅ ማለትም ፈተናን ለማሸነፍ ያደረጉዋቸው ሙከራዎች

ሁሉ አልተሳኩም:: ስለሆነም፣ «እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና» /ሮሜ 8:3/ ይላል::

«የሞት ደመወዙ ሞት ነው::» ከዚህ ለመውጣትም ሰው የውጭ ዕርዳታ አስፈለገው:: ሰው በራሱ ፍጹም ሊሆን እንደማይችል በመቀበል:: ሥጋን ለማንፃት በሥጋ ውስጥ ሆኖ አልተቻለም:: አይቻልምም:: ስለዚህ የእኛን ኃጢአተኛ ሥጋ የለበሰውን የራሱን ልጅ በመላክ እግዚአብሔር ጣልቃ ሊገባ የግድ ሆኗል:: እንደሌሎቻችን ሰዎች ሳይሆን እንደኛ ኃጠ .አት በመሥራት ለፈተና ሊወድቅ ይችል ዘንድ የሰው ባህርይ ቢኖረውም ክርስቶስ ማንኛውንም የኃጢአት ፈተና አቸንፎ ወጥቶአል:: ሮሜ 8::3 የክርስቶስ ሰብዓዊ ባህርይ «ኃጢአተኛ ሥጋ» ሲል ይገልጸዋል:: ከዚህ ጥቂት ቁጥሮች ቀደም ብሎ ጳውሎስ በሥጋ እንዴት መልካም ነገር እንደማይገኝ»ና እንዴት ሥጋ በባህርዩ እግዚአብሔርን ከመጠበቅ አንፃር እንደሚፈታተን ተናግሮአል:: /ሮሜ 7:18..23/

በዚህም ምክንያት ሥጋንም በማቸነፉ ነበር ከሥጋችን የምናመልጥበት መንገድ ያገኘነው:: ኢየሱስ የኃጢአተኛነት ባህርዩን አሳምሮ ያው ነበር:: በአንድ ወቅት «ቸር መምህር»..ማለትም «ቸር» ና ፍጹም ባህርዩን ለመግለጽ ተብሎ በአንድ ሰው በተጠራበት ጊዜ እንዲህ ሲል መልሷል:: «ሰላምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም::» /ማር 10:17.18/ ኢየሱስ ልዩ ልዩ እጹብ ድንቅ ታምራትን ከመሥራቱም የተነሣ በሌላ ወቅት ስለክርስቶስ ታላቅነት ሰዎች ምሥክርነታቸውን መስጠት ጀምረው ነበርና ኢየሱስ በዚህ ሳይኩራራ «ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር ሰለሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና» /ዮሐ 2:23..25/ ስለሰው ባህርይ በነበረው ታላቅ ዕውቀት የራሱን ክፉ ተፈጥሮ እንዴት እንደነበር ያውቅ ነበርና ምንም ይሁን ምን ክርቶስ ሰዎች በማንነቱ እንዲያደንቁት አልፈለገም::

## የኢየሱስ ሰውነት 8.4

ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ የሰው ባህርይ እንዴት እንደነበረው በወንጌል ብዙ ምሣሌዎች ይገኛሉ:: ይደክመው

እንደነበር፣ ከምንጭ ቁጭ ብሎ ውኃ ይጠጣ እንደነበር /ዮሐ 4፡6/ ተጽፎአል። በአልዓዛር መሞት «ኢየሱስ አልቅሶአል» /ዮሐ 11፡35/። ከሁሉም በላይ በመጨረሻው የስቃይ ሰዓት ላይ የተመዘገበው የሰውነቱ በቂ ማሥረጃ ነው። በመስቀል ላይ በሞት ጥላ ሥር ከማለፍ እግዚአብሔር እንዲያድነው በፀለየበት ጊዜ «አሁን ነው ነሐፍሴ የተጨነቀች» ሲል ጭንቀት ውስጥ መውደቁን አምኖ ተናግሯል። /ዮሐ 12፡27/። «ጥቂትም ወደፊት እልፍ ብሎ ወደቀና ሲፀልይ.. አባቴ ሆይ ቢቻልስ ይህች ጽዋ /ስቃይና ሞት ከእኔ ትለፍ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።» /ማቴ 26፡39/። በአንዳንድ መንገዶች የክርስቶስ ፈቃድ ወይም ፍላጎቶች ከእግዚአብሔር የተለዩ መሆናቸውን ያመላክታል። ክርስቶስ በሕይወት ዘመኑ ይረዳው ዘንድ ፈቃዱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ መስጠቱን እንረዳለን። «..እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም እንደሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዱም ቅን ነው የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።» /ዮሐ 5፡30/ ብሏል። በክርስቶስ ፈቃድና በእግዚአብሔር ፈቃድ መካከል ያለው ልዩነት ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመሆኑ በቂ ማሥረጃ ነው።

በሕይወታችን ሁሉ ከፈተናዎቻችን እየተማርን በእግዚአብሼር ዕውቀት እንድናድግ ይጠበቅብናል። ለዚህም ኢየሱስ ታላቁ አርአያችን ነው። እየሱስም ቢሆን ስለእግዚአብሔር ፍጹም ዕውቀት ከእግዚአብሔር ከእኛ በላቀና በተለየ እንደብርሃን በአንድ ጊዜ በነ ብሎ የተገለጠለት አይደለም። ከልጅነት ዘመን ጀምሮ ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገሳም /በመንፈሳዊ ብስለት/ /ኤፌ 4፡13/ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።» /ሉቃ 2፡52/ ተብሎ ተጽፎአል። «..ህፃኑም አደገ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ የእግዚአብሔር ፀጋ በእርሱ ላይ ነበረ።» /ሉቃ 2፡40/ ይላል። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች በአንድነት የክርስቶስን አካላዊ እድገትና መንፈሳዊ ብልጽግና ያመላክታሉ። ሥላሴን በሚመለከት የአትናቴዎስ ትምህርት

**እንደሚለው ልጁ እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ ይህ ሊሆን ባልቻለ ነበር፡፡ በዘመኑ መጨረሻ ላይ እንኳን ሳይቀር ለሁለተኛ ጊዜ ተመልሶ የሚመጣበት ትክክለኛ ጊዜ ክርስቶስ አለማወቁን ግልጽ ሲያደርግ አባቱ ግን ያውቅ ነበር፡፡ /ማር 13፡32/**

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም ዝግጁ መሆንን መማር ለረዥም ጊዜያት ያለብን ነው፡፡ ማንም ልጅ እንደሚያደርገው ሁሉ ክርስቶስም ለአባቱ ታማኝነትን በመማር ሂደት ማለፍ ነበረበት፡፡ ከፍጹምና ከሙሉ መንፈሳዊ ዕድገት የተነሣ /እብራ 5፡8.9/ ላይ ኢየሱስ «...ምንም ልጅ ቢሆን ከተቀበለው መከራ መታዘዝን /ለእግዚአብሔር/ ተማረ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር /በመንፈስ መብሰል ማለት ነው/ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው፡፡ «ተብሎ ተጽፏአል፡፡ «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠጨረውም፡፡ ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ፡፡ በመሰሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ፡፡»/ፊልጶ 2፡6..8/፡፡ ከላይ በተባለው ጥቅስ ላይ ክርስቶስ እንዴትበመንፈስ እየገለጸ እንደሄደ፣ ትህትናንም እየተጎናጸፈ ሄዶ ለእግዚአብሔር ፍላጎት ታዛዥ ሆኖ ራሱን በመስጠት በመስቀል እንደሞተ እንረዳለን፡፡ በዚህም በትክክል ሳጋጠሙት ሥቃዮች ሁሉ ትክክለኛ ምላሽ በመስጠት «ፍጹም እንደተደረገ» እናያለን፡፡

በእግዚአብሔር በሆነ መንገድ እንደዚያ እንዲሆን ተገዶ ሳይሆን በአዕምሮው በግሉ አመዛዝኖ ባደረገው ጥረት ኢየሱስ ጻድቅ ሊሆን እንደቻለ ከዚህ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ኢየሱስ እኛን እጅግ በእውነት ከመውደዱ የተነሣ ነው በመስቀል ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠልን፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስን በመስቀል ለእኛ ሲል እንዲሞት አድርጎታል የምንል ከሆነ ባለማቋረጥ ክብደት የምንሰጠው ኢየሱስ ሰውን በመውደዱ ለሰው ቤዛ መስቀል ላይ ሊውል ቻለ የሚለው የመጽሐፍ አባባልና የእኛም አመለካከት የሚያስኬድ ሳይሆን ነው፡፡ /ኤፌ 5፡2..25፣ራዕይ 1፡5፣ገላ 2፡20/ ኢየሱስ እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ ፍጹም ከመሆንና በኋላም በመስቀል ላይ ከመሞት ሌላ አማራጭ ሌላ ምክንያት አይኖረውም ነበር፡፡ ኢየሱስ እነዚህ አማራጮች ነበሩት የሚለው ግን ፍቅሩን እንድናደንቅና ከእርሱም ጋር ግላዊ ግንኙነት መመሥረት እንድንችል ያደርገናል፡፡

የክርስቶስ ፈቃደኝነት በፍቃዱ ሕይወቱን መስጠቱ ነበር እግዚአብሔር በእርሱ እጅግ ደስተኛ የሆነው፡፡...«ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል፡፡ እኔ በፍቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፡፡ ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትዕዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ» /ዮሐ

10፡17..18/። ኢየሱስ እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ በክርስቶስ ፈቃድ ታማኝነት እግዚአብሔር ተደሰተ የሚለውን ለመገንዘብ ከባድ ይሆናል። /ማቴ 3፡17፣12፡18፣17፡5/

በልጁ ታማኝነት አባቱ የመደሰቱን የሚገልጹት ጽሑፎች ምንም እንኳን ክርስቶስ ከህሊናው አገናዝቦ ታማኝነትን ቢመርጥም ታማኝ ያለመሆን ምርጫም እንደነበረው የሚያመላክት በቂ ማሥረጃ ነው።

## ለድኅነት ክርስቶስ ማድረግ የነበረበት

በሰውነት ባህርዩ ኢየሱስ ቀላልም ቢሆን ህመሞች፣ ድካሞች ወዘተ ልክ እንደኛ ሁሉ አጋጥሞታል። ከዚህ አኳያ፣ ኢየሱስ በመስቀል ባይሞትም እንኳን ኖሮ በሌላ መንገድ ይሞት ነበር። ለምሣሌ በእርጅና በዚህ አመለካከት ኢየሱስ በእግዚአብሔር ከሞት ይድን ዘንድ አስፈልጎአል። ይህን በብርታት በመረዳት ኢየሱስ «በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ፀሎትንና ምልጃን አቀረበ እግዚአብሔርንም ስለመፍራቱ ተሰማለት» ይላል /ዕብራ 5፡7/ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ሞት «ወደፊት እንዳይገዛው» /ሮሜ 6፡9/ /ማለትም ያ ባይሆን ኖሮ ከዚያ ቢፊት እንድገዛው አድርጎት ነበር ማለት ነው/ አድርጓል።

መዝሙረ ዳዊት በአብዛኃኙ ስለኢየሱስ የሚተነቢይ ነው። ከነዚህም ውስጥ ጥቂት ቁጥሮች በሐዲስ ኪዳን የተጠቀሱ ስለሆኑ ሌሎች ብዙ ቁጥሮችም ስለእርሱ ናቸው ማለቱ የሚያስኬድ ነው። ብዙ ቦታዎች ላይ ለመዳን /ለድኅነት/ እግዚአብሔር ከክርስቶስ የጠበቀው /የፈለገው/ በትኩረት ተመልክቷል። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህልም...

...መዝ 91፡11..12 ስለኢየሱስ በመግተ7 4፡6 ላይ ተጠቅሶአል። መዝ.91፡16 እግዚአብሔር ለኢየሱስ ድኅነት እንዴት እንደሚሰጠው ይተነበያል። «ረጅምን ዕደሜ /ዘላለማዊ ሕይወት/ አጠግበዋለሁ፤ ማዳኔንም አሳየዋለሁ» ይላል /መዝ 91፡16/ መዝ 69፡21 ስለክርስቶስ ስቅለት ይናገራል /ማቴ 27፡34/ የመዝሙረ ዳዊት ይህ ምዕራፍ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ያሰበውን ሁሉ ይገልጻል። «እግዚአብሔር ሆይ አድነኝ... ነፍሴን ተመልክተህ ተቤዛት... አቤቱ የፊትህ መድኃኒት አምላክ ሆይ ይቀበለኝ /ያድነኝ/» /መዝ 69፡1 18 19/

...መዝ 89 ክርስቶስን በሚመለከት እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ተስፋ ያንፀባርቃል። መዝ 89፡26 ሲተነበይ «...እርሱ ወደ እኔ /እግዚአብሔር/ ለዳዊት ይጮሃል፤ አባቴ አንተ ነህ፣ አምላኬ የመድኃኒቴም መጠጊያ ይላል» ለድኅነት የክርስቶስ ፀሎቶች ተሰምተዋል። የተሰሙትም በሥላሴ ከነበረው ሥልጣን ሳይሆን በራሱ መንፈሳዊነት ነበር። /ዕብ 5፡7/ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞ ት አሥነስቶ ለዘለዓለማዊ ሕይወት ክብር መስጠቱ ዋናው የሐዲስ ኪዳን ትምህርት ነው።

...«አምላክ ..ኢየሱስን አሥነሳው.. መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ

ከፍ አደረገው። »/ሐዋ 5፡30..31/ይላል

...አምላክ...ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው... እግዚአብሔር ከሙታን

> ***ያስነሣውን ኢየሱስን*» /*ሸዋ* 3፡13..15/**
>
> **…*ይህ ኢየሱስ እግዚአብሔር ያስነሣው ነው፡፡*» /*ሐዋ* 2፡24 32 33/**
>
> **…«*ክብር ያጎናጽፈው ዘንድ ኢየሱስ እግዚአብሔርን በጠየቀበት ወቅት***
>
> ***ኢየሱስ ራሱ ይህን ሁሉ ያውቅ /ያገናዝብ/ ነበር፡፡*» /*ዮሐ* 17፡5/**

እግዚአብሔር ሊሞት እንደማይችል ሲታይ ኢየሱስ እግዚአብሔር ቢሆን ኑሮ ይህ ሁሉ አባባል ቦታ ባልነበረው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ቢሆን ኑሮ ማዳን ባላስፈለገውም ነበር፡፡ ኢየሱስን ከፍ ከፍ ያደረገው እግዚአብሔር መሆኑ እግዚአብሔር ከእርሱ በላይና የተለየ መሆኑን ያመለክተያል፡፡ ክርስቶስ የሰውነት ባህርይ እንዳለው አሳማኝ ማሥረጃ ያለው በመሆኑ ይህን ሐቅ መቀበል ይኖርብናል፡፡ በምንም መንገድ ማንም ምንም አካል ሁለት ባህርያት በአንድ ጊዜ ሊኖረው በትርጉም ስለማያስኬድ፡፡

## 8.5 የእግዚአብሔርና የኢየሱስ ተዛምዶ

**እግዚአብሔር ኢየሱስን እንዴት እንዳስነሣው ስናገናዝብ በእግዞአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደማሰብ ያመራናል፡፡ የሥላሴ ትምህርት እንደሚያስቀምጠው ግንኙነታቸው «የሁለት እኩል..የሁለት ዘለዓለማዊ» ቢሆኑ ዝምድናቸው የእኩዮች ግንኙነት እንደሚኖራቸው አድርገን**

እንጸብቅ ነበር፡፡ በእግዚአብሔርና በኢየሱስ መካከል ያለው ተዛምዶ በባልና በሚስት መካከል እንዳለው ዓይነት ነው፡፡ «..የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ የሴትም ራስ ወንድ፣ የክርስቶም ራሰ ግዚአብሔር ነው፡፡» /1 ቆሮ 11፡3/ ይላል፡፡ በባልና በሚስት መካከል ያለው የዓላማ አንድነት እንዳለ ሆኖ ባል የሚስት ራስ ነው እንዲሁ እግዚአብሼርም የክርስቶስ ራስ ነው፡፡ ስለዚህ ሚስት ለባል እንደሆነች ሁሉ «ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው» /1 ቆሮ 3፡23/፡፡ እግዚአብሔር አብ ብዙ ጊዜ የክርስቶስ አምላክ እየተባለ ተገልጿል፡፡ «እግዚአብሔር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት» ተብሎ የተገለጸበት ሐቅ ክርስቶስ ወደሰማዕት ከአረገም በኋላ እንኳን የሚያሳየው በሚችነት ዘመኑ እንደነበረው ግንኙነታቸው ሁሉ አሁንም ያው የዛምዶአቸው መኖሩን ነው፡፡ በምድር የሕይወት ዘመኑ ብቻ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ያነሰ እንደነበረ የተገለጸው ሲሉ በሥላሴ ትምህርት የሚያምኑት አንዳንድ ጊዜ ይከራከራሉ፡፡ ዳሩ ግን የሐዲስ ኪዳን ደብዳቤዎች የተጻፉት ክርስቶስ ወደሰማዕት ከአረገ ከጥቂት ዓመታት በኋላና አሁንም እግዚአብሔር የክርስቶስ አምላክና አባት እንደሆነ ይነገራል፤ ኢየሱስም እስካሁን ድረስም አባቱን እንደአምላክ ነው የሚመለከተው፡፡

በሚችነት ዘመኑም ቢሆን ኢየሱስ ከአባቱ ጋር ተመሳሳይ ግንኙነት ነው የነበረው፡፡ ስለትንሣዔዉ «ወደአባቴ ወደአባታችሁ ወደአምላካችሁ» /ዮሐ 20፡17/ ሲል ተናግሮአል፡፡ በመስቀል ላይ ሳለም ስለሰውነቱ በሙሉ ግልጽ አድርጎአል «..አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?/ማቴ 27፡46/፡፡ በእግዚአብሔር በራሱ የተነገሩ ቢሆኑ እነዚህን ቃላት ለመረዳት አይቻልም፡፡ «በከፍተኛ ጩኸትና እንባ «ኢየሱስ ወደእግዚአብሔር መጸለዩ በራሱ በሁለቱ መካከል ያለውን እውነተኛ ግንኙነት ያመለክታል፡፡ /ዕብ 5፡7፣ሉቃ 6፡12/፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ ሊፀሊይ አይችልምና፡፡ አሁንም እንኳን ኢየሱስ ስለእኛ ለእግዚአብሔር ይፀልያል፡፡ /ሮሜ 8፡26..27/ 2 ቆሮ 3፡18/

የሐዲስ ኪዳን የመጨረሻ መጽሐፍ የዮሐንስ ራዕይ ከ30 ዓመታት ከክርስቶስ ክብርና ትንሣዔ በኋላ የተጻፈ ሲሆን እግዚአብሔር «የክርስቶስ አምላክና አባት» /ራዕይ 1፡6/ እንደሆነ ይናገራል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተነፃውና ክብርን የተጎናጸፈው ክርስቶስ ለምችመናን መልዕክቶች ሰጥቷል፡፡ «..ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ አምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፡፡ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፡፡ የአምላኬም ስምና የአምላኬን ከተማ ስም ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲስቱን ኢየሩሳሌም፣ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ፡፡» /ራዕይ 3፡12/፡፡ ኢየሱስ አሁንም እንኳን አባቱን እንደአምላኩ እንደሚያየው ይህ ያረጋግጣል፡፡ በዚህም ኢየሱስ እግዚአብሔር አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

በእግዚአብሔርና በክርስቶስ መካከል ያለው ግንኙነት የሚችነት ሕይወቱ ከነበረው ዛሬ ያለው ግንኙነት የተለየ አለመሆኑን አሁን አሳይተናል፡፡ ክርስቶስ ከእግዚአብሼር ጋር ያለው ግንኙነት እንደአባት፣ እንደአምላኩ ማየቱ ለእርሱም መፀለይና አሁንም ከትንሣዔው በኋላ ያንኑ ቦታ መያዝ ነው፡፡ በምድር ዓለማዊ ሕይወቱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር፡፡ /ሐዋ 3፡13..26፣ኢሣ 42፡1/፡፡ አገልጋይ የጌታውን ፈቃድ ይፈጽማል እንጂ በምንም መንገድ ከጌታው እኩል አይደለም፡፡ /ዮሐ 13፡16/ ክርስቶስ ምንም ኃይልና ሥልጣን ይኑረው የነበረውን ያገኘው በራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መሆኑን ራሱ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ «እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለዕም፡፡ አብ ሲያደርግ ያየሁትን እንጂ እኔ/ወልድ/ ከራሴ ላደርግ ምንም አይቻለኝም፡፡» /ዮሐ 5፡30 19/

## ጥናት 8 ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሥላሴ ብሎ ያስተምራል ?
   ሀ. አዎ
   ለ. የለም።
2. ከሚከተሉት መንገዶች በየትኛው ኢየሱስ ከእኛ ይለያል።
   ሀ. ኃጢአት ምንም አለመስራቱ
   ለ. የእግዚአብሄር የአንድያ ልጁ መሆኑ
   ሠ. ኃጢአት ሊሰራ የሚችል ባህርይ የነበረው አለመሆኑ
   መ. ጻድቅ ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር መወሰኑ
3. ከሚከተሉት በየትኛው መንገድ ነበር ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የሚመሳሰለው ?
   ሀ. በምድራዊ ሕይወቱ የእግዚአብሔር በህርይን መያዙ
   ለ. እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ባህርይ መያዙ
   ሐ. እግዚአብሔር የሚያውቀውን ያህል ማወቁ
   መ. ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ እኩል መሆኑ
4. ከሚከተሉት መንገዶች በየትኛው ነበር ኢየሱስ እንደኛ የነበረው?
   ሀ. የእኛን ፈተናዎች ሰብዓዊ ተሞክሮዎች ሁሉ መያዙ
   ለ. ህፃን ልጅ በነበረበት ጊዜ ኃጢአት መሥራቱ
   ሐ. ድህነትን መሻቱ
   መ. ሰብዓዊ በህርይ መያዙ
5. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኛው ትክክል ነው?
   ሀ. ኢየሱስ ፍጹም ተፈጥሮና ፍጹም በህርይ ነበረው
   ለ. ኢየሱስ ኃጢአተኛ ተፈጥሮ ነገር ግን ፍጹም በህርይ ነበረው
   ሐ. ኢየሱስ እግዚአብሔርም ሰውም ነበር
   መ. ኢየሱስ አዳም ኃጢአት ከመሥራቱ በፊት እንደነበረው የለ ተፈጥሮ ነበረው።

# 9. ጥምቀት በኢየሱስ

# 9.1 የጥምቀት ዋናው ጥቅም

ቀደም ባሉት ጥናቶች የጥምቀትን መሠረታዊ ጥቅም ብዙ ጊዜያት ጠቅሰናል፡፡ ይህ ለወንጌል መልዕክት ታማኝነት /ዕምነት/ የመጀመሪያው እርምጃ ነውና፡፡ ዕብራ 6፡2 ከመሠረታዊ ትምህርቶች ዋናው ጥምቀት መሆኑን ይናገራል፡፡ ዕውነተኛ ጥምቀት ሊከናወን የሚችለው በወንጌል ውስጥ የተገለጸውን መሠረታዊ ሐቅ በሚገባ በመገንዘብ ስለሆነ ስለጥምቀት ጥናተ4ን እስከካሁን ደረጃ ድረስ አቆይተነዋል፡፡ አሁን እነዚህን ጥናቶች ፈጽመናል፤ ስለሆነም ስለጥምቀት ጥናቱ ቀርቦአል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ አማካይነት ስለሰጠው ታላቅ ተስፋ ጋር ራስህን በእውነት ለማዛመድ ከፈለግህ ጥምቀት ፍጹም አስፈላጊ ነው፡፡

**«...ድኅነት የአይሁዳውያን ነው፡፡» /ዮሐ 4፡22/ ይህ ድኅነትን በተመለከተ የተሰጠው ተስፋ ለአብርሃምና ለዘሩ መሆኑን የሚያመለክት ስሜት ነው፡፡ ለእኛ የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ሊኖሩን የሚችሉት የዘሩ አካል ማለትም በክርስቶስ ስንጠመቅ ብቻ ነው፡፡ /ገላ 3፡22..29/**

በዚህም ኢየሱስ ለተከታዮቹ በግልጽ «...ወደዓለም ሁሉ ሂዱና ለፍጥረታት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ/ለአብርሃም በተሰጠው ተስፋ ውስጥ ተካትቶአ. ገላ 3፡8/ የሚያምንና የሚጠመቅ ይድናልና... /ማር 16፡16/ ሲል አዝዞአል፡፡ እና «የሚለው ቃል በወንጌል በማመን ብቻ እንደማንድን ይገልጻል፡፡ ጥምቀት በክርስትና ሕይወት ተጨማሪ አማራጥ ሳይሆን ለድኅነት ዋናው አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ጥምቀት ብቻ በራሱ ያድነናል ለማለት አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ዕድሜ ማመንን /ታማኝነትን/ ከአስከተለ ነው እንጂ፡፡ ኢየሱስ ይህን በማጋነን «እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደእግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» ብሏል /ዮሐ 3፡5/

**ይህ «ከውኃ መወለድ» ከጥምቀት ውኃ አንድ ሰው መውጣት እንደሚኖርበት ይመለከታል፡፡ ከዚህ በኋላ ሰው ከመንፈስ እንደገና መወለድ አለበት፡፡ ይህ በሆደት**

የሚከናወን ነው «..እንደገና መወለድ... በእግዚአብሔር ቃል» /1 ጴጥ 1፡23/ ከመንፈስ የምንወለደው ለእግዚአብሔር ቃል ከምንሰጠው ቀጣይ ምላሽ አኳያ ነው፡፡ /ጥናት 2፡2/

«በክርስቶስ ተጠምቀናል» /ገላ 3፡27/ በስሙ /ሐዋ 19፡5፣8፡16፣ ማቴ 28፣19/ ያለጥምቀት ከክርስቶስ ጋር /በክርስቶስ ውስጥ/ አይደለንምና በአዳኝ ሥራው ውስጥ አንታቀፍም፡፡/ሐዋ 4፡12/ ጴጥሮስ በዚህ ሐቅ ዙሪያ ኃይለኛ ተምሣሌት ይሰጣል፡፡ የኖኅን መርከብ በድርስቶስ ይመስለዋል□፡፡ መርከቧ ኖኅንና ቤተሰቦቹን ከፍርድ እንዳዳነች ሁሉ በክርስቶስ ጥምቀትም ከዘላለማዊ ሞት አማኞችን ያድናል ብሏል፡፡ /1 ጴጥ 3፡21/፡፡ የኖኅ ወደመርከቧ መግባትን በጥምቀት ወደክርስቶስ ከመግባት ጋር አመሳስሎታል፡፡ ከመርከቧ አጠገብ መሆን ወይም የኖኅ ወዳጅ መሆን ዋጋ ሳይሰጠው ከመርከቧ ውጭ የነበሩት ሁሉ በጎርፍ ጠፍተዋል፡፡ በክርስቶስ በመርከቧ ውስጥ መሆን ለመዳን ብቸኛው መንገድ ነው፡፡ ነበርም፡፡ ስለዚህ፤ በጥምቀት አማካይነት በክርስቶስ በመርከቧ ውስጥ መገኘት የጊዜው አንገብጋቢ አጣዳፊ ጉዳይ ነው፡፡

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያናት በዓለም ሁሉ ወንጌልንና ጥምቀትን እንዲሰብኩ የክርስቶስን ትዕዛዝ ፈጽመዋል፡፡ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍም ይህን የመዘገበ ነው፡፡ እንዴት ሰዎች ወንጌልን ከተቀበሉ በኋላ ተፋጥነው እንደሚጠመቁ ማየቱ የጥምቀትን ጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ስለመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ላይ ጎልቶ /ጠብቆ/ ይገኛል፡፡ /ምሣሌ ሐዋ 8፡12፣36

39፣9:18፣10:47፣16:15/:: አንድ ጊዜ ያለ ጥምቀት ወንጌልን መማራችን ከንቱ መሆኑን ከተገነዘብን ሥረ ነገሩን እንረዳለን::

ጥምቀት ወደድኅነት የሚያመራ ጠቃሚና አስፈላጊ መተላለፍ ያለበት መንገድ /ደረጃ/ ነው:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ጥምቀትን የሚያዘገዩ ብዙ አብዓዊ ምክንያቶች ቢፈጠሩም ተግባርን ለማከናወን ብዙ እግሮች ቢኖፐሩም በእግዚአብሔር እርዳታ አሕዛብ እነዚህን ሁሉ ለመቋቋም የሚያደርጉት ጥረት በጣሚ ጠቃሚ መሆኑን በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፈው ጽሑፍ አፈጻጸሙ እንዴት እንደሆነ በጣም የደመቀ ነው::

በከባድ የመሬት ነውጥ ባስከተለው አደጋ ከፍተኛ ጥበቃ የነበረው ወህኒ ቤት ሙሉ በሙሉ በመሰባበሩ በፊሊፒ ወህኒ ጠባቂ የነበረው ሰው በድንገት ሕይወቱ ችግር ላይ ወድቆ ነበርና እስረኞቹ የማምለጥ ቀላል አጋጣሚ ፈጥሮላቸው በነበረበት ሁኔታ ጠባቂው ቢያመልጡ ኑሮ ሊያስገድለው የሚያበቃ ጥፋት በተፈጠረበት ሰዓት በዚያን ጊዜውንም በወንጌል ተነበረው እምነት እውን ሆኖ «በዚያኑ የሌሊት ሰዓት /እርሱ/ ተጠመቀ... ወዲያውኑ በቀጥታ» /ሐዋ 16:33/

ጥምቀትን ለማዘግየት ሰበብ የሚያሻው ሰው ቢኖር እርሱ ነበር:: ከዚህ አንፃር በአካባቢው ዓለም በተፈጠረው /የመሬት ነውጥ/ ድንገተኛ ችግር በመቋቋም በሥራው ላይ የሚያስከትለውን ጫናና ራሱን ባገኘበት አስደንጋጭ የአዕምሮ ቁስል ሳይደናገጥና ሳይዘናጋ ተጠመቀ:: ለጥምቀት የሚጻጹ ብዙዎች ከዚህ ሰው መንፈስ ሊነቃቁ ይችላሉ:: እንደዚህ ያለ ብርቱ የእምነት ተግባር መሥራቱ ቀደም ሲል ጠለቅ ያለ የወንጌል ትምህርት እንደነበረውና እንደዚህ ያለ ሐቀኛ

እምነትም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንደሚመጣ በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡ /ሮሜ 10፡17፣ሐዋ 17፡11/

የሐዋርያት ሥራ 8፡26..40 ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን በሠረገላ በየሃ ሲያቋርጥ እንዴት መጽሐፍ ቅዱስ እንደተማረ መዝግቦአል፡፡ በዝርዝር ወንጌልን የጥምቀትን አስፈላጊነት ጭምር ያስረዳውን ፊሊጶስን አገኘ፡፡ ከሰብአዊ ተፈጥሮአችን አንፃር ሲታይ ውኃ በማትገኝበት ምድረ በዳ የጥምቀትን ትዕዛዝ መቀበል የማይቻል ይመስላል፡፡ ሆኖም እንደማይታዘዙ ለሚያውቃቸው አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ትዕዛዙን አይሰጥም፡፡ «በመንገድም ሲሄዱ ወደውኃ ደረሱ» ማለትም ጥምቀት የሚቻልበት የበረሃ ገነት ደረሱ /ሐዋ 8፡36/ ይላል፡፡ ጥምቀት ውኃ ውስጥ በማጥለቅ መከናወን ስለአለበት ብዙና በቀላሉ የሚደረስበት ውኃ እንደሚያስፈልግ የሚነገርለት መሠረት የሌለው ሀሳብ የዚህ ድርጊት ምላሽ ሰጥቶበታል፡፡ ትዕዛዛቱ ይጠበቁ ዘንድ እገዚአብሔር ሁልጊዜም ትክክለኛ መንገድ ይሰጣል፡፡

አዕምሮውን /ህሊናውን/ የነካው እይታ ጳውሎስ ከክርስቶስ ባገኘበት ጊዜ በተቻለው ፍጥነት «ወዲያውኑ... ተነስቶም ተጠምቆ» /ሐዋ 9፡18/ መጠመቁን መዘግየት ወይም ማፋጠን እንደገና ፈታኝ ሆኖበት ይሆናል፡፡ በአይሁዳዊው ኅብረተሰብ የነበረውን ማኅበራዊ ቦታና ከፍተኛ ሙያ የሚያሳጣ ይሆናልና፡፡ ሆኖም ይህ በአይሁድ ዓለም እንደኮከብ እየበራ የመጣው ጳውሎስ ትክክለኛና አፋጣኝ ውሣኔ በመስጠት ሊጠመቅና የቀድሞ የሕይወት መንገዱን በግልጽ ለማውገዝ በቅቷል፡፡ ለመጠመቅ የወሰደውን ምርጫ

በሚመለከት ቆየት ብሎ በአንፀባራቂው መግለጫ እንዲህ ብሏል...« ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለክርስቶስ እንደጉዳት ቆጥረዋለሁ::

በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለክርስቶስ ኢየሱስ ስለጌታዬ ዕውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቆጥረዋለሁ ስለእርሱ ሁሉን ተጎዳሁ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ..በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ በክርስቶስ ከፈ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ /ፊሊጰ 3፡7፣8 13 14/

ይህ በአቸናፊነት የመጨረሱን ብሥራት የሚገለጸውን ገመድ ለመበጣጠስ ወደፊት የሚሟሟት የአትሌት ቋንቋ ነው:: ከጥምቀት በኋላ የሚኖረንን ሕይወት የሚያመላክት የአዕምሮና የአካል ጥረት ክምችት ነው:: ወደእግዚአብሔር መንግሥት በሚደረገው እሽቅድድም የሚጀመረው በጥምቀት ነው:: ቤተክርስቲያንንና ዕምነቶችን ለመለዋወጥ ሲባል ብቻ የሚደረግ የይስሙላ ወይም የተዝናና ሕይወት ለመምራት ቀላል ወደሆነ የአኗኗር ፈሊጥ ጋር ለመጣበቅ አይደለም:: ጥምቀት በየጊዜው በሂደት ከኢየሱስ ስቅለትና ትንሣዔ ጋር የሚያገናኘን ነው:: /ሮሜ 6፡3..5/ ነእያንዳንዱ መንገድ በማይቀለው በረታሳቸው በሚበለጽጉ ሁኔታዎች የተሞላ::

የደከመ ግን በመንፈስ የተሞላው ሽማግሌው ጳውሎስ «ከሰማይ የታየኝን ራዕይ እምቢ አላልሁም»/ሐዋ 26፡19/ ለጳውሎስ እውነት እንደነበረ ሁሉ በአግባቡ ለተጠመቁት

እንዲሁ ነው:: የጥምቀት ውሣኔው ማንንም የሚፀፅት አይሆንም:: ሕይወታችንን ሙሉ ትክክለኛ ምርጫ ለማድረጋችን እናገናዝባለን እንጂ እርግጠኛ ከምንሆንባቸው ጥቂት ሰብዓዊ ውሣኔዎች አንዱ ይኸ ነው:: «ለምን ጥምቀትን አላደረግሁም?» የሚለው ጥያቄ ክብደት ባለው ማጤን መመለስ ይኖርበታል::

## 9.2 እንዴት ነበር መጠመቅ የነበረብን?

ጥምቀት በተለይ በህፃናት ግንባሮች ላይ ውኃ በመርጨት ማከናወን እንደሚቻል /ክርስቲያን ለማድረግ/ በሰፊው ተሚሠራበት እይታ ነው:: ይህ ግን ስለጥምቀት በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉትን መስፈርቶች ፍጹም ይቃረናል::

ጥምቀት የሚለው ተግሪክ ቃል በውኃ መነከርን /መረጨትን/ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መታጠብንና በፈሳሽ ውስጥ መጠመቅን ነው የሚያመለክተው:: ቃሉ በግሪክ ቋንቋ በውኃ ውስጥ የሚጠልቁ መርከቦችን፤ እንዲሁም አንድ የልብስ ቁራጭ ከአንድ ቀለም ወደሌላ ቀለም ለመለወጥ የሚጠ ቀሙበትን ቀለም ለመግለጽ «መጠመቅ» የሚለውን ይጠ ቀማሉ:: ሁለቱም ሙሉ በሙሉ መጥለምን ያሳያሉና:: ያ መጥለም ትክክለኛው የጥምቀት ቅርጽ ነው:: የሚከተሉት ጥቅሶችን ከዚህ አኳያ እንመርምር...

...«ዮሐንስም ደግሞ በሣሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያን ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር» ይላል /ዮሐ 3፡23/

ይህ «ብዙ ውኃ ልጥምቀት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡ ጥቂት የውኃ ነጠብጣብ በመርጨት የሚደረግ ቢሆን ኑሮ አንድ ባልዲ ውኃ ለመቶ ሰዎች በቂ በበቃ ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ጠርሙስ ውኃ ይዞ ወደ ሕዝቡ አልሄደም፡፡ ህዝቡ ወደዮርዳኖስ ወንዝ ዳር ጎረፈ እንጂ፡፡

…ኢየሱስም በዮሐንስ የተጠመቀው በዮርዳኖስ ወንዝ ነበር፡፡ «ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ በቀጥታ ከውኃው ወጥቶ ሄዶ» /ማቴ 3፡13..16/ ሲል በግልጽ ጥምቀቱበመጠለም መሆኑን ያለክታል፡፡ ኢየሱስ ከተጠመቀባቸው ምክንያቶች አንዱ አርአያ ለመሆን ነበር፡፡ ይኸውም የእርሱን በመጥለም መጠመቅን ካልያዘ ከልብ ኢየሱስን እከተላለሁ ማለት እንደማይችል ያረጋግጣል፡፡

> …በተመሳሳይ መንገድ ፊሊጶስና የኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ሁለቱም ወደውኃ ወረዱ፡፡ አጠመቀውም፡፡ ከውኃ ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊሊጶስን ነጠቀው፡፡ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም»ይላል /ሐዋ 8፡38 39/፡፡ የኢትዮጵያው ባለሥልጣን የበረሃ ገነትን ሲያት ፊሊጶስ እንዲያጠምቀው መጠየቁን አስታውሱ፡፡ «…ተመልከት ይኸውና ውኃ ከመጠመቅ ማን ያቆመኛል?» /ሐዋ 8፡36/ ነው ያለው፡፡ ኢትዮጵያዊው ያን ሁሉ በሚያቋርጥበት ጊዜ ቢያንስ ጠርሙስ ውኃ ሳይዝ ቀርቶ አይደለም፡፡ ጥምቀት ግንባር ላይ በመርጨት ቢሆን ኑሮ የበረሃ ገነት ሳይጠበቅ ቀደም ብሎ በረሃው ውስጥ በተከናወነ ነበር፡፡

…ጥምቀት እንደመቀበር ነው /ኮል 2፡12/ ሙሉ ለሙሉ መሸፈንን ያመለክታል፡፡

…ጥምቀት ከኃጢአት መንጻት ወይም መጽዳት ነው፡፡ /ሐዋ 22፡16/ የትክክኛ መለወጥ ነቁጥ ከህጽበት ይመሰላል፡፡ /ራዕይ 1፡5፣ጢጦ 3፡5፣ 2ጴጥ 2፡22፣ ዕብ 10፡22 ወዘተ፡፡

ይህ የእጥበት ቋንቋ በውኃ ከመነከር ይልቅ ጥምቀት መጠለም መሆኑን ይመለከታል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ወደእግዚአብሔር የሚያመራ ተቀባይነት ያለው አካሄድ በእጽበት አማካይነት ስለመሆኑ ብዙ ቦታዎች ላይ ተጽፎ ይገኛል።

ቀሳውስት ወደእግዚአብሔር ከመቅረባቸው በፊት በቅዳሴ ጊዜያት በደንብ መታጠብ ይኖርባቸዋል /ሌዋ 8፡6፣ሞጽ 40፡12/። እስራኤላውያን ከአንዳንድ ያዳደፉ ነገሮች /ኃጢአት መሆኑ ነው/ ለመጽዳት መታጠብ ነበረባቸው። /ዳግ 23፡11/

> ንአማን የተባለው አንድ ለምጽ የያዘው ሰው በእስራኤል አምላክ ይፈወስ ዘንድ ፈልጎ ነበር። ይህ ሰው በኃጢአት የተዳፈነና በኃጢአትም ምክንያት በሕይወት ሞት ውስጥ ያለን ሰው ይወክላል። የተፈወሰውም በዮርዳኖስ ወንዝ በመፀለም ነበር። በመጀመሪያ ይህን ቀላል ተግባር ለመቀበል ከብዶታል ይኸውም እግዚአብሔር ከዚህ የላቀ አስደናቂ ተግባር ከእርሱ እንደሚጠበቅ ያም ለምሣሌ አባናን በመሣሰሉ የታወቁ ግዙፍ ወንዝ እንዲፀለም እንደሚፈልግ በማሰብ ነው። በተመሳሳይም፣ ይህን ቀላል ሥራ በማከናወን መዳንን እንቀበላለን ብሎ ለማመን ከባድ ነው። በዮርዳኖስ ወንዝ ከተፀለመ በኋላ የናአማን ሥጋ «ልክ ተመልሶ የህፃን ልጅ ሥጋ ሆነና ነፃ» ይላል /2 መሣ 5፡9..14/። አሁን ሥምቀት የወንጌልን መሠረታዊ መልዕክት መጀመሪያ በሚገባ ከተረዱ በኋላ ሙሉ በሙሉ በውኃ መጠለምን የሚያመለክት ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አንዳችም ነገር ሊኖር አይገባም። ይህ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገው የጥምቀት ትርጉም በአካል ከሚያጠምቀው የግለሰብ ደረጃ ጋር የተያያዘ አይደለም። ጥምቀት የመጽሐፍ ቅዱስን /የወንጌልን/ መልዕክት /እምነት/ ከተገነዘቡ በኋላ እስከተደገረ ድረስ ተጠያቂው ራሱ ሊያጠምቅ ይችላል። ያም ሆኖ ጥምቀት የሚደረገው ጥምቀትን የሚያከናውነው ሰው በሚጸለምበት ጊዜ በያዘው ትክክለኛ ትምህርት ምክንያት ስለሆነ ትክክለኛ ትምህርቶች በሚከተል ሌላ አማኝ መጠመቁ በእርግጥ የሚመረጥ ነው። ይህ አጥማቂ ከማጥመቁ በፊት የተጠማቂውን የዕውቀት ደረጃ ከሁሉም በፊት መገምገም ስለሚችል። በእያንዳንዱ ጥናት መጨረሻ ላይ

እንደሚቀርቡት ጥያቄዎች ያሉ የውይይት መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ግለሰብ ለማጥመቅ ሲል የጥምቀት ዕምነት አራማጆች በሺህ የሚቆጠሩ ማይሎች አቋርጠው ተጉዘዋል። የአንድን ግለሰብ በጥራት ወደትክክለኛው የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ ወደሚገኝበት ማምጣት ታላቅ አስደናቂ ሥራ ነውና። ጥራት ከብዛት ጥራት ከብዛት ይልቃል።

## 9.3 የጥምቀት ትርጉም

ለጥምቀት ምክንያቶች አንዱ በመጠለም መሆኑ ወደውኃ ውስጥ ጠልቆ መግባት ወደመቃብር ይህም ከክርስቶስ ሞት ጋር የሚያገናኘንና በቀድሞው በኃጢአት በድንቁርና ሕይወታችን የነበረብንን «ሞት» የሚያመለክት ነው። ከውኃ ውስጥ ወደላይ መውጣት ደግሞ ከክርስትስ ትንሣዔ ጋር ያገናኘናል። ይህም በክርስቶስ መመለሻ ጊዜ ለዘለዓለማዊ ሕይወት መነሣታችንንና አሁንም ደግሞ በአዲስ ሕይወት ኃጢአትን በክርስቶስ ሞትና ትንሣዔ ምክንያት አቸናፊነት የተነሣ በመንፈስ በልጥገን ከመኖር ጋር ያዛምድልናል።

«ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን

ከሞቱ ጋር እንሆን ዘንድ ተጠምቀናል እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር

ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመለሰለስ

ከሞቱ ጋር አንሐደ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን»

ሞቱንም በሚመስል ሞት /በጥምቀት/ ከእርሲ ጋር ከተባበርን ትንሣዔ

ውን በሚመስል ትንሣዔ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን»ይላል፡፡

/ሮሜ 6፡3..5/

ድኅነት ሊሆን የቻለው በክርስቶስ ሞትና ትንሣዔ አማካይነር በመሆኑ እንድን ዘንድ ከእነዚህ ነገሮች ጋር ራሳችንን ማዛመድ የግድ ይኖርብናል፡፡ በአርአያነቱ ከክርስቶስ ጋር መሞትና መነሣት ማለት ጥምቀት የሚያጎናጽፈው ይህን የማድረጊያ ብቸኛ መንገዱ ነው፡፡ በውኃ መረጨት ግን ይህን የሚያሟላ ምልክት አይደለም፡፡ በጥምቀት አሮጌው ሰዎችን /የአኗኗር መንገዳችን/ «ከእርሱ ጋር በመስቀል እንደተሰቀለ /ሮሜ 6፡6/ እግዚአብሔር «ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን» በጥምቀት /ኤፌ 2፡5/ ያም ሆኖ ከጥምቀት በኋላ ቢሆን ሰብዓዊ ተፈጥሮአችን ስለአለ የሥጋ ፍላጎታችን /ሥጋዊ ሕይወታችን/ አንገቱን ማቅናቱ አይቀርም፡፡ የሥጋችን ስቅላት በጥምቀት ተጀምሮ በየጊዜው በሂደት የሚከናወን በመሆኑ ክርስቶስ ለአማንያን መስቀሌን ይዛችሁ ዕለት ዕለት በኋላየ ተከተሉኝ ወደሰልፍ እንደሚዘም ሰልፈኛ ሆናችሁ ሲል ነግሮአቸዋል፡፡ /ሉቃ 9፡23፣14፡27/ ከክርስቶስ ጋር እውነተኛ ስቅለት ቀላል ባይሆንም ከክርስቶስ ትንሣዔ ጋር መዋሃዱ ደግሞ በቃላት ሊገልጽ የማይችል ደስታና እርካታ እንዳለው እሙን ነው፡፡

ክርስቶስ «በመስቀሉ ደግሞ ሰላም አደረገ» /ቆላስ 1፡20/..«አዕምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ...በክርስቶስ እየሱስ ይጠብቃል»/ፊል 4፡7/ ይላል፡፡ ይህን በተመለከተ ኢየሱስ «...ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ /ሰላም/ አይደለም» ሲል ቃል ሰጥቶአል፡፡ /ዮሐ 14፡27/፡፡ ይህ ሰላምና እውነተኛው መንፈሳዊ ደስታ ከተሰቀለው ክርስቶስ ጋር በመዛመዳችን በዓለም ከሚገጥመን ህመም፣ ተውሳክና ችግር ይመዝናል፡፡

«...የክርስቶስ ስቃይ በእኛ ላይ እንደበዛ እንዲሁ መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና» /2 ቆሮ 1፡5/ ታላቂ ሐዋርያ ጳውሎስ በረዥሙ በድርጊት በተሞሉት የሕይወት ዘመኑ ስለነበረው ልምድ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር.. «...ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኘ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለእኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው፡፡ /ገላ 2፡20/

«...ጥምቀት አሁንም ያድነናል... በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣዔ» /ጴጥ 3፡21/ ምክንያቱም ለዘለዓለማዊ ሕይወት ከክርስቶስ ትንሣዔ ጋር መዋሃዳችን በዳግም ምዕዓቱ ጊዜ ተመሳሳይ መንገድ ይሰጠናልና፡፡ በዚህ ትንሣዔ መካፈለሰችን ነው በኋላ በመጨረሻው ጊዜ የሚያድነን፡፡ ኢየሱስ ይህን በቀላል ቃላት ገልጾታል፡፡ «እኔ ስለምኖር እናንተም ትኖሩአላችሁ» /ዮሐ 14፡19/ ይላል፡፡ ጳውሎስም እንዲሁ «ጠ ላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን

ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ /በትንሣኤው/ እንድናለን ብሏል /ሮሜ 5፡10/

ከክርስቶስ ሞትና ስቃይ ጋር በጥምቀትና በተከታታይ የሕይወት መንገዳችን አማካይነት ራሳችንን አንድ ካደረግን የከበረውን ትንሣኤውን በእርግጥ እንደምንጋራ ተደጋግሞ ተወስቶአል፡..

..«... ከእርሱ /ከኢየሱስ/ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራ

ለን ብንፀና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን» /2ጢሞ 2፡11.12/

...«..የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ደግሞ ሁልጊዜ

የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። የኢየሱስ ሕይወት

ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ

ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና።.. ጌታን ኢየሱስን ያስነሣው እኛን

ዳግም ከኢየሱስ ጋር እንዲያስነሣን ከእናንተም ጋር እንዲያቀርበን እናውቃለ

ንና.../2 ቆሮ 4፡10 11 14/

...ጳውሎስ «እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል

ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ»

ብሏል። /ፊል 3፡10.11/

## 9.4 ጥምቀትና ድኅነት

ጥምቀት ከክርስቶስ ሞት ጋር አንድ ያደርገናል ስንል በጥምቀት አማካይነት ብቻ ነው ምህረት ልንቀበል የምንችለው ማለታችን ነው። እኛ «... በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበርን በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባሥነሳው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣን በበደላችንና ሥጋችንን ባለመገረዝ ሙታን በሆን ጊዜ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጠን። በደላችንን ሁሉ ይቅር አለን» /ቆላስ 2፡12..13/። እኛ ታጥበናል... በጌታ በኢየሱስ ስም «1ቆሮ 6፡11/ .. ማለትም በኢየሱስ ስም መጠመቅ ኃጢአታችን የሚነጻበት መንገድ ነው። ይህ በዘሑልቁ 19፡13 በውኃ ያልነው መሞት ይገባቸዋል ሲል አስቀምጦታል። ከኃጢአት ለመንፃት የሚቻለው በክርስቶስ ደም መሆኑን ምዕመናን የገለጹአቸው የሚያመላክተው በጥምቀት መሆኑን ነው /ራዕ 1፡5፣7፡14፣ጢጦ 3፡5 ይህንን «የእንደገና መወለድ እጥበት» እንደሆነ አድርገው ይገልጹታል። ይኸውም የእኛ በጥምቀት «ከውኃ መወለድ» /ዮሐ 3፡5/ ለማመላከት ነው።/

ከዚህ ሁሉ አኳያ ሰዎች ለጴጥሮስ «ምን እናድርግ?» /ለመዳን ሲሉ ላቀረቡት ጥያቄ «ንሰሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም

ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» /ሐዋ 2:37.38/ ሲል ጴጥሮስ ምላሽ መስጠቱ የሚገባ ነው ይሆናል። በክርስቶስ ጥምቀት ለኃጢአት መደምሰሻው ነው። ያለጥምቀት ኃጢአት ይቅርታን አታገኝም። ስለዚህ ያልተጠመቀ የኃጢአትን ደመወዝ.ሞትን ይቀበላል። /ሮሜ 6:23/። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ካልሆነ ድኅነት የለም /ሐዋ 4:12/ እና ያንን ስም የምንጋራው በእርሱ ስም በመጠመቅ ነው። ከክርስትና ኃይማኖት ውጭ ያሉ ሁሉ ወደድኅነት መንገድ ሊያመሩ እንደማይችሉ ሐቅ ነው። እውነተኛ መጽሐፍ አማኝ ድኅነትን ያገኛሉ ብሎ አይቀበልም። የክርስቶስ ለዘለዓለማዊ ሕይወት ትንሣዔ በግሉ በኃጢአት ላይ ድል መቀዳጀቱን የሚያሳይ ምልክት ነው። በጥምቀት ራሳችን ከእርሱ ጋር አንድ ስላደረግን ከእርሱም ጋር ትንሣዔ እንዳገኘን ስለተረጋገጠልን ኃጢአት በእርሱ ላይ ሥልጣን እንደሌለው ሁሉ በእኛ ላይም እንዲሁ አይኖረውም። በጥምቀት አማካይነት «...ከኃጢአት አርነት ወጥተናል...ኃጢአትም አይገዛንም»ከጥምቀት በኋላ /ሮሜ 6:18:14/ ያም ሆኖ ከጥምቀት በኋላም ቢሆን ኃጢአት እንሠራለን። /1 ዮሐ 8:9/። ኃጢአት ከክርስቶስ ፊተያችንን ካዞርን እንደገና የኃጢአት ባሪያዎች እንሆናለን።

በክርስቶስ ዳግም መጠመቅ «ያመነና የተጠመቀ ይድናል» /ማር 16:16/። በቀጥታ ጥምቀቱ እንደተከናወነ ወዲያው የመጨረሻው ድኅነት አይሰጥም። በፍርዱ ዙፋን እንጂ /1 ቆሮ 3:15/። ድኅነትን በጥምቀት የምንቀበልና መሞትም ከነበረብን የፍርዱ ትምህርት በእርግጥ አስፈላጊ ባልሆነም ነበር። «እስከመጨረሻው የሚችል ይድናል» /ማቴ 10:22/ ይላል።

ከተጠመቀም እንኳን በኋላ ጳውሎስና / ሌሎች ክርስቲያናት ሁሉ/ ድኅነትን ተመኝቶ ነበር /ፊል 3:10..13፣1ቆሮ 9:27/፤ ስለዘለዓለማዊ ሕይወትም ተናግሮአል /ጢጦ 1:2፣3 7፣1 ተሰሎ 5:8፣ ሮሜ 8:24/ እንዲሁ «የድኅነት ወራሾች እንደሆንም ሁሉ /ዕብ 1:14/። በፍርድ ዙፋን የጻድቃን ወደዘለዓለማዊ ሕይወት ይገባሉ /ማቴ 25:46/። ጳውሎስ በአስደናቂ በመንፈስ የተነሣሣ ወደ ሮሜ ሰዎች 13:11 ላይ እንዲህ ሲል የብርሃን ብልጭታውን ያንፀባርቀዋል... ከጥምቀት በኋላ እያንዳንዷ

የምንኖርባት ዕለትና ዕለቷን የምንናልፍበት ጥንካሬ በአንድ ቀን ወደክርስቶስ ዳግም መምጪያ ሰዓት እንደሚያቀርበንና በዚህም አሁን ከአመንበት ጊዜ ወደድኅነት የበለጠ በመዳረሳችን ልንደሰት እንደምንችል እንወቅ ሲል ይገልጻል። ድኅነት እንዲሁ የሚገኝ አይደለም። እውነተኛውን ዕምነት ፈጥረንና አጥብቀን ከያዝን እንድናለን። /ዕብ 3:12..14/ ደግሞም ወንጌልን የሚጨምር መሠረታዊ ትምህርቶችን ካስታወስንና እንዲሁም በተጨማሪ ታላቁን ተስፋ ለመጠበቅ እነዚያን ነገሮች ከፈጸምን እንድናለን። /1 ጢሞ 4:16፣1 ቆሮ 15:1..2፣2 ጴጥ 1:10/

በግሪክ ቋንቋ «መዳን» የሚለው ግሥ የቀጣይ ጊዜን ስለሚያመለክት «ድኅነት» በየጊዜዉ በሂደት የሚከናወን ለወንጌል ያለንን ቀጣይ ታማኝነት በውስጣችን ያለ ነው። ስለዚህ፣ ምዕመናን ለወንጌል ባላቸው ምላሽ «መዳን እንዳለ» ይገልጻል። /1 ቆሮ 1:18/። «ዳነ» የሚለው የግሪክ ቃል ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመዋሉ «ድኅነትን» ያስቻለውና እኛም ከእርሱ ጋር በጥምቀት አንድ ማድረግ እንደምንችል ያመለክታል። /2 ጢሞ 1:9፣ ጢጦ 3:5/

ይህ ሁሉ ከሰማይዋ እሥራኤል ማለትም የምዕመናን መሠረት ከሆነችዋ ምድራዊ እስራኤል ጋር እግዚአብሔር ያሳየው ምልክት ላይ ተመልክቶአል። ከጥምቀት በፊት የምንዛመዳትን የሥጋ ዓለምንና የተሳሳተ ኃይማኖት የምትከተለዋን ግብጽን እስራኤል ለቅቀው ቀይ ባህርን አልፈው የሲናይ በረሃን ተጉዘው ቃል ወደተሰጠባት ምድርና የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ በሙሉ ወደተመሠረተባት ገብተዋል። ቀይ ባህርን ማቋረጣቸው ጥምቀትን፣/1 ቆሮ 10:1.2/ የበረሃው ጉዞ አሁን ያለንበትን ሕይወትና ከንዓን

የእግዚአብሔርን መንግሥት ያመለክታል፡፡ የይሁዳ መልዕክት ቁጥር 5 በበረሃው ጉዞ ስንቶቹ እንደአለቁ ይገልጻል፡፡ «ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብጽ ሀገር ሕዝቡን አድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ እወዳለሁ» ይላል /ይሁዳ 1፡5/፡፡ እሥራኤልም ከግብጽ እንደዳኑ ሁሉ የሚጠመቁትም እንዲሁ ይድናሉ፡፡ ከእነዚህ እስራኤላውያን አንዱ «ድነኃልን?» ተብሎ ቢጠየቅ ምላሹ «አዎ» ይሆን ነበር፡፡

በተመሳሳይ መንገድም በልባቸው ለእስራኤል ጀርባቸውን ወደግብፅ በማዞር የሥጋን ፍላጎት ወደመሚያረካ አኗኗርና የተሰሳሳተ ትምህርት እንደተከተሉ ሁሉ /ሐዋ 7፡39/ በመጠመቃቸው ከኃጢአት የዳኑት ከቆሙበት የተቀደሰ ቦታ ወዲያ የሚወድቁም አሉ፡፡ /1 ቆሮ 10፡1..12፣ዕብ 4፡1.2፣ ሮሜ 11፡17..21/

በሌሎች ነገሮች ውስጥ እንዳለው ሁሉ በጥምቀት ምን ያህል እንደምንድን ትክክለኛ ሚዛናዊ ዕይታ ያስፈልጋል፡፡ ድረጊቱ የድኅነት ዕድል ማግኛ በመሆኑ ጥምቀት ካለማድረግ ይሻላል፡፡ በክርስቶስ ስም በመጠመቅ የመዳን ተስፋ ተሰጥቶናል፡፡ የክርስቶስን ሥራ ከተከተልን ልክ ከጥምቀት ውኃ ስንወጣ እንዳለንበት ወቅት በእግዚአብሔር መንግሥት እንደምንሆን እርግጥ ነው፡፡ ከጥምቀት በኋላ ባለው በየትኛውም ጊዜያት ትሁት ስብዕና ሆነን ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ በእግዚአብሔር መንግሥት ተቀባይነት እንዳለን ከልብ ማመን ይኖርብናል፡፡ እስከመጨረሻው እርግጠኞች ልንሆን አንችልም፤ ምክንያቱም በቀጣዩ ቀን ከዚያ ልንወድቅ እንችላለንና፡፡ በዚህ ዓለም ህይወታችን የግል የመጭ መንፈሳዊ አቅጣጫችን እስከመጨረሻው በዛሬው ማንነታችን አይወሰንም፡፡

በጥምቀት ወቅት ከእግዚአብሔር ያለንን በጎ ህሊና ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን፡፡ ጥምቀት «የበጎ ህሊና ልመና ነው፡፡» /1 ጴጥ 3፡21/ይላል፡፡ ተጠማቂው ዕጩ

ያንን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን በጎ ህሊና ለመጠበቅ ቃል ይሰጣል።

ጥምቀት ወደ ታላቁ ደኅንነት የሚያመራና በክርስቶስ የሚገኝ እጅግ ጠቃሚ ተግባር ቢሆንም የጥምቀት የአንድ ጊዜ ድርጊት /ሥራ/ በራሱ ብቻ እንድናለን የሚል የተሳሳተ ስሜት በራሳችን ላይ እንድንፈጥር ያስፈልጋል። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደእግዚአብሔር መንግሥት ለገቡ አይችሉም» ይላል /ዮሐ 3፡5/ ድኅነት ከጥምቀት ብቻ አይደለም። ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ የብፅዕና፣የዕምነትና የተስፋ ውጤት ነው እንጂ።/ኤፌ 2፡8፣ሮሜ 1፡5፣ሮሜ 8፡24/

አንዳንድ ጊዜ ድኅነት በዕምነት ብቻ እንደሚገኝ ይነገረራል። ይህም እንደጥምቀት ያለው «ሥራ» ዋጋ ቢስ መሆኑ ነው? ያም ሆኖ ጀምስ 2፡17..24 ይህ ዓይነት አገላለጽ በዕምነትና በሥራ መካከል የተለያየ ግን የተሳሳተ ልዩነት እንደሚፈጥር ግልጽ ያደርጋል። እውነተኛ እምነት ለምሣሌ በወንጌል ልከኛ እምነት መሆኑን በሚያስከትለው ሥራ ለምሣሌ ጥምቀት ይገላጻል። «በሥራው ሰው ይመዘናል፤ በእምነት ብቻ አይደለም» ይላል /ቶማስ 2፡24/ በብዙ የጥምቀት ጉዳዮች ላይ ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባው ምዕመን ይጠይቃል። መልሱ ሁልጊዜ ጥምቀትን የሚጠቁም ነው /ሐዋ 2፡37፣9፡6፣10፣6፣ አስፈላጊ ምልክት ነው። የመጨረሻው የማዳን ሥራ በክርስቶስና በእግዚአብሔር ተፈጽሟልና፤ ግን እኛ የንሰሐን ሥራ መሥራት ያስፈልገናል። /ሐዋ 26፡20፣ማር 16፡15.16/

ቀደም ሲል ከኃጢአት የመፀዳዳት ቋንቋ ላይ በክርስቶስ በመጠመቅ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደሚናገኝ ተመልክተናል ኃጢ ፡አታችንን የምናጥበው በእምነትና በንሰሐ መሆኑንም በብዙ ቦታዎች ላይ

ተመልክተናል፡፡ /ሐዋ 22፡16፣ራዕ 7፡14፣ኤር 4፡14 ኢሣ 1፡16/ በሌሎች ኃጢአታችንን የሚያጥብልን እግዚአብሔር እንደሆነ ነው /ሕዝ 16፡9፣መዝ 51፡27፣1 ቆሮ 6፡11/፡፡ በመጠመቅ የራሳችንን ድርሻ ካደረግን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን እንደሚያስወግድልን ይህ በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለዚህ የጥምቀት ሥራ ወይም ድርጊት በቃሉ ለእኛ የተሰጠንን የእግዚአብሔርን ብፁዕ ወንጌል የመጨበጥ ጠቃሚ እርምጃ ነው፡፡

# እንደገና መጠመቅ ..ዳግም ጥምቀት

አንዳንድ ሰዎች ቀደም ሲል በሆነ መልኩ የፈጸሙትን ማለትም በህፃንነት ውኃ የፈሰሰባቸው ወይም በሌላ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ጥምቀት ያደረጉ ለመጠመቅ የመዳዳት ስሜት ይታይባቸዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ከጥምቀት በፊት ንሰሓና የእውነተኛው ወንጌል ተገቢ ዕምነት ሊኖር ይገባል /ሐዋ 2፡38፣ ማር 16፡15.16/፡፡ ውኃ ውስጥ ከመጥለም በፊትና የዕምነት ጥምቀት ከመፈጸሙ በፊት እነዚህ ሁሉ ነገሮች መልክ መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ማቴ 28፡19.20 ላይ ጥምቀትን መጀመሪያ ክርስቶስ ትምህርቶች በተብራራ መንገድ እንዲሰሙ ያሻል ሲል ይገልጻል፡፡ ህፃን ልጅ ንሰሓ ሊገባ ወይም ወንጌል ሊረዳ አይችልም፡፡ ለማንኛውም በውኃ መረጨት ጥምቀት አይደለም፡፡

በመዋኛ ቦታ ጠልቆ የሚወጣ ዋናተኛ ጥምቀት አላደረገም፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው በህሊናው ለእውነተኛ ወንጌል ምላሽ /አኗያ/ አምኖ አይደለም ወደውኃው የጠለቀው፡፡ በተሳሳተ ትምህርትም የሚያምኑ ውኃ ውስጥ ቢጸለሙ እንዲሁ፡፡ ጸልመወዋል ግን አልተጠመቁም፡፡

«አንድ እምነት» ብቻ አለ ማለትም እውነተኛውን ወንጌል የያዘ አንድ ትምህርት፡፡ ስለዚህም «አንድ ጥምቀት ብቻ».. ብቸኛዋን እምነት ካመኑ በኋላ የሚደረግ ጥምቀት «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠ ራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ» ይላል /ኤፌ 4፡4.6/፡፡ ሁለት ተስፋዎች የሉም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ብናምንም ባናምንም ዋጋችን በምድር ወይም በሰማይ እንቀበላለን እንደሚሉት አይሆንም፡፡ «አንድ እግዚአብሔር» ብቻ ነው ያለው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እግዚአብሔር አይደለም፡፡ በምንጠመቅበት ወቅት እንደእግዚአብሔር መንግሥት፣ የእግዚአብሔርና የኢየሱስ ባህርይ ወዘተ የመሳሰሉትን መሠረታዊ ትምህርቶች ለመረዳት ከሰነፍን የመጀመሪያው ጥምቀታችን ዋጋ ቢስ ነው የሚሆነው፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙ እየተጣራና ስለኢየሱስም አንዳንድ ነገሮችን እያስተማረ አሕዛብን አፀለመ፡፡ /ማር 1፡4፣ሉቃ 1፡77/ ይህ ግን በቂ አልነበረም፡፡ የሐዋርያት ሥራ 19፡1..5 መዝግቦ እንዳስቀመጠው ዮሐንስ ካጠመቃቸው አንዳንድ ትምህርቶችን አሟልተው ባለመጨበጣቸው ምክንያት ጥቂቶቹ እንደገና መጠመቅ

ነበረባቸው፡፡ ዮሐንስ እንዳጠመቃቸው የመጀመሪያው መነከራችን ትክክለኛ ንሰሐና አዲስ ጅማሬ አድርገን ሊሰማን ይገባል፡፡ ይህ እውነት ይሆን ይሆናል ግን አንዷ /እውነተኛዋን/ ጥምቀት ለመቀበል ያለውን አስፈላጊነት አይሽረውም፡፡ «የአንድን እምነት» ነገሮች አሟልቶ ከያዙ በኋላ የሚፈጸም ነውና፡፡

# ጥናት 9 ጥያቄዎች

1/ ያለ ጥምቀት ልንድን እንችላለን?

አዎ ፡ፀገሀተ
የለም .ትወጵለቨጵ

2/ «ጥምቀት» የሚለው ቃል ምንድን ነው?

ራስን መስጠት ፡ፀገሀተ
በውኃ መረጨት .ትወጵለቨጵ
ሐ. ዕምነት

መፀለም .ትሀፀረተጵጵነ

3/ መቸ ነው መጠመቅ ያለብን?

እውነተኛዋን ወንጌል ከተማርንና ፡ፀገሀተ
ከንሰሐ በኋላ
በህፃንነት .ትወጵለቨጵ
ሐ. በመጽሐፍ ላይ ፍላጎት ካደረብን በኋላ

አንድን ቤተክርስቲያን መቀላቀል .ትሀፀረተጵጵነ
በፈለግን ጊዜ

4/ በምን አምነን ነው የምንጠመቀው?

በሚያጠምቀን ቤተክርስቲያን ፡ፀገሀተ
በእግዚአብሔር ቃል .ትወጵለቨጵ
ሐ. በክርስቶስ

በመንፈስ ቅዱስ .ትሀፀረተጵጵነ

5/ ከሚከተሉት ውስጥ ከጥምቀት በኋላ የሚሆነው የትኛው ነው?

የአብርሃም ዘር አካል ነን ፡ፀገሀተ

ለ. እንደገና ኃጢአት ውስጥ ፈጽሞ አንወድቅም

ሐ. በእርግጠኝነት ለሁልጊዜው እንድናለን

መ. ኃጢአቶቻችን ምህረትን ያገኛሉ

6/ ለመጠመቅ ትፈልጋለህ?

አዎ ፀገሀተ

የለም ትወጽለቨጽ

# 10. ተጨባጩ የክርስቲያን ሕይወት

# 10.1 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከጥምቀት በኋላ በሥጋ በመንፈስ የምትመራ ሕይወት «ለቅድስናዋም ፍሬ» ወደፊት ማስከተል ይኖርባታል። /ሮሜ 6:22፣8:1፣ ገላመ 5:16..25/። መንፈሳዊ ፍሬ ማስከተል የምንችለው ደግሞ በእኛ ውስጥ በሚኖር የእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ነው። /ዮሐ 15:7..8/ በመንፈስ የምንመራው ስሜቱ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ቃል ማለታችን እንደሆነ አይተናል። በሕይወታችን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን በየጊዜው በማንበብና በማጥናት ለቃሉ ቅርብ መሆናችንን መጠበቅ አለብን።

የቃሉን ደንበኛ ጥናት የመጠመቅ አስፈላጊነት የሚረዳና ያንን የምፈጽምን ሰው ይፈጥራል ቃሉ በተግባራችን ላይ ተጽዕኖ እንድያሳድርና ሕይወታችን ይቀጥል ዘንድ እንዲመራ የሚፈቅድ ሂደት ነው። ጥምቀት ሌላ ሰይሆን ለእግዚአብሔር ቃል በሕይወት ሁሉ ታማኝ የመሆን የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በተለይ ከወንጌል መሠረታዊ ትምህርቶች ጋር የመተዋወቅ ተጨባጭ ችግር አለ። ይህም ቃሉ በእኛ ላይ ምንም ተጽዕኖ ወደማያደርስበት ቦታ የሚያመራን ከሆነ ነው። ቃሎቹን እናነባቸዋለን ግን በእኛ ላይ ተጨባጭ ለውጥ አያመጣም። በዚህም ምክንያት እያንዳንዱን የመጽሐፍ ጥቅስ ለማንበብ ከመጀመራችን በፊት አጭር ፀሎት ማድረግ አዋቅነት ይሆናል። «አንተ የእኔን ዓይነኖች ክፈት ከሕጎችህ አስደናቂ ነገሮችን እጨብጥ ዘንድ»ይላል /መዝ 119:18/

የእግዚአብሔር ቃል የዕየዕለት ምግባችን መሆን ይኖርበታል። በቃሉ ላይ ያለን መመካት፣ ፍላጎት ለምግብ ካለን ፍላጎት የላቀ መሆንም አለበት። «ከአፉ ከሚወጡት ቃሎቹ ለምግብ ካለኝ ፍላጎት የበለጠ ወድጃለሁ። አክብሬአለሁም» ሲል ኢዮብ ስሜቱን ገልኞአል። /ኢዮ 23:12/። ኤርምያስ እንዲሁ «ቃሎችህን አገኘሁ፤ ተመገብኋቸውም ቃልህ በእኔ አድሮ ልቤን በሀሴትና በደስታ ሞላው።» ብሏል /ኤር 15:16/። ጊዜ አግኝቶ በየቀኑ የመጽሐፍ ጥናትን ማዘውተር ለዕለት ዕለት ሕይወታችን

ግንባታ እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው። ያልተቋረጠ በየዕለቱ ጠዋት የ30 ደቂቃዎች ጥናት ማድረጉ ለመንፈሳዊ መነቃቂያ መልካም ጅምር ይሆናል። እንደዚህ ያለ የዕምነት ምሥረታ ልማድ ለፍርድ ቀን የወርቅ ሚዛን ያነግልና።

## 10.2 ፀሎት

ሌላው መበልጸግ ያለበት ጠቃሚው ልማድ ፀሎት ነው። በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው አንድ አስታራቂ ሰው የሆነው ራሱን ለሁሉ ቤዛ ሲል አሳልፎ በመስጠት ለሁላችንም ዕዳ የከፈለው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማስተዋል ጳውሎስ የክርስቶስን ሥራ በመረዳት ተጨባጭ ውጤቱን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል.. «እንግዲህ ወንዶች ሁሉ በስፍራ ሁሉ አለቁጣና አለክፉ አሳብ ... እንዲፀልዩ እፈቅዳለሁ» /1 ጢሞ 2፡5..8/ «..ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደእኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀካህናሕት የለንም። እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ፀጋ እንድናገኝ ወደፀጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ» ይላል /ዕብራ 4፡15..16/

ክርስቶስ ታላቁ ተግል ቄሳችን ሆኖ ፀሎታችንን ለእግዚአብሔር እንደሚያቀርብልን ከልብ በማመን በዕምነት በየጊዜው በመንፈስ ተነሣሥተን መፀለይ ይኖርብናል። ያም ሆኖ ፀሎታችን ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ልክ የምንሻውን ነገሮች ዝርዝር የያዘ መሆን አይገባውም። ከምግብ በፊት ስለማዕዱ ምሥጋና፣ በጉዞ ላይ ስንሳን በሰላም እንዲጠብቀን ወዘተ የመሳሰሉት የፀሎታችን ጠቃሚ አካል ሊሆኑ ይገባል።

በፀሎት ችግሮቻችንን በጌታ ፊት ማቅረቡ በራሱ ሰላማዊ ስሜት በውስጣችን መፍጠር አለበት። «በነገር ሁሉ /ለፀሎት ምንም ትንሽ ነገር የለም/ በፀሎትና በምልጃ ከምሥጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ አዕምሮንም ሁሉ የሚያልፍ

**የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠበቃል» /ፊል 4፡6..7/ ይላል፡፡**

**ፀሎታችን በእግዚአብሔር ቸርነት /ፈቃድ/ ላይ ያረፉ ከሆኑ በእርግጥ ምላሽ ያገኛሉ፡፡ /1 ዮሐ 5፡14/፡፡ የግዚአብሔርን ፈቃድ፣ መንፈሱን /አስተሳሰቡን/ የሚገልጽልንን ቃሎቹን በማጥናት ልናውቅ እንችላለን፡፡ ከዚህም አኳያ፣የመጽሐፍ ጥናታችን እንዴትና ስለምን እንደምንፀልይ ፀሎቶቻችን ኃይለኛ እንዲሆኑም ሊያስተምረን ይገባል፡፡ ስለሆነም «በእኔ ብትኖሩ ቃሎቸም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል» ብሎአል /ዮሐ 15፡7/**

በመጽሐፍ የዘወትር ጸሎትን በተመለከተ ብዙ ምሣለዎች ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡ /መዝ 119፡164፣ ዳን 6፡10/ ጠዋትና ማታ ጥቂት አጫጭር የምሥጋና ፀሎቶችን ማድረስ የመጨረሻ አነስተኛው ተግባር ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

## ስብከት 10.3

እውነተኛውን እግዚአብሔርን ከማወቅ የሚነሣው ከፈተናዎች ሁሉ የላቀው ፈተና መንፈሳዊ ራስ ወዳድ መሆን ነው፡፡ በግላችን ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት በጣም ልንረካ እንችላለን፡፡ በራሳችን መጽሐፍ ጥናትና መንፈሳዊነት ተመስጠን እነዚህን ነገሮችከሌሎች ጋር ማለትም ከአማኝ ወዳጆቻችን ከአለው ዓለም ጋር መጋራትን ችላ ልንል እንችላለን፡፡ የእገዚአብሔር ቃልና ዕውነተኛው ወንጌል በጨለማ ውስጥ እንደሚንቦገቦግ መብራት፣ ሻማ ይመሰላል፡፡ /መዝ 119፡105፣ ምሣ 4፡18/፡፡ እንደዚህ ያለ መብራት ያለው ማንም ሰው ባባልዲ ውስጥ አይደብቀውም፤ አይሸፍነውም ለሕዝብ ለአደባባይ ያሳየዋል እንጂ ሲል ኢየሱስ አመልክቶአል፡፡ /ማቴ 5፡15/» እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» በክርስቶስ በመጠመቃችሁ ምክንያትየዓለም ብርሃን ሆናችሁ ይላል /ማቴ 5፡14፣ ዮሐ 8፡12/» በኮረብታ ላይ ያለች ከተማ በእሳት መንቀሳቀሷን መደበቅ አይችልም ሲልም በቀጣይ ተናግሯል /ማቴ 5፡14/

እንደተገነዘብነው በእውነተኛ ወንጌል በእርግጥ የምንኖር ከሆን «ቅድስናችን» አብረናቸው ለምንኖራው ሰዎች አስረጂ ይሆናል፡፡

*ወደእግዚአብሐ2ር መንግሥት ተስፋ የመለየታችንን ሐቅና ከዓለማዊው መንገዶቻችው መነጠላችንንም መደበቅ አንችልም።*

*የዕውነታ ዕውቀታችንን ለምንገናኛቸው ሰዎች ሁሉ አመቺ መንገድ የምናካፍልበትን ዘዴ ማፈላለግ ይኖርብናል። ውይይቶችን ወደመንፈሳዊ ፈር በመለወጥ፣ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አባላት ጋር ትምህርትን በመወያየት፣ ጽሑፎችን በማሠራጨት፣ ካላስፈለገም በሀገሩ በማሠራጨት፣ ካላስፈለገም በሀገሩ ዜና ማሠራጫ አጫጭር ማስታወቂያዎችን በማውጣት ወዘተ ብትሃናችን እንዲንቦገቦግ /እንዲያበራ/ ማድረግ እንችላለን የምሥክርነትን ሥራ ለሌሎች ምዕማናን መተውን ማሰብ የለብንም እያንዳንዳችን የግል ሃላፊነት ተጥሎብናልና።*

*ለስብከት ከሚያመቹ መንገዶች አንዱና ዋነኛው ዕምነቶቻችንን ለቤተሰቦቻ ችንና የቅርብ ካለን ሰዎች ጋር መይሆናል ከባልና ሚስት መካከል አንዱ በዕምነት ውስጥ ካልሆነ ዕምነቶቻቸውን በግልጽ ሊያስቀምጡ ይገባል። ይህ ከተደረገ በኋላ ደጋግሞ ማንሳትና ተፅዕኖ ማሳረፍ አላዋቂነት ይሆናል። በተፅዕኖ ዕምነትን የሚቀበሉትን አይደለም እግዚአብሔር የሚፈልገው። የእኛ ተግባር እውነታውን ከማስቀመጥ አልፎ ስለምላሹ ምንነትና መጠን አያገባንም። ይህን ምሥክርነት ለመስጠት ግን ታላቅ ኃላፊነት ተጥሎብናል/ሕዝ 3:17.21/። ክርስቶስ በእኛ የሕይወት ዘመን ቢመጣ «ሁለቱ ሰዎች ሜዳ ይሆናሉ አንዱ ይወሰዳል ሌላው ይተዋል» /ሉቃ 17:36/ ይላል።*
*ለቤተሰቦቻችንና ለሥራ ባልደረቦቻችን ስለጌታ ዳግም መምጣት ተናግረን ካልነበርና እርሱ ተመልሶ ቢመጣ በእውነት ይህ ኃላፊነት የጎደለው ነገር ይሆናል።*

## 10.4 ሕይወት በቤተክርስቲያን

*የእኛን ተስፋ ከሚጋሩት ጋር መገናኘት ተግባራችን ነው። ይህ በተፈጥሮአችን ለማድረግ የምንፈልገው አንድ ነገር ሊሆን ይገባል። ከጥምቀት በኋላ ወደመንግሥቱ ለመግባት የምድረ በዳ ጉዞ እንዳለብን ከላይ ተመልክተናል። ከሌሎች አጋር ተጓዦች ጋር ግንኙነት የመፍጠር ፍላጎት ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነው። ከክርስቶስ ዳግም መምጫ የመጨረሻ ቀናት ላይ በምንገኝበት በአሁኑ ወቅት ፊት ለፊታችን ተጋርጠው የሚፈታተኑንን ውስብስብ ፈተናዎች*

ለመቋቋም እኛን ከሚመስሉን ጋር መቀራረብና መጓዝ ይኖርብናል፡፡ «...በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን እንተው እርስ በርስችን እንመካከር እንጂ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ» /ዕብራ 10፡25/
ምዕመናን በደብዳቤዎች አማካይነት መጽሐፍን ለማጥናት እርስ በርስ ለመገናኘት የመጓጓዝ፣ የቁርባን አገልግሎትና የስብከር እንቅስቃሴዎች ለማከናወን የሚቻለውን ጥረት መፈጸም ይገባቸዋል፡፡

እያንዳንዳችን ለታላቁ መንግሥት ተስፋ ከጣለም ውስጥ ተመርጠን ተጠርተናል፡፡ «ቅዱስ» የሚለው ቃል የተመረጠና የተጠራ ሰው በመሆኑ ባለፉት ጊዜያት የተጠሩ የታወቁ ምዕመናን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ዕውነተኛ ምዕመናን ይመለከታል፡፡ «ቤተክርስቲያን» የሚለው የግሪክ ቃል ሲተረጎም «የተጠሩ ግለሰቦች ጉባዔ» ..ማለትም ምዕመናን ማለት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ስለዚህ የሚገናኙበትን ህንፃውን ሳይሆን የምዕመናንን ማኅበር /ቡድን/ ነው የሚያመላክተው፡፡

በአንድ አካባቢ ወይም ከተማ ቁጥር ያላቸው ምዕመናን የሚኖሩ ከሆነ በየጊዜው የሚገናኙበት ሥፍራ የግድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ይህ በአማኙ ቤት ውስጥ ወይም በኪራይ አዳራሽ ሰወስጥ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ምዕመናን የኮሚኒቲ ማዕከላት ውስጥ ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ለዚሁ በግል በተገነቡ አዳራሾች ውስጥ ያለበለዚያም በግል ቤቶች ውስጥ ይሰበሰባሉ፡፡ የስብሰባው ዓላማ በጋራ የመጽሐፍ ጥናት አባላትን ማነፅና በስብከት ብርሃን ይንቦገቦግ ዘንድ በጋራ ለዓለም ምሥክርነት መስጠት ነው፡፡ ለምሣሌ ያህል በርሃ ግብሩ እንደዚህ ሊሆን ይችላል፡፡..

ዕሁድ.. ጠዋት በ5፡00 ሰዓት የቁርባን ሥነሥርዓት
ከሰዓት በኋላ በ12፡00 ሰዓት ሕዝባዊ የስብከት አገልግሎት
ረቡዕ.. ማታ ከምሽቱ በ2፡00 ሰዓት መጽሐፍ ጥናት ..

ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ነው:: በተሳሰረ ናኅበረሰብ ውስጥ እያንዳንዱ አባል ለሌላው አባል ስሜት ያለውና ራሱን የሰጠ መሆን ያስፈልገዋል:: ክርስቶስ ራሱ ለዚህ የላቀ አርአያነቱን አሳይቶአል:: ምንም እምኳን በመንፈሳዊነቱ የላቀ የበላይነት የነበረው ቢሆንም «የሁሉም አገልጋይ» እንደሆነ ሁሉ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሐዋርያቱን እግር አጥቦአል:: እየሱስ ምሣሌውን እንከተል ዘንድ ነው ይህን ያደረገው□ / ዮሐ 13፡14.15፣ ማቴ 20፡25..28/::

በቤተክርስቲያን የሚሰጠው ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ላይ በግልጽ የተመሠረተ መሆን አለበት:: ስለዚህ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሕዝብ የሚናገሩት እግዚአብሔርን በማንፀባረቅ በእርሱ ስም የሚናገሩ ናቸው:: እግዚአብሔር ወንድ በመሆኑ ወንዶች ብቻ በእግዚአብሔር ቃል ሕዝባዊ መግለጫ ይሰጣሉ::» ሴቶቻችሁ በቤተክርስቲያን ውስጥ በፀጥታ ያዳምጡ ይናገሩ ዘንድ ለእነርሱ አልተፈቀደምና »በግልጽ ይላል / 1 ቆሮ 14፡34/ 1ጢሞ 2፡11..15 የዚህን ምክንያት በኤደን የአትክልት ቦታ ከተፈጸመው ጋር ያያይዘዋል:: ሄዋን አዳምን ኃጢአት ይሠራ ዘንድ ስለአስተማረችው ሴት አሁን ወንድን ልታስተምር ከቶ አትችልም ማለት ነው:: እግዚአብሔር አዳምን ከሄዋን በፊት የመፍጠሩ ሐቅ « የሴት ራስ ወንድ» ስለመሆኑ የሚያሳይ ምልክት ነው:: /1 ቆሮ 11፡3/ እና በመሆኑም በመንፈሳዊነት ወንድ ሴትን መምራት ይኖርበታል እንጂ በተቃራኒው አይደለም::

በነዚህ ሁሉ ነገሮች ምክንያት «ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር ሴት በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሠለጥን አልፈቅድም:: አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና በኋላም ሄዋን ተፈጠረች:: የታለለም አዳም አይደለም ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች፤ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ በመውለድ ትድናለች» 1 ጢሞ 2፡11..15/

መጽሐፍ የወንዶችና የሴቶች ምዕመናን የተለያዩ ሚናዎች ግልጽ አድርጎ ማስቀመጡን ከዚህ እንረዳለን፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ሴቶች «አግብተው ልጆች ወልደው ቤታቸውን መምራት» እንዳለባቸው ታዝዘዋል /1 ጢሞ 5፡14/፡፡ ይህም የሚያሳየው የእነርሱ የመንፈሳዊ አገልግሎት ተሳትፎ በቤታቸው ውስጥ ባላቸው የላቀ ሚና ላይ መሆኑን ስለዚህ በቤተክርስቲያን የሕዝብ ሥራ ለወንዶች መተው አለበት ባል በሚስቱ ላይ ጌትነት ሊኖረው አይገባም፡፡ ይልቁንም ክርስቶስ እኛን እንዳፈቀረን ሁሉ ሚስቱን ይውደዳት፡፡ /ኤፌ 5፡25/

«...እናንተ ባሎች ሆይ እንግዲህ ደካማ ፍጥረት ስለሆነ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፡፡ ፀሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ፀጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአችሁ» ይላል /1 ጴጥ 3፡7/

በመንፈሳዊ ቃላት በክርስቶስ መጠመቅ ወንድንም ሴትንም እኩል ያደርጋል /ገላ 3፡27..28/፡፡ ያም ሆኖ ግልጽ የሆነውን «ወንድ የሴት ራስ ነው» የሚለውን መርህ አይለውጠ ውም፡፡ /1 ቆሮ 11፡3/ በተጨባጩም በመንፈሳዊው ነገሮች በቤተክርስቲያንም ሆነ በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ራስነት አይሽረውም፡፡

ይህን መሠረታዊ መርህ መቀበልዋን ለማሳየት የሴት ምዕመን ወንድም የእግዚአብሔርን ቃል በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ ራስዋን የሚሸፍን ልብስ መልበስ ይገባታል፡፡ ይህ ማለት በተጨባጥ በቤተክርስትያን ጉባዔዎች ስብሰባዎች ሁሉ ሴቶች ቆብ ወይም ሻሽ መልበስ ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡ የወንዶችና የሴቶች ሚናዎች ልዩነት በፀጉሮቻቸው ላይ በሚያስቀምጡት ልብስ መገለጽ ይገባዋል /1 ቆሮ 11፡14..15/ «..ራስዋን ሳትሸፍን የምትፀልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን /ባልዋን/ ታዋርዳለች፡፡ እንደተላጨች ያህል አንድ ነውና፡፡ ባትሸፍን ፀጉርዋን ደግሞ ትቁረጥ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቁረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን ወንድ የእግዚአብሔር ምሣሌና ክብር ስለሆነ ራሱን

መከናነብ አይገባውም ሴት ግን የወንድ ክብር ናት ሴት ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት አይደለምና ሴት ስለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ከሴት አይደለምና /1 ቆሮ 11፡5 6 10/

## 10.5 የዳቦ ቆረሳው

ከፀሎትና ከመጽሐፍ ጥናት ጎን ለጎን የክርስቶስ መስዋዕትነት የሚዘከርበት የዳቦ ቆረሳውና የወይን መጠጡ የክርስቶስ ትዕዛዝን የመቀበላችን መገለጫ በመሆኑ እጅግ ጠ ቃሚ ነው፡፡ «ለእኔ ማስታወሻ ይህን አድርጉ» /ሉቃ 22፡19/ ሲል አዝዞአል፡፡ እስከ ዳግም መምጫው ጊዜም ይህን ያደርጉ ዘንድ ክርስቶስ የሚፈልገው ነው፡፡ ዳግም ስመጣ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር እንደገና ዳቦውን /መሥዋዕቱን/ና ወይኑን አብሮ ይካፈላል፡፡ /1 ቆሮ 11፡26፤ሉቃ 22፡16..18/

ዳቦው የክርስቶስን ሥጋ፣ ወይኑ ደግሞ ደሙን ይዘክራል /1 ቆሮ 11፡23..27/ የመጀመሪያዎቹ አማኞች ይህን ሥርዓት በየጊዜው ጠብቀው /ሐዋ 2፡42..46/ ቢቻል በየሣምንቱ /ሐዋ 20፡7/ ያከብሩ ነበር፡፡ ክርስቶስን ከልብ የምናፈቅር ከሆነ ትዕዛዛቱን እንጠብቃለን /ዮሐ 15፡11..14/፡፡ እውነተኛ ግላዊ ግንኙነት ከእርሱ ጋር ካለን እንዳዘዘን መሥዋዕትነቱን በማስታወስ ያስገኘልንን ታላቅ ድኅነት እያስታወስን ራሳችንን እናጽናናለን፡፡ ጌታ በመስቀል ላይ ያሳለፈውን ሥቃይ በፀእታ በሀርምሞ ከማሰብና ማስታወስ ጋር ፈጽሞ የሚነጻጸር አይደለም፡፡

የዳቦው መቆረስ በመሠረቱ መሥዋዕትነቱን ከማዘከር አልፎ በራሱ ይህን በማድረግ የሚመጣ ተአምር የለም፡፡ በሙሴ ሕግ በፋሲካ በዓል ይደረግ የነበረው ዓይነት ነው /ሉቃ 22፡15፣1 ቆሮ 5፡7.8/፡፡ እግዚአብሔር ሙሴ በቀይ ባህር አቋርጦ ከግብጽ የወጣበት ታላቅ የድኅነት ሥራ የማስታወሻ

መንገድ ነው። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመዋሉና እኛም ከእርሱ ጋር በጥምቀት አንድ በመሆናችን ድነት በክርስቶስ ማግኘታችንን የዳቦው የመቆረስ ቅዳሴ ወደኋላ በመውሰድ ያስታውሰናል ማለት ነው። ስለዚህ፣ በተፈጥሮአችን ልንጠ ብቀው የሚገባ ትዕዛዝ ነው። ዳቦውንና ወይኑን መውሰዳችን ለክርስቶስ ፍቅር እንዳለንና በእርግጥም ድነትን የሚመለከቱ ነገሮችን ሁሉ እንደገና እውን እንዲሆን ያለንን ቁርጠኝነት ያሣያል። ስለዚህ፣ በሣምንት አንድ ጊዜ መቁረብ የጤናማ መንፈሳዊ ሁኔታን ያመለክታል። ከምዕመናን ጋር በአንድነት ማድረግ የማይችል ብቻውን ማድረግ ይችላል። ይህን ትዕዛዝ ላለመጠበቅ /ለማቆም/ ምንም ዓይነት ምክንያት ሊኖር አይገባም። ለቅዳሴው ዳቦና ወይን እንዲኖር የሚቻለው ሁሉ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፤ ሆኖም በአንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ያለዚህም ቢሆን ክርስቶስን በዚሁ ሥርዓይ ማስታወስ ይቻላል። ኢየሱስ «የወይን ፍሬ» ተጠቅሟል /ሉቃ 22፡18/ እናም ስለዚህ ቀይ የወይን ፍሬ መጠቀም ይችላል።

የክርስቶስን የስቃዮችና የመስዋዕትነት ምልክቱን መካፈል የአንድ ወንድ ወይም ሴት በታላቅ ክብር ሊይዘው የሚገባ ዐቢይ ጉዳይ ነው። ዳቦውና ወይኑ ምን እንደሚወክሉ ተገቢ ትኩረት ሳይሰጥ ያለአግባብ ቁርባን መሳተፍ /መካፈል/ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ እንደማንሳት ያህል ይቆጠራል።

> «ይህን ዳቦ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ
> ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና። ስለዚህ ሳይገባው
> ይህን ዳቦ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም
> ዕዳ አለበት» ይላል /1 ቆሮ 11፡26..27/ ከዚህም

አኳያ፣ ይህን የቁርባን ሥርዓት የሚደረግበት ጊዜና ቦታ ፀጥታ የተሞላበት የአንድ ሰው ሀሳቡ ሳይከፋፈልና ሳይቋረጥ የሚፈስበት መሆን ይኖርበታል። ይህ በጣም ጠዋት ወይም ሌሊት ዘግየት ብሎ በመኝታ ክፍል ወይም በሌላ ተስማሚ

ቦታ ሊደረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሰው ራሱን ይፈትን እንዲሁም /ራሱን በመፈተሽ ትሁት መንፈስ / ከዳቦው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፡፡ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና» ሲል ይመክረናል /1 ቆሮ 11፡28/፡፡ ስለዚህ፣ አዕምሮአችን በክርስቶስ መስዋዕትነት ላይ መትከል አለብን፡፡ ይኸውም ምናልባት ስለስቅለቱ በወንጌል የተጻፈውን በጥልቅ በማሰብ ይሆናል፡፡ ይህን በአግባቡ በመፈጸም ለክርስቶስ ከሚኖረን አመለካከት አኳያ ራሳችንን ለመመርመር ህሊናችን ይገደዳል፡፡

የቁርባን አፈጻጸም የሚከተለው አግባብ ያለው ሥርዓት ይሆናል ...

ፀሎት፡. እግዚአብሔር ፀሎቱንና ስብሰባውን እንዲባርከው ሁሉ፣ ለቃሉ ዓይኖ ቻችንን እንዲከፍተው፣ የሌሎች ምዕመናን ፍላጎቶችን ማስታወስ፣ የእዝጊአብሔርን ፍቅር ማወደስ በተለይ ክርስቶስ ያሳየንን ፍቅር እናም ሌሎች ልዩ ልዩ አስፈላጊ ጉዳዮችን በተመለከተ መፀለይ፡፡ .1

በመጽሐፍ በግልጽ በተቀመጠው መሠረት በዕለቱ መነበብ ያለበትን መጽሐፍ ማንበብ .2

ከተነበበው መጽሐፍ ሊቀስም የሚገባውን ትምህርት ማብራራትና እርሱንም በአንክሮ /በተመስጦ ማሰብ፤ ማለትም ፀሎታችንን ዋናው ዓላማ የሆነውን ክርስቶስን የማስታወስ ተግባር.. አጥብቆ ማሰብ፡፡ .3

የመጀመሪያይቱን ወደቆሮንቶስ ሰዎች 11፡23..29 ማንበብ .4

በሀርምሞ በተመስጦ ራስን የመፈተሽ ጊዜ መስጠት .5

ለዳቦው መፀለይ .6
ዳቦውን ቆርሶ ከዚያ ትንሽ መብላት .7
ለጽዋው መጸለይ .8
አንድ ጉንጭ ወይን መጠጣት .9
የማጠቃለያ ፀሎት .10

ጠቅላላ ሥርዓቱ ከአንድ ሰዓት ያላነሰ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

## 10 .6 ጋብቻ

በተጠመቁ ጊዜ ያላገቡ ወንደላጤዎችን በተመለከተ ባለው ሁኔታ እንጀምራለን፡፡ ያላገቡ በዚያው እንዲቀጥሉ ወይም ቢያንስ ራሳቸውን ለጌታ ሥራ አሳልፈው በመስጠት ወንደላጤ ሆነው እንዲኖሩ የኢየሱስ፣ የጳውሎስና የሌሎች ምሣሌዎች አርአያነት በመጽሐፍ ከተጻፈው ተጣምሮ ይገኛል፡፡ /1 ቆሮ 7፡7..9፣ 32.38፣ 2ጢሞ 2፡4፣ ማቴ 19፡11..19/ «ነገር ግን ብታገባ ኃጢአት አልሠራህም» /1 ቆሮ 7፡28/ ይላል፡፡ ብዙዎቹ ሐዋርያት ያገቡ ነበሩ /1 ቆሮ 9፡5/ እግዚአብሔር በሚፈልገው መልኩ የሚፈጽም ጋብቻ አያሌ አካላዊና መንፈሳዊ ጥቅሞችን እንዲያመጣ ተደርጎ የታቀደ ነው፡፡ «በሁሉም ዘንድ ጋብቻ ክቡር ነው፤ አልጋውም የረከሰ አይደለም» /ዕብራ 13፡4/ «መልካም አይደለም... ሰው ብቻውን ሊሆን » /ዘፍ 2፡18..24/ ለመንፈሳዊ ነገሮች እጅግ ከፍተኛ ብቃት /አሳቢነት/ ከሌለው በስተቀር፡፡ ከዚህም የተነሣ «ሚስት ያገኘ በረከትን አገኘ ከእግዚአብሔርም ሞገስን ይቀበላል.. አስተዋይ ሚስት ከእግዚእብሔር ዘንድ ናት»/ምሣ 18፡22፣ 19፡14/

እነዚህ ጥቅሶች ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት ዝሙት መሆኑን ያመላክታሉ። ዝሙት /ባላገቡ መካከል የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት/ና አመንዝራነት /ያገቡ ወይም ከሁለት አንዱ ያገባ ግን ከሌላ ጋር ወሲብ ማድረግ/ የተወገዘ ሲሆን ይህ የሞራል ዝቅጠት በሐዲስ ኪዳን ብዙ ቦታ ላይ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥተውበታል። ሁሉም የመጽሐፍ ደብዳቤዎች ይህን ይዘዋል። የሚከተሉት ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው። ሐዋ 15፡20፣ ሮሜ 3፡5፣ 1 ተሰሎ 4፡3፣ ይሁዳ 7፣ 1 ጴጥ 4፡3፣ ራዕ 2፡21/

በዘፍጥረት 2፡24 መሠረታዊ መርሆ ላይ የወንድና የወንድ የወሲብ ግንኙነት ኃጢአት መሆኑ ግልጽ ሆኖአል። ሴትና ወንድ ተጋብተው ርስ በርሳቸው እየተጋገዙ፣ እየተፋቀሩ ይኖሩ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የወንድና የወንድ ወሲብ በመጽሐፍ ብዙ ቦታ ላይ ተደጋግሞ ተወግዞአል። ሰዶም የጠፋበት አንዱ ወንጀል ይህ ነበር /ዘፍ 18፡19/። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደዚህ ያሉ ድርጊቶች እግዚአብሔርን በጣም እንደሚያስቆጡት፣ ከመንግሥቱም እንደሚያሠርዙ ግልጽ አድርጓል /ሮሜ 1፡18..22፣ 1 ቆሮ 6፡9..10/

በእንደዚህ ያሉ ድርጊቶች ውስጥ መግባት ያለቀለትና እግዚአብሔርም ሊረዳው ከሚችለው በላይ አድርጎ በመውሰድ ከዚያ ለመውጣት አለመሞከር ዳግሞ ስህተት ነው። ይቅርታ የእግዚአብሔር ገንዘቡ ነውና ይቅርታውን የሚጠይቁ ይቅርታ የማያልቅበት እግዚአብሔር ይሰጣቸዋል /መዝ 130፡4/። በቆሮንቶስ ቤ/ክርስቲያን ምህረትን ተቀብለዋል »አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ስካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም»

## 10.7 ኅብረት

በማወቅና የእግዚአብሔርን መንገዶች በመተግበር ከእግዚአብሔርና «በክርስቶስ» አማካይነት ወዳጅ ከሆንነው ከሌሎች ጋር ኅብረት አለን። ከሌሎች ወዳጆች ጋር ያለንን ኃላፊነት ችላ ማለት ቀላል ነው፡.. « መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈል /ይኸውም ለወዳጅነት/ አትርሱ »ይላል /ዕብራ 13፡16/። ፊል 1፡5 ላይ ስለእኛ «በወንጌል ኅብረትን» ይናገራል። የኅብረታችን መሠረቱ በእውነተኛው ወንጌል ላይ የሠፈረው ትምህርት ይሆናል። በዚህም ምክንያት የእውነተኛ አማኞች የኅብረት ፍቅር በሌሎች ድርጅቶች ወይም ቤተክርስቲያናት ከሚኖረው ሌላ ዓይነት ኅብረት የላቀ ነው። ከዚህም ወዳጅነት የተነሣ ረዥም ጉዞ አቋርጠው ሄደው ኅብረት ይመሠርታሉ። ርቀት ሌላም አይወስናቸውም። ብቸኛ የሆኑ አውነተኛ አማኞችንም በፖስታ፣ በስልክ በመገናኘት ግንኙነት ይፈጥራሉ። ጳውሎስ «ስለመንፈሳዊ ወዳጅነት» ይናገራል። /ፊል 2፡1/ ..ማለትም በእርሱ መንፈስ /ቃል/ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን መንፈስ /አስተሳሰብ/ በጋራ ለመከተል ኅብረት በዓለም ዙሪያ የሚመሠረት ይሆናል።

የኅብረት /የወዳጅነት/ መግለጫዎች ከሆኑት አንዱና ታላቁ በአንድነት የምንወስደው /የምንካፈለው/ የቁርባን ቅዳሴ ነው። የመጀመሪያዎቹ አማኞች »በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት ዳቦውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር... በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም ዳቦ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ይመገቡ ነበር» /ሐዋ 2፡42..46/። «..የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰው ዳቦ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አንድ ዳቦ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን ሁላችን ያን አንዱን ዳቦ /ክርስቶስን ነው/ እንካፈላለንና» /1 ቆሮ 10፡16.17/። ስለዚህ የክርስቶስን መሥዋዕትነት መታሰቢያ ከሥራው ተጠቃሚ ከሚሆኑት ጋር ሁሉ የመካፈል ግዴታ አለብን። አውነታውን

አውቀው በክርስቶስ ስም አምነው በአግባቡ የተጠመቁ ብቻ ይህን ለመካፈል ይችላሉ። ከዚህ ውጭ ካሉት ጋር መካፈል ግን መቀለድ ይሆናል።
«ብቸኛውን ዕምነት» በያዘው የወል ትምህርታዊ እውነታዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም እኛ ከእግዚአብሔር፣ ከክርስቶስና ከሌሎች ምዕመናን ጋር ያለን ኅብረት። የሕይወት መንገዳችን በነዚህ ውስጥ ከተጠቀሱት መርሆዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል...

«...እግዚአብሔር ብርሃን ነው። ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት። ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን አውነታንም አናደርግም። ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሀን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን። የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» / 1 ዮሐ 1:5..7/ ይላል።

ከዚህ አንድ አማኝ ትምህርቶችን ሲከለክል /ሲያግድ/ ወይም ከመጽሐፍ ትምህርት በግልጽ የሚቃረን አኗኗር ሲኖር ኅብረቱ መቆም እንዳለበት ይረጋገጣል። «..ፍሬ ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ ይልቁንም ግለጡት እንጂ» /ኤፌ 5:11/ ይላል።

ኅብረትን በተመለከተ በመጽሐፍ ከተጻፉት ውስጥ 1 ቆሮ 6:14..18 በግልጽ እንዲህ ሲል አስቀምጦታል..

«..ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከዓመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስስ ከቤልሆል ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው? የእግዚአብሔርን ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነ ነው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። ስለዚህም ጌታ ከመካከላቸው ውጡ

-ና የተለያችሁ ሁሉ ርኩስንም አትንኩ ይላል፡፡ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ እኔም እቀበላችኋለሁ ለእናንተም አባት አሆናለሁ፡፡ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል፡፡»

የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ብርሃን እንደሆነ ከላይ አይተናል፡፡ እነዚያ ጥቅሶች የተሳሳቱ ትምህርቶች ከሚሰጡ ቤተክርስቲያናት ጋር ኅብረት መፍጠር ለምን እንደሌለብን፤ እውነታን ከማይቀበሉት ጋር ጋብቻ ማድረግ ለምን እንደሌለብን፤ ምድራዊ አኗኗርን መዘንጋት /መመልከት እንደሌለብን/ ለምን እንደሚያስፈልግ ግልጽ አድርገውታል፡፡ ከዓለም ራሳችንን በመለየት የእግዚአብሔር ምርጥ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች የመሆን ልዩ ክብር እንጎናጸፋለን፡፡ ተመሳሳይ ኅብረት በዓለም ዙሪያ ካላቸው ሁሉ ጋር ቤተሰባዊ ኅብረትም ይኖረናል፡፡ አንድ ብቸኛ እውነተኛ ቤተክርስቲያን ነው ያለው /ኤፌ 1፡23/፡፡ ይህም የተመሠረተው በአንድ ተስፋ፣ በአንድ አምላክ፣ በአንድ ጥምቀትና በአንድ እምነት ላይ ነው /ኤፌ 4፡4..6/፡፡ የዚህ የአንድ ክፍል አካል ሆኖ በሌላ ክፍል ደግሞ ከሌሎች ኃይማኖታዊ ድርጅቶች /እውነተኛ እምነት ካልያዙ/ ጋር ኅብረት መፍጠር አይቻልም፡፡ ብርሃን ከጨለማ ጋር ኅብረት እንደሌለው እያየን በጨለማ ውስጥ እንድንሆን ካወጀን ከጨለማ ጋር ኅብረት ለመፍጠር መርጠ ናል ማለት ነው፡፡

እነዚህም ጥናቶች በጥንቃቄ ተከታትላችሁ ከሆነ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ግማሽ መንገድ ላይ የሚያቆመን እንደማይሆን በእርግጥ መናገር ይቻላል፡፡ በጥምቀት በክርስቶስ ውስጥ ነን፡፡ ያለበለዚያ ያለጥምቀት ከእርሱ ውጭ ነን፡፡ እውነተኛውን ትምህርት በመጨበጥና በተግባር ለዚሁ ታማኝ በመሆን በብርሃን ውስጥ ነን ያለዚያም ያ ካልሆነ በጨለማ ውስጥ ነን ማለት ይሆናል፡፡ በሁለቱም እግሩን ሊሰድ የሚችል የለምና፡፡

የእነዚህ ነገሮች እውቀታችን በተወሰነ ደረጃ ለእግዚአብሔር ኃላፊነት ይሰጠናል፡፡ አሁን እንደማንኛውም መንገደኛ የየዕለት ሕይወታችንን እንደዚሁ እንደዓለማዊው ሰው አናሳልፈውም፡፡ እግዚአብሔር ለመልሳችን ክብደት

ሰጥቶ ይጠባበቃል፡፡ ሁለቱም እግዚአብሔርና ጌታ ኢየሱስ እንዲሁም ሁሉም እውነተኛ አማኞች ትክክለኛ ውሳኔ እንድትወስድ ፍላጎታቸው ነው፡፡ ሆኖም ምንም እግዚአብሔር፣ ክርስቶስና እኛ አንተን ለመርዳት የምንችለውን ሁሉ ብናደርግም በመጨረሻው የተዘረጋልህን ታላቅ ተስፋ ለመጨበጥ በራስህ ነፃ ፈቃድ በምትሰጠው ውሳኔ ነው የሚወሰነውና ለመጠመቅና ይህን ለመከተል እባክህ ዛሬውኑ ፈጽም፡፡

## ጥናት 10 ጥያቄዎች

1/ «ቅዱስነት» ማለት ምንድን ነው?

ሀ/ አማኝ ካልሆኑ ጋር ግንኙነት አለማድረግ
ለ/ ከኃጢአት መለየትና የእግዚአብሔርን ነገሮች መፈጸም
ሐ/ ወደቤተክርስቲያን መሄድ
መ/ ለሌሎች መልካም ማድረግ

2/ ስለዳቦ መቁረስ ከሚከተሉት ዐረፍተነገሮች የትኞቹ ናቸው እውነት?

ሀ/ በየሣምንቱ ማድረግ ይኖርብናል
ለ/ በፋሲካው በዓል በዓመት አንድ ጊዜ ማድረግ አለብን
ሐ/ ዳቦውና ጽዋው ቃል በቃል ወደኢየሱስ ሥጋና ደም ይለወጣል
መ/ ዳቦውና ጽዋው የኢየሱስን ሥጋና ደም ይወክላሉ /ይዘክራሉ/

3/ ስለጋብቻ ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው እውነት?

ሀ/ አውነተኛ አማኞችን ነው ማግባት ያለብን
ለ/ ለአማኞች ፍቺ የተፈቀደ ነው
ሐ/ የትዳር ጓደኛው አማኝ ያልሆነ/ች/ ያገባ አማኝ አብሮ ለመቆየት መሞከር አለበት
መ/ በጋብቻ ባል ክርስቶስን፣ ሚስት ምዕመናንን ይወክላሉ።

Carelinks, PO Box 152, Menai NSW 2234 AUSTRALIA

www.carelinks.net email: info@carelinks.net